# መ ጽ ሐ ፈ ፡ ኩ ፋ ሌ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመላለሱት ፡ ዘመኖች ፡
ሁሉ ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ተብለው ፡ የሚቆጠሩ ፡
የዘመኖችን ፡ ሥራ ፡ ለማወቅ ፡ አምልኮቱና ፡
ሕጉ ፡ የሚነገርባቸውን ፡ የዘመኖችን ፡ አከ
ፋፈል ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ሕጉ ፡ ትእዛዙ ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ሁለቱን ፡ የዕ
ንቍ ፡ ጽላት ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሙሴን ፡— ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ ውጣ ፡ እንዳ
ለው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ለሙሴ ፡
እንደ ፡ ነገረው ፡ የዘመኑን ፡ አከፋፈል ፡ ነገር ፡
የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ በወጡበት ፡
በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ። በሦስ
ተኛው ፡ ወር ÷ ያ ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ ስድ
ስተኛው ፡ ቀን ÷ እግዚአብሔር ፡— ከእኔ ፡ ዘንድ ፡
ወደዚህ ፡ ተራራ ፡ ውጣ ÷ በጻፍኹውም ፡ መጠን ፡
ልብ ፡ ታስደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ሕጉና ፡ ሥርዓቱ ፡
የተጻፈባቸውን ፡ ሁለቱን ፡ የዕንቍ ፡ ጽላት ፡ እሰ
ጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ለሙሴ ፡ ተናገረ ።
፪፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚገለጥበት ፡
ተራራ ፡ ወጣ ። የእግዚአብሔርም ፡ ብርሃን ፡
በደብረ ፡ ሲና ፡ ተገለጠ ። ስድስት ፡ ቀንም ፡
ደመና ፡ ጋረደው ።
፫፤ በሰባተኛይቱም ፡ ቀን ፡ በደመና ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡
ሙሴን ፡ ጠራው ÷ የእግዚአብሔርም ፡ ብርሃን ፡
በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ሲነድድ ፡
አየ ።
፬፤ ሙሴም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አርባ ፡
ሌሊት ፡ ተቀመጠ ። እግዚአብሔርም ፡ ያለፈው
ንም ፡ የሚመጣውንም ፡ ሕጉ ፡ የሚጠበቅበትን ÷
አምልኮቱ ፡ የሚነገርበትን ÷ የዘመኑንም ፡ ሁሉ ፡
አከፋፈል ፡ ነገር ፡ አመለከተው ።
፭፤ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ በምነግርህ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ልብህን ፡ አኑር ። በአንተና ፡ በእኔ ፡ መካ
ከል ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ዛሬ ፡ በልጆቻቸው ፡ የሚ
ደረገውን ፤ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ሥርዓት ፡ ለማ
ስፈረስ ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡
ተለየኋቸው ፡ ልጆቻቸው ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡
በመጽሐፍ ፡ጻፈው ፡ አለው ።
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ በመጣበ ፮
ቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ይናገራል ። በፈረድሁባ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ በሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡
ይልቅ ፡ እኔ ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ያው
ቃሉ ፤ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ያለሁ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡
ያውቃሉ ።
አንተም ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ የነገርሁህን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ፯፤
ነገር ፡ ጻፍ ። እኔ ፡ ቀኍጣቸውን ፡ አውቃለሁና ÷
ማርና ፡ ወተትን ፡ የምታስገኝ ፡ አገርን ፡ ለልጆ
ቻችሁ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይስ
ሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ማልሁላቸው ፡ አገር ፡
ሳላገባቸው ፡ ክሣደ ፡ ልቡናቸው ፡ ጽኑ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አውቃለሁና ፡ በልተው ፡ ጠግበው ፡ ከመ
ከራቸው ፡ ሁሉ ፡ ወደማያድናቸው ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡
ጣዖት ፡ ይመለሳሉና ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ጻፍ ፡ አለው ።
ይህች ፡ መጽሐፍ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ሥርዓት ፡ ፰፤
ትሁንባቸው ። እኔ ፡ የማዝዛቸውን ፡ ትእዛዜን ፡
ሁሉ ፡ ይዘነጋሉና ÷ አሕዛብንም ፡ ተከትለው ፡
ወደ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ይሄዳሉና ÷ ለጣዖቶቻቸ
ውም ፡ ይገዛሉና ፡ በእነርሱ ፡ መከራንና ፡ ጭን
ቅን ፡ ጦርን ፡ ለማምጣትም ፡ መሰናክል ፡ ይሆ
ንባቸዋል ።
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በመከራ ፡ ተይዘው ፡ ይጠፋሉ ፡ ፱፤
በጠላቶቻቸውም ፡ እጅ ፡ ይወድቃሉ ። ትእዛዜ
ንና ፡ ሥርዓቴን ÷ የመሐላዬንም ፡ በዓላት ፡ ሰን
በታትንም ÷ በመካከላቸውም ፡ የለየሁትን ፡
ንዋየ ፡ቅድሳቴን ፤ ስሜ ፡ በእርሱ ፡ ይጠራ ፡
ዘንድ ፡ ያድርበትም ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ መካ
ከል ፡ ያከበርሁትን ፡ ቤተ ፡ መቅደሴንና ፡ ድንኳ
ኔን ፡ ትተዋልና ፡ ይጠፋሉ ።
ኮረብታን ፡ መስጊድን ፡ ጣዖትን ፡ ሠርተው ፡ ለመ ፲፤
ሳት ፡ እየራሳቸው ፡ ይሰግዳሉ ። ልጆቻቸው
ንም ፡ ለአጋንንት ÷ በልቡናቸው ፡ ስተው ፡ ለሠ
ሩትም ፡ ጣዖት ፡ ሁሉ ፡ ይሠዋሉ ፤ አዳኝባቸው ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ነቢያትን ፡ እሰድዳለሁ ።
ነገር ፡ ግን ፡ አይሰሙም ፤ ነቢያትንም ፡ ይገድ
ላሉ ።

፲፩፡ ሕግን ፡ የሚሹ ፡ ሰዎችንም ፡ ይገድሉአቸዋል ፤
ከአገርም ፡ አስወጥተው ፡ ይሰድዱአቸዋል ፤
ሁሉን ፡ ያበዝናሉ ፤ በፊቱም ፡ ክፉ ፡ ሥራን ፡
መሥራት ፡ ይጀምራሉ ።
፲፪፤ ከእነርሱም ፡ ፊቱን ፡ እመልሳለሁ ፤ ለመበዝበ
ዝና ፡ ለመማረክ ፡ ለመዘረፍ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡
በአሕዛብ ፡ እጅ ፡ እጥላቸዋለሁ ፤ ከኢየሩሳሌ
ምም ፡ መካከል ፡ አርቃቸዋለሁ ፤ በአሕዛብም ፡
አገር ፡ እበትናቸዋለሁ ።
፲፫፡ ሕጌን ፡ ሁሉ ÷ ትእዛዜንም ፡ ሁሉ ÷ ፍርዴንም ፡
ሁሉ ÷ ሥርዓቴንም ፡ ሁሉ ፡ ይዘነጋሉ ። የወ
ሩን ፡ መባቻና ፡ ሰንበትን ÷ በዓሉንና ፡ ኢዮቤ
ልዩን ፡ ሥርዓቱንም ፡ ይዘነጋሉ ።
፲፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በፍጹም ፡ ሰውነታቸውና ፡
በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ በፍጹም ፡ እውቀታ
ቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለ
ሳሉ ። እኔም ፡ ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ እሰ
በስባቸዋለሁ ።
፲፭፤ እገለጥላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይፈልጉኛል ። በፍጹም ፡
ሰውነታቸውና ፡ በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ በፈለ
ጉኝም ፡ ጊዜ ÷ እኔ ፡ በእውነት ፡ ብዙ ፡ ፍቅርን ፡
እገልጥላቸዋለሁ ÷ በፍጹም ፡ ሰውነቴና ፡ በፍ
ጹም ፡ ልቡናዬም ፡ ወደ ፡ ቀና ፡ ሕግ ፡ እመል
ሳቸዋለሁ ።
፲፮፤ ለመርገም ፡ ያይደለ ፡ ለበረከት ፡ ይሆናሉ ፤
ተገዥ ፡ ያይደሉ ፡ ገዥ ፡ ይሆናሉ ፤ በመካከላ
ቸውም ፡ የምመሰገንበትን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡
እሠራለሁ ፤ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡ እኖ
ራለሁ ፤ አባታቸው ፡ እሆናቸዋለሁ ፤ እነርሱም ፡
በሚገባ ፡ በእውነት ፡ ልጆቼ ፡ ይሆናሉ ፤ ፈጣሪ
ያቸው ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ፡ ፈጽሜ ፡
አልለያቸውም ፡ አለው ።
፲፯፤ ሙሴም ፡ በግምባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ጸለየ ፤ እንዲ
ህም ፡ አለ ፡— አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ÷ በልቡናቸው ፡
ስሕተት ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ ማደሪያዎችህ ፡
የሆኑ ፡ ወገኖችህን ፡ አትተው ። ይገዙአቸው ፡
ዘንድ ፡ አንተንም ፡ እንዲበድሉ ፡ ያደርጓቸው ፡
ዘንድ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ በአሕዛብ ፡ እጅ ፡ አት
ጣላቸው ።
፲፰፤ አቤቱ ÷ ይቅርታህ ፡ በወገኖችህ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ይበል ÷ የቀና ፡ ልቡናንም ፡ ፍጠርላቸው ።
በፊትህ ፡ ለማጣላት ÷ ከባለምዋልነትህም ፡
ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ከእውነተኛው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
ለማሰነካከል ፡ የሰይጣን ፡ መንፈስ ፡ አይሠልጥ
ንባቸው ።
፲፱፤ እነርሱስ ፡ በታላቅ ፡ ኃይልህ ፡ ከግብጽ ፡ ሰዎች ፡
እጅ ፡ ያዳንካቸው ፡ ወገኖችህና ፡ ማደሪያዎችህ ፡
ናቸው ። ንጹሕ ፡ ልቡናን ፡ ፍጠርላቸው ። የተ
ቀደሰ ፡ መንፈስንም ፡ አሳድርባቸው ÷ ከዛሬ ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙም ፡ ድረስ ፡ በኃጢአ
ታቸው ፡ አይሰነካከሉ ።
፳፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡—
እኔ ፡ ክርክራቸውንም ፡ አሳባቸውንም ፡ አው
ቃለሁ ፤ ክፉደ ፡ ልቡናቸውም ፡ ጽኑ ፡ ነው ።
የአባቶቻቸውን ፡ ኃጢአት ፡ ፍዳና ፡ የራሳቸ
ውን ፡ ኃጢአት ፡ ፍዳ ፡ እስኪያውቁ ፡ ድረስ ፡
አይሰሙም ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በፍጹም ፡ ቅንነትና ፡ በፍጹም ፡ ፳፩፤
ልቡና ፡ በፍጹም ፡ ሰውነትም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
ይመለሳሉ ። የልጆቻቸውን ፡ ልቡና ፡ ቈላፍነ
ትና ፡ የልቡናቸውን ፡ ቈላፍነት ፡ እቈርጣለሁ ።
ንጹሕ ፡ ልቡናን ፡ እፈጥርላቸዋለሁ ።
ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ፳፪፤
እኔን ፡ ከመከተል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዳይመለሱ ፡
አነጻቸዋለሁ ፤ ልቡናቸውም ፡ እኔን ፡ ትከተላ
ለች ፤ ትእዛዜንም ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማሉ ።
አባት ፡ እሆናቸዋለሁ ÷ እነርሱም ፡ ልጆች ፡ ፳፫፤
ይሆኑኛል ፤ ሁሉም ፡ የሕያው ፡ አምላክ ፡
ልጆች ፡ ይባላሉ ። አለቃ ፡ ሁሉ ፡ ሰውም ፡
ያውቃቸዋል ። እነርሱ ፡ ልጆቼ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ÷
እኔም ፡ በሚገባና ፡ በእውነት ፡ አባታቸው ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ እንድወድዳቸውም ፡ ያውቋቸዋል ።
አንተም ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ የምነግር ፳፬፤
ህን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ÷ የፊቱንና ፡ የኋላውን ÷
ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለውንም ÷ ሕጉ ፡ አምልኮቱ ፡
በሚነገርበት ፡ በዓመት ፡ ቍጥር ፡ እስከ ፡ ዘላ
ለም ፡ ድረስ ፡ የሚሆነውን ፡ የዘመኑን ፡ አከፋ
ፈል ፡ ሁሉ ÷ እኔ ፡ ወርጄ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እስክኖር ፡ ድረስ ፡ የሚደረገው
ንም ፡ ሁሉ ፡ ጻፍ ፡ አለው ።
መልአክ ፡ ገጹንም ፡— ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ፳፭፤
ጀምሮ ፡ ለዘላለም ፡ የምመሰገንበትን ፡ ቤተ ፡
መቅደስ ፡ በመካከላቸው ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ፡
እግዚአብሔርም ፡ ለሁሉ ፡ ተገልጦ ፡ እስኪ
ታይ ፡ ድረስ ፡ የሚሆነውን ፡ ለሙሴ ፡ ጻፍለት ፡
አለው ።
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ÷ ለያ ፳፮፤
ዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ÷
በደብረ ፡ ጽዮንም ፡ ለዘላለም ፡ ገዥ ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ፤ ጽዮን ፡ የምትባል ፡
ኢየሩሳሌምም ፡ የከበረች ፡ ትሆናለች ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በእስራኤል ፡ ሠራዊት ፡ ፊት ፡ የሚሄድ ፡ ፩፤
መልአክ ፡ ገጹም ፡ የዘመኖች ፡ አከፋፈል ፡ የተ
ጻፈበትን ፡ ጽላት ፡ ያዘ ።
ይኸውም ፡ ለሕግና ፡ ለምስክርነት ፡ በሱባዔ ፡ ፪፤
የሚቈጠረው ፡ የዘመኑ ፡ አከፋፈል ፡ ከዓለም ፡
ፍጥረትና ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ከተፈጠረበት ፡
ቀን ፡ ጀምሮ ÷ ሰማያትና ፡ ምድር ÷ ፍጥረታቸ
ውም ፡ ሁሉ ፡ የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡ እንደ ፡ መሆ
ናቸው ፡ እስኪታደሱ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ የተጻ
ፈበትን ፤
የምድር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መሆናቸውም ፡ ፫፤
የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡
በደብረ ፡ ጽዮን ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ÷ ከእስራ
ኤል ፡ ለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለደኅንነት ፡
ለሰላምና ፡ ለበረከት ፡ ሊሆኑ ፡ ብርሃናትም ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



እስኪታደሱ ፡ ድረስ ፤ ከዚህች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡
ምድር ፡ ጸንታ ፡ በምትኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
እንደዚሁ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የሚደረገው ፡ ሁሉ ፡
የተጻፈበትን ፡ ጽላት ፡ ያዘ ።
፬፤ መልአክ ፡ ገጹም ፡ ሙሴን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ታገዝዞ ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡—
የፍጥረትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጻፍ ፤ እግዚአብሔር ፡
አምላክ ፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ፍጥረቱን ፡
ሁሉ ፡ ፈጥሮ ፡ እንደ ፡ ጨረሰ ፤
፭፤ በሰባተኛይቱ ፡ ቀን ፡ እንዳረፈ ፤ ከዕለታቱም ፡
ሁሉ ፡ እንደ ፡ ለያት ፤ ለሥራውም ፡ ሁሉ ፡ ምል
ክት ፡ አድርጎ ፡ እንዳኖራት ፡ ጻፍ ፡ አለው ። በመ
ጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ሰማዮችን ፡
ፈጥሮአልና ፤ ምድርንም ፡ ውኃዎችንም ፡ በፊቱ ፡
የሚያገለግል ፡ ፍጥረትንም ፡ ሁሉ ፡ ፈጥሮአ
ልና ።
፮፤ መላእክተ ፡ ገጽንም ፤ የሚያመሰግኑ ፡ መላእክ
ትንም ፤ በእሳት ፡ አካል ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡
መላእክትንም ፤ በጨለማና ፡ በብርሃን ፡ አካል ፡
ላይ ፡ የተሾሙ ፡ መላእክትንም ፤ በውርጭና ፡
በበረድ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ መላእክት
ንም ፤
፯፤ በውኃ ፡ ላይ ፡ በመብረቅና ፡ በነጐድጓድ ፡ ላይ ፡
የተሾሙ ፡ መላእክትንም ፤ በነፋሳት ፡ ላይ ፡
የተሾሙ ፡ መላእክትን ፤ በቊርና ፡ በውርጭ ፡
በመጸውና ፡ በክረምት ፡ በበጋና ፡ በጸደይ ፡
በምድርና ፡ በሰማይ ፡ ባሉ ፡ ነፋሳት ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ የተሾሙ ፡ መላእክትን ፤ በወንዙ ፡ ሁሉ ፡
በብርሃንና ፡ በጨለማ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕ
ርይ ፡ እውቀቱ ፡ በዘጋጃቸው ፡ በምሽትና ፡ በመ
ንጋት ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ መላእክትን ፡ ፈጥሮአ
ልና ። የፍጥረትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጻፍ ፡ ብሎ ፡
ነገረው ።
፰፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ፍጥረቱን ፡ አይተን ፡ ስለ ፡ ፈጠ
ረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ፈጽመን ፡ አመ
ሰገንነው ፤ በመጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ታላ
ላቆች ፡ ፍጥረቶችን ፡ ፈጥሮአልና ።
፱፤ በሁለተኛይቱም ቀን ፡ በሐኖስና ፡ በውቅያኖስ ፡
መካከል ፡ ጠፈርን ፡ ፈጥሮአልና ፤ በዚያችም ፡
ቀን ፡ ውኃዎች ፡ ተከፍለው ፡ እኩሌቶቹ ፡ ወደ ፡
ላይ ፡ ወጥተዋልና ፤ እኩሌቶቹ ፡ ከጠፈር ፡
በታች ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ መካከል ፡
ወርደዋልና ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡
ሥራ ፡ ሠራ ።
፲፤ በሦስተኛይቱም ፡ ቀን ፡— ውኃዎች ፡ ከምድር ፡
ላይ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ይወሰኑ ፡
ምድርም ፡ ትገለጥ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡
አደረገ ።
፲፩፤ ውኃዎችም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ እንደዚሁ ፡ አደ
ረጉ ። ከምድር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡
ሄደው ፡ ከዚህ ፡ ከጠፈር ፡ በታች ፡ በውቅያኖስ ፡
ተወሰኑ ፤ ምድርም ፡ ተገለጠች ።
፲፪፤ በዚያችም ፡ ቀን ፡ በየመወሰኛቸው ፡ የባሕር ፡
ጥልቆችን ፡ ፈጠረላት ፤ ፈሳሾችንም ፡ ሁሉ ፥
የውኃዎችንም ፡ መወሰኛዎች ፥ በተራራዎች ፡
ሥር ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ምንጮች ፡ ሁሉና ፡
በተራራዎች ፡ ሥር ፡ ያሉ ፡ የውኃዎችን ፡ መወ
ሰኛዎች ፡ ሁሉ ፥ በምድር ፡ ያሉ ፡ የውኃዎች
ንም ፡ ጕድጓድ ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረላት ። በየዘሩ ፡
የሚዘራውንም ፡ ዘር ፤ የሚበላውንም ፡ ዘር ፡
ሁሉ ፤ የሚያፈሩ ፡ እንጨቶችንም ፡ ዘሮችንም ፥
በገነት ፡ ለተድላ ፡ ደስታ ፡ የተፈጠሩ ፡ ተክሎች
ንም ፤ በሦስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ እነዚህን ፡ አራቱን ፡
ታላላቆች ፡ ፍጥረቶች ፡ ፈጠረ ።
በአራተኛይቱም ፡ ቀን ፡ ጨረቃንና ፡ ፀሐይን ፡ ፲፫፤
ከዋክብትን ፡ ፈጥሮ ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ያበሩ ፡
ዘንድ ፡ በጠፈር ፡ አኖራቸው ። ሌሊትንና ፡ ቀን
ንም ፡ አስገዛቸው ፤ በጨለማና ፡ በብርሃን ፡
መካከል ፡ ለመለየት ፡ ድምበር ፡ አደረጋቸው ።
እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ምል ፲፬፤
ክት ፡ እንዲሆን ፡ ለሱባዔዎችና ፡ ለቀኖች ፥ ለበዓ
ሎችና ፡ ለወሮች ፥ ለኢዮቤላትና ፡ ለዘመኖች ፥
በዓመት ፡ ለሚመላለሱ ፡ ሰዓቶች ፡ ሁሉ ፡ ምል
ክት ፡ እንዲሆን ፤ በጨለማና ፡ በብርሃን ፡ መካ
ከል ፡ ድምበርን ፡ እንዲለይ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡
የሚበቅለውና ፡ የሚያድገው ፡ ሁሉ ፡ ይድን ፡
ዘንድ ፡ ለማዳን ፡ ፀሐይን ፡ ፈጠረ ፤ በአራተኛ
ይቱ ፡ ቀን ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ ፍጥረቶች ፡
ፈጠረ ።
በአምስተኛይቱም ፡ ቀን ፡ በጥልቅ ፡ ውኃዎች ፡ ፲፭፤
መካከል ፡ ያሉትን ፡ ታላላቆች ፡ አንበሪዎችን ፡
ፈጠረ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ በሥልጣኑ ፡
ተፈጥሮአልና ፤ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሁሉ ፥ በው
ኃዎችም ፡ ውስጥ ፡ የሚመላለስ ፡ ፍጥረት ፡
ሁሉ ፥ የሚበሩ ፡ ወፎች ፡ ሁሉና ፡ ዓሣዎችም ፡
ወገኖቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ተፈጥረዋልና ፤
ፀሐይም ፡ ሕይወት ፡ ሊሆናቸው ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ፲፮፤
ወጥቶአልና ፥ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚኖር ፡ ፍጥረ
ትም ፤ በምድር ፡ በሚበቅለውም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
በሚያፈራውም ፡ እንጨት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በሥ
ጋዊ ፡ በደማዊ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ወጥቶአልና ፤ በአ
ምስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ ፍጥረ
ቶች ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ።
በስድስተኛይቱም ፡ ቀን ፡ እንስሳትንና ፡ አራዊ ፲፯፤
ትን ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚመላለሰውንም ፡
ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረት ፡ ከፈጠረ ፡ በኋላ ፡ ፩፤
አንድ ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ ፤ ሴትና ፡ ወንድን ፡ አድ
ርጎ ፡ ፈጠራቸው ፤ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡
ፍጥረትና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ፍጥረት ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ አሠለጠነው ። በአራዊትና ፡ በአዕ
ዋፍም ፡ ላይ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመላለሰው ፡
ፍጥረት ፡ ሁሉና ፡ በእንስሳት ፡ ላይ ፤ በዓለ
ሙም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ አሠለጠነው ፤ በስ
ድስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ እነዚህን ፡ አራቱን ፡ ፍጥረ
ቶች ፡ ፈጠረ ።

፪፤ የተፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሆነ ፤ በስድስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ በምድርና ፡
በሰማይ ፡ በጥልቁና ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ በጨ
ለማና ፡ በብርሃን ፡ መከከል ፡ በዓለምም ፡ ላይ ፡ ያለ
ውን ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ፈጥሮ ፡ ጨረሰ ።
፫፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ በሰባተኛይቱ ፡
ቀን ፡ ከሥራችን ፡ ሁሉ ፡ ዕረፍት ፡ የምናደርግ ፡
እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ የምትሆን ፡
ሰባተኛይቱን ፡ ቀን ፡ ምልክት ፡ አድርጎ ፡ ሰጠን ።
፬፤ የሚያመሰግኑ ፡ መላእክት ፡ ሁሉና ፡ መላእክተ ፡
ገጽ ፡ ሁሉ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ብዙ ፡ ወገኖች ፡
ናቸው ። በምድርና ፡ በሰማይ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ይህንን ፡ እናከብር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘን ።
፭፤ እንዲህም ፡ አለን ፡— እነሆ ÷ እኔ ፡ ከአሕዛብ ፡
መከከል ፡ ወገኖቼን ፡ እለያቸዋለሁ ፤ ቀዳሚት
ንም ፡ እንዳከበርኋት ፡ አከብራቸዋለሁ ። ለእኔ ፡
እለያቸዋለሁ ፤ እንደዚህ ፡ አከብራቸዋለሁ ።
፮፤ ልጆቼ ፡ ይሆናሉ ÷ እኔም ፡ አባትን ፡ እሆናቸ
ዋለሁ ፤ ካየሁት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ የያዕቆብን ፡
ልጅ ፡ መረጥሁት ፤ ለእኔ ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ አድ
ርጌ ፡ ጻፍሁት ፤ ለዘላለሙም ፡ አከበርሁት ።
፯፤ ከሥራ ፡ ሁሉ ፡ ያርፉበት ፡ ዘንድ ፡ በሱባዔ ፡ የም
ትቈጠር ፡ ቀዳሚትን ፡ አመለክታቸዋለሁ ።
በዓል ፡ በሚያከብሩበት ፡ ገንዘብ ፡ እንደዚሁ ፡
ምልክት ፡ አደረግሁበት ።
፰፤ እነርሱም ፡ በሰባተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ለመብላት ፡ ለመጠጣት ፤ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ ለማመስገን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ በአን
ድነት ፡ በዓልን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ከአሕዛብ ፡
ሁሉ ፡ ተለይቶ ፡ የሚታይ ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡
ለይቶ ፡ እንዳከበረው ፡ ምልክት ፡ አደረገ ።
፱፤ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድ
ርጎ ፡ የሚቀበለው ፡ መሥዋዕት ፡ ያርግ ፡ ዘንድ ፡
በፊቱ ፡ መሥዋዕትን ፡ ሠዋ ፤ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ያዕቆብ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ አበው ፡ ሀያ ፡
ሁለት ፡ ናቸው ። እስከ ፡ ሰባተኛይቱ ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ፍጥረትን ፡ ፈጠረ ። ይህም ፡
የከበረና ፡ የተለየ ፡ ሰንበቱ ፡ ነው ። ያም ፡ የከ
በረና ፡ የተለየ ፡ ነው ።
፲፤ ይህ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ለምስጋና ፡ በረከት ፡ ሆነ ።
ሰባተኛይቱን ፡ ቀን ፡ ቀድሞ ፡ ለይቶ ፡ እንዳከበ
ራት ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ የከበሩና ፡ የተለዩ ፡ ሕጉ
ንና ፡ አምልኮቱን ፡ የሚጠብቁ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡
ለዚህ ፡ ተሰጠው ።
፲፩፤ በመጀመሪያይቱ ፡ ሱባዔ ፡ ምድርና ፡ ሰማይን ፡
በስድስት ፡ ቀን ፡ የተፈጠረውንም ፡ ፍጥረት ፡
ሁሉ ፡ ፈጠረ ። እግዚአብሔር ፡ ለፍጥረቱ ፡
ሁሉ ፡ የከበረች ፡ በዓል ፡ የምትደረግበት ፡ ቀንን ፡
ሰጠ ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ የሚሠ
ራበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ÷ የሚሽ
ራትም ፡ ሰው ፡ ሞትን ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።
፲፪፤ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ።
እነርሱ ፡ ያችን ፡ ዕለት ፡ ይጠብቁ ፡ ያከብሩአ
ትም ፡ ዘንድ ፡ ሥራንም ፡ ሁሉ ፡ እንዳይሠሩበት ፡
እንዳይሽሩአትም ፡ ከዕለታት ፡ ሁሉ ፡ እርስዋ ፡
የከበረች ፡ ናትና ።
የሚሽራትም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ ይሙት ፤ ፲፫፤
የተባረከችና ፡ የተቀደሰች ፡ ቀን ፡ ናትና ፡ የእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ በትውልዳቸው ፡ ይህችን ፡ ቀን ፡
እንዲጠብቁ ፡ ከምድርም ፡ እንዳይጠፉ ፡ ሥራን ፡
የሚሠራበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለሙ ፡ ሞትን ፡
ይሙት ።
የሚጠብቃት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሥራም ፡ ሁሉ ፡ ፲፬፤
የሚያርፍበት ፡ ሰው ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡
እኛ ፡ የተቀደሰና ፡ የተባረከ ፡ ይሆናል ።
ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡— የዚህችን ፡ ቀን ፡ ፍር ፲፭፤
ድዋን ፡ ፈጽመህ ፡ ንገር ፤ በዓልን ፡ ያድርጉበት ፤
የማይገባ ፡ ሥራን ፡ ለመሥራትም ፡ የተዘጋጁ ፡
እንዳይሆኑ ፡ በልቡናቸው ፡ ስሕተት ፡ አይተ
ዋት ፤ የሚታየውን ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለእርስዋ ፡
ለማድረግ ፡ የሚበላውን ፡ የሚጠጣውን ፡ ሁሉ ፡
ያዘጋጁበት ፡ ዘንድ ፡ ንገራቸው ።
ውኃን ፡ ለመቅዳት ፡ በአደባባያቸው ፡ ሸክሙን ፡ ፲፮፤
ሁሉ ፡ ለማግባት ፡ ለማውጣት ፡ የተዘጋጁ ፡ ሁነው ፡
አይታዩ ፤ እነርሱም ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ በቤታ
ቸው ፡ ያላዘጋጁትን ፡ ሥራ ፡ አይሥሩ ።
በኢዮቤልዩ ፡ ከሚቈጠር ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ ተለ ፲፯፤
ይታ ፡ የከበረች ፡ ናትና ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡ ከአ
ንዱ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ አያውጡበት ፡
አያግቡበት ። በምድር ፡ ዕረፍት ፡ ያደርጉበት ፡
ዘንድ ፡ ለሥጋዊ ፡ ለደማዊ ፡ ሁሉ ፡ ሳይታወቅ ፡
እኛ ፡ በሰማይ ፡ ዕረፍት ፡ አደረግንበት ።
ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አከበራት ፤ ፲፰፤
ከእስራኤል ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ዕረፍት ፡ ሊያደርግ
ባት ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አልመረጠም ፤ በልቶ ፡
ጠጥቶ ፡ በምድር ፡ ዕረፍትን ፡ ሊያደርግባት ፡
ለእርሱ ፡ ብቻ ፡ ሰጠው ።
ከቀኑ ፡ ሁሉ ፡ ተለይታ ፡ ለበረከትና ፡ ለመከበር ፡ ፲፱፤
ለማመስገኛም ፡ ልትሆን ፡ ይህችን ፡ ቀን ፡ የፈ
ጠረ ፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ አከበ
ራት ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ሥርዓት ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆችና ፡ ለትውልዳቸው ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡
ሆኖ ፡ ተሰጠ ።

## ምዕራፍ ፬ ።

ከሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ፩፤
በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ታዘን ፡ እንስሳትን ፡
ሁሉና ፡ አራዊትን ፡ ሁሉ ÷ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚ
መላለሰውን ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉና ፡ አዕዋፍን ፡
ሁሉ ÷ በውኃውም ፡ ውስጥ ፡ የሚመላለሰውን ፡
ፍጥረት ፡ ሁሉ ÷ በየወገናቸው ፡ በየመልካቸው ፡
ወደ ፡ አዳም ፡ አመጣን ።
በመጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ አራዊትን ÷ በሁለተኛ ፪፤
ይቱ ፡ ቀን ፡ እንስሳትን ÷ በሦስተኛይቱ ፡ ቀን ፡
አዕዋፍን ÷ በአራተኛይቱ ፡ ቀን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
የሚመላለሰውን ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ÷ በአምስተ
ኛይቱም ፡ ቀን ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ የሚመላለሰ
ውን ፡ ፍጥረት ፡ አመጣን ። አዳምም ፡ በየስማ

ቸው ፡ ጠሯቸው ፤ ስማቸውም ፡ አዳም ፡ እን
ዳወጣላቸው ፡ እንደዚያው ፡ ሆነ ።
፫፤ በእነዚህ ፡ በአምስቱ ፡ ቀኖች ፡ አዳም ፡ ይህን ፡
ሁሉ ፡ ፍጥረት ÷ በምድር ፡ ያለውንም ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሁሉ ÷ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ሆነው ፡ ያይ ፡ ነበር።
በምድር ፡ ያለውን ፡ ወገንንም ፡ ሁሉ ፡ ያይ ፡
ነበር ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ ነበረ ። እንደ ፡
እርሱ ፡ ያለ ፡ ረዳትንም ፡ ለእርሱ ፡ ያገኘው ፡ ማግ
ኘት ፡ የለም ።
፬፤ እግዚአብሔርም ፡ ለኛ ፡ እንዲህ ፡ አለን ፡— እንደ ፡
እርሱ ፡ ያለ ፡ ረዳትን ፡ እንፍጠርለት ፡ እንጂ ፡
አዳም ፡ ብቻውን ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አገባብ ፡ አይ
ደለም ፡ አለ ፤ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በአ
ዳም ፡ እንቅልፍን ፡ አመጣበት ፤ እርሱም ፡ ተኛ ።
፭፤ ከአጥንቶቹ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ አጥንት ፡ አን
ሥቶ ፡ ሔዋንን ፡ ፈጠራት ። የዚህችም ፡ የሔ
ዋን ፡ መፈጠርዋ ፡ ከአጥንቶች ፡ መካከል ፡ ነው ፤
ስለ ፡ እርስዋም ፡ ፋንታ ፡ ሥጋን ፡ ሞላ ። ሰው ፡
አደረጋት ። አዳምንም ፡ ከእንቅልፉ ፡ አነቃው ፤
፮፤ አዳምም ፡ በስድስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ከእንቅልፉ ፡
ነቅቶ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጣት ÷
አወቃትም ። እርሱም ፡— ከእኔ ፡ ከባልዋ ፡ ተገ
ኝታለችና ፡ ይህች ፡ የአጥንቴ ፡ ፍላጭ ፡ የሥ
ጋዬ ፡ ቍራጭ ፡ ናት ፤ ሚስት ፡ ትሁነኝ ፡ አለ ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንድ ፡ አካል ፡
ይሆናሉ ።
፯፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ እናትና ፡ አባቱን ፡
ትቶ ፡ ሚስቱን ፡ ይከተላል ፤ ከእርስዋም ፡ ጋር ፡
አንድ ፡ ይሆናል ፤ ሁለቱም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አካል ፡
ይሆናሉ ።
፰፤ በመጀመሪያይቱ ፡ ሱባዔ ፡ አዳም ፡ ተፈጠረ ፤
ሁለተኛይቱም ፡ ሱባዔ ፡ ሔዋንን ፡ ፈጥሮ ፡ አሳ
የው ፤ ስለዚህም ፡ በአደፍነት ፡ ጊዜ ፡ ወንድ ፡
ልጅ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እንዲጠበቅ ፡ ሴት ፡ ልጅም ፡
ሁለት ፡ ሱባዔ ፡ እንድትጠበቅ ፡ ሥርዓት ፡
ተሠራ ።
፱፤ በተፈጠረባት ፡ ምድር ፡ ለአዳም ፡ አርባ ፡ ቀን ፡
ከተፈጸመለት ፡ በኋላ ፡ ይገዛትም ፡ ይጠብቃ
ትም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አስገባነው ። ሚስቱ
ንም ፡ በሰማንያ ፡ ቀን ፡ አስገባናት ።
፲፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኤዶም ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡
ገነት ፡ ገባች ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ብት
ወልድ ፡ ቀድሞ ፡ አዳም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቆይቶ ፡
እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በአራስነትዋ ፡
ትቆይ ፡ ዘንድ ፤ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ንጽሕ ፡
በሚሻ ፡ ደምዋ ፡ ትቆይ ፡ ዘንድ ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡
ለምትወልድ ፡ ሴት ፡ በጽላተ ፡ ሰማይ ፡ ሥርዓት ፡
ተጻፈ ።
፲፩፤ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ አትንካ ፤ ለወንድ ፡ ልጅ ፡
የታዘዘውን ፡ ይህንን ፡ ቀን ፡ እስክትፈጽም ፡
ድረስ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ እንዳትገባ ፡
ሥርዓት ፡ ተጻፈ ። ሴት ፡ ልጅ ፡ ብትወልድ ፡
ቀድሞ ፡ ሔዋን ፡ ሁለት ፡ ሱባዔ ፡ ቆይታ ፡ እንደ ፡
ተፈጠረች ፡ ሁለት ፡ ሱባዔ ፡ በአራስነትዋ ፡
ትቆይ ፤ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ቀንም ፡ ንጽሕ ፡ በሚሻ ፡
ደምዋ ፡ ትቆይ ፤ ሁሉም ፡ ሰማንያ ፡ ቀን ፡ ይሆ
ናሉ ።
እነዚህን ፡ ሰማንያ ፡ ቀኖች ፡ ከጨረሰች ፡ በኋላ ፡ ፲፪፤
ገነት ፡ ከዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ የከበረች ፡ ናትና ÷ በው
ስጥዋም ፡ የበቀለው ፡ እንጨት ፡ ሁሉ ፡ የከበረ ፡
ነውና ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አገባናት ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሴት ፡ ልጅና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ፲፫፤
ለምትወልድ ፡ ሴት ፡ የእነዚህ ፡ ቀኖች ፡ ሥርዓት ፡
ተሠራ ፤ ለሴት ፡ ልጅና ፡ ለወንድ ፡ ልጅ ፡ የታ
ዘዙ ፡ እነዚህ ፡ ቀኖች ፡ እስኪፈጸሙ ፡ ድረስ ፡
ንዋየ ፡ ቅድሳትን ፡ ሁሉ ፡ አትንካ ፡ ወደ ፡ መቅ
ደስም ፡ አትግባ ። እስራኤል ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡
ይጠብቅው ፡ ዘንድ ፡ የተጻፈው ፡ ሕግና ፡ ሥር
ዓት ፡ ይህ ፡ ነው ።
በመጀመሪያው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ኢዮ ፲፬፤
ቤልዩ ፡ አዳምና ፡ ሚስቱ ፡ በገነት ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡
ሲገዙ ÷ ሕጉንም ፡ ሲጠብቁ ፡ ኖሩ ። ሥራንም ፡
አስተማርነው ፤ ለማገልገል ፡ ተገልጦ ፡ የሚታ
የውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ስናስተምረው ፡ ኖርን ፤
እርሱም ፡ ሲያገለግል ፡ ኖረ ።
እርሱ ፡ ግን ፡ ዕራቁቱን ፡ ነበረ ፤ ዕራቁቱንም ፡ ፲፭፤
እንደ ፡ ሆነ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ÷ አያፍርም ፡
ነበር ። ተክልንም ፡ ከአራዊትና ፡ ከወፎች ፡ ከእ
ንስሳትም ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ፤
ሬፍውን ፡ ለቅሞ ፡ ይበላ ፡ ነበር ፤ በልቶም ፡ የተ ፲፮፤
ረፈውን ፡ ለእርሱም ፡ ለሚስቱም ፡ ያኖር ፡ ነበር ፤
የሚጠብቀውንም ፡ ያኖር ፡ ነበር ፤ ጠንቅቆ ፡
ቈጥሮ ፡ በዚያ ፡ የፈጸማቸው ፡ ሰባቱ ፡ ዘመን ፡
ባለቀ ፡ ጊዜ ።
ሁለተኛውም ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ ሰባተ ፲፯፤
ኛው ፡ ቀን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚሄድ ፡ እባብ ፡
መጥቶ ፡ ወደ ፡ ሔዋን ፡ ቀረበ ። በምድር ፡ ላይ ፡
የሚሄድ ፡ እባብ ፡ ሔዋንን ፡— በገነት ፡ ካሉ ፡
እንጨቶች ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡—
ከእርሱ ፡ አትብሉ ፡ ብሎ ፡ ያዘዛችሁ ፡ ምንድር ፡
ነው ? አላት ።
እርስዋም ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፡— እግዚአብ ፲፰፤
ሔር ፡— በገነት ፡ ካለ ፡ እንጨት ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡
ብሉ ÷ በገነት ፡ መካከል ፡ ካለ ፡ ከዕፀ ፡ በለስ ፡
ፍሬ ፡ ግን ፡ አትብሉ ÷ እንዳትሞቱ ፡ በእጃች
ሁም ፡ አትንኩ ፡ አለን ።
በምድር ፡ ላይ ፡ የሚሄድ ፡ እባብም ፡ ሔዋንን ፡— ፲፱፤
ከእርሱ ፡ በበላችሁበት ፡ ቀን ፡ ዓይነ ፡ ልቡና
ችሁ ፡ እንዲበራ ፡ አምላክም ፡ እንድትሆኑ ፡
ክፉውንና ፡ በጎውንም ፡ እንድታውቁ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ያውቃልና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሞትን ፡
የምትሞቱ ፡ አይደለም ፡ አላት ።
ሔዋንም ፡ እንጨቱ ፡ ያማረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ለማየ ፳፤
ትም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ÷ ፍሬውንም ፡ ለመብላት ፡
ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡
ከእርሱ ፡ ቈርጣ ፡ በላች ። ሰውነትዋንም ፡ በቀደ
መው ፡ በበለሱ ፡ ቅጠል ፡ ሸፈነች ። ለአዳምም ፡
ሰጠችው ፡ እርሱም ፡ በላ ። ዓይኖቹም ፡ አዩ ፤

ዕራቁቱን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የበለስ ፡
ቅጠል ፡ አምጥቶ ፡ ሰፍቶ ፡ ደክ ፡ አድርጎ ፡ ሰውነ
ቱን ፡ ሸፈነ ።
፳፭፤ እግዚአብሔርም ፡ የምድርን ፡ እባብ ፡ ረገመው ፤
ለዘላለሙም ፡ ፈረደበት ።
፳፮፤ ሔዋንንም ፡ የምድር ፡ እባብ ፡ የነገራትን ፡ ነገር ፡
ሰምታ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በልታለችና ፡ ፈረደባት ፤
ኀዘንሽን ፡ ፃር ፡ ጋርሽንም ፡ ፈጽሜ ፡ አበዛዋ
ለሁ ፤ አገነሽ ፡ ተክዘሽ ፡ ልጅን ፡ ውለጂ ፤ ከወለ
ድሽም ፡ በኋላ ፡ መመለሻሽ ፡ ወደ ፡ ባልሽ ፡
ይሁን ፤ እርሱም ፡ ይግዛሽ ፡ አላት ።
፳፯፤ አዳምንም ፡— የሚስትህን ፡ ነገር ፡ ሰምተህ ፡
ከእርሱ ፡ እንዳትበላ ፡ ከዘዝሁህ ፡ ከዚያ ፡ ከዕፀ ፡
በለስ ፡ በልተሃልና ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ምድር ፡ የተ
ረገመች ፡ ትሁን ፤ እሾህና ፡ አሜከላ ፡ ይብቀል
ብህ ፤ አንተ ፡ ከምድር ፡ ተገኝተሃልና ፡ ወደ ፡
ምድርም ፡ ትመለሳለህና ፡ ከእርስዋ ፡ ወደ ፡ ተገ
ኘህባት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡
ጥረህ ፡ ግረህ ፡ እንጀራህን ፡ ብላ ፡ አለው ።
፳፰፤ የቁርበት ፡ ልብስን ፡ አልብሶ ፡ ከገነት ፡ አሰናበ
ታቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩፤ አዳም ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ከገነት ፡ ሲወጣ ፡ በጎ ፡
መዓዛ ፡ አድርጎ ፡ እንዲቀበለው ፡ ዕጣን ፥ ቀን
ዓት ፥ ልባንጃ ፥ ስንቡል ፡ የሚባል ፡ ሽቱ ፡ ፀሐይ ፡
ሲወጣ ፡ ሰውነቱን ፡ በሰወረበት ፡ ቀን ፡ በጥ
ዋት ፡ ዓጠነ ።
፪፤ በዚያችም ፡ ቀን ፡ የእንስሳትና ፡ የአራዊት ፡ ሁሉ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚመላለሰው ፡ ፍጥረትና ፡ የወ
ፎች ፡ የሚንቀሳቀሰውም ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
አፍ ፡ በአንድ ፡ አንደበት ፡ ከመናገር ፡ ተከለከለ ።
ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡
በአንድ ፡ አንደበትና ፡ በአንድ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገሩ ፡
ነበርና ።
፫፤ በኤዶም ፡ ገነት ፡ የሚኖረውን ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡
ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ ከገነት ፡ አስወጥቶ ፡ አሰናበተ ።
፬፤ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በየተፈጥሮ
አቸውና ፡ በየወገናቸው ፡ ወደ ፡ ተፈጠሩላቸው ፡
ቦታ ፡ ተበተኑ ።
፭፤ ለአዳም ፡ ብቻ ፥ ከእንስሳትና ፡ ከአራዊት ፡ ሁሉ ፡
ተለይቶ ፥ ሰውነቱን ፡ ይሸፍን ፡ ዘንድ ፡ ልብስን ፡
ሰጠው ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሥርዓቱን ፡ ፍርድ ፡
የሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰውነታቸውን ፡ እን
ዲሰውሩ ፡ እንጂ ፡ አሕዛብ ፡ እንደሚገለጡ ፡
እንዳይገልጡ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተጻፈ ።
፮፤ በአራተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ሔዋንና ፡ አዳም ፡
ከኤዶም ፡ ገነት ፡ መጥተው ፡ በተፈጠሩበት ፡
ኤልዳ ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ኖሩ ። አዳምም ፡
የሚስቱን ፡ ስም ፡ ሔዋን ፡ አላት ፡ እስከ ፡ መጀ
መሪያው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ድረስ ፡ ልጅ ፡ አልነበሩ
ቸውም ።
፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በግብር ፡ አወቃት ፤ እርሱ ፡ ግን ፡
በኤዶም ፡ ገነት ፡ እንደ ፡ ተማረ ፡ ምድርን ፡ ያር
ሳት ፡ ይቈፍራት ፡ ነበር ።
በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ኢዮቤ ፰፤
ልዩ ፡ ቃየንን ፡ ወለደችው ፤ በአራተኛው ፡
ሱባዔ ፡ አቤልን ፡ ወለደችው ፤ በአምስተኛው ፡
ሱባዔ ፡ ልጅዋን ፡ አዋንን ፡ ወለደቻት ።
እግዚአብሔር ፡ ከአቤል ፡ እጅ ፡ መሥዋዕትን ፡ ፱፤
ተቀብሎአልና ፥ በቃየን ፡ እጅ ፡ ግን ፡ መሥዋ
ዕትን ፡ አልተቀበለምና ፡ በሦስተኛው ፡ ኢዮ
ቤልዩ ፡ መጀመሪያ ፡ ቃየን ፡ አቤልን ፡ በምድረ ፡
በዳ ፡ ገደለው ፤ በግፍ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ እየተከሰሰ ፡
ደሙ ፡ ከምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ጮኸ ።
በግፍ ፡ ስለ ፡ ገደለው ፡ ስለ ፡ አቤል ፡ እግዚአብ ፲፤
ሔር ፡ ቃየንን ፡ ዘለፈው ፤ የወንድሙ ፡ የአቤ
ልን ፡ ደም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ስላፈሰሰ ፡ ዘመኑን ፡
አረዘመበት ፤ በምድርም ፡ ረገመው ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወንድሙን ፡ በተንኰል ፡ የሚገ ፲፩፤
ድል ፡ ሰው ፡ የተረገመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰማይ ፡
ጽላት ፡ ተጻፈ ። ያዩ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡— ይሁን ፡
ይደረግ ፡ አሉ ። አይቶም ፡ ያልተናገረ ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ እርሱ ፡ የተረገመ ፡ ይሁን ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኛ ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ በጨ ፲፪፤
ለማና ፡ በብርሃን ፡ በሁሉም ፡ የሚደረገውን ፡
ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ በፈጣሪያችን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ እንናገር ፡ ዘንድ ፡ መጣን ፡ አሉ ፤
ሔዋንና ፡ አዳምም ፡ ስለ ፡ አቤል ፡ አራት ፡ የዘ
መን ፡ ሱባዔ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ኖሩ ።
በአምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ፲፫፤
ደስ ፡ አለው ። ዳግመኛም ፡ አዳም ፡ ሔዋንን ፡
በግብር ፡ አወቃት ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች
ለት ። ቃየን ፡ ስለ ፡ ገደለው ፡ ስለ ፡ አቤል ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሁለተኛ ፡ ልጅ ፡
ተክልን ፡ ብሎአልና ፡ ስሙን ፡ ሴት ፡ አለው ፤
የአቤልም ፡ ምትክ ፡ ማለት ፡ ነው ።
በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ልጇን ፡ አዙራን ፡ ወለ ፲፬፤
ዳት ፤ ቃየንም ፡ እኅቱ ፡ አዋን ፡ ሚስት ፡ ትሆ
ነው ፡ ዘንድ ፡ አገባት ፤ በአራተኛውም ፡ ኢዮ
ቤልዩ ፡ መጨረሻ ፡ ሄኖንን ፡ ወለደችለት ።
በአምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጀመሪያው ፡ ፲፭፤
ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ቤቶች ፡ ተሠሩ ። ቃየንም ፡ ከተማ ፡ ሠራ ፡ ስም
ዋንም ፡ በልጁ ፡ በሄኖሕ ፡ ስም ፡ ጠራት ።
አዳምም ፡ ሚስቱ ፡ ሔዋንን ፡ በግብር ፡ አወ ፲፮፤
ቃት ። ዳግመኛም ፡ ዘጠኝ ፡ ልጆችን ፡ ወለደች
ለት ።
ሴት ፡ በአምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአምስተ ፲፯፤
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ እኅቱን ፡ አዙራን ፡ ሚስት ፡ አድ
ርጎ ፡ አገባት ።
በአራተኛውም ፡ ዓመት ፡ ሄኖስን ፡ ወለደችለት ። ፲፰፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በመ
ሐላ ፡ ጊዜ ፡ መጥራት ፡ የጀመረ ፡ እርሱ ፡ ነው ።
በሰባተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ፲፱፤
ሄኖስ ፡ ሚስት ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ እኅቱ ፡ ኖአ
ምን ፡ አገባ ፤ በአምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሦስተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ወለደችለት ፤ ስሙንም ፡

ቃይናን ፡ አለው ።
፲፬ በስምንተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መጨረሻ ፡ ቃይ
ናን ፡ እኅቱን ፡ሙአሊሲትን ፡ ሚስት ፡ አድርጎ ፡
አገባ ፤ በዘጠኘኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጀመሪ
ያው ፡ ሱባዔ ፡ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሦስተኛው ፡
ዓመት ፡ ልጅ ፡ ወለደችለት ፤ ስሙንም ፡ መላል
ኤል ፡ አለው ።
፲፭ በአሥረኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡
መላልኤል ፡ ሚስት ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ የአበ
ቱን ፡ ወንድም ፡ የበራኪኤልን ፡ ልጅ ፡ ዲናን ፡
አገባ ። በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡
ዓመት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደችለት ፡ ስሙንም ፡
ያሮድ ፡ አለው ። በዘመኑ ፡ ትጉሃን ፡ የተባሉ ፡
የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ የሚሆኑ ፡ የሴት ፡
ልጆች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የቀና ፡ ሥራንና ፡ ፍር
ድን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ሊያስ
ተምሩአቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወርደዋልና ።
፲፮ በአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ያሮድ ፡
ሚስት ፡ አገባ ፤ ስምዋም ፡ በረከ ፡ ይባላል ፤ ይህ
ችውም ፡ የአበቱ ፡ እኅት ፡ የራሱየል ፡ ልጅ ፡ ናት ፤
በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡
ሚስት ፡ አገባ ፤ በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአራተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ በአምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ወንድ ፡
ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስሙን ፡
ሄኖክ ፡ አለው ፤ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ከተፈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ መጽሐፍ
ንና ፡ ትምህርትን ፡ ጥበብንም ፡ ተማረ ።
፲፯ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በየወራቸው ፡ እንደ ፡ ሥርዓታ
ቸው ፡ የዘመኑን ፡ ጊዜ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
ወራቸው ፡ ሥርዓት ፡ የሰማይን ፡ ምልክት ፡ በመ
ጽሐፍ ፡ ጻፈ ።
፲፰ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ምስክርን ፡ ጻፈ ። ለእስራ
ኤልም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ አሰማባቸው ፤
በሱባዔ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ቊጥሮችን ፡ እርሱ ፡ ተና
ገረ ፤ የዘመኖችንም ፡ ቀን ፡ እርሱ ፡ ተናገረ ፤
ወሮችንም ፡ ሡራ ፤ እኛ ፡ እንደ ፡ ነገርነው ፡ ዘመ
ኖችን ፡ የሚቈጥሩባቸው ፡ ሱባዔዎችንም ፡ ተና
ገረ ። የተደረገውን ፡ ገና ፡ የሚደረገውንም ፡
ቊርጥ ፡ ፍርድ ፡ እስከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
በዘመናቸው ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የሚ
ደረገውን ፡ ሌሊት ፡ በሕልሙ ፡ ራእይን ፡ አየ ፤
አወቀም
፲፱ ለምስክርነት ፡ ጻፈው ። በሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ በየትውልዳቸው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምስ
ክር ፡ ሊሆን ፡ አኖረው ።
፳ በአሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ ሚስት ፡ አገባ ። ስምዋም ፡ አድኒ ፡
ይባላል ፤ ይህችውም ፡ የዳንኤል ፡ ልጅ ፡ የአ
ባቱ ፡ እኅት ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ለእርሱ ፡ ሚስት ፡ ልት
ሆነው ፡ አገባት ።
፳፩ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ ወንድ ፡
ልጅ ፡ ወለደችለት ። ስሙንም ፡ ማቱሳላ ፡ ብሎ ፡
ጠራው ።
፳፪ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ከሚያገለግሉ ፡
መላእክት ፡ ጋር ፡ ስድስት ፡ የኢዮቤላት ፡ ዘመኖ
ችን ፡ ኖረ ። በምድር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በሰማ
ይም ፡ ያለውን ፡ የፀሐይንም ፡ ሥልጣን ፡ አሳ
ዩት ።
ሁሉንም ፡ ጻፈ ። ከሰው ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ በኃጢ ፳፫
አት ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ በደል ፡ ለሠሩት ፡ ለትጉ
ሃን ፡ አዳኘባቸው ። እነዚህ ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡
ጋር ፡ ሊረክሱ ፡ በግብር ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡
ጀምረዋልና ፡ ሄኖክ ፡ በሁሉም ፡ አዳኘባቸው ፡
አሰማባቸው ።
ከሰው ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ። ፳፬
ለጌትነት ፡ ለክብር ፡ ወደ ፡ ኤዶም ፡ ገነት ፡ ወሰ
ድነው ፤ እነሆ ፡ በዚያ ፡ የዘላለም ፡ ቅጣትንና ፡
ቊርጥ ፡ ፍርድን ፡ የአዳምን ፡ ልጆች ፡ ኃጢ
አት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ በዚያ ፡ ይጽፋል ።
ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ልጅ ፡ ያሰማ ፡ ዘንድ ፡ ቊርጥ ፡ ፳፭
ፍርድም ፡ እስከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሰ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡
ለምልክት ፡ ተሰጥቶአልና ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ በኤ
ዶም ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የጥፋት ፡ ውኃን ፡
አመጣ ።
ለእግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አራት ፡ በታ ፳፮
ዎች ፡ አሉትና ፤ እርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚ
ቀበለው ፡ ዕጣን ፡ በሠርክ ፡ አስቀድሞ ፡ በቀትር ፡
ጊዜ ፡ መቅደስን ፡ ዐጠነ ፤ እርሱ ፡ እነዚህም ፡ የኤ
ዶም ፡ ገነትና ፡ የምሥራቁ ፡ ደብር ፤ ይህ ፡ ዛሬ ፡
አንተ ፡ ያለህበትም ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ናቸው ፤
ይህን ፡ ዓለም ፡ ለማንጻት ፡ በሚደረግ ፡ በአዲስ ፡
ሕግ ፡ ይነጻል ።
ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ምድር ፡ ከኃጢአትና ፡ ከበ ፳፯
ደል ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡
ዘመን ፡ ትነጻለች ።
በአሥራ ፡ አራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ማቱሳላ ፡ ፳፰
ሚስቱን ፡ አድናን ፡ አገባ ፤ ይህችውም ፡ የአበቱ ፡
እኅት ፡ ልጅ ፡ የአዝራኤል ፡ ልጅ ፡ ናት ።
በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአንደኛው ፡ ዘመን ፡ ፳፱
ልጅ ፡ ወለደ ። ስሙንም ፡ ላሜህ ፡ አለው ።
በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተ ፴
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ ላሜህ ፡ ሚስት ፡ አገባ ፤ ስምዋም ፡
ቤቴናስ ፡ ይባላል ፤ ይህችውም ፡ የአበቱ ፡ የእ
ኅት ፡ ልጅ ፡ የበራኪኤም ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ሚስት ፡
ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ አገባት ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

በዚህም ፡ ሱባዔ ፡ ልጅ ፡ ወለደችለት ፤ ከኀ ፩
ዘኔ ፡ ሁሉና ፡ ከሥራዬ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከረገማት ፡ ምድር ፡ የሚያረጋጋኝ ፡ ነው ፡ ሲል ፡
ስሙን ፡ ኖኅ ፡ አለው ።
በአሥራ ፡ ዘጠኝኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መጨረሻ ፡ ፪
በሰባተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡
አዳም ፡ ሞተ ። ልጆቹም ፡ ሁሉ ፡ በተፈጠረበት ፡
ምድር ፡ ቀበሩት ።
እርሱም ፡ አስቀድሞ ፡ በምድር ፡ ተቀበረ ። ፫
ከሺህ ፡ ዓመትም ፡ ሰባ ፡ ዓመትን ፡ አጐደለ ፤

ሮሆችውም ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ እንደ ፡ አንዲት ፡
ቀን ፡ ነበረች ።
፬፡ ከእርሱ ፡ በበላችሁበት ፡ ቀን ፡ ትሞታላችሁ ፡
ተብሎአልና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ክፉ ፡ እውቀትን ፡
የሚያሳውቅ ፡ ዕፅን ፡ ስለ ፡ በላ ፡ ተጻፈ ፡ በእር
ስዋ ፡ ሞቶአልና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የአንዲቱን ፡
ቀን ፡ ዓመቶች ፡ አልጨረሰም ።
፭፡ በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መጨረሻ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡
በኋላ ፡ ቃየን ፡ ሞተ ፡ ቤቱ ፡ በላዩ ፡ ተናደ ፡ በቤ
ቱም ፡ ውስጥ ፡ በድንጋዮቹ ፡ ሞተ ። አቤልን ፡
በድንጋይ ፡ ገድሎታልና ፡ በእውነት ፡ ፍርድ ፡
በድንጋይ ፡ ሞተ ።
፮፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በልንጀራውን ፡ በገደለበት ፡
መሣሪያ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡
ተጻፈ ።
፯፡ በሀያ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ኖኅ ፡ ሚስት ፡
አገባ ። ስምዋም ፡ አምዛራ ፡ ይባላል ። ይህ
ችውም ፡ የእኅቱ ፡ ልጅ ፡ የራዚኤል ፡ ልጅ ፡
ናት ፡ ሚስት ፡ ልትሆነው ፡ አገባት ። በመጀ
መሪያው ፡ ዓመት ፡ በአምስተኛው ፡ ሱባኤ ፡
በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ሴምን ፡ ወለደችለት ።
፰፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡
ያፌትን ፡ ወለደችለት ።
፱፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይበዙ ፡ ዘንድ ፡
በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡
ተወለዱላቸው ። የእግዚአብሔር ፡ መላእክ
ትም ፡ በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአንዲቱ ፡ ዓመት ፡
እነዚህን ፡ አዩአቸው ። እነዚያ ፡ ላዩአቸው ፡
መልክ ፡ መልካሞች ፡ ናቸውና ፡ ከመረጡአ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ ሚስት ፡ ሊሆኑአቸው ፡ አገቡአ
ቸው ፤ ወንዶች ፡ ልጆችንም ፡ ወለዱላቸው ፡
እነዚህም ፡ ረዓይት ፡ ናቸው ።
፲፡ ኃጢአትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በዛች ፤ ከሰው ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አራዊትና ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ እስከ ፡
ሰማይ ፡ ወፎችም ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እስከሚኖረ
ውም ፡ ሁሉ ፡ ድረስ ፡ የሥጋ ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ
ውን ፡ አከፉ ። ሁሉም ፡ ሥርዓታቸውንና ፡ ሥራ
ቸውን ፡ አጠፉ ። እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይበላሉ ፡
ጀመር ። ኃጢአትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በዛች ።
ለሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ የክፉ ፡ አሳብ ፡ ተሰጣቸው ፤
በዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ነገር ፡ ተደረገ ።
፲፩፡ እግዚአብሔር ፡ ምድርን ፡ እነሆ ፡ ጠፍታ ፡ አያት ፤
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓትን ፡ አጠፋት ፡ ሁሉም ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በዚሁ ፡ ዓለም ፡ ያለ
ውን ፡ ሁሉ ፡ አከፉት ፡ ሰውንና ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ የፈጠረውን ፡ የሥጋ ፡ ወገንን ፡ ሁሉ ፡
አጠፋዋለሁ ፡ አለ ።
፲፪፡ ኖኅ ፡ ብቻ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በለምዋልነ
ትን ፡ አገኘ ። ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የሰደዳቸውን ፡
መላእክቱን ፡ ግን ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ሊዩቶ ፡
ፈጽሞ ፡ ያጠፉቸው ፡ ዘንድ ፡ ተቆጣ ። በምድ
ርም ፡ ውስጥ ፡ አስረን ፡ እንገዛቸው ፡ ዘንድ ፡
አዘዘን ።
፲፫፡ እነርሱም ፡ እነሆ ፥ በመካከላቸው ፡ ብቻቸውን ፡
ተማዘዋል ፡ ከፊቱ ፡ በሰይፍ ፡ ያጠፉቸው ፡ ዘንድ ፡
ከሰማይ ፡ በታችም ፡ ያርቃቸው ፡ ዘንድ ፡ በል
ጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ወጣ ።
እነርሱ ፡ ሥጋውያን ፡ ናቸውና ፡ ረድኤቱ ፡ ፲፬፡
በሰው ፡ ላይ ፡ አያድርም ። ዘመናቸውም ፡ መቶ ፡
ሀያ ፡ ዘመን ፡ ይሁን ፡ አለ ።
እያንዳንዳቸው ፡ በልንጀሮቻቸውን ፡ ይገድሉ ፡ ፲፭፡
ዘንድ ፡ በመካከላቸው ፡ ሰይፍን ፡ ሰጣቸው ።
ሁሉም ፡ በሰይፍ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ይህ
ንን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፤ ከምድርም ፡
ጠፉ ፤ አባቶቻቸው ፡ ግን ፡ ጥፋታቸውን ፡ ያዩ ፡
ነበር ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ባፈረሱ ፡ ፲፮፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ሊደረግ ፡ የጸናች ፡
ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ እስከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ ይገዛሉ ። ሥራቸውም ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተገለጠ ፡ ነው ፤ ከበታቸ
ውም ፡ ሁሉን ፡ አጠፉ ፤ በኃጢአታቸው ፡ ሁሉ ፡
ያልተፈረደበት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ አልቀ
ረም ።
በሰውነታቸው ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ፲፯፡
እንዳይበድሉ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ደግና ፡ እው
ነተኛ ፡ ኖኅን ፡ ፈጠረላቸው ፤ ሁሉም ፡ በየወ
ገኑ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ።
የሁሉም ፡ ቅጣት ፡ ተዘጋጀ ፡ በሰማይም ጽላት ፡ ፲፰፡
ተጻፈ ። የሚሰወር ፡ በደልም ፡ የለም ፤ ሁሉም ፡
ጸንተው ፡ ይኖሩበት ፡ ዘንድ ፡ ከተሠራችላቸው ፡
ሥራቸው ፡ የተለወጡ ፡ ናቸው ።
ጸንተው ፡ በይኖሩበት ፡ ለፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ለየ ፡ ፲፱፡
ወገኑም ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ተጻፈ ። በምድርና ፡
በሰማይ ፡ በጨለማና ፡ በብርሃን ፡ በሲኦልም ፡
በጥልቅም ፡ በጨለማም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የተሰ
ወረ ፡ የለም ።
መቻያቸው ፡ ሁሉ ፡ የተዘጋጀ ፡ ፈጽሞም ፡ የተ ፡ ፳፡
ጻፈ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ገናናውን ፡ እንደ ፡
ገናንነቱ ፡ ታናሹንም ፡ እንደ ፡ ታናሽነቱ ፡ አን
ዱንም ፡ አንዱንም ፡ እንደ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይፈር
ድበታል ።
እርሱ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የሚያደላ ፡ አይደለም ። ፳፩፡
ለአንዱም ፡ ለአንዱም ፡ ፍርድ ፡ እፈርዳለሁ ፡
ባለ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ መማለጃን ፡ የሚቀበል ፡ አይ
ደለም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አን
ዱም ፡ አንዱም ፡ መማለጃ ፡ ቢሰጥ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡
አያደላም ፡ የእውነት ፡ ዳኛ ፡ ነውና ፡ ከእርሱ
መማለጃ ፡ አይቀበልም ።
ይህ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ፳፪፡
ተጻፈ ። በእውነት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ከተመለሱ ፡
በደላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ይላቸዋል ። ኃጢ
አታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ያስተሰርይላቸዋል ።
ከኃጢአታቸው ፡ ሁሉ ፡ የተመለሱ ፡ ሰዎች ፡ ፳፫፡
ሁሉ ፡ በዓመት ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይቅር ፡
ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ተጻፈ ፥ ተዘጋጀ ። ከጥፋት ፡
አስቀድሞ ፡ ምክራቸውንና ፡ ሥርዓታቸውን ፡
በጠፉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተጻፈ ።

፳፬፤ በእርሱ ፡ ደግነት ፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ ስላዳናቸው ፡
ልጆቹ ፡ እርሱ ፡ በለምዋልነትን ፡ አግኝቶአልና ።
ከኖኅ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ እነርሱ ፡ በለምዋልነትን ፡
አላገኙም ። በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ልቡ ፡ እውነ
ተኛ ፡ ናትና ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ ከተ
ሠራለት ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ አልወጣም ።
፳፭፤ እግዚአብሔርም ፡— በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አራዊትና ፡ እስከ ፡
እንስሳ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ እስከሚኖረውና ፡
እስከ ፡ ወፎችም ፡ ድረስ ፡ ይጥፋ ፡ አለ ።
፳፮፤ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ ኖኅንም ፡
ለእርሱ ፡ መርከብን ፡ እንዲሠራ ፡ አዘዘው ።
፳፯፤ ኖኅም ፡ ዓመታት ፡ በሚቈጠሩበት ፡ በሁለተ
ኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአምስተኛው ፡ ሱባኤ ፡
በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ እንዳዘዘው ፡ ሁሉ ፡
መርከብን ፡ ሠራ ።
፳፰፤ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ በሁለተኛው ፡ ወር ፡
እስከ ፡ አሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
እርሱ ፡ ገባ ። ያገባንለትም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መር
ከብ ፡ ገባ ።
፳፱፤ እግዚአብሔርም ፡ በአሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡
ማታ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡን ፡ በውጪ ፡ ዘጋው ፤
እግዚአብሔር ፡ ሰባቱን ፡ የሰማይ ፡ ሽሽቴ ፡ ከፈተ ፤
ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ጥልቁንም ፡ ውኃ ፡ በሰበ ፡ ስቍረት ፡
አወጣው ።
፴፤ ሸሸቴዎችም ፡ ከሰማይ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አርባ ፡
ሌሊት ፡ ዝናብን ፡ ያወርዱ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ።
፴፩፤ የጥልቁም ፡ ምንጮች ፡ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ውኃን ፡
እስኪሞላ ፡ ድረስ ፡ ውኃዎችን ፡ ያወጡ ፡ ነበር ፤
ውኃዎችም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በዙ ፤ ውኃው ፡
በረጅሙ ፡ ተራራ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ አም
ስት ፡ ክንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።
፴፪፤ ውኃዎች ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ ። መርከቢቱም ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለች ። በውኃውም ፡
ላይ ፡ ትመላለስ ፡ ነበር ፤ ውኃዎችም ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ወር ፡ ማለት ፡ መቶ ፡
አምሳ ፡ ቀን ፡ ጸንተው ፡ ነበር ። መርከቢቱም ፡
ሄደች ÷ ከአራራት ፡ ተራራዎችም ፡ በአንዱ ፡
ሉባር ፡ በሚባል ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ዐረፈች ።
፴፫፤ በአራተኛውም ፡ ወር ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ የጥልቁ ፡
ምንጮች ፡ ተገቱ ። የሰማዩም ፡ ሸሸቴ ፡ ተገታ ።
፴፬፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ የምድሩ ፡ ጥልቅ ፡
አፍ ፡ ሁሉ ፡ ተከፈተ ። ውኃዎችም ፡ ወደ ፡
ታችኛይቱ ፡ ጥልቅ ፡ ይወርዱ ፡ ጀመር ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩፤ በአሥረኛው ፡ ወር ፡ መባቻም ፡ የተራሮች ፡
ራሶች ፡ ታዩ ፤ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻም ፡
ምድር ፡ ታየች ÷ ውኃዎችም ፡ በአምስተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡
ደረቁ ። በአሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ በሁለ
ተኛው ፡ ወር ፡ ምድር ፡ ደረቀች ።
፪፤ በሀያ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ መርከቢቱን ፡ ከፈታት ፤
ከውስጥዋም ፡ ወፎችንና ፡ አውሬዎችን ፡ ተሐ
ውስ ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ አሰናበተ ። በሦስተ
ኛውም ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ኖኅ ፡ ከመርከብ ፡ ወጣ ።
በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፤ በም
ድርም ፡ ላይ ፡ ታየ ። ከኖኅ ፡ ጋር ፡ በመርከብ ፡
ካሉ ፡ በቀር ፡ በእርስዋ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ጠፍቶ
አልና ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ ሠውቶ ፡ በደሙ ፡
የዓለሙን ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ አስተሰረየ ።
ስቡንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ አጤሰ ። ላምን ፡ ፫፤
ፍየልንና ፡ የበግ ፡ አውራን ፡ ርግብንና ፡ ዋኖስ
ንም ፡ ሠውቶ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ስቡን ፡ አሻ
ተተ ። በዘይት ፡ የታሸ ፡ መሥዋዕትንም ፡ በእ
ርሱ ፡ ላይ ፡ ጨመረ ።
ደሙንም ፡ አምጥቶ ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ ቈንዶ ፡ በር ፬፤
በሬ ፡ ጨመረበት ። እግዚአብሔር ፡ የሚወደ
ውን ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ አቀረበ ።
እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድርጎ ፡ ተቀበ ፭፤
ለው ፤ ምድር ፡ ጸንታ ፡ በምትኖርበት ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ፡ የጥፋት ፡ ውኃ ፡ ምድርን ፡ እንዳያጠፋ ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ መሐላን ፡ ተማማለ ። አዝመ
ራና ፡ ዘር ፡ እንዳይለወጥ ÷ ክረምትና ፡ በጋ ፡
ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ለዘላለሙ ፡
ፈጽመው ፡ እንዳይለውጡ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
መሐላን ፡ ተማማለ ።
እናንተም ፡ ብዙ ÷ በምድርም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ፮፤
ሁኑ ፤ በላይዋም ፡ ብዙ ÷ ለበረከትም ፡ ሁኑ ፤
በመንቀጥቀጣችሁና ፡ በመፍራታችሁ ፡ መካ
ከል ፡ በባሕርና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ባሉ ፡ አራዊት ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ፍርሃትን ፡ አመጣለሁ ።
ከብቶችንና ፡ አውሬዎችን ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ፯፤
ዓለም ፡ የሚኖረውንና ፡ በክንፍ ፡ የሚበሩትን ፡
በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ዓሣዎችንም ÷ እነሆ ÷
ሰጠኋችሁ ፤ ሁሉን ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
እህል ፡ ምግብ ፡ ሊሆናችሁ ፡ ሰጠኋችሁ ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ደም ፡ የነፍስ ፡ ማደሪያ ፡ ነውና ፡ ፰፤
ከሰውነታችሁ ፡ መካከል ፡ ደማችሁን ፡ እንዳል
ፈልግ ፡ ከደም ፡ ጋር ፡ ብርንዶ ፡ አትብሉ ።
ከሰው ፡ እጅ ፡ የአውሬዎችን ፡ ደም ፡ እመረም
ራለሁ ። የሰውንም ፡ ደም ፡ ከሰዎች ፡ እጅ ፡ እመ
ረምራለሁ ፤ የሰውን ፡ ደም ፡ ያፈሰሰ ፡ ደሙ ፡
ይፈሳል ፤ እግዚአብሔር ፡ አዳምና ፡ ሔዋንን ፡
በእርሱ ፡ መልክ ፡ ፈጥሮአቸዋልና ፡ በሰው ፡ እጅ ፡
የፈሰሰ ፡ የሰውን ፡ ደም ፡ እመረምራለሁ ፤ እና
ንተም ፡ ብዙ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡
ሁኑ ፡ አላቸው ።
ልጆቹና ፡ ኖኅም ፡ በሥጋው ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ብር ፱፤
ንዶውን ፡ ሁሉ ፡ እንዳይበሉ ፡ ማሉ ፤ ይህ ፡
ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
በዚህ ፡ ወራት ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር ፡
ፈጣሪ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሐላን ፡ ተማ
ማለ ።
ስለዚህ ፡ ነገር ÷ ሙሴ ÷ አንተም ፡ ከእስራኤል ፡ ፲፤
ልጆች ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ በተራራ ፡ በመ
ሐላ ፡ ላይ ፡ መሐላን ፡ ትማማል ፡ ዘንድ ፡ ተናገ
ረህ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡

ጋር ፡ ስለ ፡ ትማማለበት ፡ መሐላ ፡ ነገር ፡ በላያ
ቸው ፡ ደምን ፡ ትረጫለህ ።
፲፩ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
የወፎችንና ፡ የአውሬዎችን ፡ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ እን
ዳትበሉ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ትጠብቁአት ፡ ዘንድ ፡
ይህች ፡ ምስክር ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የተጻፈች ፡
ናት ።
፲፪ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
የአውሬን ፡ የወፎችንና ፡ የከብቶችን ፡ ሥጋ ፡
ብርንዶውን ፡ የበላ ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ይጠፋል ፤
ልጆቹም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋሉ ።
፲፫ ስማቸው ፡ ጸንቶ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ልጆቻቸውም ፡
በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በፈጣሪያችን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ብርንዶውን ፡
ሁሉ ፡ እንዳይበሉ ÷ ሙሴ ÷ አንተም ፡ የእስራ
ኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ።
፲፬ በቀኑ ፡ ሁሉ ፡ በመሠዊያው ፡ አንጻር ፡ በደም ፡
ስለ ፡ እናንተ ፡ እየለመኑ ፡ እንዲኖሩ ፡ ለልጅ ፡
ልጅ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ የዘላለም ፡ ሕግ ፡ ነውና ፡
ለዚህ ፡ ሕግ ፡ የዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ። ይጠ
ብቁት ፡ ዘንድ ፡ እንዳይጠፉም ፡ ማታና ፡ ጥዋት ፡
ስለ ፡ እነርሱ ፡ ሁልጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ኃጢአታቸውን ፡ ያስተሰርያሉ ።
፲፭ ዳግመኛ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥፋት ፡ እንዳይደረግ ፡
ለልጆቹና ፡ ለኖኅ ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ምልክት ፡
ሰጣቸው ፤ ምድርን ፡ ለማጥፋት ፡ ዳግመኛ ፡
በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ እንዳ
ይደረግ ፡ ለዘላለሙ ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ምልክት ፡
ሊሆን ፡ ብርሃኑን ፡ በደመና ፡ ውስጥ ፡ ሥሎ ፡
አሳየ ።
፲፮ ፈጽሞ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ጽኑ ፡ መሐላ ፡ በዓመት ፡
በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ የቍ
ጥር ፡ በዓልን ፡ የሚያደርጉ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተሠራ ፤ በሰማይ ፡ ጽላትም ፡
ተጻፈ ።
፲፯ ይህችም ፡ በዓል ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ከተፈጠረ
በት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡
በሰማይ ፡ ስትሠራ ፡ ኖረች ፤ ይኸውም ፡ ሀያ ፡
ሰባት ፡ ኢዮቤልዩና ፡ አምስት ፡ የዓመት ፡ሱባዔ ፡
ነው ፤ ልጆቹና ፡ ኖኅም ÷ ኖኅ ፡ እስከሚሞት
በት ፡ ቀን ፡ ድረስ ÷ ሰባት ፡ ኢዮቤልዩና ፡ አንድ ፡
የዓመት ፡ ሱባዔ ፡ ጠበቁት ።
፲፰ ኖኅ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አብርሃም ፡
ዘመን ፡ ድረስ ፡ ልጆቹ ፡ ሕግን ፡ አፈረሱ ÷ ብር
ንዶውንም ፡ በሉ ። አብርሃም ፡ ብቻ ፡ ሕግን ፡
ጠበቀ ÷ ያዕቆብና ፡ ይስሐቅም ፡ እስከ ፡ አንተ ፡
ዘመን ፡ ድረስ ፡ ጠበቁት ። በዚህ ፡ ተራራ ፡ እስ
ከደረሳቸው ፡ ድረስ ፡ በዘመንህም ፡ የእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ሕግን ፡ ዘነጉ ።
፲፱ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ፤
ይህችንም ፡ በዓል ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ በዘ
መናቸው ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁአት ። በሱባዔ ፡ የም
ትደረግ ፡ በዓል ፡ ናትና ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
በዚህ ፡ ወር ፡ ይህችን ፡ በዓል ፡ ያድርጉ ፡
የመጀመሪያውም ፡ አገዛዝ ፡ የሚሰበሰብበት ፡ ፳
በዓል ፡ ናትና ፡ በዓል ፡ ያድርጉ ። ይህችውም ፡
ሁለት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ የሚያደርጉበት ፡ ቀን ፡
ናት ። በየጊዜዋ ፡ ታደርጋት ፡ ዘንድ ፡ በጻፍሁ
ልህ ፡ በዚህ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡
ጽፌልሃለሁና ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ሥራዋ ፡ እንደ ፡
ተጻፈ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ከዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
የሚያደርጉአት ፡ ይህች ፡ በዓል ፡ ለሰውና ፡ ለመ
ላእክት ፡ ናት ።
የታሰቡ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ÷ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፳፩
በየወገናቸው ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡
ወር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያደርጉአት ፡ ዘንድ ፡ ቍርበ
ኑንም ፡ ነገርሁህ ።
በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻ ÷ በአራተኛው ፡ ፳፪
ወር ፡ መባቻ ÷ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ መባቻ ÷
በአሥረኛውም ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ እነዚህ ፡ የመታ
ሰቢያ ፡ ቀኖች ፡ ናቸው ። ለአራተኛውም ፡ ክፍለ ፡
ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ያላቸውም ፡ ቀኖች ፡ ናቸው ፤
እነዚህም ፡ ለስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ የተጻፉ ፡
የተዘጋጁ ፡ ናቸው ።
እነርሱም ፡ ለእርሱ ፡ መታሰቢያ ፡ እስኪሆኑ ፡ ፳፫
ድረስ ፡ ኖኅ ፡ በዓላትን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ለዘላለም ፡
ሠራቸው ።
በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ለራሱ ፡ መርከ ፳፬
ብን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ታዘዘ ፤ በእርስዋም ፡
ምድር ፡ ደረቀች ፡ መስኮቱንም ፡ ከፍቶ ፡ ምድ
ርን ፡ አየ ።
በአራተኛውም ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ፳፭
የጥልቁ ፡ ምንጭ ፡ ደረቀ ። የሰማዩም ፡ ሻሻቴ ፡
ተገታ ።
በሰባተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ በምድር ፡ ያለ ፡ ፳፮
የምንጭ ፡ ጉድጓድ ፡ ሁሉ ፡ ተከፈተ ፤ ውኃዎ
ችም ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ጥልቅ ፡ ይወርዱ ፡
ጀመር ።
በአሥረኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ የተራሮች ፡ ራሶች ፡ ፳፯
ታዩ ÷ ኖኅም ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡
እነርሱን ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ መታሰቢያ ፡
ሊሆኑ ፡ በዓላት ፡ አደረጋቸው ። እነዚህ ፡ እን
ዲህ ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ጽላ
ትም ፡ ያወጡአቸዋል ።
ከእነርሱ ፡ አንዲቱም ፡ አንዲቱም ፡ አሥራ ፡ ፳፰
ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ ናቸው ፤ ከመጀመሪያይቱ ፡
እስከ ፡ ሁለተኛይቱ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛይቱ ፡ እስከ ፡
አራተኛይቱ ፡ አሥራ ፡ ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ ናቸው ።
ትእዛዝ ፡ የተጻፈባቸው ፡ ቀኖች ፡ ሁሉ ፡ ቀን ፡ ፳፱
የሚቈጠርባቸው ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ሱባዔ ፡ ይሆ
ናሉ ። ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ዓመቱ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡
ተቈጥሮ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተጻፈ ። ከዓመት ፡
እስከ ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡
ሦስት ፡ ዓመት ፡ መተላለፍ ፡ የለውም ።
አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በዓመቱ ፡ ፴
በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አራት ፡
ቀንን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ እዘዛቸው ፡ የተቈጠረ ፡
ዓመትንም ፡ ይሁን ። ጊዜውንም ፡ ከቀኑ ፡ ከበ

ዓሉ ፡ አሳልፈው ፡ አጠፉት ። ሁሉ ፡ እንደ ፡ ምስ
ክርነታቸው ፡ ይደርስባቸዋልና ፡ ቀኑን ፡ እያስ
ቀሩ ፡ በዓሉንም ፡ እያጥፉ ።
፴፩፤ ቢተላለፉአቸው ÷ እንደ ፡ እርሱ ፡ ትእዛዝም ፡
ባያደርጉአቸው ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ጊዜ
ዎቻቸውን ፡ ያጠፋሉ ።
፴፪፤ ዓመታትም ፡ ከዚህ ፡ ወደዚያ ፡ ይለዋወጣሉ ÷
ጊዜዎችም ፡ ይጠፋሉ ÷ ዓመታቱም ፡ ይለዋወ
ጣሉ ÷ ሥርዓታቸውንም ፡ ያፈርሳሉ ፤ የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ይዘነጋሉ ። የዓመ
ቶችንም ፡ ቍጥር ፡ አያገኙም ፤ ጊዜውንና ፡
የወሩን ፡ መባቻ ፡ ሱባዔውንም ፡ የዘመኑን ፡
ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ያፈርሳሉ ።
፴፫፤ እኔ ፡ አውቃለሁና ÷ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እኔ ፡
እነግርሃለሁ ÷ መጽሐፉ ፡ በፊቴ ፡ እንዲህ ፡ ተጽ
ፎአልና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የምነግርህ ፡ ከልቤ ፡ አው
ጥቼ ፡ አይደለም ፤ በዓሉን ፡ እንዳይረሱ ፡ ከሳቱ ፡
በኋላ ፡ አእምሮአቸውንም ፡ ካጡ ፡ በኋላ ፡ የቀኑ ፡
ቍጥር ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተጻፈ ።
፴፬፤ እርስዋ ፡ ጊዜዎችን ፡ ትለውጣለችና ፤ ከዓመታ
ቱም ፡ ለዓመት ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ትቀድማለችና ፤
በጨረቃ ፡ አጎዳደል ፡ ጨረቃን ፡ የሚመለከቱ ፡
ይሆናሉ ።
፴፭፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሥርዓትን ፡ ከለወጡ ፡ በኋላ ፡
ዓመታት ፡ ይመጡላቸዋል ፤ ምስክር ፡ የምት
ሆን ፡ ቀንንም ፡ የተናቀች ፡ ያደርጋሉ ። ንጹሑን ፡
ቀን ፡ ሁሉ ፡ ከረከሰው ፡ ቀን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ያደ
ርጋሉ ፤ ሱባዔዎችንና ፡ ወራቶችን ፡ ቍጥሩንና ፡
በዓሉንም ፡ ይስታሉና ፤ የረከሰውንም ፡ ቀን ፡
ከንጹሑ ፡ ቀን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ያደርጋሉ ።
፴፮፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ አዝዝሃለሁ ፤ ልጆችህ ፡
አንተ ፡ ከሞትህ ፡ በኋላ ፡ ሥርዓትን ፡ ይለውጣ
ሉና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አራቱን ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡
ዓመትን ፡ እንዳያደርጉ ፡ ታሰማቸው ፡ ዘንድ ፡
አሰማሃለሁ ።
፴፯፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሱባዔውንና ፡ የወሩን ፡ መባቻ ፡
በዓሉንና ፡ ጊዜውንም ፡ ይስታሉ ፤ ከሰው ፡ ሁሉ ፡
ጋር ፡ ብርንዶውን ፡ ሁሉ ፡ ይበላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፤ በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተኛው ፡ ሱባዔ ፡
በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ መርከብ ፡ ባረፈችበት ፡
ስሙ ፡ ሉባር ፡ በሚባል ፡ ከአራራት ፡ ተራሮች ፡
በአንዱ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ኖኅ ፡ ወይንን ፡ ተከለ ።
፪፤ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በሰባተ
ኛው ፡ ወር ፡ ፍሬውን ፡ ለቀመ ። ከእርሱ ፡ ጠጅ ፡
ጥሎ ፡ በዕቃ ፡ አኖረው ÷ እስከ ፡ አምስተኛው ፡
ዓመት ፡ እስከ ፡ መጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
ጠበቀው ።
፫፤ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ይህችን ፡ ቀን ፡
በደስታ ፡ በዓል ፡ አደረገ ÷ ለእግዚአብሔርም ፡
መሥዋዕትን ፡ ሠዋ ። የራሱን ፡ ኃጢአት ፡ ያስ
ተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ ከላሞች ፡ አንድ ፡ ወይፈንን ÷
አንድ ፡ የበግ ፡ አውራን ÷ ዓመት ፡ የሆናቸው ፡
ሰባት ፡ በጎችን ÷ አንድ ፡ የፍየል ፡ ጠቦትንም ፡
ሠዋ ።
ስለ ፡ ልጆቹም ፡ አስቀድሞ ፡ ጠቦትን ፡ ሠዋ ፤ ፬፤
ከደሙም ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡
በሥጋው ፡ ላይ ፡ አኖረ ። መሥዋዕት ፡ በሠዋ
በት ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ስቡን ፡ ሁሉ ፡ አጤሰ ።
የበግ ፡ አውራንና ፡ ላሙን ፡ በጎቹንም ፡ ሠውቶ ፡
ሥጋቸውን ፡ ሁሉ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አኖረ ።
በዘይት ፡ የታሸ ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ሁሉ ፡ በላ
ያቸው ፡ አኖረ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ በእ ፭፤
ሳቱ ፡ ላይ ፡ ወይኑን ፡ ረጨ ። አስቀድሞ ፡ ዕጣ
ኑን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አኖረ ፤ እግዚአብ
ሔር ፡ የሚወደውንም ፡ በጎ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ።
መሥዋዕቱም ፡ ወደ ፡ ፈጣሪ ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ዐረገ ፤ ከዚህ ፡ ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ እርሱን ፡
ደስ ፡ አለው ። ልጆቹንም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።
በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ገብቶ ፡ ሰክሮ ፡ ፮፤
ተኛ ፤ በድንኳኑም ፡ ተኝቶ ፡ ዕርቃኑን ፡ ጣለ ።
ካምም ፡ አባቱ ፡ ኖኅን ፡ ዕራቁቱን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፯፤
አይቶ ፡ ወጥቶ ፡ በውጪ ፡ ላሉ ፡ ለሁለቱ ፡ ወን
ድሞቹ ፡ ነገራቸው ።
ሴም ፡ ልብሱን ፡ ይዞ ፡ ተነሣ ፤ ያፌትና ፡ እር ፰፤
ሱም ፡ ልብሳቸውን ፡ ከጫንቃቸው ፡ አውርደው ፡
አለበሱት ÷ ፊታቸውንም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መል
ሰው ፡ የአባታቸውን ፡ ኃፍረት ፡ ሸፈኑ ።
ኖኅ ፡ ከእንቅልፉ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ታናሹ ፡ ልጁ ፡ ፱፤
በእርሱ ፡ ላይ ፡ ያደረገበትን ፡ ሁሉ ፡ አወቀ ÷
ልጁንም ፡ ረገመው ፤ የተረገመ ፡ ከንዓን ፡ ለወ
ንድሞቹ ፡ ተገዥ ፡ ባሪያን ፡ ይሁን ፡ አለ ።
ሴምን ፡ መረቀው ፤ የሴም ፡ ፈጣሪ ፡ ይመስገን ፡ ፲፤
አለ ÷ ከነዓንም ፡ ባሪያው ፡ ይሁን ፤ እግዚአ
ብሔርም ፡ የያፌትን ፡ አገር ፡ ያስፋለት ፡ አለ ፤
እግዚአብሔርም ፡ በሴም ፡ ድንኳን ፡ ይደር ፡
ከነዓንም ፡ ባሪያው ፡ ይሁን ፡ አለ ።
ካምም ፡ ታናሹን ፡ ልጁን ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ረገ ፲፩፤
መው ፡ አወቀ ። ልጁን ፡ ረግሞታልና ፡ ለእርሱ ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ሆነበት ፤ እርሱ ፡ ከአባቱ ፡ ተለየ ፤
ልጆቹም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡
ሚስጥሮምና ፡ ኵሽ ፡ ከነዓንና ፡ ፉጥ ፡ ናቸው ።
ኖኅ ፡ አገርን ፡ አቀና ፡ የአገሪቱንም ፡ ስም ፡ በሚ
ስቱ ፡ ስም ፡ አኤልታማክ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ።
ያፌትም ፡ አይቶ ፡ በወንድሙ ፡ ቀና ፤ እርሱም ፡ ፲፪፤
አገርን ፡ አቀና ፡ ስምዋንም ፡ በሚስቱ ፡ ስም ፡
አዶታኔሴስ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ።
ሴም ፡ ግን ፡ ከአባቱ ፡ ከኖኅ ፡ ጋር ፡ ተቀመጠ ፤ ፲፫፤
በአባቱም ፡ ቃል ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ አገርን ፡
አቀና ÷ እርሱም ፡ በሚስቱ ፡ በሴዴቄተልባብ ፡
ስም ፡ ስምዋን ፡ ጠራ ።
እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ አገሮች ÷ እነሆ ÷ በሉባር ፡ ፲፬፤
ተራራ ፡ አቅራቢያ ፡ ናቸው ። ሴዴቄተልባብ ፡
በተራራው ፡ አንጻር ፡ በምሥራቅ ፡ ናት ÷
አኤልታማክም ፡ በሰሜን ፡ አንጻር ፡ ናት ÷ አዶ
ታኔሴስም ፡ በምዕራብ ፡ ናት ።

፲፭፡ እነዚህ ፡ የሴም ፡ ልጆችም ፡ ኤላምና ፡ አሱር ፡
አርፋክስድ ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ ጥፋት ፡
ከተደረገበት ፡ ከአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡
የተወለዱ ፡ ናቸው ። የሉድ ፡ ልጅ ፡ አራምም ፡
ኢያፌትን ፡ ወለደ ÷ ኢያፌትም ፡ ማጎግንና ፡
ጎሜርን ፡ ወለደ ፤ ኢዮአያም ፡ ቶቤልንና ፡ ሞስ
ክፍን ፡ ቱሬስን ፡ ወለደ ። የኖኅ ፡ ልጆች ፡ እነ
ዚህ ፡ ናቸው ።
፲፮፡ ኖኅም ፡ በሀያ ፡ ስምንተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የል
ጆቹን ፡ ልጆች ፡ እውነት ፡ ሥራን ፡ ይሠሩ ፡
ዘንድ ÷ የሰውነታቸውንም ፡ ኃፍረት ፡ ይሸፍኑ ፡
ዘንድ ÷ የፈጠራቸው ፡ እግዚአብሔርንም ፡
ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ÷ እናትና ፡ አባታቸውን ፡
ያከብሩ ፡ ዘንድ ÷ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ባልንጀ
ራውን ፡ ይወድ ፡ ዘንድ ÷ ሰውነታቸውንም ፡ ከኃ
ጢአትና ፡ ከዝሙት ፡ ከበደል ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡
ያዛቸው ፡ ጀመር ።
፲፯፡ ትጉሃኑ ፡ ከታዘዘላቸው ፡ ሕግ ፡ ወጥተው ፡ በሰው ፡
ልጆች ፡ ኋላ ፡ ስላደረጉት ፡ ዝሙት ፡ በእነዚህ ፡
በሦስቱ ፡ ኃጢአቶች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥፋት ፡
ተደርጎአልና ፡ ያዛቸው ፡ ጀመር ።
፲፰፡ ከመረጡአቸው ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ሚስትን ፡
አገቡ ። አስቀድመው ፡ ኃጢአትን ፡ ሠሩ ።
ኃይለኞች ፡ የሆኑ ፡ ልጆችንም ፡ ወለዱ ፡ ሁሉም ፡
በመልክ ፡ አይመሳሰሉም ።
፲፱፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ባልንጀራውን ፡ ይበላው ፡
ነበር ። አርበኛው ፡ አርበኛውን ፡ ገደለው ፤
ናፊልም ፡ ኢልዮንን ፡ ገደለው ፤ ኢልዮንም ፡
የሰውን ፡ ልጅ ፡ ገደለው ። ሰውም ፡ ባልንጀራ
ውን ፡ ገደለው ፤ ሁሉም ፡ በደልን ፡ ያደርግ ፡
ዘንድ ፡ በደል ፡ ወደ ፡ ማድረግ ÷ ንጹሕ ፡ ደም
ንም ፡ ያፈስ ፡ ዘንድ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ ወደ ፡
ማፍሰስ ፡ ተመለሰ ። ምድርም ፡ በደልን ፡ ሞላች ፤
እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ ወፎችንና ፡
አውሬዎችን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖረውንና ፡
የሚመላለሰውን ፡ ሁሉ ፡ ይበሉ ፡ ጀመር ።
፳፡ ብዙ ፡ ደም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ፈሰሰ ፤ የሰው ፡
ልቡናው ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ነገርንና ፡ ከን
ቱን ፡ ያስብ ፡ ጀመር ።
፳፩፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ከዚህ ፡
ዓለም ፡ ሁሉን ፡ አጠፋ ። በምድርም ፡ ስላፈሰ
ሱት ፡ ደም ፡ ሁሉን ፡ አጠፋ ፤ ልጆቼ ፡ እናንተና ፡
እኔ ፡ ቀረን ፡ ከእኛም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡
የገባው ፡ ሁሉ ፡ ቀረ ።
፳፪፡ በጥፋት ፡ ሥራ ፡ ጸንታችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡
ጀምራችኋልና ፡ እናንተ ፡ በእውነት ፡ ሥራ ፡
ጸንታችሁ ፡ የምትኖሩ ፡ እንዳልሆናችሁ ÷
እነሆ ÷ እኔ ፡ የቀደመ ፡ ሥራችሁን ፡ አየሁ ።
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ከባልንጀራችሁ ፡ ትለያላ
ችሁ ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡ ትቀናናላችሁ ።
፳፫፡ ልጆቼ ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ እንዳ
ትኖሩ ፡ እኔ ፡ አያለሁና ፡ ትለያያላችሁ ፤ አጋን
ንትም ፡ በልጆቻችሁና ፡ በእናንተ ፡ እነሆ ፡
ማሳት ፡ ጀመሩ ።
አሁንም ፡ እኔ ፡ ከሞትሁ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፳፬፡
የሰውን ፡ ደም ፡ ታፈስላችሁ ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡
እናንተ ፡ እፈራለሁ ። የሰውን ፡ ደም ፡ የሚያፈ
ስስ ፡ ሁሉ ፡ ብርንዶንም ፡ የሚበላ ፡ ሁሉ ÷
ሁሉም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋሉና ፤ ብርንዶን ፡
የሚበላ ፡ ደምንም ፡ የሚያፈስስ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ አይቀርምና ፡ እናንተም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
ትጠፉላችሁ ።
ወደ ፡ መቃብር ፡ ይወርዳሉና ÷ ቊርጥ ፡ ፍርድ ፡ ፳፭፡
ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ ይወርዳሉና ፤ በጸና ፡
ሞት ፡ ነፍስም ተይዘው ፡ ጥልቅ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡
ወደ ፡ ገሃነም ፡ ይወርዳሉና ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡
ልጅ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ከሕይወት ፡ አይቀርለትም ።
በደሙ ፡ ሁሉ ፡ በዘመናችሁ ፡ ያረዳችሁት ፡ ፳፮፡
ደም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚወረወር ፡ የከብትና ፡
የአውሬም ፡ ደም ፡ በእናንተ ፡ አይገኝ ።
በምድር ፡ ላይ ፡ የሚፈሰውን ፡ ደም ፡ በመቀበር ፡ ፳፯፡
ስለ ፡ ሰውነታችሁ ፡ ምጽዋት ፡ መጽውቱ ÷
ብርንዶም ፡ ከሚበላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አት
ሁኑ ። ብርንዶ ፡ እንዳትበሉ ፡ በፊታችሁ ፡ ሕጋ
ችሁን ፡ አጽኑ ። እኔ ፡ እንደዚህ ፡ ታዝዤለሁና ፡
ደሙን ፡ ቅበሩ ።
በእናንተ ፡ አሰማበችኋለሁ ፡ በልጆቻችሁም ፡ ፳፰፡
ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ አሰማባቸዋለሁ ፤ በምድር ፡
ላይ ፡ ደምን ፡ ከሚያፈስ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
በሰውነታችሁ ፡ ደማችሁን ፡ የሚመራመሩአ
ችሁ ፡ እንዳይሆኑ ፡ ነፍስን ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አት
ብሉአት ፤ ምድር ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ደምን ፡ ባፈ
ሰሰ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ የምትነጻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምድር ፡
በላይዋ ፡ ከፈሰሰ ፡ ደም ፡ አትነጻምና ፡ ነፍስን ፡
ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አትብሉአት ።
አሁንም ፡ ልጆቼ ፡ ቃሌን ፡ ስሙኝ ፤ በዚህ ፡ ፳፱፡
ዓለም ፡ በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንታችሁ ፡ ትኖሩ ፡
ዘንድ ÷ ክብራችሁም ፡ ከጥፋት ፡ በዳነኝ ፡ በፈ
ጣሪዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡
እውነተኛ ፡ ፍርድን ፡ ፍረዱ ።
እናንተም ፡ ሄዳችሁ ÷ እነሆ ÷ አገሮችን ፡ ታቀ ፴፡
ናላችሁ ÷ በውስጣቸውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ያለውን ፡ ተክል ፡ ሁሉ ፡ ትተክላላችሁ ። ተክ
ሉም ፡ ሁሉ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የሚያፈ
ራውን ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ለመብላት ፡ የማይለቀም ፡
ይሆናል ።
በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ፍሬው ፡ ይለያል ፤ የፍ ፴፩፡
ሬውን ፡ መጀመሪያ ፡ የሚቀበለውን ፡ ምድርና ፡
ሰማይን ፡ በፈጠረ ፡ ክፍ ፡ ባለ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ይሠዋሉ ፤ ሁሉንም ፡ የዘይቱንና ፡ የወይ
ኑን ፡ መጀመሪያ ÷ የአዝመራውንም ፡ መጀመ
ሪያ ፡ በሚቀበል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አሰ
ተካክለው ፡ ይሠዋሉ ፤ የቀረውን ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በደብተራ ፡ አሪት ፡ የሚያገ
ለግሉ ፡ ካህናት ፡ መሥዋዕቱን ፡ በሚቀበልበት ፡
በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ይብሉት ።
ሄኖክ ፡ የአባታችሁን ፡ አባት ፡ ልጁን ፡ ማቱሳ ፴፪፡
ላን ፡ እንዲሁ ፡ አዝዞታልና ፤ ማቱሳላም ፡ ልጁን ፡

ላሚህን ፡ አገዘታልና ፤ ላሜህም ፡ እኔን ፡ ልጁን ፡
አባቶቹ ፡ ያዘዙትን ፡ ሁሉ ፡ አገዘኛልና ፡ እና
ንተ ፡ በእውነት ፡ በሚገባ ፡ ተክላችሁን ፡ ሁሉ ፡
ትተዉ ፡ ዘንድ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ዕረ
ፍትን ፡ አድርጉ ፤ እናንተም ፡ ትከብራላችሁ ፤
ተክላችሁም ፡ ሁሉ ፡ የበጀ ፡ ይሆናል ።
፴፫ እኔም ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ሄኖክ ፡ ልጁን ፡ እንዳዘ
ዘው ፡ አዛችኋለሁ ፤ በመጀመሪያው ፡ ኢዮቤ
ልዩ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡
ማቱሳላ ፡ እስከሚሞትበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልጆ
ቹን ፡ የልጆቹንም ፡ ልጆች ፡ አሰምቶ ፡ አዘዘ ።
፴፬ በሀያ ፡ ዘጠኘኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጀመሪ
ያው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ አርፋ
ክስድ ፡ ሚስት ፡ አገባ ፡ ስምዋም ፡ ራሱእያ ፡
ይባላል ፤ ይህችውም ፡ የኤላም ፡ ልጅ ፡ የሱ
ስን ፡ ልጅ ፡ ናት ። በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡
ሱባዔ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፡ ስሙ
ንም ፡ ቃይናም ፡ አለው ፤ ልጁም ፡ አደገ ፡ አባ
ቱም ፡ መጽሐፍን ፡ አስተማረው ።
፴፭ አምባን ፡ የሚያገዝዝበት ፡ ቦታንም ፡ ይፈልግ ፡
ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ የቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ በድንጋይ ፡ የቀ
ረጹትን ፡ መጽሐፍ ፡ አገኘ ። በእርስዋም ፡ የተ
ጻፈውን ፡ አንብቦ ፡ ተረጐማት ። ጥንቆላን ፡ ጨረ
ቃንና ፡ ፀሐይን ፡ ከዋክብትንም ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡
ምልክትን ፡ ሁሉ ፡ በሚመለከቱ ፡ ገንዘብ ፡ ትጉ
ሃኑ ፡ ያስተማሩትን ፡ ትምህርትን ፡ ሁሉ ፡ በእር
ስዋ ፡ እንዳለ ፡ በእርስዋ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡
ዘነጋ ።
፴፮ ጻፋት ፡ የእርስዋንም ፡ ነገር ፡ አልተናገረም ።
ስለ ፡ እርስዋ ፡ በእርሱ ፡ እንዳይቆጣ ፡ የእርስዋን ፡
ነገር ፡ ለመናገር ፡ ኖኅን ፡ ይፈራዋልና ።
፴፯ በሠላሳው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡
በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ሚስትን ፡ አገባ ፡ ስም
ዋም ፡ ሚልካ ፡ ይባላል ፤ ይህችውም ፡ የያፌት ፡
ልጅ ፡ የአበዳይ ፡ ልጅ ፡ ናት ።
፴፰ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች
ለት ፡— መልክትን ፡ ተልኬአለሁ ፡ ብሎአልና ፡
ስሙንም ፡ ሳላ ፡ አለው ፤ ሳላም ፡ አደገ ፡ ሚስ
ትንም ፡ አገባ ፤ ስምዋም ፡ ሙአክ ፡ ይባላል ፤ ይህ
ችውም ፡ የአባቱ ፡ እኅት ፡ የኬሴድ ፡ ልጅ ፡ ናት ።
፴፱ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአምስተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ሚስ
ትን ፡ አገባ ። በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ልጅን ፡
ወለደችለት ፡ ስሙን ፡ ኤቦር ፡ አለው ። እርሱም ፡
ሚስትን ፡ አገባ ፤ ስምዋም ፡ አዙራድ ፡ ይባ
ላል ፤ ይህችውም ፡ የአብሮድ ፡ ልጅ ፡ ናት ።
፵ በሠላሳ ፡ ሁለተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በሦስተኛው ፡ ዘመን ፡ በስድስተኛው ፡
ዓመት ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ በተወ
ለደበት ፡ ዘመን ፡ የኖኅ ፡ ልጆች ፡ ምድርን ፡ ሊካ
ፈሉ ፡ ጀምረዋልና ፡ ስሙን ፡ ፋሌክ ፡ አለው ፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ስሙ ፡ ፋሌክ ፡ ተባለ ፤ እርስ ፡
በእርሳቸው ፡ አስተካክለው ፡ ተካፈሉ ፡ ለኖ
ኅም ፡ ነገሩት ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

በሠላሳ ፡ ሦስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በፊቱ ፡ ፩
እንዲህ ፡ ሆነ ፤ ለካምና ፡ ለሴም ፡ ለያፌት ፡ ርስት ፡
ልትሆናቸው ፡ ከአንደኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመ
ሪያው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ከተላክን ፡
ከእኛ ፡ አንዱ ፡ ባለበት ፡ ምድርን ፡ ሦስት ፡ አድ
ርገው ፡ ከፈሉአት ፤ ልጆቹን ፡ ጠራ ፡ ልጆቻቸ
ውና ፡ እነርሱም ፡ ቀረቡ ፡ ሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ በያ
ዙት ፡ ዕጣ ፡ ምድርን ፡ ከፈሉ ።
እጃቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ከአባታቸው ፡ ከኖኅ ፡ ፪
እጅ ፡ መጽሐፉን ፡ ተቀበሉ ። ርስት ፡ አድርጎ ፡
የሚይዘው ፡ የሴም ፡ ዕጣ ፡ ለልጆቹ ፡ ለልጅ ፡
ልጆቹም ፡ ለዘላለሙ ፡ በመጽሐፍ ፡ የአገሩ ፡
መከከል ፡ ወጣ ። አርበኞች ፡ ካሉበት ፡ ተራራ ፡
መከከል ፡ ከውኃውም ፡ መውጫ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ጤና ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ወጣ ።
እድሉም ፡ በዚህ ፡ ወንዝ ፡ መከከል ፡ ወዳለ ፡ ፫
ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ይደርሳል ፤ ይህ ፡ ፈሳሽ ፡ ከእር
ስዋ ፡ እስከሚወጣበት ፡ እስከ ፡ ጥልቁ ፡ ውኃ ፡
እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ወደዚያ ፡ ይሄዳል ። ውኃ
ውም ፡ ወደ ፡ ሜአት ፡ ባሕር ፡ ይፈሳል ፤ ይህም ፡
ፈሳሽ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ይሄዳል ፤
በግራ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለያፌት ፡
ደረሰ ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውም ፡ አገር ፡
ሁሉ ፡ ለሴም ፡ ደረሰ ።
ወደ ፡ ካራሶ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ይሄዳል ። ፬
ይኸውም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የሚደርስ ፡ ሕፅነ ፡
ልሳን ፡ ነው ። ዕጣውም ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡
ባሕር ፡ ይደርሳል ። ይህች ፡ ባሕር ፡ ልሳነ ፡
ባሕረ ፡ ግብጽ ፡ ትባላለችና ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡
ወደምታሳይ ፡ ወደ ፡ ልሳን ፡ መግቢያ ፡ እስኪቀ
ርብ ፡ ድረስ ፡ አቅንቶ ፡ ይሄዳል ።
ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ትዘነበላለች ፡ ወደ ፡ ፭
ታላቁ ፡ ባሕር ፡ መግቢያ ፡ ወደ ፡ ውኃውም ፡
ዳርቻ ፡ ትደርሳለች ፡ ወደ ፡ አፈራም ፡ ግራ ፡
ትደርሳለች ፤ ግዮን ፡ ወደሚባል ፡ ፈሳሽ ፡ ውኃ ፡
እስክትቀርብ ፡ ድረስ ፡ ትደርሳለች ፡ ወደ ፡ ግዮ
ንም ፡ ውኃ ፡ ቀርባ ፡ ወደዚህም ፡ ፈሳሽ ፡ ዳርቻ ፡
ትደርሳለች ።
ወደ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ቀኝ ፡ እስክትቀ ፮
ርብ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ትሄዳለች ፡
ከኤዶም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ምሥራቅ ፡ ከአገሩም ፡
ሁሉ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለሳል ።
ስሙ ፡ ራፋ ፡ ወደሚባል ፡ ተራራ ፡ ምሥራቅ ፡
እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ይመጣል ፡ ወደ ፡ ጤና ፡
ፈሳሽ ፡ መውጫ ፡ ዳርም ፡ ይወርዳል ።
ይህችም ፡ እድል ፡ ለዘላለም ፡ ሊይዙአት ፡ በዕ ፯
ጣው ፡ ለሴም ፡ ለልጆቹ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቹም ፡
እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ወጣች ። ይህ ፡ እድል ፡
የልጆቹና ፡ የሴም ፡ ዕጣ ፡ ነውና ፡ ኖኅም ፡ ደስ ፡
አለው ።
የሴም ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፤ ፰
እግዚአብሔርም ፡ በሴም ፡ ማደሪያ ፡ በረድኤት ፡

ይደር ; ብሎአልና ፡ በአፉ ፡ በትንቢት ፡ የተናገ
ረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አሰበ ። ገነትም ፡ ከከበሩ ፡
የከበረች ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ማደሪያ ፡ እንደ ፡
ሆነች ፡ አውቆአልና ፡ ይመስገን ፡ አለ ፤ ደብረ ፡
ሲና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መካከል ፡ ናት ፤ ደብረ ፡
ጽዮንም ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ናት ፤ እነዚህ ፡
ሦስቱ ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ አንጻር ፡ ለም
ስጋና ፡ ተፈጠሩ ።
፱፤ በአፉ ፡ ትንቢት ፡ እንዲናገር ፡ ያደረገውን ፡ የመ
ላእክት ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እስከ ፡ ዘላ
ለም ፡ ድረስ ፡ አመሰገነው ፤ የምርቃትና ፡ የበረ
ከት ፡ እድል ፡ ለሴም ፡ እንደ ፡ ደረሰው ÷ ለል
ጆቹ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቹም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡
እንዲደረሳቸው ፡ አወቀ ።
፲፤ የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ አገርና ፡ ኤዶም ፡ ሁሉ ፡
ህንደኬና ፡ ቀራንዮም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ደረሱት ፡
አወቀ ። ኤርትራ ፡ አውራጃውም ፡ የደጋውና ፡
የበሳንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፤ የሳኔር ፡ አገር ፡ ሁሉና ፡
የከፍቱር ፡ ደሴቶች ፡ ሁሉ ፤ በግራ ፡ ያለ ፡ የአ
ሱር ፡ ተራራና ፡ አማና ፡ የአሱርና ፡ የኤላም ፡
አገር ፡ ሁሉ ÷ ሱሳና ፡ ባቢልም ፡ የአራራት ፡
አገር ፡ ሁሉና ፡ መእዳይም ፤ በግራ ፡ የአሱር ፡
ተራራ ፡ አውራጃና ፡ የባሕሩ ፡ ማዶ ፡ እነዚህ ፡
ሁሉ ፡ የሴም ፡ ዕጣዎች ፡ ናቸው ። ይህችም ፡
ኢየሩሳሌም ፡ የተባረከች ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ናት ።
በውስጥዋም ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነው ።
፲፩፤ የካም ፡ ዕጣና ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ ግዮን ፡ ማዶ ፡
በገነት ፡ ቀኝ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወጣ ÷
ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ይደርሳል ። ዋዕይ ፡ ወደ ፡ ጸና
በት ፡ ተራራ ፡ ሁሉ ፡ ይደርሳል ፤ በአጤል ፡ አን
ጻር ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ይደርሳል ። ወደ ፡
ማዕከክ ፡ ባሕር ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡
ወደ ፡ ፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ ይደርሳል ። ይህች
ውም ፡ የሚጠፋው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡
የሚወርድባት ፡ አገር ፡ ናት ። ወደ ፡ ግራ ፡ ወደ ፡
ጋዴት ፡ ዳርቻ ፡ ይወጣል ። ወደ ፡ ግዮን ፡ ፈሳሽ ፡
እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡
ወደ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ፈሳሽ ፡ ይመጣል ።
፲፪፤ ፈሳሽ ፡ ግዮንም ፡ በገነት ፡ ቀኝ ፡ እስኪቀርብ ፡
ድረስ ፡ ይሄዳል ። ለዘላለሙ ፡ የሚይዙት ፡ ለካም ፡
ለልጆቹም ፡ ለወገናቸውም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ድረስ ፡ በዕጣ ፡ የወጣች ፡ ይህች ፡ አገር ፡ ናት ።
፲፫፤ ለያፌትም ፡ ሦስተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ። ጤና ፡ ወደሚ
ባል ፡ ወንዝ ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡ ፈሳሾች ፡ መውጫ ፡
ግራ ፡ ወጣ ። ወደ ፡ ግራው ፡ ምሥራቅ ÷ ወደ ፡
ጎግ ፡ አውራጃም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ምሥራቃቸ
ውም ፡ ሁሉ ፡ ይደርሳል ፤ ከግራውም ፡ ወደ ፡
ግራው ፡ ይደርሳል ። ወደ ፡ ቁልጥ ፡ ተራራ ፡
ወደ ፡ ማኡት ፡ ባሕርና ፡ ወደ ፡ ግራውም ፡ ይደ
ርሳል ። ወደ ፡ ባሕሩ ፡ መውጫ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡
ወደ ፡ ጋዴት ፡ ምሥራቅም ፡ ይመጣል ። ወደ ፡
ፋራ ፡ መግቢያ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ይሄዳል ።
ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ማኡታ ፡ ባሕር ፡ ወደ
ሚሄድ ፡ ወደ ፡ አፌራግ ፡ ይመለሳል ፤ ወደ ፡
ውኃው ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ ራፋ ፡ ተራራ ፡ እስኪቀ
ርብ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ወዕዳ ፡ ፊለግ ፡ ወደ ፡ ምሥ
ራቁ ፡ ግራ ፡ ይሄዳል ። ግራውንም ፡ ይዞረዋል ።
ለዘላለሙ ፡ በርስትነት ፡ ዕጣ ፡ የሚይዙት ÷ ለያ ፲፬፤
ፌት ፡ ለልጆቹም ፡ የወጣለት ፡ ምድር ፡ ይህች ፡
ናት ። ሰፊ ፡ የሚሆኑ ፡ አውራጃዎቹ ፡ አምስት ፡
ናቸው ። በግራ ፡ በኩል ፡ ያለች ፡ አገርም ፡ ሰፊ ፡
ናት ። ነገር ፡ ግን ፡ የያፌት ፡ አገር ፡ ቀዝቃዛ ፡
ናት ፤ የካምም ፡ አገር ፡ በረሀ ፡ ናት ÷ ከዋዕዩና ፡
ከውርጭ ፡ ጋር ፡ የተቀላቀለች ፡ ናትና ፤ የሴም ፡
አገር ፡ ግን ፡ ቆላም ፡ ደጋም ፡ አይደለችም ።
ካም ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ አካፈለ ። መጀመሪያ ፡ ፲፭፤
ዕጣ ፡ ለኩሳ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወጣ ÷ ምዕራቡ ፡
ለምጽራይም ፡ ወጣ ÷ ምዕራቡም ፡ ለፉጥ ፡ ወጣ ÷
ምዕራቡም ፡ ለከነዓን ፡ ወጣ ፤ የባሕሩም ፡ መግ
ቢያ ፡ አንጻር ፡ የከነዓን ፡ ዕጣ ፡ ነው ።
ሴምም ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ አካፈለ ። መጀመ ፲፮፤
ሪያ ፡ ዕጣ ፡ ለኤላምና ፡ ለልጆቹ ፡ ወጣ ። ወደ ፡
ምሥራቅ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ የፈሳሹ ፡ የጤ
ግሮስ ፡ ምሥራቅ ፡ የህንደኬ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ከኤ
ርትራ ፡ ጋር ፡ በእጁ ፡ ነው ። የዲዳን ፡ ውኃ ፡ የሞ
ብሬ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ የሱሳ ፡ አገር ፡ ሁሉና ፡
ኤላም ፡ እስከ ፡ ጤና ፡ ፈሳሽና ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡
ባሕር ፡ ድረስ ፡ ዘበውእደ ፡ ፈርናከም ፡ ሁሉ ፡
በእጁ ፡ ነው ።
ለአሶርም ፡ ሁለተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ÷ ነነዌና ፡ የአ ፲፯፤
ሱር ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሳድና ፡ ሰናዖርም ፡ እስከ ፡
ህንደኬ ፡ አቅራቢያ ፡ ድረስ ፡ ለእርሱ ፡ ሆኑ ።
ወደ ፡ ወድፋ ፡ ፈሳሽም ፡ ይደርሳል ።
ለአርፋክስድም ፡ ሦስተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ። የከላ ፲፰፤
ውዴዎን ፡ አውራጃ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለኤርትራ ፡
ባሕር ፡ የቀረበ ÷ የኤፍራጤስ ፡ ምሥራቅም ፡
ወደ ፡ ግብጽ ፡ እስከምታሳይ ፡ እስከ ፡ ልሳነ ፡
ባሕር ፡ አቅራቢያ ፡ ድረስ ፡ የምድረ ፡ በዳው ፡
ውኃ ፡ ሁሉ ፡ የሳኔርና ፡ የደጋው ፡ አገር ፡ አማ
ናም ፡ እስከ ፡ ኤፍራጤስ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
የእርሱ ፡ ዕጣ ፡ ነው ።
ለአራምም ፡ አራተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ፤ በኤፍራ ፲፱፤
ጤስና ፡ በጤግሮስ ፡ መካከል ፡ የመስጴጦምያ ፡
አገር ፡ ሁሉ ፡ በከላውዴዎን ፡ ግራ ፡ ወዳለ ፡
እስከ ፡ አሱር ፡ አቅራቢያ ፡ ድረስ ፡ የአራራትም ፡
አገር ፡ ሁሉ ፡ የአራም ፡ ዕጣ ፡ ሆነ ።
ለሉድም ፡ አምስተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ፤ የአሱር ፡ ፳፤
ተራራ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ እስኪቀ
ርብ ፡ ድረስ ፡ የእርሱ ፡ ዕጣ ፡ ነው ። ወደ ፡ ወን
ድሙ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ዕጣ ፡ ወደ ፡ ምሥራቁም ፡
ይደርሳል ።
ያፌትም ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ ፳፩፤
ከፈለ ። መጀመሪያ ፡ ዕጣ ፡ ከግራው ፡ አንጻር ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጤና ፡ ፈሳሽ ፡ ድረስ ፡ ምሥራቅ ፡
ለሴሜር ፡ ወጣ ። በግራ ፡ በኩል ፡ የግራው ፡
ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ ለሚአት ፡ ባሕር ፡ እስኪቀርብ ፡
ድረስ ፡ ለማጎግ ፡ ወጣ ።
ከምዕራብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ደሴቶች ፡ ድረስ ፡ ፳፪፤

እስከ ፡ ደሴቶቹም ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ለሁሉቱ ፡
ወንድሞቹ ፡ ሁሉ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ ለማዳይም ፡
ደረሰ ።
፳፫ ለኢዮአያንም ፡ አራተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ፤ ደሴቱ ፡
ሁሉ ፡ በሉድም ፡ አንጻር ፡ ያሉ ፡ ደሴቶችም ፡
የእርሱ ፡ ዕጣዎች ፡ ናቸው ።
፳፬ ለቶቤልም ፡ እስከ ፡ ሁለተኛይቱ ፡ ልሳን ፡ ድረስ ፡
ወደ ፡ ሉድ ፡ ዕጣ ፡ በምትቀርብ ፡ በልሳን ፡ መከ
ከል ፡ አምስተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ። የሁለተኛይ
ቱም ፡ ልሳን ፡ አውራጃ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛይቱ ፡
ልሳን ፡ ድረስ ፡ ነው ።
፳፭ ለሞሳክም ፡ ስድስተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ። እስከ ፡
ጋዲር ፡ ምሥራቅ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ የሦስ
ተኛይቱም ፡ ልሳን ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ የእርሱ ፡
ዕጣ ፡ ነው ።
፳፮ ለቲራስም ፡ ሰባተኛ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ። በባሕር ፡
መከከል ፡ ያሉ ፡ ለካም ፡ ዕጣ ፡ የሚቀርቡ ፡ ታላ
ላቅ ፡ የሚሆኑ ፡ አራቱ ፡ ደሴቶች ፡ የከማቱሬ ፡
ደሴቶችም ፡ በርስትነት ፡ ዕጣ ፡ ለአርፋክስድ ፡
ልጆች ፡ ወጣ ፥ የኖኅም ፡ ልጆች ፡ ለልጆቻቸው ፡
በአባታቸው ፡ በኖኅ ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡
ከፈሉ ። በዕጣው ፡ ያልወጣለትን ፡ እድል ፡
ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ የወደደውን ፡ አንዱንም ፡ አን
ዱንም ፡ አምሎ ፡ ረገመ ።
፳፯ ሁሉም ፡ በራሳቸው ፡ በልጆቻቸውም ፡ ይደረግ ፡
ይደረግ ፡ አሉ ። የሚያጸይፍ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡
ክፉ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ሁሉ ፤ ምድርን ፡ የሚያ
ጸይፍ ፡ ሥራንና ፡ በደልን ፡ ኃጢአትንና ፡ ዝሙ
ትንም ፡ ስለ ፡ ሞሉአት ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
በእሳትና ፡ በሰይፍ ፡ በሚፈረድባቸው ፡ ገንዘብ ፡
ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ እስከሚደረግባት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
በየወገናቸው ፡ ይደረግ ፡ ይደረግ ፡ አሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ በዚህ ፡ ኢዮብልዩ ፡ በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡
የረከሱ ፡ አጋንንት ፡ የኖኅን ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡
ያስቱአቸው ፡ ጀመሩ ፤ አእምሮአቸውን ፡ እያ
ሳጡ ፡ ያጠፉአቸው ፡ ጀመሩ ።
፪ የኖኅም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡ ኖኅ ፡
መጥተው ፡ የሚያስቱና ፡ የሚያደነቁሩ ፡ የልጅ ፡
ልጆቻቸውንም ፡ የሚገድሉ ፡ የአጋንንትን ፡
ነገር ፡ ነገሩት ።
፫ ኖኅም ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለመነ ፡— ይቅርታህን ፡ አድርገህ ፡ ያዳንኸኝ ፥
ልጆቼንም ፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ ያዳንካቸው ፤
የጥፋትን ፡ ልጅ ፡ እንዳጠፋኸው ፥ እንድጠ
ፋም ፡ ያላደረግኸኝ ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ይቅር
ታህ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ ቸርነትህም ፡ በሰውነቴ ፡
ተገልጣለችና ፤ በሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ያሉ ፡ የነፍሳት ፡
ፈጣሪ ፡ ይቅርታህ ፡ በልጆቼ ፡ ላይ ፡ ይገለጥ ፥
የክፉ ፡ አጋንንትም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳያጠ
ፉአቸው ፡ በላያቸው ፡ አይሠልጥኑ ፡ አለ ።
፬ አንተም ፡ እኔን ፡ አክብረኝ ። የብዙ ፡ ብዙ ፡ እን
ሆን ፡ ዘንድ ፡ ምድርንም ፡ እንሞላት ፡ ዘንድ ፥
ልጆቼንም ፡ አብዛቸው ። አንተም ፡ የእነዚህ ፡
ፍጥረቶች ፡ አባቶቻቸው ፡ ትጉሃኖች ፡ ያደረጉ
ትን ፡ ታውቃለህ ። በሕይወት ፡ ያሉትን ፡ እነ
ዚህን ፡ ረቂቃን ፡ አጋንንት ፡ ይህ ፡ መቻያ ፡ በሚ
ደረግበት ፡ በገሃነም ፡ እግዛቸው ፤ እነርሱ ፡ ክፉ
ዎች ፡ ናቸውና ፥ ለማጥፋትም ፡ ተፈጥረዋልና ፡
ፈጣሪዬ ፡ የእኔን ፡ የባሪያህን ፡ ልጆች ፡ አያጥፉ ፤
በሕይወት ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስም ፡ አይሠ
ልጥኑ ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ መቻያቸውን ፡ ታውቃለ
ህና ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡
በጻድቃን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አይሠልጥኑ ፡ አለ ።
ፈጣሪያችንም ፡ ሁሉን ፡ አስረን ፡ እናግዝ ፡ ፭
ዘንድ ፡ አዘዘን ። የአጋንንት ፡ አለቃ ፡ ሰይጣን ፡
መጥቶ ፡— አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፥ ከእነርሱ ፡ አጋን
ንትን ፡ ከጥፋት ፡ አስቀርልኝ ፥ ቃሌን ፡ ይስሙ ፤
ከእነርሱ ፡ ከልቀሩልኝ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ የፈ
ቃዴን ፡ ሥልጣን ፡ ማድረግ ፡ አልችልምና ።
እኔ ፡ የማዛቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ያድርጉ ። የሰው ፡
ልጆች ፡ ኃጢአታቸው ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከመ
ቻያዬ ፡ አስቀድሞ ፡ እነርሱ ፡ ለማጥፋትና ፡ ለማ
ሳት ፡ ተፈጠሩ ።
በፊቱ ፡ አሥረኛው ፡ ነገድ ፡ ይቅሩ ፤ ዘጠኝኛው ፡ ፮
ነገድ ፡ ግን ፡ መቻያ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡
ያውርዱአቸው ፡ አለ ። በቀና ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡
የሚኖሩ ፡ እንዳይደሉ ፡ በእውነት ፡ ሥራም ፡
የሚጣሉ ፡ እንዳይደሉ ፡ ያውቃልና ፡ ለኖኅ ፡
ፈውስ ፡ የሚደረግባቸውን ፡ ሁሉ ፡ እናስተም
ረው ፡ ዘንድ ፡ ከእኛ ፡ አንዱን ፡ አዘዘው ።
እኛም ፡ እንደ ፡ ቃሉ ፡ አደረግን ፤ ፈጽመው ፡ ፯
የከፉ ፡ አጋንንትን ፡ መቻያ ፡ ባለበት ፡ በገሃነም ፡
አስረን ፡ አጋዝን ። አሥረኛውን ፡ ነገድ ፡ ግን ፡
በሰይጣን ፡ ትእዛዝ ፡ በምድር ፡ መቻያ ፡ ይሆኑ ፡
ዘንድ ፡ አስቀረን ። በምድር ፡ እንጨቶችም ፡
ያድን ፡ ዘንድ ፡ አጋንንት ፡ ከሚያመጡት ፡ ደዌ ፡
የሚድንበትን ፡ ሁሉ ፡ ከሚያስቱበት ፡ ጋር ፡
ለኖኅ ፡ ነገረው ።
ኖኅም ፡ ፈውስ ፡ በሚደረግበት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ፰
በመጽሐፍ ፡ እንዳስተማርነው ፡ ሁሉን ፡ ጻፈ ።
የኖኅን ፡ ልጆች ፡ እየተከተሉ ፡ የሚያስቱ ፡ ክፉ
ዎች ፡ አጋንንትም ፡ ተጋዙ ።
ከልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ እርሱን ፡ ይወ ፱
ደው ፡ ነበርና ፡ የጻፋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡
ለታላቅ ፡ ልጁ ፡ ለሴም ፡ ሰጠው ። ኖኅም ፡
እንደ ፡ አባቶቹ ፡ ሞተ ፤ አራራት ፡ በሚባል ፡
አገር ፡ በሉባር ፡ ተቀበረ ፤ በሕይወት ፡ ዘጠኝ ፡
መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ጨረሰ ። ይህም ፡ አሥራ ፡
ዘጠኝ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ሁለት ፡ ሱባዔና ፡ አምስት ፡
ዓመት ፡ ነው ። በእውነተኛ ፡ ሥራውና ፡ በእ
ውነት ፡ ፍጹም ፡ ስለሚሆንባት ፡ ሥራው ፡ ከሄ
ኖክ ፡ በቀር ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ዘመንን ፡ ያበዛ ፡ የለም ። ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ በሚ
ደረግባት ፡ ቀን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሥራውን ፡
ሁሉ ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡
ባሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ የሄኖክ ፡

ፍጥረቱ ፡ ደግ ፡ ነውና ።
፲፤ በሠላሳ ፡ ሦስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ከሁለተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ፋሌክ ፡ ስምዋ ፡
ሉምና ፡ የሚባል ፡ ሚስትን ፡ አገባ ፡ ይህችውም ፡
የሲናዖር ፡ ልጅ ፡ ናት ። በዚሁ ፡ ሱባዔ ፡ በአ
ራተኛው ፡ ዓመት ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች
ለት ። ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ሰናዖር ፡ አገር ፡
ስለ ፡ ተሰደዱ ፡ በሰናዖር ፡ አገር ፡ ግምብንና ፡
አምባን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በጽኑ ፡
ምክር ፡ እነሆ ፡ ክፉዎችን ፡ ሆኑ ፡ ብሎአልና ፡
ስሙን ፡ ራግው ፡ አለው ። ወደ ፡ ሰማይ ፡ እን
ወጣበታለን ፡ ሲሉ ፡ በዘመኑ ፡ ግምብና ፡ አም
ባን ፡ እንሥራ ፡ ብለው ፡ አስበዋልና ፡ ይሠሩ ፡
ጀመር ።
፲፩፤ በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ጡቡን ፡ ሠርተው ፡ በእ
ሳት ፡ ተኰሱ ። ጡቡም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡
ሆነላቸው ፤ የሚመርጉበት ፡ ጭቃውም ፡ ከባ
ሕር ፡ በሰናዖር ፡ አገርም ፡ ከውኃዎች ፡ ምንጭ ፡
የሚወጣ ፡ የባሕር ፡ አረፋን ፡ ሆነላቸው ።
፲፪፤ በአርባ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሠሩት ። ፍጹም ፡
ጡብ ፡ አድርገው ፡ ሲሠሩት ፡ ኖሩ ። ወርዱ ፡
ሦስት ፡ ክንድ ፥ ቁመቱ ፡ አሥር ፡ ክንድ ፤
አንድ ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ አቈልቋዩ ፡ ሦስት ፡
ክንድ ፡ ነው ። ቁመቱ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ከአ
ራት ፡ መቶ ፡ ከሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ከሁለት ፡
ስንዝር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ። አቈልቋዩ ፡
አሥራ ፡ ሦስት ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ።
፲፫፤ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ እንዲህ ፡
አለን ፦ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ የሆነ ፡ ወገን ፡ ግምብ ፡
ይሠሩ ፡ ጀመር ፤ ኑ ፡ አሁን ፡ ከእነርሱ ፡ ፈጽ
መን ፡ እንዳናጠፋ ፡ አንዱም ፡ የአንዱን ፡ ቋንቋ ፡
እንዳይሰማ ፥ ኑ ፡ ወርደን ፡ በቋንቋ ፡ እንለያ
ቸው ፤ በአሕዛብም ፡ አገር ፡ ይበተኑ ፤ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ እስከሚደረግበት ፡
ቀን ፡ አንዲት ፡ ምክር ፡ጸንታ ፡ በላያቸው ፡
አትኑር ፡ አለን ።
፲፬፤ እግዚአብሔር ፡ ወርዶ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ የሠሩ
ትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለወጠ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡
የአንዱን ፡ ነገር ፡ አልሰማም ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ግምብንና ፡ መንደርን ፡ መሥራት ፡ ተዉ ።
፲፭፤ በዚያ ፡ ፈጣሪ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ቋንቋ ፡ ለው
ጦአልና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሰናዖር ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡
የተበተኑባት ፡ አገር ፡ ተባለች ፤ ከዚያም ፡ በየ
አገሩ ፡ ቋንቋቸው ፡ በየወገናቸው ፡ ተበተኑ ።
፲፮፤ እግዚአብሔርም ፡ ታላቅ ፡ ነፋስን ፡ አምጥቶ ፡
ግምባቸውን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ገለበጠ ፡ እነሆ ፥
እርሱም ፡ በሰናዖር ፡ አገር ፡ በባቢሎንና ፡ በአ
ሦር ፡ አገር ፡ መከከል ፡ ነው ። ስምዋንም ፡ ድቀት ፡
አላት ። በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡
ዓመት ፡ በሠላሳ ፡ አራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በእ
ርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰናዖር ፡ አገር ፡ ተበተኑ ።
፲፯፤ ካምና ፡ ልጆቹ ፡ ለእርሱ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀች ፡
በደቡብ ፡ አገር ፡ በዕጣ ፡ ወዳገኛት ፡ አገር ፡ ሄዱ ።
ከነዓንም ፡ እስከ ፡ ግብጽ ፡ ውኃ ፡ መፍሰሻ ፡
ድረስ ፡ ያለችውን ፡ የደጋውን ፡ አገር ፡ እጅግ ፡
ያማረች ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አየ ። ወደ ፡ ርስቱ ፡
አገር ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ መግቢያ ፡ አገር ፡ አልሄ
ደም ፥ በደጋው ፡ አገር ፡ ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ በባሕሩና ፡ በደጋው ፡
ዙሪያ ፡ ኖረ ።
አበቱ ፡ ካም ፡ እና ፡ ወንድሞቹ ፡ ኩሳ ፡ ሚጽሬ ፲፰፤
ምም ፦ የአንተ ፡ ዕጣ ፡ ባልሆነች ፡ አገር ፡ ኖረሃ
ልና ፡ በዕጣም ፡ አልወጣችልንምና ፡ እንዲህ ፡
አታድርግ ፡ አሉት ። እንደዚህ ፡ ብታደርግ ፡ ልጆ
ችህና ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ምድር ፡ ትጠፋላችሁና ፤
በጠብ ፡ በክርክር ፡ የተረገማችሁ ፡ ትሆናላችሁ ፤
ልጆችህም ፡ በጠብ ፡ ይጠፋሉ ፥ አንተም ፡ ፈጽ
መህ ፡ ትጠፋለህ ።
ለሴምና ፡ ለልጆቹ ፡ በዕጣቸው ፡ ወጥቶአልና ፡ ፲፱፤
በሴም ፡ አገር ፡ አትኑር ፤ አንተ ፡ የተረገምህ ፡ ነህ ።
በአባታችን ፡ በኖኅና ፡ በከበረው ፡ ፈራጅ ፡ ፊት ፡
ለመረገም ፡ በመሐላ ፡ ከተዘጋጀን ፡ ከኖኅ ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ፡ ተለይተህ ፡ አንተ ፡ የተረገምህ ፡ ትሆና
ለህ ፡ አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡ አልሰማቸውም ፤
እርሱ ፡ ከኤማት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ግብጽ ፡ መግ
ቢያ ፡ ድረስ ፡ በደጋው ፡ አገር ፡ ኖረ ፤ ልጆቹም ፡
እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ኖሩ ። ስለዚህ ፡
ነገር ፡ ይህች ፡ አገር ፡ የከነዓን ፡ አገር ፡ ተባለች ።
ያፌትና ፡ ልጆቹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሄዱ ፡ እድ ፳፤
ላቸው ፡ በሆነ ፡ አገርም ፡ ኖሩ ።
ማዳይም ፡ ውኃ ፡ ያለባትን ፡ አገር ፡ አየ ፥ ነገር ፡ ፳፩፤
ግን ፡ በፊቱ ፡ ደስ ፡ አላሰኘችውም ። ከኤላምና ፡
ከአሱር ፥ የሚስቱ ፡ ወንድም ፡ ከሆነ ፡ ከአርፋ
ክስድም ፡ ለምኖ ፡ እስከዚህች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
የሚስቱ ፡ ወንድሞች ፡ አቅራቢያ ፡ በሚሆን ፡
በመቄዶን ፡ አገር ፡ ኖረ ። የልጆቹን ፡ በታና ፡
የእርሱን ፡ በታ ፡ ሜቄዶኒን ፡ በአባታቸው ፡ በማ
ዳይ ፡ ስም ፡ ጠሩው ።
በሠላሳ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተ ፳፪፤
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ራግው ፡
ስምዋ ፡ ዑራ ፡ የምትባል ፡ ሚስትን ፡ አገባ ፤
ይህችውም ፡ የኬሴድ ፡ ልጅ ፡ የዑር ፡ ልጅ ፡
ናት ። ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፡ ስሙንም ፡
ሴሮሕ ፡ አለው ።
በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተኛው ፡ ሱባዔ ፡ የኖኅ ፡ ፳፫፤
ልጆች ፡ ሰውን ፡ ለመግደልና ፡ ለመማረክ ፥
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ወንድሙን ፡ ለመግደል ፡
የሰውንም ፡ ደም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ለማፍሰስ ፥
ጽኑ ፡ አምባዎችን ፡ ግምብና ፡ ቅጥርንም ፡ ሠር
ተው ፥ መዋጋት ፡ ጀመሩ ። አንዱ ፡ ወገን ፡ በአ
ንዱ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ በመንግ
ሥትም ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመሾም ፥ ሕዝቡ ፡
በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አሕዛቡም ፡ በአሕዛቡ ፡ ፊት ፡
ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ለመሄድ ፡ አገርም ፡ ከአገር ፡ ጋር ፡
ለመጣላት ፥ ሁሉም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡
መማሪያንም ፡ ለመግዛት ፡ ለልጆቻቸውም ፡ ሰል
ፍን ፡ ለማስተማር ፡ ይዋጉ ፡ ጀመር ። አንዱ ፡
አገር ፡ ከአንዱ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ይመራረኩ ፡ ጀመር ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ሴት ፡ ባሪያንና ፡ ወንድ ፡ ባሪያንም ፡ ይገዙ ፡
ጀመር ።
፳፬፤ የኬሴድ ፡ ልጅ ፡ ዑርም ፡ በከላውዴዎን ፡ ያለች ፡
ዑር ፡ የምትባል ፡ አምባን ፡ ሠራ ÷ ስምዋንም ፡
በአባቱ ፡ ስምና ፡ በእርሱ ፡ ስም ፡ ጠራ ። ጣዖቶ
ችን ፡ ሠሩ ፡ አንዳንዱም ፡ አንዳንዱም ፡ መጥቶ ፡ ለራሱ ፡
ለሠራው ፡ ጣዖት ፡ ይሰግዳል ÷ ምስልንና ፡ ጣዖ
ትን ፡ ኃጢአትንም ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ፤ የክፉ ፡
አጋንንትም ፡ ኃጢአትንና ፡ በደልን ፡ ክህደት
ንም ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ይረዱ ፡ ያስቱ ፡ ነበር ።
፳፭፤ የሚያጣላ ፡ ሰይጣንም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለማሠ
ራት ፡ ይበረታ ፡ ነበር ፤ ኃጢአትንና ፡ በደልን ፡
ሁሉ ፡ ፈጽሞም ፡ ለማጥፋት ፡ ክህደትን ፡ ሁሉ ፡
ለማሠራት ፡ በምድርም ፡ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡
ከእጁ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ የአጋንንትን ፡ እጅ ፡ ይልክ ፡
ነበር ።
፳፮፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በደልንና ፡ ኃጢአትን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
መሥራት ፡ ተመልሶአልና ÷ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሴ
ሮሕ ፡ ስም ፡ ሴሮክ ፡ ተባለ ። አደገ ፤ ለሚስቱ ፡
እናት ፡ አባት ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ በከላውዴ
ዎን ፡ ዕጣ ፡ በዑር ፡ ኖረ ። ጣዖትንም ፡ ያመልክ ፡
ጀመር ፤ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአ
ምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
ሚስትን ፡ አገባ ÷ ስምዋም ፡ ሚልካ ፡ ይባላል ፤
ይህችውም ፡ የአባቱ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ የካቤር ፡
ልጅ ፡ ናት ፤ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡
ዓመት ፡ ናኮርን ፡ ወለደችለት ።
፳፯፤ አደገ ፡ በከላውዴዎን ፡ ዕጣ ፡ በዑርም ፡ ኖረ ።
አባቱም ፡ ለማምዋረት ፡ በሰማይ ፡ ምልክትም ፡
ለመጠንቆል ፡ የከዋክብትን ፡ ቍጥርም ፡ አስተ
ማረው ።
፳፰፤ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በስድስተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ሚስ
ትን ፡ አገባ ÷ ስምዋም ፡ ኢዮስካ ፡ ይባላል ።
ይህችውም ፡ የከለዳውያን ፡ ወገን ፡ የኔስቴግ ፡
ልጅ ፡ ናት ። በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሰባተኛው ፡
ዓመት ፡ ታራ ፡ የሚባል ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለ
ደችለት ።
፳፱፤ የሚያጣላ ፡ ሰይጣንም ፡ ወፎችንና ፡ ቁራዎችን ፡
ምድርን ፡ ለማጥፋት ÷ በምድር ፡ ላይ ፡ የተዘራ
ውንም ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ሰደደ ። የሰውን ፡
ልጆች ፡ አዝመራቸውን ፡ ይቀሙ ፡ ዘንድ ፡ ሳያ
ርሱ ፡ ቁራዎች ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ዘሩን ፡ ይለ
ቅሙ ፡ ጀመር ። ወፎችና ፡ አሞራዎች ፡ ያስቸግ
ሩአቸው ፡ ነበርና ÷ ዘራቸውንም ፡ ይበሉባቸው ፡
ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ስሙን ፡ ታራ ፡ አለው ።
፴፤ ከወፎችም ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ዓመቶች ፡ ድርቅ ፡
ይሆኑ ፡ ጀመር ፤ የእንጨቱንም ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡
ከዛፎች ፡ ላይ ፡ እየለቀሙ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ፤ በዘ
መናቸው ፡ ከምድር ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ጥቂትም ፡
ማዳን ፡ ቢችሉ ፡ በጽኑ ፡ ኃይል ፡ ነበር ። በሠ
ላሳ ፡ ዘጠኝኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ታራ ፡ ሚስት ፡
አገባ ÷ ስምዋም ፡ ኤድና ፡ ይባላል ፤ ይህችውም ፡
የአባቱ ፡ የእኅቱ ፡ ልጅ ፡ የምትሆን ፡ የአብራም ፡
ልጅ ፡ ናት ። በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡
ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ። የልጁ ፡ ልጅ ፡
ሳይፀነስ ፡ ሙቶአልና ፡ ስሙን ፡ በእናቱ ፡ አባት ፡
ስም ፡ አብራም ፡ አለው ።
ያም ፡ ልጅ ፡ ጣዖታቱን ፡ በመከተል ፡ ኃጢአት ፴፩፤
ንም ፡ በመሥራት ፡ ሁሉ ፡ እንዲስት ፡ የምድ
ርን ፡ ስሕተት ፡ ያውቅ ፡ ጀመር ።
አባቱም ፡ መጽሐፍን ፡ አስተማረው ፤ የሁለት ፡ ፴፪፤
ሱባዔ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ከእርሱ ፡ ጋር ፡
በጣዖት ፡ እንዳይሰግድ ፡ አባቱን ፡ ከመከተል ፡
ተለየ ።
የሰዎች ፡ ልጆች ፡ ከሚበድሉት ፡ በደል ፡ ያድ ፴፫፤
ነው ፡ ዘንድ ፡ የተናቀ ፡ ጣዖቱን ፡ በመከተል ፡
ዕጣውም ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ እንዳይሆን ፡ ሁሉን ፡
ወደ ፡ ፈጠረ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይለምን ፡
ጀመር ።
በምድር ፡ ዘርን ፡ ለመዝራት ፡ የሚዘሩበት ፡ ጊዜ ፡ ፴፬፤
ደረሰ ፤ ዘራቸውን ፡ ከአሞራዎች ፡ ይጠብቁ ፡
ዘንድ ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ወጡ ።
አብራምም ፡ ከወጡ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ወጣ ። ፴፭፤
እርሱም ፡ የአሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡
ነበረ ፤ ብዙዎች ፡ ቁራዎችም ፡ ዘርን ፡ ይለቅሙ ፡
ዘንድ ፡ መጡ ። አብራምም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ሳያርፉ ፡ በፊታቸው ፡ ይሮጥ ፡ ነበር ÷ ዘርን ፡ ለመ
ልቀም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሳያርፉ ፡— ወደ ፡ መጣ
ችሁበት ፡ በታ ፡ ተመለሱ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡
አትውረዱ ፡ እያለ ፡ ይጮህ ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡
ተመለሱ ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ቁራዎችን ፡ ለመከልከል ፡ ፴፮፤
ሰውን ፡ አስቀመጡ ። አብራም ፡ ባለበት ፡ በዚያ ፡
እርሻ ፡ ሁሉ ፡ ከቁራዎቹ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ቁራ ፡
አላረፈም ።
በእርሻዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ ፴፯፤
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሲጮኹና ፡ አሞራዎቹን ፡ ሁሉ ፡—
ተመለሱ ፡ ሲላቸው ፡ ይሰሙት ፡ ነበር ፤ በከላው
ዴዎን ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ስሙ ፡ ገነነ ፡ ከበረ ።
የሚዘሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ፴፰፤
እርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ። የዘሩ ፡ ወራት ፡ እስኪ
ፈጸም ፡ ድረስም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይሄድ ፡ ነበር ።
ምድራቸውን ፡ ዘሩ ÷ በዚያም ፡ ዓመት ፡ የሚ
በቃ ፡ እህልን ፡ አገቡ ፤ በልተውም ፡ ጠገቡ ።
በአምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአንዱ ፡ ዓመት ፡ አብ ፴፱፤
ራም ፡ የበሬ ፡ ዕቃ ፡ ለሚሠሩት ፡ ሰዎች ፡ እን
ጨት ፡ መጥረብን ፡ አስተማራቸው ።
በምድር ፡ ላይ ፡ የበሬ ፡ ዕቃን ፡ ሠሩ ፤ በላዩ ፡ ፵፤
ዘርን ፡ ያኖር ፡ ዘንድ ፡ በድግሩ ፡ አንጻር ፡ እር
ፍን ፡ ሠራ ÷ ዘሩም ፡ በእርፉ ፡ ጫፍ ፡ ወርዶ ፡
በምድር ፡ ይሰወር ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከአ
ሞራዎች ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ አልፈሩም ፡ ነበር ፤
በእርፉ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ድግሩንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
አኖሩ ።
ዘርንም ፡ ዘሩ ፤ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ አብራም ፡ ፵፩፤
እንዳዘዛቸው ፡ ሁሉን ፡ አደረጉ ። ከዚያ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



በኋላ ፡ ከአሞራዎቹ ፡ የተነሣ ፡ አልፈሩም ።
፴፪፤ በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡
አብራም ፡ አባቱ ፡ ታራን ፡— አባቴ ፡ ብሎ ፡
ጠራው ። እርሱም ፡— ልጄ ፡ ሆይ ፥ እነሆ ፥ እኔ ፡
አለሁ ፡ አለው ። እርሱም ፡— ምንም ፡ ምን ፡
ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ የላቸውምና ፡ አንተ ፡ ከም
ታመልካቸውና ፡ በፊታቸው ፡ ከምትሰግድላ
ቸው ፡ ከእነዚህ ፡ ከጣዖታቱ ፡ ለእኛ ፡ የምናገ
ኘው ፡ ምን ፡ ረድኤት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አለን ?
ድዳዎች ፡ ናቸውና ፥ ልቡናንም ፡ የሚያስቱ ፡
ናቸውና ፡ አታምልኳቸው ።
፴፫፤ ሰማይን ፡ የፈጠረ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብ ፡
ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ የሚሰጥ ፥ በምድር ፡
ላይ ፡ ሁሉን ፡ የሚያደርግ ፥ ሁሉን ፡ በቃሉ ፡
የፈጠረ ፥ ከፊቱ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ደኅንነት ፡
የሚገኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምልኩ ፨
፴፬፤ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ የሌላቸው ፡ ጣዖታቱን ፡ እና
ንተ ፡ ለምን ፡ ታመልካላችሁ ? እነርሱ ፡ የሰው ፡
ሥራ ፡ ናቸውና ፥ እናንተ ፡ በጫንቃችሁ ፡ ትሸ
ከሙአቸዋላችሁና ፥ ለሚሠሩአቸው ፡ ሰዎች ፡
ጽኑ ፡ ተዋርዶ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ከእነርሱ ፡
ረድኤት ፡ አይገኝምና ፤ ለሚያመልኩአቸውም ፡
ሰዎች ፡ የልቡና ፡ ስሕተት ፡ ናቸውና ፡ አታም
ልኩአቸው ፡ አለ ።
፴፭፤ አባቱ ፡— ልጄ ፡ ሆይ ፥ እኔም ፡ አውቃለሁ ፤
ነገር ፡ ግን ፡ በፊታቸው ፡ አገለግል ፡ ዘንድ ፡
ካህን ፡ ጣዖት ፡ ላደረጉኝ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ አደ
ርጋለሁ ? እውነት ፡ ነገርንም ፡ ብነግራቸው ፥
ያመልኩአቸው ፡ ያመሰግኑአቸው ፡ ዘንድ ፡
ልቡናቸው ፡ እነርሱን ፡ ተከትላለችና ፡ ይገድሉ
ኛል ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እንዳይገድሉህ ፡ ዝም ፡
በል ፡ አለው ።
፴፮፤ ለሁለቱ ፡ ወንድሞቹም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ነገራ
ቸው ፥ እርሱንም ፡ ተቆጡት ፡ ዝም ፡ አለ ።
፴፯፤ በአርባው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተኛ ፡ ሱባዔ ፡
በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ አብራም ፡ ሚስት ፡ አገባ ፥
ስምዋም ፡ ሶራ ፡ ይባላል ፤ ይህችውም ፡ የአባቱ ፡
ልጅ ፡ ናት ፤ ሚስት ፡ ሆነችው ።
፴፰፤ በሦስተኛው ፡ ሱባኤ ፡ በሚቆጠር ፡ በሦስተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ወንድሙ ፡ አራን ፡ ሚስት ፡
አገባ ። በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቆጠር ፡ በሰባተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ወለደችለት ፥ ስሙንም ፡
ሎጥ ፡ አለው ። ወንድሙ ፡ ናኮርም ፡ ሚስት ፡
አገባ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩፤ አብራም ፡ በሕይወት ፡ በኖረበት ፡ በስሳው ፡
ዘመን ፥ ይኸውም ፡ በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአ
ራተኛው ፡ ዓመት ፥ አብራም ፡ ሌሊት ፡ ተነሥቶ ፡
የጣዖታቱን ፡ ቤት ፡ አቃጠለ ፥ በቤት ፡ ያለው
ንም ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ አቃጠለ ።
፪፤ ያወቀ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ የለም ፡ ሌሊት ፡ ተነሥ
ተው ፡ ጣዖታቸውን ፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ ያወጡ ፡
ዘንድ ፡ ወደዱ ።
ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ አራን ፡ ተወረወረ ፥ በላ ፫፤
ዩም ፡ እሳት ፡ ነደደበት ፤ በእሳት ፡ ተቃጥሎ ፡
የከላውዴዎን ፡ ዕጣ ፡ በምትሆን ፡ በኢኑር ፡
በአባቱ ፡ በታራ ፡ ፊት ፡ ሞተ ። የከላውዴዎን ፡
ዕጣ ፡ በምትሆን ፡ በኢኑር ፡ ቀበሩት ።
ታራም ፡ የከላውዴዎን ፡ ዕጣ ፡ ከምትሆን ፡ ፬፤
ከዑር ፡ ወጣ ። ወደ ፡ ከነዓንና ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡
ምድር ፡ ወደ ፡ ካራንም ፡ ምድር ፡ ይመጡ ፡
ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ወጣ ፥ ልጆቹም ፡ መጡ ።
አብራምም ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ በካራን ፡ ሁለት ፡ ፭፤
የዓመቶች ፡ ሱባዔ ፡ ተቀመጠ ።
በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ፮፤
አብራም ፡ ተነሣ ፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡
ከማታ ፡ እስከ ፡ ጥዋት ፡ ድረስ ፡ ከዋክብትን ፡
ይቆጥር ፡ ዘንድ ፥ የዓመቱ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ እን
ዲሆን ፥ ዝናብ ፡ ያዘንቡም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አያዘ
ንቡም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ሌሊት ፡
ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ።
ብቻውን ፡ ተቀምጦ ፡ ይቆጥር ፡ ነበር ፤ በልቡ ፯፤
ናው ፡ ነገር ፡ ታሰበ ፤ የከዋክብት ፡ ምልክት ፡
ሁሉ ፥ የፀሐይና ፡ የጨረቃ ፡ ምልክት ፡ ሁሉ ፡
በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነው ። እኔ ፡ ለምን ፡ እመራ
መራለሁ ? ጥዋትም ፡ ማታም ፡ ያዘንብ ፡ ዘንድ ፡
ቢወድ ፡ ያዝንብ ፤ እንዳያዘንብም ፡ ቢወድ ፡
አያዝንብ ፤ ሁሉ ፡ በእጁ ፡ ነው ፡ አለ ።
በዚህችም ፡ ሌሊት ፡ ለመነ ፡— ፈጣሪዬ ፥ ፈጣ ፰፤
ሪዬ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ብቻ ፡ ለእኔ ፡ ገናና ፡ ፈጣሪ ፡
ነህ ፤ አንተ ፡ ሁሉን ፡ ፈጠርህ ፤ የቃልህ ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሁሉ ፡ ጸንቶ ፡ ኖረ ። እኔ ፡ አንተን ፡ ማም
ለክ ፡ ወደድሁ ፤ ክፋዎች ፡ ከሆኑ ፡ በሰው ፡
ልቡና ፡ ከሚሠለጥኑ ፡ ከመናፍስት ፡ እጅ ፡
አድነኝ ፤ ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፥ በአምልክ ፡ አንተን ፡
ከመከተል ፡ አያስቱኝ ፤ እኔንም ፡ ልጄንም ፡
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ለዘላ
ለም ፡ እንዳንስት ፡ አድርገን ፡ አለ ።
የከላውዴዎን ፡ ዕጣ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ዑርም ፡ ፱፤
ብመለስ ፥ ወደ ፡ እነርሱ ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ እነ
ርሱ ፡ ሰውነቴን ፡ በፊቴ ፡ ይፈልጋሉ ፤ ወይም ፡
በዚህ ፡ ቦታ ፡ እቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ብትወድ ፡
በዚህ ፡ ቦታ ፡ ያችን ፡ የቀናች ፡ ጎዳና ፡ በፊትህ ፡
አቅናልኝ ፤ በእኔ ፡ በባሪያህ ፡ እጅ ፡ አድርግ ፤
ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፥ በልቡናዬ ፡ ስሕተት ፡ ጸንቼ ፡
አልኑር ፡ አለ ።
እርሱም ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፥ ፲፤
እነሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ ተላከ ፡— አንተ ፡ ከሀገርህ ፥ ከአ
ባትህ ፡ ወገንና ፡ ከዘመዶችህ ፡ ተለይተህ ፡ ወጥ
ተህ ፡ እኔ ፡ ወደማሳይህ ፡ አገር ፡ ሂድ ፤ እጅግ ፡
ብዙ ፡ ወገን ፡ አደርግሃለሁ ፥ አከብርሃለሁ ፥ ስም
ህንም ፡ ከፍ ፡ አደርጋለሁ ፥ በሀገሩም ፡ ሁሉ ፡
የከበርህ ፡ ትሆናለህ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በአ ፲፩፤
ንተ ፡ ይባረካሉ ፤ የሚመርቁህን ፡ እመርቃቸ
ዋለሁ ፥ የሚረግሙህንም ፡ እረግማቸዋለሁ ፤

ለአንተም ፡ አምላክን ፡ እሆንልሃለሁ ፡ ለልጅ ፡
ልጆችህም ፡ ለወገኖችህም ፡ ሁሉ ፡ እሆናቸዋ
ለሁ ፤ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለሚነሡ ፡ ሰዎች ፡ አም
ላካቸው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ አትፍራ ፤ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ አምላክህ ፡
እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ተላከ ።
፲፪፤ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔርም ፡— ምሥጢ
ርን ፡ ግለጥለት ፡ ዕዝነ ፡ ልቡናውም ፡ እንዲሰማ ፡
ይሁን ፡ ጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ ከፈረሰበት ፡ ቀን ፡
ጀምሮ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ከሚናገርበት ፡
ቋንቋ ፡ ተለይቶአልና ፡ የተረዳች ፡ ቋንቋን ፡ በአ
ንደበቱ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ግለጥለት ፡ አለኝ ።
፲፫፤ ምሥጢርን ፡ ገለጥሁለት ፡ ዕዝነ ፡ ልቡናውም ፡
እንዲሰማ ፡ አንደበቱም ፡ እንዲናገር ፡ አደረ
ግሁ ፤ ፍጥረቱ ፡ በተፈጠረበት ፡ በዕብራይስ
ጥም ፡ ቋንቋ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እናገር ፡ ጀመርሁ ፤
የአባቶችን ፡ መጽሐፎች ፡ ወሰደ ፡ እነዚያም ፡
የዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈባቸው ፡ ናቸው ።
ተናገራቸው ፡ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ይማራ
ቸው ፡ ጀመር ። የጸነነውን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ እነግ
ረው ፡ ነበር ፤ ዝናብ ፡ በሚዘንብባቸው ፡ በስድ
ስቱ ፡ ወሮች ፡ ተማራቸው ።
፲፬፤ በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሚቆጠር ፡ በሰባተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ ከአባቱ ፡ ጋር ፡
ተነጋገረ ፤ ከካራን ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ሄዶ ፡ አይቶ
አት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሄድ ፡
ነገረው ።
፲፭፤ አባቱ ፡ ታራም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ በሰላም ፡
ሂድ ፡ የፍቅር ፡ አምላክ ፡ ጐዳናህን ፡ ያቅናልህ ፤
እግዚአብሔርም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡
ይኑር ፤ ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቅህ ፤ በሚ
ያዩህ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ቸርነትንና ፡ ይቅርታን ፡
መወደድን ፡ ይስጥህ ፤ በአንተ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገ
ርን ፡ ለማድረግ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አይሠ
ልጥኑብህ ፤ በሰላም ፡ ሂድ ።
፲፮፤ በእርስዋ ፡ ለመኖር ፡ ለዓይኖችህ ፡ ያማረች ፡
አገር ፡ ብታይ ፡ መጥተህ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ውሰ
ደኝ ፤ ለአንተ ፡ ልጅ ፡ ይሆንህ ፡ ዘንድ ፡ የወን
ድምህን ፡ የአራን ፡ ልጅ ፡ ሎጥንም ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ ውሰደው ፤ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡
ከአንተ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፤ በደኅና ፡ እስክትመለስ ፡
ድረስ ፡ ወንድምህ ፡ ናኮርን ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ትተ
ኸው ፡ ሂድ ፤ ሁላችንም ፡ በአንድነት ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ እንሄዳለን ፡ አለው ።
፲፯፤ አብራምም ፡ ሚስቱን ፡ ሶራን ፡ የወንድሙን ፡
የአራን ፡ ልጅ ፡ ሎጥንም ፡ ይዞ ፡ ከካራን ፡ ወደ ፡
ከነዓን ፡ ሄደ ። ወደ ፡ ሱርም ፡ መጣ ፡ እስከ ፡ ሰቂ
ሞንም ፡ ድረስ ፡ ተመላለሰ ፤ ረጅም ፡ ግራር ፡ ባለ
በት ፡ ሰፍራ ፡ አደረ ፤ ከኢማት ፡ መግቢያ ፡
ጀምሮ ፡ ረጅም ፡ ግራር ፡ እስካለበት ፡ ድረስ ፡
አገሪቱ ፡ እጅግ ፡ ያማረች ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እነሆ ፡
አየ ።
፲፰፤ እግዚአብሔርም ፡— ለልጆችህና ፡ ለአንተ ፡ ይህ
ችን ፡ አገር ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ አለው ። በዚያም ፡
መሥዊያን ፡ ሠራ ፤ ለታየው ፡ ለእግዚአብሔር ፡
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ።
ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ በምሥራቅ ፡ አንጻር ፡ ወዳ ፲፱፤
ለች ፡ ወደ ፡ ዓጌ ፡ በምዕራብ ፡ አንጻርም ፡ ወዳ
ለች ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ተራራ ፡ ሄደ ፡ በዚያም ፡
ድንኳን ፡ ተከለ ፤ ባያትም ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ አገ
ሪቱ ፡ ሰፊ ፡ ናት ፡ እጅግም ፡ ያማረች ፡ ናት ፡
ሁሉም ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ይበቅላል ፤ ወይን ፡
በለስ ፡ ሮማን ፡ ወይራ ፡ ግራር ፡ ቡጥን ፡
ዘይት ፡ ዋንዛ ፡ ሰኖበር ፡ የደጋውም ፡ እንጨት ፡
ሁሉ ፡ የሚበቅልበት ፡ ናት ፤ ውኃውም ፡ በተ
ራራው ፡ ላይ ፡ ይሄዳል ።
የከላውዴዎን ፡ ዕጣ ፡ ከምትሆን ፡ ከዑር ፡ አው ፳፤
ጥቶ ፡ ወደዚህ ፡ ተራራ ፡ ያመጣውን ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ አመሰገነው ።
በሰባተኛው ፡ ሱባኤ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ፳፩፤
በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤
በዚህ ፡ ተራራ ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፡ የእግዚአ
ብሔርንም ፡ ስም ፡ ጠራ ፡— አንተ ፡ አምላኬ ፡
ሆይ ፡ የዘላለም ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ አለ ።
እግዚአብሔር ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡
ይኖር ፡ ዘንድ ፡ በሕይወት ፡ በኖረበት ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ፡ እንዳይለየው ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ።
ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ሄደ ፡ እስከ ፡ ፳፪፤
ኬብሮንም ፡ ደረሰ ። ኬብሮንም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተሠ
ራች ። በዚያም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ።
ሎጥ ፡ እስኪ.ገባ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አገር ፡
ሄደ ።
በሀገርም ፡ ራብ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቆ ፳፫፤
ጠር ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ አብራም ፡ ወደ ፡
ግብጽ ፡ ሄደ ፤ ሚስቱ ፡ ከእርሱ ፡ ሳትለይ ፡ በግ
ብጽ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ። የግብጽ ፡ ክፍል ፡
የምትሆን ፡ ጣይናስም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከኬብሮን ፡
በኋላ ፡ በሰባት ፡ ዓመት ፡ ተሠራች ። /
ፈርዖን ፡ የአብራምን ፡ ሚስት ፡ ሶራን ፡ በቀማው ፡ ፳፬፤
ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ አብራም ፡ ሚስት ፡
ስለ ፡ ሶራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈርዖንን ፡ በደዌ ፡
ገረፈ ፡ ቤተ ፡ ሰቡንም ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡ መቅሠ
ፍት ፡ ገረፈ ።
አብራምም ፡ በገንዘብ ፡ በላሞችና ፡ በበጎች ፡ ፳፭፤
በፈረሶችና ፡ በአህዮች ፡ በግመሎችም ፡ በሴ
ቶች ፡ ባሪያዎችና ፡ በወንዶች ፡ ባሪያዎች ፡
በወርቅና ፡ በብርም ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ነበረ ።
የወንድሙ ፡ ልጅ ፡ ሎጥም ፡ በገንዘብ ፡ እንደ ፡
እርሱ ፡ የከበረ ፡ ነበረ ።
ፈርዖንም ፡ የአብራምን ፡ ሚስት ፡ ሶራን ፡ ፳፮፤
መለሰ ። ከግብጽም ፡ ተነሥቶ ፡ በምዕራብና ፡
በቤቴል ፡ ምሥራቅ ፡ መካከል ፡ በዓጌ ፡ ባለ ፡
መሠዊያ ፡ በታ ፡ ቀድሞ ፡ ድንኳኑን ፡ ተክሎበት ፡
ወደ ፡ ነበረው ፡ በታ ፡ ሄደ ።
በደኅና ፡ የመለሰው ፡ ፈጣሪውን ፡ እግዚአብሔ ፳፯፤
ርንም ፡ አመሰገነው ።

፳፰፡ በአርባ ፡ አንድ ፡ ኢዮቤልዩ ÷ በመጀመሪያው ፡
ሱባዔ ፡ በሚቈጠር ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡
እንዲህ ፡ ሆነ ፤ ወደዚህ ፡ ቦታ ፡ ተመለሰ ፡ በመ
ሠዊያውም ፡ ላይ ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ÷
የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ጠራ ፡— ገናና ፡
አምላክ ፡ የምትሆን ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሆይ ÷ የዘላለም ፡ አምላኬ ፡ ነህ ፡ አለ ።
፳፱፡ ከዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈጠር ፡ በአራተኛው ፡
ዘመን ፡ ሎጥ ፡ ከእርሱ ፡ ተለየ ÷ ሎጥም ፡ በሰ
ዶም ፡ ኖረ ። የሰዶም ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ እጅግ ፡
ኃጢአተኞች ፡ ነበሩ ። የወንድሙ ፡ ልጅ ፡ ከእ
ርሱ ፡ ስለ ፡ ተለየ ፡ በልቡ ፡ አዘነ ። ሎጥ ፡ በተማ
ረከበት ፡ በዚያ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ አልነበረውምና ።
፴፡ ሎጥ ፡ ከእርሱ ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ሱባዔ ፡
በሚቈጠር ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አብራምን ፡ ተናገረው ፡— በዚያ ፡ ትኖር ፡
ዘንድ ፡ ባለህበት ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ አንገትህን ፡
አቅንተህ ፡ አራቱን ፡ ማዕዘን ፡ ተመልከት ፤
ይህችን ፤ የምታያትን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡
እሰጥሃለሁና ÷ ለልጆችህም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ድረስ ፡ እሰጣቸዋለሁና ።
፴፩፡ ልጆችህን ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ አደርጋለሁ ፤
ሰው ፡ የባሕር ፡ አሸዋን ፡ መቊጠር ፡ ይችል ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ልጆችህም ፡ ይቈጠራሉ ፤ ተነሥ
ተህ ፡ ቁመትዋን ፡ ወርድዋን ፡ ዙራት ፤ ለልጆ
ችህ ፡ እሰጣታለሁና ፡ ሁሉን ፡ ተመልከት ፡
አለው ።
፴፪፡ አብራምም ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ሄዶ ፡ በዚያ ፡
ተቀመጠ ።
፴፫፡ በዚያም ፡ ዓመት ፡ የኤላም ፡ ንጉሥ ፡ ኮሎዶጎ
ሞር ፡ መጣ ÷ የሰናዖርም ፡ ንጉሥ ፡ አማልፋል ÷
የሲላር ፡ ንጉሥም ፡ አሪአክ ÷ የአሕዛብ ፡ ንጉ
ሥም ፡ ቲርጋል ፡ መጡ ÷ የሰዶምንም ፡ ንጉሥ ፡
ወጉት ።
፴፬፡ የሰዶም ፡ ንጉሥ ፡ ሸሸ ፤ የጨው ፡ አገር ፡ በሚ
ሆን ፡ በሴላስ ፡ ዲማው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በጦር ፡
ተወግተው ፡ ወደቁ ፤ አደማንና ፡ ሰዶምን ፡
ሰቤኤንንም ፡ ማረኩ ፤ የአብራምን ፡ የወንድ
ሙን ፡ ልጅ ፡ ሎጥንም ፡ ማረኩ ÷ ገንዘቡ
ንም ፡ ሁሉ ፡ ዘረፉ ÷ እስከ ፡ ዳንም ፡ ድረስ ፡ ሄደ ።
፴፭፡ ከጦር ፡ የዳነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ የወን
ድሙ ፡ ልጅ ፡ ሎጥ ፡ እንደ ፡ ተማረከ ፡ ለአብ
ራም ፡ ነገረው ። አሽከሮቹን ፡ አስጊጦ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ አሥራት ፡ ቀዳምያትን ፡ ይሰጡ ፡
ዘንድ ፡ አብራም ፡ በእርሱም ፡ በልጆቹም ፡ ሥር
ዓትን ፡ ሠራ ። እግዚአብሔርም ፡ ለዘላለም ፡
ይይዙት ፡ ዘንድ ፡ በፊቱ ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ለካህ
ናቱ ፡ ሊሰጡት ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓትን ፡ ሠራ ።
፴፮፡ ከሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሥራት ፡ ይሰጡ ፡
ዘንድ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ሠርቶታልና ፡
ለዚህ ፡ ሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ዘመን ፡ የለውም ። ከእ
ህሉም ÷ ከወይኑም ÷ ከዘይቱም ÷ ከላሞችም ÷
ከበጎችም ÷ ከፍየሎችም ፡ አሥራት ፡ ይሰጡ ፡
ዘንድ ፡ ሥርዓት ፡ አድርጎ ፡ ሠራ ።

እርሱም ፡ በፊቱ ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ሊበሉት ፡ ፴፯፡
ሊጠጡት ፡ ለካህናት ፡ ሰጠ ።
የሰዶምም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ደረሰ ÷ በፊ ፴፰፡
ቱም ፡ ሰገደ ፡— ጌታችን ፡ አብራም ፡ ሆይ ÷
ያዳንኸውን ፡ ሰው ፡ ስጠን ÷ ምርኮው ፡ ግን ፡
ላንተ ፡ ይሁንህ ፡ አለው ።
አብራምም ፡— እኔ ፡ አብራምን ፡ አከበርሁት ፡ ፴፱፡
የምትል ፡ እንዳትሆን ÷ ከእኔ ፡ ጋር ፡ የሄዱ ፡
ጐልማሶች ፡ እድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ይውሰዱ ፡
እንጂ ፡ ከበሉት ፡ በቀር ፡ ከአንተ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡
የክር ፡ ፈትል ፡ የጫማ ፡ ጠፍር ፡ እንዳልወስድ ፡
ገናና ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ እጆቼን ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ አደርጋለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡
የሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ኤሴኬልና ፡ አውናን ፡ መምሬ ፡
እነርሱ ፡ እድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ይውሰዱ ፡
አለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈ ፩፡
ጠር ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በሦስተኛው ፡
ወር ፡ መብቻ ፡— አብራም ! አትፍራ ÷ ጠበቃህ ፡
እኔ ፡ ነኝ ÷ ዋጋህም ፡ እጅግ ፡ ይበዛል ፡ ሲል ፡
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሕልም ፡ ወደ ፡ አብ
ራም ፡ መጣ ።
አቤቱ ÷ ምን ፡ ትሰጠኛለህ ? እኔ ፡ ልጅ ፡ ሳል ፪፡
ወልድ ፡ በሞት ፡ እሄዳለሁ ፤ የደማስቆ ፡ ሰው ፡
የሚሆን ፡ የአማቲየል ፡ ልጅ ፡ የማሴት ፡ ልጅ ፡
ኤልኤዘር ፡ እርሱ ፡ ይወርሰኛል ፤ ለእኔ ፡ ግን ፡
ልጅ ፡ አልሰጠኸኝም ፤ ልጅ ፡ ስጠኝ ፡ አለ ።
ከባሕርይህ ፡ የሚወለድ ፡ ልጅ ፡ እርሱ ፡ ይወር ፫፡
ስሃል ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ አይወርስህም ፡ አለው ።
ወደ ፡ ውጪ ፡ አውጥቶ ፡— ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተመ ፬፡
ልከቶ ÷ መቊጠር ፡ ይቻልህ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡
ከዋክብትን ፡ ቊጠር ፡ አለው ። ሰማይን ፡ አየ ፤
ከዋክብትንም ፡ ተመለከተ ፡— ልጅህ ፡ እንደዚህ ፡
ይሆናል ፡ አለው ። እግዚአብሔርንም ፡ አመ
ነው ፤ ማመኑም ፡ ጽድቅ ፡ ሆኖ ፡ ተቈጠረለት ።
ለዘላለም ፡ ይዞሃት ፡ ልትኖር ፡ ለአንተም ፡ ከአን ፭፡
ተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችህ ፡ ልትሆን ፡ የከነዓናው
ያንን ፡ አገር ፡ እሰጥህ ፡ ዘንድ ፡ የከላውዴዎን ፡
ዕጣ ፡ የምትሆን ፡ ከዑር ፡ ያወጣሁህ ፡ እኔ ፡
አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ አለው ።
አቤቱ ÷ አቤቱ ÷ እንድወርሳት ፡ በምን ፡ አው ፮፡
ቃለሁ ? አለ ።
ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሆነውን ፡ ወይፈን ÷ ሦስት ፡ ፯፡
ዓመት ፡ የሆነውን ፡ ፍየል ÷ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሆ
ነውን ፡ በግ ÷ ዋኖስና ፡ ርግብንም ፡ አምጣልኝ ፡
አለው ።
ይህን ፡ ሁሉ ፡ በወር ፡ እኩሌታ ፡ አመጣ ። እርሱ ፡ ፰፡
ግን ፡ የኬብሮን ፡ አቅራቢያ ፡ በምትሆን ፡ በማ
ምሬ ፡ ባለ ፡ ግራር ፡ ሥር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።
በዚያም ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አረደ ÷ ፱፡
በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ደማቸውን ፡ አፈሰሰ ፤
ከሁለት ፡ ከሁለት ፡ አደረጋቸው ÷ በየመልካቸ

ውም ፡ በአንጻራቸው ፡ አኖራቸው ÷ አዕዋፍን ፡
ግን ፡ ጨርሶ ፡ አልቆረጣቸውም ። ወፎችም ፡
ወደ ፡ መሥዋዕት ፡ ይወርዱ ፡ ነበር ።
፲፤ አብራም ፡ ግን ፡ ይከለክላቸው ፡ ነበር ፤ ወፎች ፡
ይበሉአቸው ፡ ዘንድ ፡ አላሰናበተም ፡ ነበር ።
፲፩፤ ፀሐይ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ በአብራም ፡
እንቅልፍ ፡ መጣበት ፤ እነሆ ÷ የሚያስፈራ ፡
ጽኑ ፡ ጨለማ ፡ በላዩ ፡ ወደቀበት ።
፲፪፤ ልጅህ ፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡ ስደተኛ ፡ እንዲሆን ፤
አራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እንዲገዙአቸውና ፡
መከራ ፡ እንዲያጸኑባቸው ፡ ፈጽመህ ፡ እወቅ ፡
ተብሎ ፡ ለአብራም ፡ ተነገረ ። ለሚገዙላቸው ፡
ወገኖችም ፡ እኔ ፡ እፈርድላቸዋለሁ ።
፲፫፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ጋር ፡ ከዚያ ፡
ይወጣሉ ። አንተም ፡ አባቶችህ ፡ ወደ ፡ ሄዱ
በት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ በሰላም ፡ ትሄዳለህ ፤
በበጎ ፡ እድማናም ፡ ትቀበራለህ ።
፲፬፤ በአራተኛው ፡ ትውልድ ፡ ወደዚህ ፡ ይመለሳሉ ፤
እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ አለመመለሳቸው ፡ የአ
ሞራውያን ፡ ኃጢአት ፡ አልተፈጸመምና ፡ ስለ
ዚህ ፡ ነው ።
፲፭፤ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ ተነሣ ፤ ፀሐይም ፡ ገባ ፤ እሳ
ትም ፡ ይነድ ፡ ጀመር ፤ እነሆ ÷ ምድጃው ፡ እየ
ጤሰ ፡ እሳቱ ፡ እየነደደ ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡
አለፈ ።
፲፮፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአብራም ፡
ጋር ፡ ተማማለ ፡— ከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ታላቁ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ÷ ይኸውም ፡ ኤፍ
ራጥስ ፡ የሚባል ፡ ወንዝ ፡ ነው ÷ ይህችን ፡ አገር ፡
ለልጆችህ ፡ እሰጣለሁ ፤ የቄኔውስንና ፡ የዜቄኔ
ዜውስን ÷ የቀድሞኔውስን ÷ የፌራዚውስንና ፡
የራፌኢያን ÷ የፌከሬውስን ÷ የኤዌውስንና ፡
የአሞሬዎስን ÷ የከናኔዎስንና ፡ የጌርጌሲዎስን ፡
የኢያሴውስንም ፡ አገር ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ተማ
ማለ ።
፲፯፤ አብራምም ፡ ሄዶ ፡ መሠዊያውን ፡ አዘጋጀ ፤ አዕ
ዋፍን ÷ መሥዋዕታቸውን ÷ ወይናቸውንም ፡
አቀረበ ፤ እሳት ፡ በላው ።
፲፰፤ በዚያች ፡ ወር ፡ ከአብራም ፡ ጋር ፡ ተማማልን ፤
ይኸውም ፡ ከኖኅ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተማማልነው ፡
መሐላ ፡ ነው ።
፲፱፤ አብራምም ፡ በዓልንና ፡ ሥርዓትን ፡ እስከ ፡ ዘላ
ለም ፡ ድረስ ፡ አጸናለት ፤ አብራምን ፡ ደስ ፡
አለው ፤ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ለሚስቱ ፡ ለሶራ ፡
ነገራት ፤ ልጅ ፡ እንዲወለድለት ፡ አመነ ። እር
ስዋ ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ አትወልድም ፡ ነበር ፤ ሶራ ፡
ባልዋ ፡ አብራምን ፡ መከረችው ፡— ከእርስዋ ፡
የተወለደ ፡ ልጅን ፡ አሳድግልሃለሁና ፡ ከግብጽ ፡
በመጣኋት ፡ በአገልጋዬ ፡ በአጋር ፡ ድረስባት ፡
አለችው ።
፳፤ አብራምም ፡ የሚስቱ ፡ የሶራን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፡—
እንዳልሽ ፡ አድርጊ ። ሶራም ፡ ከግብጽ ፡ ያመጣ
ቻትን ፡ አገልጋይዋን ፡ አጋርን ፡ አምጥታ ፡
ሚስት ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ ለባልዋ ፡ ለአብራም ፡
ሰጠቻት ።
ደረሰባት ÷ ፀነሰች ÷ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፤ ፳፩፤
በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈጠር ፡ በአምስተኛው ፡
ዓመት ፡ ስሙን ፡ እስማኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።
በዚያም ፡ ዓመት ፡ አብራም ፡ በሕይወት ፡ የኖረ
በት ፡ ዘመን ፡ ሰማንያ ፡ ስድስት ፡ ዘመን ፡ ነው ።
በዚህ ፡ በአራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአምስተ ፳፪፤
ኛው ፡ ዓመት ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ በወሩ ፡ እኩ
ሌታ ፡ የዘራው ፡ የስንዴ ፡ አዝመራ ፡ ከሚደርስ
በት ፡ አስቀድሞ ፡ አብራም ፡ በዓል ፡ አደረገ ።
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ የእህሉን ፡ መጀመሪያውን ፡ ፳፫፤
እህል ፡ አዲስ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ አቀረበ ፤ ወይፈኑንና ፡ የበጉን ፡
ሙክት ፡ በጉንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ሠዋ ፤
ስቡንና ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ወይናቸውንም ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ከነጭ ፡ ዕጣን ፡
ጋር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቀረበ ።
እግዚአብሔር ፡ አብራምን ፡ ተነጋገረው ፡— ፳፬፤
ያማረ ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ ነኝ ። በፊቴ ፡ ተገዘር ፤
ፍጹም ፡ ሁን ፤ በአንተና ፡ በእኔ ፡ መካከል ፡ መሐ
ላዬን ፡ አጸናለሁ ፤ እጅግ ፡ አከብርሃለሁ ።
አብራምም ፡ በግምባሩ ፡ ወደቀ ÷ እግዚአብሔ ፳፭፤
ርም ፡ ተናገረው ፡— እነሆ ÷ ሥርዓቴ ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ÷ ለብዙ ፡ አሕዛብም ፡
አባት ፡ አደርግሃለሁ ፡ አለው ።
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስምህ ፡ አብራም ፡ አይባል ፤ ፳፮፤
የብዙ ፡ አሕዛብ ፡ አባት ፡ አድርጌሃለሁና ፡ ከዛሬ ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ስምህ ፡ አብር
ሃም ፡ ይባል ። አንተን ፡ ፈጽሜ ፡ አከብርሃለሁ ፡
የአሕዛብንም ፡ አገር ፡ እሰጥሃለሁ ÷ ነገሥታቱ ፡
ከአንተ ፡ ይወለዳሉ ።
በአንተና ፡ በእኔ ፡ መካከል ፡ በዘመናቸው ፡ የዘ ፳፯፤
ላለም ፡ ሥርዓት ፡ ልትሆን ÷ ከአንተም ፡ በኋላ ፡
በልጆችህ ፡ መካከል ፡ መሐላዬን ፡ አጸናለሁ ፤
አምላክ ፡ እሆንህ ፡ ዘንድ ÷ ለዘላለሙ ፡ ልትገ
ዛት ፡ ተሰደህ ፡ በሄድህበት ፡ በከነዓን ÷ ከአን
ተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችህ ፡ አምላክ ፡ እሆናቸው ፡
ዘንድ ፡ መሐላዬን ፡ አጸናለሁ ፤ አምላካቸውም ፡
እሆናቸዋለሁ ።
እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ እንዲህ ፡ ፳፰፤
አለው ፡— አንተ ፡ መሐላዬን ፡ ጠብቅ ፤ ከአን
ተም ፡ በኋላ ፡ የሚነሡ ፡ ልጆችህ ፡ ይጠብቁ ፤
ወንድ ፡ ወንዱን ፡ ሁሉ ፡ ግዘሩ ÷ የሰውነታችሁ
ንም ፡ ሰንከፍ ፡ ሁሉ ፡ ተገዘሩ ፤ በእናንተና ፡
በእኔ ፡ መካከል ፡ ለልጅ ፡ ልጅም ፡ ለዘላለም ፡
የሥርዓቱ ፡ ምልክት ፡ ይሆናል ።
በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ ወንድ ፡ ወንዱን ፡ ሁሉ ፡ ፳፱፤
በየወገናችሁ ፡ ግዘሩት ። እቤት ፡ የተወለደ
ውን ÷ ከአሕዛብም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በወርቅ ፡
የገዛችሁትን ፡ ከልጆችህ ፡ ወገን ፡ ያይደለም ፡
ቢሆን ፡ ይገዘሩ ፤ እቤትህ ፡ የተወለደም ፡ በወር
ቅህም ፡ የገዛኸው ፡ ቢሆን ፡ ይገዘሩ ።
ለዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ሊሆን ፡ መሐላዬ ፡ በሰው ፴፤
ነታችሁ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ። ግዙር ፡ ያልሆነ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ወንድ ፡ ልጆችሁ ፡ ሁሉ ፡ በስምንተኛይቱ ፡ ቀን ፡
የሰውነቱን ፡ ሰንከፍ ፡ ያልተገዘረውም ፡ ሁሉ ፡
ሥርዓቴን ፡ አፍርሶአልና ፡ ያች ፡ ሰውነት ፡ ከወ
ገንዋ ፡ ተለይታ ፡ ትጥፋ ፡ አለው ።
፴፩፡ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡— ሚስትህ ፡ ሰራ ፡
ስምዋ ፡ ሳራ ፡ ነውና ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስምዋ ፡
ሶራ ፡ አይባል ፤ አከብራታለሁ ÷ ከእርስዋም ፡
ልጅ ፡ እሰጥሃለሁ ፤ እርሱንም ፡ አከብረዋለሁ ÷
ታላቅ ፡ ወገንም ፡ ይሆናል ÷ የአሕዛብም ፡ ነገሥ
ታት ፡ ከእርሱ ፡ ይወለዳሉ ፡ አለው ።
፴፪፡ አብርሃም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በግምባሩ ፡ ወደቀ ።
በልቡ ፡— በመቶ ፡ ዘመኔ ፡ ልጅ ፡ እወልድ ፡ ነበ
ርን ? ሳራስ ፡ በዘጠና ፡ ዘመንዋ ፡ ልጅ ፡ ትወ
ልድ ፡ ነበርን ? በቸርነትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡
ደስ ፡ አለው ።
፴፫፡ አብርሃምም ፡ እግዚአብሔርን ፡— እስማኤል ፡
በፊትህ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ አለው ።
፴፬፡ እግዚአብሔርም ፡— እንዳልህ ፡ ይሁን ፡ አለው ÷
ሳራም ፡ ልጅ ፡ ትወልድልሃለች ÷ ስሙንም ፡
ይስሐቅ ፡ ትለዋለህ ፤ መሐላዬንም ፡ የዘላለም ፡
ሥርዓት ፡ ሊሆን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አጸናለሁ ÷
ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ ለሚነሡ ፡ ለልጆቹም ፡ አጸና
ለሁ ።
፴፭፡ ስለ ፡ እስማኤልም ፡ የለመንኸውን ፡ ሰማሁህ ፤
እነሆ ÷ አከብረዋለሁ ÷ አገነዋለሁ ÷ ፈጽሜ ፡
አበዛዋለሁ ፤ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትንም ፡
ይወልዳል ÷ በብዙ ፡ ወገን ፡ ላይም ፡ እሾመዋ
ለሁ ።
፴፮፡ መሐላዬን ፡ ግን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ወራት ፡
በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ሳራ ፡ ከምትወልድልህ ፡
ከይስሐቅ ፡ ጋር ፡ አጸናለሁ ። ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይህ
ንን ፡ ተናግሮ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡
አብርሃም ፡ ካለበት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ።
፴፯፡ አብርሃምም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለው ፡ አደ
ረገ ፤ ልጁን ፡ እስማኤልን ÷ በቤት ፡ የተወለደ ፡
ባሪያውን ፡ ሁሉ ÷ በወርቁ ፡ የገዛውንም ፡ በቤቱ ፡
ያለ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ሁሉ ፡ ወስዶ ፡ የሰውነታ
ቸውን ፡ ሰንከፍ ፡ ገዘረ ።
፴፰፡ በዚህችም ፡ ቀን ፡ አብርሃም ፡ ተገረዘ ፤ ቤተ ፡
ሰቦቹም ÷ በወርቅ ፡ የገዛቸው ፡ ባሪያዎቹም ፡
ሁሉ ÷ ከአሕዛብም ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የተወ
ለዱ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተገረዙ ። ይህችም ፡
ሕግ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡
ሆነች ።
፴፱፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነውና ÷ በሰማይ ፡ ጽላትም ፡
ተጽፎአልና ፡ የዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፤ ከስ
ምንቱ ፡ ቀንም ፡ አንዲት ፡ ቀንም ፡ መተላለፍ ፡
የለም ።
፵፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀንም ፡ ድረስ ፡ የሰውነቱን ፡
ሰንከፍ ፡ ያልተገረዘ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከጥፋት ፡
ልጆች ፡ ወገን ፡ ነውና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብ
ርሃም ፡ ከማለለት ፡ ሥርዓት ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡
አይደለም ።
፵፩፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ምል
ክት ፡ የለውም ፤ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔ
ርን ፡ መሐላ ፡ ስላፈረሰ ፡ ፈጽሞ ፡ ከምድር ፡
ተነቃቅሎ ፡ ለመጥፋት ፡ ተዘጋጅቶአልና ፡
ምልክት ፡ የለውም ። የሚያመሰግኑ ፡ መላእክ
ትና ፡ መላእክተ ፡ ገጽ ፡ ሁሉ ፡ ከተፈጠሩበት ፡
ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ተፈጥሮአቸው ፡ እንዲህ ፡ ነውና ።
በሚያመሰግኑ ፡ መላእክትና ፡ በመላእክተ ፡ ፵፪፡
ገጽ ፡ አንጻር ፡ ንጹሐን ፡ ከሆኑ ፡ ከመላእክትና ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡
መረጠው ።
አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዝ ፤ የዚ ፡ ፵፫፡
ህን ፡ መሐላ ፡ ምልክት ፡ ይጠብቁ ÷ ለልጆቻቸ
ውም ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሁን ፤ ለዘላለም ፡
ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ለመሐላ ፡ ሥርዓት ፡ ሠርቶአልና ፡ ከም
ድር ፡ እንዳይጠፉ ፡ ይሁኑ ። እስማኤልን ፡ ወን
ድሞቹንና ፡ ልጆቹን ፡ ዔሳውንም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በባለምዋልነት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አላቀረባቸ
ውም ፤ ምንም ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ቢሆኑ ፡
አልመረጣቸውና ፡ እነርሱን ፡ አልመረጠም ።
ወገን ፡ ይሆነው ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡ ለይቶ ፡ ፵፬፡
መረጠ ። ሕዝቡ ፡ አሕዛቡ ፡ ሁሉ ፡ የእርሱ ፡
ወገኖች ፡ ናቸውና ÷ ሁሉም ፡ ለእርሱ ፡ ይገባ
ልና ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ለይቶ ፡ ሰበሰበው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ ያስቱአቸው ፡ ዘንድ ፡
አጋንንትን ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ አሠለጠነ ።
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ገዢአቸው ፡ እርሱ ፡ ፵፭፡
ብቻ ፡ ነውና ፡ መልአክም ፡ ቢሆን ፡ ሰይጣንም ፡
ቢሆን ፡ ማንንም ፡ አላሠለጠነም ። እርሱ ፡ ይጠ
ብቃቸዋል ። ከአጋንንትና ፡ ከመላእክት ፡ እጅ ፡
ትእዛዙን ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉም ፡
እጅ ፡ ይመራመራቸዋል ። እነርሱ ፡ ልጆቹ ፡
ይሆኑት ፡ ዘንድ ፡ እርሱም ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ አምላክ ፡ ይሆናቸው ፡
ዘንድ ፡ ያከብራቸዋል ።
አሁንም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይህችን ፡ ሥር ፡ ፵፮፡
ዓት ፡ ሐሰት ፡ እንዳያደርጉ ፡ እኔ ፡ እነግርሃለሁ ።
በሰውነታቸው ፡ ከመገረዛቸው ፡ የተነሣ ፡ ልጆ
ቻቸውን ፡ ሳይገርዙ ፡ ይቀራሉና ÷ የቤልሆርም ፡
ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡
ሳይገረዙ ፡ ይተዋሉና ፡ እንደዚህች ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡
ልጆቻቸውን ፡ አይገርዙም ።
መሐላውን ፡ አፍርሰዋልና ÷ ከሕጉም ፡ ወጥተ ፡ ፵፯፡
ዋልና ፡ ያች ፡ጽኑ ፡ መዓት ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ታዛ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ትደረጋለች ። የዚ
ህን ፡ ምልክት ፡ ሥርዓቱን ፡ እንዳልፈጸሙ ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈጽሞ ፡ ለመጥፋት ፡ ሰውነታ
ቸውን ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ አድርገዋልና ፡ ተበሳ
ጭተው ፡ ተሳደቡ ።
በዚህች ፡ ዓለም ፡ ለሚሠራው ፡ ስሕተት ÷ ኃጢ ፡ ፵፰፡
አቱ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሰረይ ፡ ዘንድ ፡ እንግ
ዲህ ፡ የኃጢአት ፡ ስርየት ፡ የላቸውም ።
በአራተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ በግራሩ ፡ አንጻር ፡ ፵፱፡
ባለ ፡ በወይራው ፡ ሥር ፡ ለአብርሃም ፡ ታየነው ÷

ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ተነጋገርን ። ከሚስቱ ፡ ከሳራ ፡
ልጅ ፡ እንዲሰጠው ፡ እኛ ፡ ነገርነው ፤ ሳራም ፡
ይህንን ፡ ነገር ፡ ከአብርሃም ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተነጋ
ገርን ፡ ሰምታለችና ፡ ሳቀች ። እኛም ፡ ዘለፍናት ፤
ፈርታ ፡ ስለ ፡ ተነገረው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሳቀች ፡
መሳቅዋን ፡ አሌ ፡ አለች ።
፳፤ የልጅዋንም ፡ ስም ፡ ስሙ ፡ ይስሐቅ ፡ ተብሎ ፡
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነገርናት ። ያን
ጊዜም ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ በተመለስን ፡ ጊዜ ፡ እር
ስዋ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ፀነሰች ።
፳፩፤ በዚህም ፡ ወር ፡ እግዚአብሔር ፡ በገሞራና ፡ በሰ
ዶም ፡ በዮርዳኖስ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉና ፡ በሳቦኤ
ምም ፡ ፍርዱን ፡ ፈረደ ። በድኝና ፡ በእሳት ፡
አቃጠላቸው ፤ እጅግ ፡ ኃጢአተኞችና ፡ ክፉ
ዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በሰውነታቸውም ፡ እንዲሴ
ሰኑ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ኃጢአት ፡ እንዲሠሩ ፥
እነሆ ፥ ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ነገርሁህ ፡
እስከዚህች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አጠፉቸው ።
፳፪፤ እንደዚሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡
ኃጢአት ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ በሠሩባቸው ፡ ቦታ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡ ፍርድ ፡ ያለ ፡ ፍር
ድን ፡ ያደርጋል ።
፳፫፤ እግዚአብሔር ፡ አብርሃምን ፡ በቸርነት ፡ አስቦታ
ልና ፡ ሎጥን ፡ አዳነው ፥ ከጥፋትም ፡ መካከል ፡
አወጣው ። ከአዳም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ
ዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተሠርቶ ፡
የማይታወቅ ፡ ኃጢአትን ፡ እርሱም ፡ ከልጆቹ ፡
ጋር ፡ በምድር ፡ ሠራ ፤ አባት ፡ በልጁ ፡ ደርሶአ
ልና ።
፳፬፤ ፈጽሞ ፡ ያጠፉቸው ፡ ዘንድ ፥ በሰዶምም ፡ እንደ ፡
ተደረገው ፡ ፍርድ ፡ ፍርዳቸውንም ፡ ያደርግ ፡
ዘንድ ፥ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሰውን ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ እንዳያስ
ቀርለት ፥ እነሆ ፥ ታዘዘ ። በልጆቹም ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ዕዳ ፡ መሆኑ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ታወቀ ።
፳፭፤ በዚህም ፡ ወር ፡ አብርሃም ፡ ከኬብሮን ፡ ተጕዞ ፡
ሄዶ ፡ በጌራሮን ፡ ተራሮች ፡ ባሉ ፡ በሱርና ፡ በቃ
ዴስ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠ ።
፳፮፤ በአምስተኛው ፡ ወር ፡ እኩሌታም ፡ ከዚያ ፡
ተጕዞ ፡ በተማማለበት ፡ ጕድጓድ ፡ አጠገብ ፡
አደረ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩፤ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ እኩሌታ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ሳራን ፡ በረድኤት ፡ ጎበኛት ፥ እንዳለ
ውም ፡ አደረገላት ። ፀንሳ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለ
ደች ። በሦስተኛው ፡ ወር ፥ በወሩም ፡ እኩሌታ ፡
እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ በነገረው ፡ ቀን ፡
ከአዝመራው ፡ አስቀድሞ ፡ በሚደረገው ፡ በዓል ፡
ይስሐቅ ፡ ተወለደ ።
፪፤ አብርሃምም ፡ ልጁን ፡ በስምንተኛይቱ ፡ ቀን ፡
ገረዘው ፤ ለዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ሊሆን ፡ እንደ ፡
ተሠራ ፡ በማለው ፡ መሐላ ፡ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡
ተገረዘ ።

በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈጠር ፡ በስድስተ ፫፤
ኛው ፡ ዓመት ፡ አብርሃም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤርሳ
ቤህ ፡ መጥተን ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ እንመለስ ፡
ዘንድ ፡ ለሳራ ፡ እንደ ፡ ነገርናት ፡ አሳየነው ። እር
ስዋም ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ፀነሰች ።
በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ተመለስን ፥ ሳራንም ፡ ፬፤
በፊታችን ፡ ፀንሳ ፡ አገኘናት ፥ ሳራንም ፡ መረቅ
ናት ። ዳግመኛም ፡ ሰባት ፡ ልጅ ፡ እስኪወልድና ፡
ሳይሞት ፡ እስኪያይ ፡ ድረስ ፡ እንዳይሞት ፡ የታ
ዘዘለትን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ነገርናት ።
በይስሐቅም ፡ ስም ፡ ልጅ ፡ ይጠራለት ። የልጅ ፡ ፭፤
ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ይሆናሉ ፥ ከአሕዛብም ፡
ጋር ፡ ይቈጠራሉ ።
ከይስሐቅም ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡ ፮፤
ይሆናል ፥ የልዑል ፡ የእግዚአብሔር ፡ እድል ፡
ፈንታ ፡ ይሆናልና ፤ ከአሕዛብ ፡ ጋር ፡ አይቈጠ
ርም ።
ከሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ተለይቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፯፤
ጌጥ ፡ ያለው ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፥ ለክህነ
ትና ፡ ለመንግሥትም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፥ ክቡር ፡
ወገንም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ልጁ ፡ ሁሉ ፡ ይስሐቅ ፡
ወደሚያመልከው ፡ አምላክ ፡ እድልነት ፡ ወረደ ።
ጎዳናችንን ፡ ሄደን ፡ የነገርነውን ፡ ሁሉ ፡ ለሳራ ፡ ፰፤
ነገርናት ፤ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ፈጽሞ ፡
ብዙ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።
ላዳነውና ፡ ተሰዶ ፡ በሄደበት ፡ አገር ፡ ደስ ፡ ላሰ ፱፤
ኘው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ መሠዊያን ፡
ሠራ ።
በዚህም ፡ ወር ፡ በቤርሳቤህ ፡ በሠራው ፡ መሠ ፲፤
ዊያ ፡ አቅራቢያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ የደስታ ፡ በዓል ፡
አደረገ ።
በዚህችም ፡ በዓል ፡ ለባሪያዎቹና ፡ ለእርሱ ፡ ድን ፲፩፤
ኳን ፡ ተከለ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አስቀድሞ በጥላ ፡
የሚደረግ ፡ በዓልን ፡ እርሱ ፡ አደረገ ።
በዚህም ፡ በሰባቱ ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥ ፲፪፤
ዋዕት ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ በየቀኑ ፡ ዕለት ፡ /
ዕለት ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ሲያቀርብ ፡ ነበር ፥
ሁለት ፡ ጠቦቶች ፥ ሁለት ፡ የበግ ፡ ሙክት ፥
ሰባት ፡ በግ ፤ ስለ ፡ ልጆቹና ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ያስተ
ሰርይለት ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠዋ ፡
አንድ ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ አቀረበ ።
ድኅነት ፡ ለሚደረግበት ፡ መሥዋዕትም ፡ ሰባት ፡ ፲፫፤
የበግ ፡ ሙክት ፥ ሰባት ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፥ ሰባት ፡
በግ ፥ ሰባት ፡ የፍየል ፡ ሙክት ፡ ሠዋ ። መሥ
ዋዕታቸውንና ፡ ፍልቅ ፡ አድርገው ፡ አፍስ
ሰው ፡ የሚጠጡት ፡ ወይናቸውን ፡ በስባቸው ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ አቀረበ ። በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድርጎ ፡
ሊቀበለው ፡ የተመረጠ ፡ ዕጣንንም ፡ በመሠዊ
ያው ፡ ላይ ፡ ጥዋት ፡ ጥዋት ፡ ያጥን ፡ ነበር ።
ማታ ፡ ማታም ፡ ሽቱን ፡ ያጥን ፡ ነበር ። ነጭ ፡ ፲፬፤
ዕጣን ፥ ሚን ፡ የሚባል ፡ ሽቱ ፥ ልባንጃ ፡ የሚባል ፡
ሽቱና ፡ ቀንዓትን ፥ ከርቤና ፡ ናርዶስ ፡ የሚባል ፡
ሽቱ ፥ ስልቡል ፡ ቀበርቾም ፡ እነዚህን ፡ ሰባቱን ፡
ሁሉ ፡ ያጥን ፡ ነበር ፤ የተከለሰውንና ፡ የተለቀ

መውን ÷ በሚዘን ፡ የተከከለውንና ፡ አንድ ፡
የሆነውን÷ንጹሕ፡የሆነውንም፡ያቀርብ፡ነበር።
፲፭፡ በፍጹም፡ሰውነቱና፡በፍጹም፡ልቡናው፡ደስ፡
ብሎት ፡ እርሱ ፡ ከቤቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
ሰባት፡ቀን፡ይህን፡በዓል፡አደረገ። ከእርሱም፡
ጋር ፡ በዕድ ፡ ያልተገረዘ ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ አልነ
በረም ።
፲፮፡ ለዘላለም፡የሚኖር፡እውነተኛ፡ልጅ፡ይስሐቅ፡
ከእርሱ፡እንዲወለድ፡ስላወቀና፡ስለ፡ተረዳ፡
ፈቃዱን፡ለመፈጸም፡ፈጥሮታልና፡አዳምን፡
የፈጠረ፡አምላኩን፡አመሰገነው። ሁሉን፡እን
ዳደረገ፡እንደ ፡ እርሱ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከእር
ሱም፡የከበረ፡ልጅ፡ይወለዳል ።
፲፯፡ ደስ፡ብሎት፡አከበራት ። የዚህችንም፡በዓል፡
ስምዋን፡የእግዚአብሔር፡በዓል፡አላት ። ይህ
ችንም፡በዓል፡ልዑል፡አምላክ፡ደስ፡ብሎት፡
የሚቀበላት፡የእግዚአብሔር፡በዓል፡አላት ።
፲፰፡ ለዘላለም ፡ አከበርነው ፤ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚ
ነሣ ፡ ልጁንም ፡ ሁሉ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ በሰ
ማይ፡ጽላት፡እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በጊዜዋ ፡ ጊዜ ፡
ያቺን፡በዓል ፡ አድርጎአልና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ጸንቶ፡በሚኖርበት፡ዘመን፡ሁሉ፡አከበርነው።
፲፱፡ ስለዚህ፡ነገር፡ለእስራኤል፡ሕግ፡ሊሆን፡በሰ
ማይ፡ጽላት፡ተጻፈ። እስከ፡ዕለተ፡ምጽአት፡
ድረስ፡ባለ፡ዘመኑ፡ሁሉ፡ለልጆቻቸው፡የዘ
ላለም ፡ ሕግ ፡ ሊሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዶ ፡
ሊቀበለው÷በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ደስ ፡ ብሎአ
ቸው ፡ ሰባት ፡ ቀን፡በጥላ፡የሚደረግ፡በዓልን፡
የሚያከብሩ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ተጻፈ ።
፳፡ በዓሉን፡ያደርጉት፡ዘንድ÷በጥላም፡ይቀመጡ፡
ዘንድ÷በራሳቸውም፡አክሊል፡ይደፉ፡ዘንድ÷
ከፈሳሹም፡የአኻያውን፡ቅጠል፡ጫፍ፡ይይዙ፡
ዘንድ÷በእስራኤል፡የዘላለም፡ሥርዓት፡ሆኖ፡
ተጽፎአልና፡ለዚህ፡ሥርዓት፡የተወሰነ፡ዘመን፡
የለውም ።
፳፩፡ አብርሃምም ፡ የሰሌኑን ፡ ጫፍ ፡ ለጋውን ÷
ያማረ ፡ የእንጨቱንም ፡ ፍሬ ፡ ይዞ ፡ በየቀኑ ፡
ዘንባባውን፡ይዞ፡ሰባት ፡ ቀን ፡ የመሠዊያውን፡
ዙሪያ ፡ ይዞር ፡ ነበር ።
፳፪፡ ጥዋት ፡ ጥዋትም ፡ ሁሉን፡ለፈጠረ፡ለአምላኩ፡
ለእግዚአብሔር ፡ እየተገዛ ፡ ያመሰግን ፡ ነበር ።
፳፫፡ በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡
በሚቈጠር ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ይስሐቅ፡ ጡት፡
ጣለ ።
፳፬፡ ልጁ ፡ ይስሐቅ ፡ ጡት ፡ በጣለበት ፡ ቀን፡ በሦስ
ተኛው ፡ ወር ፡ አብርሃም ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ አደ
ረገ ። የግብጽ፡ሴት፡የምትሆን፡የአጋር፡ልጅ፡
እስማኤልም ፡ በአባቱ ፡ በአብርሃም ፡ ፊት ፡ በበ
ታው ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።
፳፭፡ ልጆቹን ፡ አይቶአልና÷ ልጅንም ፡ ሳይወልድ ፡
አልሞተምና ፡ አብርሃም ፡ ደስ ፡ አለው ። እግ
ዚአብሔርንም ፡ አመሰገነው ።
፳፮፡ ሎጥ፡ከእርሱ፡በተለየበት፡ቀን፡የተናገረውን፡
ነገር ፡ አሰበ ። ምድርን ፡ ይወርሳት ፡ ዘንድ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅን ፡ ሰጥቶ
ታልና ፡ ደስ ፡ አለው ÷ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግ
ዚአብሔርንም ፡ በአፉ ፡ አመሰገነው ።
ሳራም ፡ እስማኤልን ፡ ሲጫወትና ፡ ሲዘፍን ፡ ፳፯፤
አየችው÷አብርሃምንም፡እጅግ ደስ ፡ ብሎት፡
አየች ። እስማኤልንም፡በየችው፡ጊዜ፡ቀንታ፡
አብርሃምን፡— የዚህች፡የባሪያ፡ልጅ፡ከልጄ፡
ከይስሐቅ ፡ ጋር ፡ ርስት ፡ አይወርስምና ፡ ይህ
ችን ፡ ባሪያ ፡ ከልጅዋ ፡ ጋር ፡ አስወጥተህ ፡ ስደ
ዳት ፡ አለችው ።
ከእርሱ ፡ ለይቶ ፡ ይሰዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ፳፰፤
ልጁና ፡ ስለ ፡ ባሪያው ፡ በአብርሃም ፡ ፊት ፡
ኀዘን ፡ ሆነ ።
እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡— ስለ ፡ ባሪያ ፳፱፤
ህና ፡ ስለ ፡ ልጅህ ፡ በፊትህ ፡ ኀዘን ፡ አይደረግ÷
በይስሐቅ፡ስምህ፡ይጠራልሃልና፤ልጅም፡ይጠ
ራልና ፡ ሳራ ፡ የነገረችህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ስማና ፡
አድርግ ። ስለዚያች ፡ ባሪያ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ አት
ዘን ፤ ከልጆችህ ፡ ወገን ፡ ነውና ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡
አደርገዋለሁ ፡ አለው ።
አብርሃምም ፡ በጥዋት ፡ ገሥግሦ ፡ ሄዶ ፡ ውኃ ፡ ፴፤
ያለበትን ፡ ረዋትና ፡ ዳቦውን ፡ አምጥቶ ፡ ለአ
ጋር ፡ አሸከማት ÷ ልጁንም ፡ አሳዝሎ ፡ ሸኛት፤
በቤርሳቤ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እየተቅበዘበዘች ፡
ሄደች ።
ውኃው ፡ ከረዋትዋ ፡ አለቀ ÷ ልጁም ፡ ተጠማ÷ ፴፩፤
መሄድም ፡ ተሳነው ÷ ሕፃኑም ፡ ወደቀ ፤ እናቱ ፡
አነሣችው ፡ ሄዳ ፡ በአንዲት ፡ የዘይት ፡ እንጨት ፡
ሥር ፡ አኖረችው ፡— የልጁን ፡ ሞት ፡ አላይም ፡
ብላለችና ፡ ጦር ፡ ወርውሮ ፡ የሚያደርሱበት ፡
አንዲት ፡ ምዕራፍ ፡ ያህል ፡ ርቃ ፡ ሄዳ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ተቀመጠች ፤ በዚያም ፡ ተቀምጣ ፡
አለቀሰች ።
ከከበሩ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ መልአክ ፡— አንቺ ፡ ፴፪፤
አጋር ÷ ለምን ፡ ታለቅሻለሽ ÷ እግዚአብሔር ፡
ቃልሽን ፡ ሰምቶአልና ÷ ሕፃኑንም ፡ በዓይኔ ፡
ምሕረት ፡ አይቶታልና ፡ ተነሥተሽ ፡ ሕፃኑን ፡
አንሥተሽ ፡ በእጅሽ ፡ ያዢው አላት ።
ዓይኖችዋንም ፡ ገልጣ ፡ ውኃ ፡ ያለበትን ፡ ጕድ ፴፫፤
ጓድ ፡ አየች ፤ ሄዳም ፡ ረዋትዋን ፡ ውኃ ፡ ሞላች፤
ልጅዋንም ፡ አጠጣች ፤ ተነሥታም ፡ ወደ ፡
ፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሄደች ።
ሕፃኑም ፡ አድጎ ፡ አዳኝ ፡ ሆነ ÷ እግዚአብሔ ፴፬፤
ርም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡ ኖረ ። እናቱም ፡
ከግብጽ ፡ ሴቶች ፡ ሚስት ፡ አጋበችው ÷ ወንድ ፡
ልጅን ፡ ወለደችለት ። በለመንሁት ፡ ጊዜ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ለእኔ ፡ ቅርቤ ፡ ነው ፡ ብላለችና ፡
ስሙንም ፡ ናቢአት ፡ አለችው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተኛው ፡ ሱባኤ ፡ በመ ፩፤
ጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡
እንዲህ ፡ ሆነ ። በዚህ ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ ሁለተ
ኛው ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲወደው ፡ ስለ ፡

አብርሃም ፡ በሰማይ ፡ ቃሎች ፡ ተሰሙ ፤ በሚና
ገረው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የታመነ ፡ ሆኖአልና ።
፪፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ ሰይጣን ፡ መጥቶ ፡ በአምላክ ፡
ፊት ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— እነሆ ÷ አብርሃም ፡
ልጁ ፡ ይስሐቅን ፡ ይወደዋል ÷ ከሁሉም ፡
ይልቅ ፡ እርሱ ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል ፤ በመሠዊያው ፡
ላይ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ያቀርበው ፡ ዘንድ ፡
ንገረው ።
፫፤ ይህን ፡ ነገር ፡ ቢያደርግ ፡ አንተ ፡ ታያለህ ፤ በም
ትፈትነው ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ የታመነ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ታውቃለህ ፡ አለው ። እግዚአብሔር ፡
ግን ፡ አብርሃም ፡ በነገረው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ የታ
መነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃል ÷ በአገሩ ፡ በድርቅ ፡
ፈትኖታልና ፤ በነገሥታቱም ፡ ገንዘብ ፡ ፈትኖ
ታልና ፤ ዳግመኛም ፡ በሚስቱ ፡ መቀማት ፡ ፈት
ኖታልና ፤ በመገረዝም ፡ ፈትኖታልና ፤ በሰደዳ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ በአጋርና ፡ በልጁ ፡ በእስማኤል ፡
ፈትኖታልና ፤ በፈተነው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ የታ
መነ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶአልና ፤ ሰውነቱም ፡ ቸል ፡
አላለችምና ፡ የታመነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃል ።
፬፤ የታመነ ፡ ነውና ÷ እግዚአብሔርንም ፡ ይወዳ
ልና ÷ ሥራውን ፡ አላቆየም ።
፭፤ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡— አብርሃም ÷
አብርሃም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ አብርሃምም ፡—
አቤት ÷ አለሁ ፡ አለ ። የምትወደውን ፡ ልጅህን ፡
ይስሐቅን ፡ ይዘህ ፡ ከፍ ፡ ወዳለች ፡ ተራራ ፡
ሂድ ፤ እኔ ፡ ከምነግርህ ፡ ከተራሮች ፡ ወደ ፡ አን
ዲቱ ፡ ተራራ ፡ አውጣው ፡ አለው ።
፮፤ ከዚያም ፡ በነግህ ፡ ገሠገሠ ፤ በቅሎውን ፡ ጭኖ ፡
ሁለቱንም ፡ ብላቴኖቹን ፡ ልጁ ፡ ይስሐቅንም ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይዞ ÷ ለመሥዋዕት ፡ የሚሆን ፡
እንጨትንም ፡ ፈልጦ ፡ አሸክሞ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡
እግዚአብሔር ፡ ወዳዘዘው ፡ ቦታ ፡ ሄደ ።
፯፤ ቦታውንም ፡ በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ አየ ÷ ውኃ ፡ ወዳለ
በት ፡ ጕድጓድም ፡ ደረሰ ፤ ብላቴኖቹን ፡— በቅሎ
ውን ፡ ይዛችሁ ፡ ከዚህ ፡ ቆዩኝ ፤ ልጄና ፡ እኔ ፡
ሄደን ፡ ሰግደን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንመለሳለን ፡
አላቸው ።
፰፤ መሥዋዕት ፡ የሚሠዋበትን ፡ እንጨት ፡ ለልጁ ፡
ለይስሐቅ ፡ አሸክሞ ÷ ወቅለምቱንና ፡ እሳቱን ፡
በእጁ ፡ ይዞ ÷ እስከዚያ ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ሁለቱ ፡
ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ ሄዱ ።
፱፤ ይስሐቅም ፡ አባቱን ፡— አባቴ ፡ አለው ፤ እር
ሱም ፡— ልጄ ÷ እነሆ ÷ አለሁ ፡ አለው ። እነሆ ÷
እሳቱና ፡ ወቅለምቱ ፡ እንጨቱም ፡ አለ ፤ አባቴ ÷
ለመሥዋዕት ፡ የሚሆነው ፡ በግ ፡ ወዴት ፡ ነው ?
አለው ።
፲፤ ልጄ ፡ ሆይ ÷ ለመሥዋዕት ፡ የሚሆነውን ፡ በግ ፡
እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ አለው ። እግዚአብ
ሔር ፡ ወዳለበት ፡ ተራራ ፡ ቦታ ፡ ቀረበ ፤ መሠ
ዊያ ፡ ሠራ ÷ እንጨቱንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡
ከመረ ፤ ልጁን ፡ ይስሐቅን ፡ አስሮ ፡ በመሠዊ
ያው ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ አስተኛው ።
፲፩፤ ልጁ ፡ ይስሐቅን ፡ ይሠዋው ፡ ዘንድ ፡ ወቅለም
ቱን ፡ ለማንሣት ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ። እኔም ፡ በፊቱ ፡
ቆምሁ ፤ ሁሉን ፡ በሚገዛ ፡ በሰይጣንም ፡ ፊት ፡
ቆምሁ ።
እግዚአብሔርም ፡— እርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፲፪፤
የሚፈራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቄአለሁና ፡ በይስ
ሐቅ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ እንዳያወርድ ፡ በእርሱም ፡
ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳያደርግ ፡ ንገረው ፡
አለ ።
በሰማይ ፡ ሆኜ ፡— አብርሃም ÷ አብርሃም ፡ ብዬ ፡ ፲፫፤
ጠራሁት ። እርሱም ፡ ደንግጦ ፡— እነሆ ÷ እኔ ፡
አለሁ ፡ አለኝ ። በይስሐቅ ፡ ላይ ፡ እጅህን ፡ አታ
ውርድ ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈራ ፡
እንደ ፡ ሆንህ ፡ ዛሬ ፡ አውቄአለሁና ፤ ከእኔም ፡
ለበኵር ፡ ልጅህ ፡ አልራራህምና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታድርግ ፡ አልሁት ፤
የሰውን ፡ ልቡና ፡ የሚገዛ ፡ ሰይጣንም ፡ አፈረ ።
አብርሃምም ፡ ዓይኖቹን ፡ አቅንቶ ፡ አየ ። እነሆ ÷ ፲፬፤
ቀንዱን ፡ በሳቤቅ ፡ እንጨት ፡ የተያዘ ፡ አንድ ፡
በግ ፡ ሲወርድለት ፡ አየ ። አብርሃምም ፡ ሄዶ ፡
ያንን ፡ የበግ ፡ አውራ ፡ አምጥቶ ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡
ፋንታ ፡ ለመሥዋዕት ፡ አቀረበው ።
አብርሃምም ፡ ያንን ፡ ቦታ ፡— እግዚአብሔር ፡ ፲፭፤
የታየበት ፡ ቦታ ፡ ይበል ፡ ዘንድ ፡— እግዚአብ
ሔርን ፡ ያየሁበት ፡ አለው ፤ ተራራውም ፡ ደብረ ፡
ጽዮን ፡ ነው ።
እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ በሰማይ ፡ ሆኖ ፡ ፲፮፤
ዳግመኛ ፡ በስሙ ፡ ጠራው ፤ በእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ እንነግረው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ታየነው ፤
እግዚአብሔርም ፡— በራሴ ፡ ማልሁ ፡ አለ ፡ አል
ነው ።
ይህን ፡ ነገር ፡ አድርገሃልና ÷ ለምትወደው ፡ ፲፯፤
ለበኵር ፡ ልጅህ ፡ ከእኔ ፡ አልራራህለትምና ፡
ፈጽሜ ፡ እንዳከብርህ ፤ በባሕር ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡
አሸዋና ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኮከብ ፡ ልጅህን ፡ ፈጽሜ ፡
እንዳበዛው ÷
ልጆችህም ፡ የጠላቶቻቸውን ፡ አገር ፡ እንዲወ ፲፰፤
ርሱ ÷ ቃሌን ፡ ስለ ፡ ሰማህ ፡ ፈንታ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ያሉ ፡ አሕዛብንም ፡ ሁሉ ፡ እንዲወርሱ ÷
እኔ ፡ በዘዝሁህ ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ለእኔ ፡ የታመንህ ፡
እንደ ፡ ሆንህ ፡ ለሁሉ ፡ ነገርሁ ፤ በሰላም ፡ ሂድ ፡
አለው ።
አብርሃምም ፡ ወደ ፡ ብላቴኖቹ ፡ ሄደ ። ከዚያም ፡ ፲፱፤
ተነሥተው ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ሄዱ ።
አብርሃርም ፡ በመሐላ ፡ የውኃ ፡ ጕድጓድ ፡ አደረ ።
ያችን ፡ በዓል ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ የደ
ስታ ፡ በዓል ፡ አደረጋት ። በሄደባቸው ፡ በሰባቱ ፡
ቀኖች ፡ መጠን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ አላት ።
በሰላም ፡ ተመለሰ ።
ሰባት ፡ ቀን ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይህችን ፡ በዓል ፡ ፳፤
ለማድረግ ፡ በልጆቹና ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ ታዘዘ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ እንዲህ ፡ ታው
ቆአል ፤ ተጽፎአል ።
በአርባ ፡ ሁለተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጀመሪ ፳፩፤
ያው ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈጠር ፡ በአንዱ ፡ ዓመት ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



አብርሃም ፡ ተመልሶ ፡ በኬብሮን ፡ አንጻር ፡
ሁለት ፡ የዓመት ፡ ሱባዔ ፡ኖረ ። ይህችውም ፡
ቃርያታርበት ፡ ናት ።
፳፪፤ በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሚ
ቈጠር ፡ በመ፪መሪያው ፡ ዓመት ፡ ሳራ ፡ በሕይ
ወት ፡ የኖረችበት ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ፥ በኬብ
ሮን ፡ ሞተች ።
፳፫፡ አብርሃምም ፡ አልቅሶ ፡ ይቀብራት ፡ ዘንድ ፡
ሄደ ። ልቡናው ፡ ይታገሥ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲ
ሁም ፡ በአፉ ፡ በተናገረው ፡ ነገር ፡ ቸል ፡ አይልም ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈተንነው ። በዚህም ፡ የታገሠ ፡
ሆኖ ፡ ተገኘ ፤ በውስጡ ፡ ሬሳውን ፡ ሊቀብር ፡
የመቃብር ፡ ቦታ ፡ ይሰጡት ፡ ዘንድ ፡ ከኬጢ ፡
ልጆች ፡ ጋር ፡ በልቡና ፡ ትዕግሥት ፡ ተነግሮአ
ልና ፡ አልተበሳጨም ።
፳፬፤ እግዚአብሔርም ፡ በሚያዩት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ፊት ፡ በለምዋልነትን ፡ ሰጠው ፡ ከኬጢ ፡ ልጆች ፡
በየዋሃት ፡ ለመነ ፤ በግራሩ ፡ አንጻር ፡ ያለች ፡
እጥፍነት ፡ ያላት ፡ ዋሻ ፡ ሰጡት ። ይህችውም ፡
ኬብሮን ፡ ናት ። አርባ ፡ ብር ፡ ሸጡለት ።
፳፭፤ እነርሱ ፡— ያለ ፡ ዋጋ ፡ እንስጥህ ፡ ብለው ፡ ለመ
ኑት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ የቦታውን ፡ ዋጋ ፡ ብሩን ፡
ፈጽሞ ፡ ሰጥቶአልና ፡ ከእነርሱ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡
አልወሰደም ፤ ዳግመኛም ፡ ሰገደላቸው ።
፳፮፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እጥፍነት ፡ ባላት ፡ ዋሻ ፡ ሬሳዋን ፡
ቀበረ ። ሳራ ፡ በሕይወት ፡ የኖረችበት ፡ ሞላ ፡
ዘመንዋ ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ሰባት ፡ ሆነ ፤ እነዚህም ፡
ሁለት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ አራት ፡ ሱባዔና ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ ናቸው ። ሳራ ፡ በሕይወት ፡ የኖረችብ
ቸው ፡ የዘመኖችዋ ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ነው ።
፳፯፤ አብርሃም ፡ በተፈተነበት ፡ ገንዘብ ፡ የታመነ ፡
ልቡናው ፡ የታገሠ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘበት ፡ ይህ ፡
መከራ ፡ አሥር ፡ ነው ፤ ለእርሱ ፡ ይሰጣት ፡
ዘንድ ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ለልጁ ፡ ይሰጣት ፡
ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ከነዓን ፡ የነገረውን ፡
ነገር ፡ እንቢ ፡ አላለም ፡ በዚያ ፡ ሬሳውን ፡ ይቀ
ብር ፡ ዘንድ ፡ ቦታንም ፡ ለመነ ። የታመነ ፡ የሚ
ታገሥ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶአልና ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡
የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ተብሎ ፡ ተጻፈ ።
፳፰፤ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ለልጁ ፡ ለይስሐቅ ፡ ሚስ
ትን ፡ አጋባው ፥ ስምዋም ፡ ርብቃ ፡ ይባላል ፤
ይህችውም ፡ የአብርሃም ፡ ወንድም ፡ የናኮር ፡
ልጅ ፡ የሚሆን ፡ የባቱኤል ፡ ልጅና ፡ የላባ ፡
እኅት ፡ ናት ። የአብርሃም ፡ ወንድም ፡ የናኮር ፡
ሚስት ፡ የሚልካ ፡ ልጅ ፡ ባቱኤልም ፡ ርብቃ
ንና ፡ ላባን ፡ ወለዳቸው ።
፳፱፡ አብርሃምም ፡ ከሳራ ፡ አስቀድሞ ፡ አጋር ፡ በሞ
ተች ፡ ጊዜ ፡ በቤቱ ፡ ከተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡
የምትሆን ፡ ሦስተኛ ፡ ሚስትን ፡ አገባ ፥ ስም
ዋም ፡ ኬጡራ ፡ ይባላል ፤ እርስዋም ፡ ዮክሳንንና ፡
ዘንበሬን ፡ ማዳንንና ፡ ማድያን ፡ ሰሂያንና ፡ ኢያ
ዝቦትን ፡ እነዚህን ፡ ስድስቱን ፡ ወለደችለት ።
፴፡ በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ዘመን ፡ በስድስተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ርብቃ ፡ ለይስ
ሐቅ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፥ ዔሳውንና ፡ ያዕቆብን ፡
ወለደችለት ።
ያዕቆብ ፡ ፍጹም ፡ ቅን ፡ ነበረ ፥ ዔሳው ፡ ግን ፡ ፴፩፤
ጨካኝ ፡ ቀማኛ ፡ ጠጕራም ፡ ነበረ ፤ እነዚህም ፡
ጐልማሶች ፡ አደጉ ።
ያዕቆብ ፡ መጻፍን ፡ ተማረ ፥ ዔሳው ፡ ግን ፡ አርበ ፴፪፤
ኛና ፡ አዳኝ ፡ ነበረና ፡ አልተማረም ። ሰልፍን ፡
ክፉ ፡ ሥራንም ፡ ሁሉ ፡ ተማረ ፤ አብሃርምም ፡
ያዕቆብን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፤ ይስሐቅ ፡ ግን ፡ ዔሳ
ውን ፡ ይወድ ፡ ነበር ።
አብርሃም ፡ የዔሳውን ፡ ሥራ ፡ አየ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፴፫፤
በያዕቆብ ፡ ስም ፡ ልጅ ፡ እንዲጠራለት ፡ አወቀ ።
ርብቃን ፡ ጠርቶ ፡ እርስዋ ፡ ከዔሳው ፡ ይልቅ ፡ ፴፬፤
ያዕቆብን ፡ ፈጽማ ፡ እንድትወደው ፡ አይቶአ
ልና ፡ የያዕቆብን ፡ ነገር ፡ አዘዛት ።
ልጄ ፡ ሆይ ፥ ያዕቆብን ፡ ልጄን ፡ ጠብቂ ፤ እርሱ ፡ ፴፭፤
ስለ ፡ እኔ ፡ ፋንታ ፡ በሰዎች ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡
ለበረከት ፡ ይሆናልና ፤ ለሴምም ፡ ልጆች ፡ መመ
ኪያ ፡ ይሆናልና ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚኖሩ ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጠቢቃ ፡ ሊሆንለት ፡
እግዚአብሔር ፡ እርሱን ፡ እንዲመርጥ ፡ አውቃ
ለሁና ።
እነሆ ፥ ልጄ ፡ ይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ይልቅ ፡ ዔሳ ፴፮፤
ውን ፡ ይወዳል ፤ አንቺ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ያዕቆብን ፡
ስትወጂው ፡ እኔ ፡ አይቻለሁ ፤ ዳግመኛም ፡ ለእ
ርሱ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ማድረግን ፡ ጨምሪለት ።
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ለዘላለም ፡ እስከሚነሣ ፡ ትው ፴፯፤
ልድ ፡ ሁሉ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እርሱ ፡
ለበረከት ፡ ይሆነኛልና ፡ ዓይኖችሽ ፡ ወዳጅሽን ፡
ያዕቆብን ፡ ይመልከቱ ። ከልጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡
እርሱን ፡ ፈጽሚ ፡ ወድጃለሁና ፤ ለዘላለም ፡ ይከ
ብራልና ፡ ልጁም ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ የሚሞላ ፡
ይሆናልና ፡ እጆችሽ ፡ ይጽኑ ። ልብሽም ፡ በል
ጅሽ ፡ በያዕቆብ ፡ ደስ ፡ ይበለው ፡ ሰው ፡ የባሕር ፡
አሸዋ ፡ መቍጠር ፡ ይችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እን
ደዚሁም ፡ የእርሱን ፡ ዘር ፡ ይቈጠራል ።
እግዚአብሔር ፡ እኔን ፡ ልጁን ፡ የመረቀባቸው ፡ ፴፰፤
በረከቶች ፡ ሁሉ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ለልጁና ፡
ለያዕቆብ ፡ ይሁኑ ። በልጁም ፡ ስሜ ፡ ይከበራል ፤
የአባቶቼ ፡ የኖኅና ፡ የሴም ፡ የመላልኤልና ፡ የኄ
ኖክ ፡ የሴትና ፡ የሄኖስ ፡ የአዳምም ፡ ስም ፡ ይከ
በራል ፤ እነርሱም ፡ ምድርንና ፡ ሰማይን ፡ ለማ
ጽናት ፥ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ብርሃናትንም ፡
ለማደስ ፡ ይሆናሉ ፡ አላት ።
ያዕቆብንም ፡ ጠርቶ ፡ በእናቱ ፡ በርብቃ ፡ ፊት ፡ ፴፱፤
ሳመው ፥ መረቀውም ፥ እንዲህም ፡ አለው ፡—
ልቡናዬ ፡ የወደደችህ ፡ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡ ያዕቆብ ፡
ሆይ ፥ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ አምላክ ፡ ያክብ
ርህ ።
አዳምን ፡ ያከበረባቸው ፥ ሄኖክን ፥ ኖኅን ፥ ፵፤
ሴምን ፡ ያከበረባቸውን ፡ በረከቶችንም ፡ ሁሉ ፡
ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ መረቀው ። የነገረኝን ፡ ሁሉ ፡
እሰጥሃለሁ ፡ ያለኝንም ፡ ሁሉ ፤ ጠፈር ፡ በአድ
ማስ ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ በልጅህና ፡ በአ

ንት ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ያጽናልህ ።
፵፩ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ያርቁህ ፡ ዘንድ ፡
የሰይጣን ፡ መናፍስት ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ አይሠል
ጥኑብህ ። በልጆችህም ፡ ላይ ፡ አይሠልጥኑ ።
ይኸውም ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ድረስ ፡ የምታመልከው ፡ አምላክህ ፡ ነው ።
፵፪ እግዚአብሔር ፡ ለአንተ ፡ አባት ፡ ይሁንህ ፡ አን
ተም ፡ ልጅ ፡ ሁነው ። ለሕዝቡም ፡ በለ ፡ ዘመኑ ፡
ሁሉ ፡ አለቃ ፡ ሁን ፤ ልጄ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡
ኑር ፡ አለው ።
፵፫ ከአብርሃም ፡ ዘንድ ፡ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡
ወጡ ፡ ርብቃም ፡ ያዕቆብን ፡ በፍጹም ፡ ልቡ
ናዋ ፡ በፍጹም ፡ ሰውነትዋ ፡ ከዔሳው ፡ ይልቅ ፡
እጅግ ፡ ፈጽማ ፡ ወደደችው ፤ ይስሐቅም ፡ ከያ
ዕቆብ ፡ አብልጠ ፡ ዔሳውን ፡ ይወደው ፡ ነበር ።
፵፬ በአርባ ፡ ሁለት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በሚቈጠር ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
አብርሃም ፡ እስማኤልንና ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡
ልጆቹን ፡ ይስሐቅንና ፡ ሁለቱን ፡ ልጆቹን ፡
ስድስቱን ፡ የኬጡራንን ፡ ልጆችና ፡ ልጆቻቸ
ውንም ፡ ጠርቶ ፡
፵፭ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ እው
ነት ፡ ሥራንም ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ በሰልፉ ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ እርሱ ፡ ሊሆኑ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ በል
ንጀራውን ፡ ይወድ ፡ ዘንድ ፡ አንዱም ፡ አን
ዱም ፡ በአንዱም ፡ በአንዱም ፡ ላይ ፡ ጸንተው ፡
ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።
፵፮ እውነት ፡ ለመፍረድ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ እው
ነት ፡ ለመናገር ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ በተማማል
ነው ፡ መሐላ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይገርዙ ፡ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ ካዘዘን ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ እንዳይተላለፉ ፡ ከዝ
ሙት ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአትም ፡ እንጠበቅ ፡ ዘንድ ፡
ዝሙትንና ፡ ኃጢአትን ፡ ከመካከላችን ፡ እና
ርቅ ፡ ዘንድ ፡ ካዘዘን ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይወጡ ፡
አዘዛቸው ።
፵፯ ሴት ፡ ሁሉ ፡ ብትሴስንባችሁ ፡ ልጅም ፡ ብት
ሆን ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉአት ፡ ዓይናቸው ፡ በየው ፡
ልባቸው ፡ በሰበው ፡ አይሰስኑ ። የከነዓን ፡ ልጆች ፡
ከምድር ፡ ይጠፋሉና ፡ ከከንዓን ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡
ልትሆናቸው ፡ በእጃቸው ፡ አይጨብጡ ።
፵፰ በረዓይት ፡ የተፈረደባቸውን ፡ ፍርድ ፡ በሰዶም ፡
ሰዎች ፡ የተፈረደባቸውን ፡ ፍርድና ፡ ስለ ፡ ክፉ
ታቸው ፡ ስለ ፡ ኃጢአትና ፡ ስለ ፡ ዝሙት ፡
እንደ ፡ ተፈረደባቸው ፡ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡
በሠሩት ፡ ዝሙት ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ነገራቸው ።
፵፱ እናንተም ፡ ከኃጢአትና ፡ ከዝሙት ፡ ሁሉ ፡
የማይገባውንም ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከመሥራት ፡
ተጠበቁ ። ስማችንን ፡ እንዳታሰድቡት ፡ ኑሮ
አችሁንም ፡ ሁሉ ፡ ለትምክህት ፡ እንዳታደርጉ ፡
ልጆቻችሁንም ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡
ለጥፋት ፡ እንዳታደርጉ ፡ ተጠበቁ ። እንደ ፡
ሰዶም ፡ የተረገማችሁ ፡ ትሆናላችሁ ፡ ልጆቻች
ሁም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ልጆች ፡ ይሆናሉ ።

ልጆቼ ፡ እኔ እዳኝባችኋለሁ ፡ ሰማይን ፡ የፈ ፶
ጠረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ውደዱት ፡ ትእዛዙንም ፡
ሁሉ ፡ ጠብቁ ፡ ጣዖታቸውን ፡ ኃጢአታቸውን ፡
ተከትላችሁ ፡ አትሂዱ ። ተመትተው ፡ የተሠሩ ፡
ጣዖታትንም ፡ ለእናንተ ፡ አትሥሩ ፡ ከንቱ ፡
ነውና ፤ እፍ ፡ እፍንጫ ፡ የተቀረጸላቸውን ፡
ጣዖቶች ፡ አትሥሩ ፤ እነርሱ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡
ናቸውና ፡ ምንምን ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ የላ
ቸውም ፤ ያመኑባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡
ናቸውና ፡ አታምልኩአቸው ፡ አትስገዱላቸው ።
እናንተ ፡ ግን ፡ ልዑል ፡ አምላክን ፡ አምልኩ ፤ ፶፩
ሁልጊዜም ፡ ስገዱለት ፤ በየጊዜው ፡ የገጹ ፡ ረድ
ኤቱን ፡ አለኝታ ፡ ተስፉ ፡ አድርጉ ፤ ፍርድን ፡
ፍረዱ ፤ ለእናንተ ፡ እውነት ፡ ይፈረድላችሁ ፡
ዘንድ ፡ ቸርነቱንም ፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡
በፊቱ ፡ የቀና ፡ ሥራንና ፡ እውነት ፡ ሥራን ፡
ሥሩ ። የማታውንና ፡ የጥዋቱን ፡ ዝናብ ፡ ያዘን
ብላችሁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የደከማችሁ
በትን ፡ ሁሉና ፡ እርሻችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይባርክላ
ችሁ ፡ ዘንድ ፡ እውነት ፡ ፍርድን ፡ ፍረዱ ።
እህልንና ፡ ውኃን ፡ ይባርክልሃል ፤ ከባሕርይ ፡ ፶፪
የተከፈለ ፡ ልጅህን ፡ የምድርህንም ፡ ዘር ፡
የበጎችህን ፡ መንጋና ፡ የላሞችህን ፡ መንጋ ፡
ይባርክልሃል ። በዚህም ፡ ዓለም ፡ ለበረከት ፡
ትሆናለህ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይወዱአ ፶፫
ችኋል ። እኔ ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ የተባረኩ ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ልጆቻችሁ ፡ በስሜ ፡ ይባረካሉ ።
ለልጁ ፡ ለእስማኤልና ፡ ለኬጡራ ፡ ልጆች ፡
እድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ሰጥቶ ፡ ከልጁ ፡ ከይስ
ሐቅ ፡ ለይቶ ፡ አሰናበታቸው ። የቀረ ፡ ገንዘቡን ፡
ሁሉ ፡ ለልጁ ፡ ለይስሐቅ ፡ ሰጠው ።
ልጁ ፡ እስማኤል ፡ ሄደ ፤ የኬጡራም ፡ ልጆች ፡ ፶፬
የልጅ ፡ ልጆቻቸውም ፡ በአንድነት ፡ ሄዱ ። ከፋ
ርሞን ፡ ጀምሮ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አንጻር ፡ በም
ሥራቅ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ባቢሎን ፡ መግቢያ ፡
ድረስ ፡ በአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ኖሩ ፤ እነዚህ ፡ ከእነዚህ ፡
ጋር ፡ አንድ ፡ ሆኑ ። ስማቸውም ፡ ዓረብ ፡ ነጋዴ ፡
እስማኤላውያን ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሰባተውኛ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈ ፩
ጠር ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ አብርሃም ፡ ልጁን ፡
ይስሐቅን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡—
እኔ ፡ አረጀሁ ፤ ዘመኔን ፡ ጠግቤአለሁና ፡ የምሞ
ትበትን ፡ ቀን ፡ አላውቅም ።
እነሆ ፡ እኔ ፡ የመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ፪
ዘመን ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፤ በሕይወት ፡ በኖርሁበት ፡
ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሳስበው ፡ ኖርሁ ።
በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ የአምላኬን ፡ ፈቃድ ፡ እፈ
ጽም ፡ ዘንድ ፡ በቀና ፡ ሕጉም ፡ ጸንቼ ፡ እኖር ፡
ዘንድ ፡ ስፈልግ ፡ ኖርሁ ። በሕያውነት ፡ የሚ
ኖር ፡ ንጹሕ ፡ የሚሆን ፡ የታመነ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡
ጻድቅ ፡ የሚሆን ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ የፈ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ጠረኝን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ለማድ
ረግ ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ሰውነቴ ፡ ጣዖትን ፡
ጠላች ።
፫ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ነው ÷ ሕጉን ፡ በሚያፈ
ርሱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ÷ መሐላውንም ፡ በሚያ
ፈርሱ ፡ ሰዎች ፡ ይፈርድባቸዋልና ፡ በእርሱ ፡
ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ ነገር ÷ ለሰው ፡ ፊት ፡ ማድላ
ትና ፡ መማለጃ ፡ መቀበል ፡ የለም ።
፬ ልጄ ፡ ሆይ ÷ አንተም ፡ ትእዛዙን ÷ ሥርዓቱን ÷
ሕጉን ፡ ጠብቅ ። ርኩሳን ፡ የሚሆኑ ፡ ጣዖታትን ፡
ተከትለህ ፡ አትሂድ ። የተቀረጹ ፡ ጣዖታቱንም ÷
ተቀርጸው ፡ የተሠሩትንም ፡ አታምልክ ።
፭ ብታርድም ፡ ወዶ ፡ ሊቀበልህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ጋር ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ መሥዋዕትን ፡ ሠዋ ÷
ደማቸውንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አፍስስ ፡
የሚጤሰውንም ፡ ስብ ፡ ከስንዴው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡
መሠዊያው ፡ አቅርብ ፤ በዘይት ፡ የታሸውንም ፡
መሥዋዕት ፡ ፍልቅ ፡ አድርገው ፡ ከሚጠጡት ፡
ወይን ፡ ጋር ፡ ሁሉንም ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ መሠ
ዊያው ፡ አውጣው ። ድኅነት ፡ እንደሚደረግ
ባት ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊቱ ፡
በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድርጎ ፡ ሊቀበለው ፡ የሚጤሰውን ፡
ስብ ፡ በሆዱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለው ፡ ስብ ፡ በመሠ
ዊያው ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ አኑር ።
፮ በሆድ ፡ ዕቃው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ÷
ሁለቱን ፡ ኵላሊቱንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡
ስብንም ፡ ሁሉ ÷ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ÷
ግልገል ፡ ጉልበቱንም ÷ ከኵላሊቱ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡
ተጠቀለለ ።
፯ እግዚአብሔር ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድርጎ ፡ ሊቀበ
ለው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አቅርብ ፡ እግዚአብሔር ፡
በፊቱ ፡ ወዶ ፡ ሊቀበለው ÷ ከመሥዋዕቱ ፡ ጋር ፡
ፍልቅ ፡ አድርገው ፡ ከሚጠጡት ፡ ከወይኑም ፡
ጋር ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ሊሆን ÷ የሚሠዋውን ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርብ ። ሥጋው
ንም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ÷ በማግሥቱም ፡ ብላ ።
፰ በማግሥቱ ፡ ይህ ፡ ሥጋው ፡ እስኪበላ ፡ ድረስ ፡
ፀሐይ ፡ አይግባ ፤ እግዚአብሔር ፡ ወዶ ፡ አይቀ
በለውምና ፡ ለሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አይቅር ። የተ
መረጠ ፡ አይደለምና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አይበላ ።
የበሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የኃጢአታቸውን ፡
ፍዳ ፡ ይቀበላሉ ።
፱ በቀደሙ ፡ አባቶቼ ፡ በኖኅና ፡ በሄኖክ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ አግኝቻለ
ሁና ፡ በመሥዋዕትህ ፡ ሁሉ ፡ ጨው ፡ ጨምር
በት ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሚሠዋው ፡
መሥዋዕት ፡ ሁሉ ፡ የጨው ፡ ሥርዓት ፡ አይ
ቅር ።
፲ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ እነዚህን ፡ እንጨቶች ፡ ብቻ ፡
ታገባ ፡ ዘንድ ፡ መሥዋዕት ፡ ስለሚሠዋላቸው ፡
እንጨቶች ፡ ተጠበቅ ። እነዚህም ፡ ሰኖባር ÷
ቀረጥ ÷ ሰገድ ÷ ሽነት ÷ ወይራ ÷ ዋንዛ ÷ ዶቅማ ÷
ጠዶ ÷ ዘይት ÷ ብርስነት ÷ ጥድ ÷ ሰሙ ፡ አር
በት ፡ የሚባል ፡ ቀጋ ÷ ሾላ ፡ ናቸው ።
ከእነዚህም ፡ እንጨቶች ፡ ወገን ፡ ከስቡ ፡ በታች ፡ ፲፩
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አኑር ። መጥነህም ፡ አኑ
ራቸው ፤ የነቀዘውን ፡ የበሰበሰውን ፡ እንጨት ፡
ሁሉ ፡ አታኑር ። ምንምን ፡ ፈጽሞ ፡ ነውር ፡
ነቀፋ ፡ የሌለባቸውን ፡ ያማሩትንና ፡ የጸኑትን ፡
እንጨቶች ÷ የአዲሱንም ፡ ተክል ፡ እንጨት ፡
አኑር ።
መዓዛ ፡ ተለይቶታልና ÷ እንደ ፡ ቀደመውም ፡ ፲፪
በእርሱ ፡ መዓዛ ፡ የለምና ፡ አሮጌውን ፡ እንጨት ፡
አታኑር ። መዓዛው ፡ ልዩ ፡ ነውና ÷ መዓዛውም ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይደርሳልና ፡ ከእ
ነዚህ ፡ እንጨቶች ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንጨት ፡ አታ
ቅርብ ።
ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ÷ ሥራህን ፡ ፲፫
ሁሉ ፡ ታቃና ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝሁህን ፡ አድርግ ።
በየጊዜው ፡ ሰውነትህን ፡ ንጹሕ ፡ አድርግ ፤ መሥ
ዋዕት ፡ ለመሠዋት ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ሳት
ሄድ ፡ ሰውነትህን ፡ በውኃ ፡ ታጠብ ÷ ወደ ፡
መሥዋዕቱ ፡ ሳትቀርብ ፡ እጅህንና ፡ እግርህን ፡
ታጠብ ።
መሥዋዕቱንም ፡ አቅርበህ ፡ በጨረስህ ፡ ጊዜ ፡ ፲፬
እጅህንና ፡ እግርህን ፡ ታጠብ ። በሰውነታችሁ ፡
ላይ ፡ በልብሳችሁም ፡ ላይ ፡ ደም ፡ ሁሉ ፡ አየ
ታይ ።
ልጄ ፡ ሆይ ÷ በደረው ፡ ደም ፡ እንዳትሠዋ ፡ ፈጽ ፲፭
መህ ፡ ተጠበቅ ። አፈር ፡ አልብሰው ፡ ደም ፡ ነፍስ
ናትና ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ደም ፡ አትብሉ ።
ምንምን ፡ ደም ፡ አትብላ ፤ ያለ ፡ ፍርድ ፡ በከ
ንቱ ፡ እንዳይፈስ ፡ በሐሰት ፡ ፈርደህ ፡ የሰውን ፡
ሁሉ ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ መማለጃ ፡ አትቀበል ።
በማይገባ ፡ የሚፈስ ፡ ደም ፡ ምድርን ፡ ያጠፋታ
ልና ፤ የገደለውን ፡ ሰው ፡ ቢገድሉት ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ደም ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ አትነጻም ።
በሰው ፡ ደም ፡ መማለጃንና ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ ፲፮
አትቀበል ። በፈሰሰ ፡ በሰው ፡ ደም ፡ ፍዳ ፡ በል
ዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደም ፡ በደም ፡
ይመለሳል ። መልአክ ፡ ሁቃቤውም ፡ ለበጎ ፡
ነገር ፡ ይጠብቀዋል ፤ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ትጠ
በቅ ፡ ዘንድ ፡ ከሞት ፡ ሁሉ ፡ ያድንህ ፡ ዘንድ ፡
መማለጃና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አትቀበል ።
ልጄ ፡ ሆይ ÷ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ÷ ኃጢአት ÷ ፲፯
ክፋት ÷ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ የሚያስጸይፍ ፡ የተ
ናቀ ፡ የተጠላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡
እውነት ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ እኔ ፡ የሰውን ፡ ሁሉ ፡
ሥራ ፡ አያለሁ ።
በሥራቸው ፡ ጸንተህ ፡ እንዳትኖር ÷ ፍለጋቸ ፲፰
ውንም ፡ እንዳትከተል ÷ በልዑል ፡ አምላክ ፡
ፊት ፡ ለሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ስሕተታቸውን ፡
እንዳትስት ፡ ተጠበቅ ። ይህን ፡ ያደረግህ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ከአንተ ፡ ገጹ ፡ ረድኤቱን ፡ ይሰውራል ÷
ወደ ፡ ኃጢአትህም ፡ ፍዳ ፡ ይመልስሃል ። ከም
ድር ፡ ነቃቅሎ ፡ ያጠፋሃል ። ልጅህንም ፡ ከሰ
ማይ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ነቃቅሎ ፡
ያጠፋል ፤ ስምህና ፡ ልጅህ ፡ ከዓለሙ ፡ ሁሉ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ይጠፋል ።
፳፭ ከሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአታቸውም ፡ ሁሉ ፡
ራቅ ፤ የልዑል ፡ አምላክን ፡ ሕግ ፡ ጠብቅ ፤ ፈቃ
ዱንም ፡ ፈጽም ። ሥራህን ፡ ሁሉ ፡ አቅና ፡
በሥራህ ፡ ሁሉ ፡ ያከብርሃል ። በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡
ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ እውነተኛ ፡
ልጅን ፡ ከአንተ ፡ ያስነሣል ። ከሰማይ ፡ በታች ፡
ባለ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የእኔ ፡ ስም ፡ የአንተም ፡
ስም ፡ ይታወቃል ።
፳፮ ልጄ ፡ ሆይ ÷ ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በተድላ ፡
በደስታ ፡ ጸንተህ ፡ ኑር ፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡
የሚሆን ፡ የእኔም ፡ የአንተም ፡ አምላክ ፡ ፈቃ
ዱን ፡ ለመፈጸም ፡ ያጽናህ ። ልጅህን ፡ ሁሉ ÷
የልጅ ፡ ልጅህንም ÷ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚ
ኖርበት ፡ ዘመን ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ለበረከት ፡
ትሆን ፡ ዘንድ ፡ በፍጹም ፡ በረከት ፡ ያክብር ፡
አለው ፤ ከእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡
ወጣ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ በአርባ ፡ አራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጀመ
ሪያው ፡ ሱባዔ ፡ አብርሃም ፡ በሞተበት ፡ በሁለ
ተኛው ፡ ዓመት ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ። በመጀመሪ
ያው ፡ አዝመራ ፡ ወራት ፡ የዚህችን ፡ በዓል ፡
ሱባዔ ፡ በዓል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እስማኤልና ፡
ይስሐቅ ፡ ከቤርሳቤህ ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡
አብርሃም ፡ መጡ ።
፪ አብርሃምም ፡ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ ልጆቹ ፡ መጥተዋ
ልና ፡ ደስ ፡ አለው ። በቤርሳቤህ ፡ ያለ ፡ የይስ
ሐቅ ፡ ገንዘቡ ፡ ብዙ ፡ ነበረና ፡ ይስሐቅ ፡ ሄዶ ፡
ገንዘቡን ፡ ጐብኝቶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ይመለስ ፡
ነበር ።
፫ በዚህም ፡ ወራት ፡ እስማኤል ፡ አባቱን ፡ ያይ ፡
ዘንድ ፡ መጣ ። ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ መጡ ።
፬ ይስሐቅም ፡ ስቡን ፡ ለማጤስ ፡ መሥዋዕት ፡
ሠዋ ፤ አባቱ ፡ በኬብሮን ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡
ላይ ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ። በወንድሙ ፡ በእ
ስማኤል ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ፍሪዳን ፡
አረደ ።
፭ ርብቃም ፡ ከአዲሱ ፡ ስንዴ ፡ ትኩስ ፡ ዳቦ ፡ ጋገ
ረች ÷ ያነን ፡ ብልቶ ፡ ሳይሞት ፡ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ሊያመሰግን ፡ ከመጀመሪያው ፡
አዝመራ ፡ ፍሬ ፡ ለአባቱ ፡ ለአብርሃም ፡ ያገባ ፡
ዘንድ ፡ ለልጅዋ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሰጠችው ።
፮ ይስሐቅም ፡ አብርሃም ፡ ይበላና ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡
ድኅነት ፡ የሚደረግበትን ፡ ያማረውን ፡ መሥዋ
ዕት ፡ በያዕቆብ ፡ እጅ ፡ ሰደደለት ። በልቶ ፡ ጠጥቶ ፡
ምድርንና ፡ ሰማይን ÷ የምድርን ፡ ስፋት ፡ ሁሉ ፡
የፈጠረ ፡ ልዑል ፡ አምላክን ፡ አመሰገነው ።
ይበሉ ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ ፈጣሪያቸውንም ፡ ያመ
ሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ሰጣቸው ።
፯ አሁንም ፡ አብርሃም ፡— ይህችን ፡ ቀን ፡ አሳይ
ተኸኛልና ፡ እኔ ፡ ለአንተ ፡ እገዛለሁ ፤ እነሆ ÷
እኔ ፡ የመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፤
አርጅቻለሁ ÷ ዘመኔም ፡ ተፈጽሞአል ፤ ዘመኖ
ቼም ፡ ሁሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሆኑልኝ ÷ የጠ
ላት ፡ ሰይፍም ፡ ድል ፡ አልነሣኝም ፡ አለ ።
በሰጠኸኝ ፡ ሁሉ ÷ በልጆቼም ÷ በሕይወት ፡ ፰
በኖርሁበትም ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እስከዚህች ፡ ቀን ፡
ድረስ ÷ አምላኬ ÷ ይቅርታህ ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያህ ፡
ይደረግልኝ ፤ የተመረጠ ፡ ወገን ፡ ይሆንህ ፡
ዘንድ ÷ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ተለ
ይቶ ፡ ከዛሬ ፡ጀምሮ ፡ በየጊዜው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
እስከሚነሣው ፡ ትውልድ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ድረስ ፡
ርስት ፡ ይሆንህ ፡ ዘንድ ÷ ለልጅ ፡ ልጆቼም ፡
ይደረግላቸው ፡ አለው ።
ያዕቆብንም ፡ ጠርቶ ፡— ልጄ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ÷ ፱
ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ ያክብርህ ፤ በፊቱ ፡
ፈቃዱን ፡ ለመፈጸምና ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ ለመሥ
ራት ፡ ያበርታህ ። እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ባለ ፡ ዘመኑ ፡
ሁሉ ፡ በማደሪያው ፡ ወገን ፡ ትሆኑት ፡ ዘንድ ፡
በአንተም ፡ በልጆችህም ፡ በረድኤት ፡ ማደርን ፡
ይውደድ ።
አንተም ፡ ልጄ ፡ ያዕቆብ ÷ ቀርበህ ፡ ሳመኝ ፡ ፲
አለው ፤ ቀርቦም ፡ ሳመው ።
አንተ ፡ ልጄ ፡ ያዕቆብ ፡ የከበርህ ፡ ነህ ። የልዑል ፡ ፲፩
የእግዚአብሔርም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ የከበሩ ፡ ናቸው ። በሰው ፡ ሁሉ ፡ መካ
ከል ፡ ይከብር ፡ ዘንድ ፡ ከልጆችህ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እውነተኛ ፡ ልጅን ፡ ይስጥህ ። አሕዛብ ፡
ይገዙልህ ፤ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ በልጅህ ፡ ፊት ፡
ይስገዱ ፤ በሰው ፡ ፊት ፡ አርበኛ ፡ ሁን ፤ በሴት ፡
ልጆች ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ሠልጥነህ ፡ ኑር ።
ያንጊዜ ፡ የተለየ ፡ ወገን ፡ ለመሆን ፡ ሥራዎ ፲፪
ችህ ፡ እውነተኛ ፡ ይሆናሉ ፤ የልጆችህም ፡
ሥራዎች ፡ እውነተኛ ፡ ይሆናሉ ። ልዑል ፡ አም
ላክ ፡ እኔን ፡ የመረቀበቸው ÷ ኖኅንና ፡ አዳም
ንም ፡ የመረቀበቸው ፡ ምርቃኖችንም ፡ ሁሉ ፡
ይስጥህ ። በልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ልጆች
ህን ፡ ለማክበር ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ በአ
ንተ ፡ ይደሩ ።
ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ባለማወቅ ፡ የሠራኸውን ፡ ፲፫
ኃጢአትህን ፡ ሁሉ ፡ ታስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ ከኃ
ጢአትህ ፡ ሁሉ ፡ ያንጻህ ፡ ያበርታህ ። አገሩንም ፡
ሁሉ ፡ ትወርስ ፡ ዘንድ ፡ ያክብርህ ። በዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ ማደሪያው ፡ ልትሆን ፡ ወገን ፡ ያድርግህ ፡
ዘንድ ፡ መሐላውን ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ያጽና ።
ምድር ፡ ጸንታ ፡ በኖረችበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ለአ ፲፬
ንተም ፡ ለልጅህም ፡ እርሱ ፡ በህልውና ፡ በእው
ነት ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ፈጣሪ ፡ ይሁንህ ።
አንተም ፡ ልጄ ፡ ያዕቆብ ! ነገሬን ፡ አስብ ÷ የአ ፲፭
ባትህን ፡ የአብርሃምንም ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ። ከአ
ሕዛብም ፡ ተለይ ÷ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ አትብላ ÷
ሥራቸውንም ፡ አትሥራ ። ሥራቸው ፡ የረከሰ ፡
ነውና ÷ አካሄዳቸውም ፡ ሁሉ ፡ የረከሰ ፡ ነውና ÷
የተናቀም ፡ ነውና ÷ መሥዋዕታቸውም ፡ የሚ
ያጸይፍ ፡ ነውና ፡ ባልንጀራ ፡ አትሁናቸው ።
ለሬሳዎች ፡ ፍሪዳ ፡ ያርዳሉ ÷ ለአጋንንትም ፡ ይሰ ፲፮

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ግዳሉ ÷ በመቃብርም ፡ ይበላሉ ÷ ሥራቸውም ፡
ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ብላሽ ፡ ነው ። ለማሰብ ፡ ልብ ፡ የላ
ቸውም ። ዓይናቸውም ፡ የሚያይ ፡ አይደለም ።
ሥራቸውስ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
፲፯ እንጨቱን ፡— ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ÷ ድንጋዩ
ንም ፡— ጌታዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ÷ የምታድነኝ ፡
አንተ ፡ ነህ ፡ እያሉ ፡ እነርሱ ፡ እንዴት ፡ ይስታሉ ?
እንዲህ ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ የለውም ።
፲፰ ልጄ ፡ ያዕቆብ ! አንተን ፡ ግን ፡ ገናና ፡ ፈጣሪ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይርዳህ ፤ ሰማይን ፡ የፈጠረ ፡
አምላክ ፡ ያክብርህ ፤ ከስሕተታቸው ፡ ሁሉና ፡
ከኃጢአታቸውም ፡ ያርቅህ ።
፲፱ ልጄ ፡ ያዕቆብ ! ከከንዓን ፡ ልጆች ፡ ዘር ፡ ሚስት ፡
እንዳታገባ ፡ ተጠበቅ ። ከነዓን ፡ በካም ፡ በደል ፡
ስለ ፡ ሳተ ፡ ዘራቸው ፡ ሁሉ ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡
ለመጥፋት ፡ ተዘጋጅቶአልና ÷ ዘሩም ፡ ሁሉ ፡
ከምድር ፡ ይደመሰሳልና ÷ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ በሚ
ደረግበትም ፡ ቀን ፡ ከእነርሱ ፡ የሚድን ፡ የለ
ምና ፡ ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ዘር ፡ ሚስት ፡ አታግባ ።
፳ ጣዖት ፡ ለሚያመልኩ ፡ ለተጠሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በጻድቃን ፡ አገር ፡ ምንምን ፡ አለኝታ ፡ የላቸው
ምና ÷ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ ይወርዳሉና ÷ ቍርጥ ፡
ፍርድ ፡ ወዳለበትም ፡ ቦታ ፡ ይሄዳሉና ÷ በምድ
ርም ፡ ላይ ፡ ምንምን ፡ ስም ፡ አጠራር ፡ የላቸው
ምና ፡ የሰዶም ፡ ልጆች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡
ጠፉ ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
እንደዚሁ ፡ ይጠፋሉ ።
፳፩ ልጄ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ! አትፍራ ፤ የአብርሃም ፡
ልጅ ፡ ሆይ ! አትደንግጥ ፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡
ከጥፋት ፡ ይጠብቅህ ÷ ከስሕተትም ፡ ሥራ ፡
ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ያድንህ ።
፳፪ ይህንም ፡ ቤት ፡ ስሜን ፡ በእርሱ ፡ አስጠራ ፡
ዘንድ ፡ ሠራሁልህ ። በረከትን ፡ አጸናሁልህ ፡
ለአንተም ፡ ለልጆችህም ፡ ለዘላለም ፡ ተሰጠች ።
፳፫ ቤቴን ፡ አንተ ፡ ትሠራለህና ፡ የአብርሃም ፡ ቤት ፡
ትባላለች ። ስሜንም ፡ በአምላክ ፡ ፊት ፡ ለዘላ
ለም ፡ ታጸናለህ ፡ ልጅህና ፡ ስምህ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡
ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ አለው ። ይህንንም ፡ አዝዞ ፡
መርቆ ፡ ጨረሰ ።
፳፬ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ አልጋ ፡ አንድነት ፡ ተኙ ።
ያዕቆብም ፡ በአባቱ ፡ አባት ፡ በአብርሃም ፡ አጠ
ገብ ፡ ተኛ ። ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሳመው ፡ እርሱም ፡
ልቡናውን ፡ ደስ ፡ አለው ። ልቡናውም ፡ በእ
ርሱ ፡ ላይ ፡ ነው ። በፍጹም ፡ ልቡናው ፡ መረ
ቀው ።
፳፭ ለዘላለም ፡ ልትወርሳትና ፡ ለዘላለም ፡ ይከብር ፡
ዘንድ ፡ የከበረ ፡ ልጅን ፡ ልወልድ ፡ ያችን ፡ አገር ፡
ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ የከለዳውያን ፡ ዕጣ ፡ ከምት
ሆን ፡ ከዑር ፡ ያወጣኸኝ ፡ የሁሉ ፡ አምላክና ፡
የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ÷
፳፮ በእርሱ ፡ ደስ ፡ በሚላቸው ፡ በይቅርታዬ ፡
ሁሉና ፡ በልቡናዬ ፡ ሁሉ ፡ የምወደውን ፡ ልጄን ፡
ያዕቆብን ፡ ባርከው ። ይቅርታህና ፡ ብዙ ፡ ቸርነ
ትህ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱና ፡ ለልጆቹም ፡
ይደረግ ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡
እስከሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ አትለየው ፤
ቸል ፡ አትበለው ።
እነርሱ ፡ ይጠብቁህ ፡ ዘንድ ÷ አንተም ፡ ማደሪ ፳፯
ያህ ፡ የሚሆን ፡ ወገንህን ፡ ፈጽመህ ፡ ታከብረው ፡
ዘንድ ፡ ልጆቹንና ፡ እርሱን ፡ ለማየት ፡ ዓይኖ
ችህ ፡ የተገለጡ ፡ ይሁኑ ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ይህ ፡
ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ እስከሚኖርባቸው ፡ ዘመኖች ፡
ድረስ ፡ በበረከትህ ፡ ሁሉ ፡ አክብረው ።
መሐላህንና ፡ ይቅርታህን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ÷ ከል ፳፰
ጆቹም ፡ ጋር ÷ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚኖሩ ፡ ከልጅ ፡
ልጆቹም ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ ፈቃድህ ፡ አጽና ፡
አለ ። ሁለቱን ፡ ሁሉ ፡ የያዕቆብን ፡ ጣቶች ፡ በዓይ
ኖቹ ፡ ላይ ፡ አኖረ ÷ ከአማልክት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡
አምላክን ፡ አመሰገነው ፡ ፊቱንም ፡ ሸፈነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

እግሩን ፡ ዘርግቶ ፡ የዘላለም ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀ ፩
ላፉ ፤ ሞተ ፤ በሞት ፡ ወደ ፡ አባቶቹ ፡ ሄደ ።
በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያዕቆብ ፡ በአጠገቡ ፡ ተኝቶ ፡
ነበር ÷ የአባቱ ፡ አባት ፡ አብርሃምም ፡ እንደ ፡
ሞተ ፡ አላወቀም ።
ያዕቆብም ፡ ከእንቅልፉ ፡ ተቀሰቀሰ ። እነሆ ÷ አብ ፪
ርሃም ፡ ቀዝቅዞ ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ።
አባቴ ፡ አባቴ ፡ አለ ። የመለሰለት ፡ ቃል ፡ የለም ፤
አብርሃም ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አወቀ ።
ከአጠገቡም ፡ ተነሥቶ ፡ ፈጥኖ ፡ ሄደ ። ለእናቱ ፡ ፫
ለርብቃ ፡ ነገራት ። ርብቃም ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡
ይስሐቅ ፡ ሄዳ ፡ ነገረችው ፤ አንድነት ፡ ሄዱ ።
ያዕቆብም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሄደ ። በእጁም ፡
መብራት ፡ ይዞ ፡ ነበር ። በሄዱም ፡ ጊዜ ፡ አብር
ሃምን ፡ ሞቶ ፡ ሬሳውን ፡ ተጋድሞ ፡ አገኙት ።
ይስሐቅም ፡ በአባቱ ፡ ፊት ፡ ወድቆ ፡ አለቀሰ ፤
ሳመውም ።
በአብርሃም ፡ ቤት ፡ ልቅሶ ፡ ተሰማ ። ልጁ ፡ እስ ፬
ማኤል ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ አብር
ሃም ፡ ሄዶ ፡ ለአባቱ ፡ ለአብርሃም ፡ አለቀሰለት ።
እርሱና ፡ የአብርሃም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሁሉ ፡ ጽኑ ፡
ልቅሶን ፡ አለቀሱ ። ልጆቹ ፡ ይስሐቅና ፡ እስማ
ኤልም ፡ እጥፍነት ፡ ባላት ፡ ዋሻ ፡ በሚስቱ ፡
በሳራ ፡ አጠገብ ፡ ቀበሩት ። ቤተ ፡ ሰቦቹም ፡
ሁሉ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አለቀሱለት ።
እስማኤልና ፡ ይስሐቅ ፡ ልጆቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ፭
የኬጡራም ፡ ልጆች ፡ በቦታቸው ፡ አለቀሱለት ።
የአብርሃም ፡ ልቅሶ ፡ ኀዘን ፡ ተፈጸመ ።
እርሱም ፡ ሦስት ፡ ኢዮቤልዩና ፡ አራት ፡ የዓመት ፡ ፮
ሱባዔ ÷ ይኸውም ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡
ዓመት ፡ በሕይወት ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ።
አረጀ ፡ ዘመኑንም ፡ ፈጸመ ። የቀደሙ ፡ ሰዎች ፡
በሕይወት ፡ የሚኖሩበት ፡ ዘመናቸው ፡ አሥራ ፡
ዘጠኝ ፡ ኢዮቤልዮች ፡ ነበረ ።
ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከአሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ፯
ኢዮቤልዮች ፡ ይጐድሉ ፡ ጀመር ፤ ከኢዮቤል
ዮች ፡ በማጕደል ፡ ከአብርሃም ፡ በቀር ፡ ፈጥኖ ፡

ለማርጀት ÷ በሥራቸው ፡ ክፋት ፡ ከብዙ ፡ መከራ ፡
የተነሣ ፡ ዘመናቸውን ፡ በመሰልቸት ፡ ዘመናቸ
ውን ፡ ያጎድሉ ፡ ጀመር ።
፰ ፤ አብርሃም ፡ ግን ፡ ከፈጣሪው ፡ ጋር ፡ በሥራው ፡
ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ነበረና ፡ በለ ፡ ዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በእ
ውነት ፡ ደስ ፡ ሲያሰኘው ፡ ነበረ ።
፱ ፤ ከመከራ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ፈጥኖ ፡ እስኪያረጅ ፡
ድረስ ÷ እነሆ ÷ አራቱን ፡ ኢዮቤልዮች ፡ በሕይ
ወት ፡ አልጨረሰም ። ዘመኑንም ፡ ሰለቸ ፤ ከዛሬ ፡
ጀምሮ ፡ ጽኑ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ እስከሚደረግ
በት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሚነሡ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
ሁለቱን ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ሳይጨርሱ ፡ ፈጥነው ፡
ያረጃሉ ።
፲ ፤ ከእርጅናቸውም ፡ የተነሣ ፡ እውቀታቸው ፡ የም
ትለያቸው ፡ ትሆናለች ፤ ፍጹም ፡ እውቀታቸ
ውም ፡ ትለያቸዋለች ።
፲፩ ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ኢዮቤልዩና ፡
የኢዮቤልዩ ፡ እኩሌታ ፡ ቢኖር ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡—
ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኖረ ፡ ይላሉ ።
፲፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ዘመኑ ፡ በሽታ ፡ ጣር ፡ ገዓር ፡
መከራ ፡ ነው ፤ ፍቅርም ፡ አልነበረም ፤ በመቅ
ሠፍት ፡ ላይ ፡ መቅሠፍት ÷ በቍስል ፡ ላይ ፡
ቍስል ÷ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ÷ ሐሰት ፡ በመ
መስከር ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡ መመስከር ÷ በበሽታ ፡
ላይ ፡ በሽታ ፡ ይመጣላቸዋልና ፡ ፍቅር ፡ አልነበ
ረም ።
፲፫ ፤ እንደዚሁም ፡ ክፉ ፡ መቻያ ፡ ሁሉ ÷ ይህ ፡ መከ
ራው ፡ ከዚህ ፡ ከደዌው ፡ ጋር ፡ ኋቿ ÷ ውርጭ ÷
በረድ ÷ ዋግ + እንቅልፍ ÷ ግዳጅ ÷ የሆድ ፡
በሽታ ÷ ድርቅ ፡ ሞት ÷ ሾተል ÷ መማረክ ÷
መቅሠፍት ፡ ሁሉ ÷ መከራውም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
በረከሰ ፡ ዝሙት ፡ በሚያስጸይፍ ፡ ሥራቸውና ፡
በኃጢአት ፡ ምድርን ፡ በምታረክስ ፡ በዚህች ፡
በክፉ ፡ ትውልድ ፡ ላይ ፡ ይመጣል ።
፲፬ ፤ ያንጊዜም ፡ የቀደሙ ፡ አባቶቻችን ፡ ዘመናቸው ፡
ብዙ ፡ ነበረ ÷ እስከ ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ይኖሩ ፡
ነበር ÷ ይኸውም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይፈጸም ፡
ነበር ፡ ይላሉ ።
፲፭ ፤ እነሆ ÷ እኛ ፡ በሕይወት ፡ የምንኖርበት ፡ ዘመ
ናችን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነው ። ሰው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡
ኖረ ፡ ቢባል ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ፤ እጅግም ፡
ቢበዛ ፡ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ክፉ ፡
ነው ፤ በዚያችም ፡ በክፉ ፡ ትውልድ ፡ ዘመን ፡
ምንምን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የለም ።
፲፮ ፤ በዚያችም ፡ ትውልድ ፡ ልጆች ፡ አባቶቻቸ
ውን ÷ ሽማግሌዎቻቸውንም ፡ የሚሳደቡ ፡ ይሆ
ናሉ ። በኃጢአት ፡ በበደል ፡ ምክንያት ፡ በአን
ደበታቸው ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ በመናገራቸው ፡
እነዚያ ፡ በሚሠሩት ፡ በክፉ ፡ ሥራቸው ፡ በእር
ሱና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተ
ማማለበትን ፡ ሥርዓት ፡ ስለ ፡ ተወ ።
፲፯ ፤ ሕጉን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዙንም ፡ ሁሉ ፡
ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ ሥርዓቱንም ፡ ሕጉንም ፡ ሁሉ ፡
ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ÷ የተማማለበትን ፡ ሥርዓት ፡
ስላፈረሱ ፡ አባቶቻቸውን ፡ ይሰድባሉ ። ሁሉም ፡
ክፉ ፡ ሥራን ፡ እስከ ፡ መሥራት ፡ ድረስ ፡ ደር
ሰው ፡ ኃጢአት ፡ ከመሥራት ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡
ወደ ፡ ግራም ፡ ማለት ፡ የላቸውም ። የሰው ፡
ሁሉ ፡ አፍ ፡ በደልን ፡ ይናገራል ። ሥራቸውም ፡
ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያጸይፍ ፡ ነው ። ሥራቸው ፡
ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ÷ የረከሰም ፡ ነው ÷ ጥፋ
ትም ፡ ነው ።
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እነሆ ÷ ምድር ፡ ፲፰ ፤
ትጠፋለች ። ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ክህደት ፡ ነውና ፡
የወይን ፡ ዘር ፡ የላቸውም ÷ ዘይትም ፡ የላቸ
ውም ÷ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋሉ ።
እንስሳትና ፡ አራዊት ÷ በባሕር ፡ ያሉ ፡ ዓሣዎ ፲፱ ፤
ችና ፡ ወፎችም ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ አስቀድመው ፡
ይጠፋሉ ። እነዚህ ፡ ከእነዚህ ፡ ጋር ፡ ይጣላሉ ።
ሕፃናቱ ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ጋር ÷ ሽማግሌዎች ፡
ከሕፃናቱ ፡ ጋር ÷ ድሀ ፡ ከባለጸጋ ፡ ጋር ÷ ታናሹ ፡
ከታላቁ ፡ ጋር ÷ ጦም ፡ አዳሪው ፡ ከዳኛው ፡
ጋር ÷ ሕጉ ፡ መሐላው ፡ ስለ ፡ ፈረሰ ፡ ይጣላሉ ።
መሐላውንና ፡ ሥርዓቱን ÷ በዓሉን ÷ የወር ፳ ፤
ኁን ፡ መባቻ ÷ ሱባዔውን ÷ ኢዮቤልዩን ÷ ፍር
ዱን ፡ ሁሉ ፡ ዘንግተዋልና ፡ ሕጉ ፡ ስለ ፡ ፈረሰ ፡
ይጣላሉ ። ክፉ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ሥራቸው ፡ ይመ
ልሱአቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሰልፍ ፡ ሰይፍ ፡ ይዘው ፡
ይነሣሉ ። ሕግን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡
ብዙ ፡ ደም ፡ እስኪፈስ ፡ ድረስ ፡ አይመለሱም ።
እነዚህ ፡ በእነዚህ ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ። በእውነ
ተኛ ፡ ሥራ ፡ ያልጸኑ ፡ ሰዎችም ፡ ከክፋታቸው ፡
አይመለሱም ።
አንዱም ፡ አንዱም ፡ የባልንጀራውን ፡ ገንዘብ ፡ ፳፩ ፤
ሁሉ ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመ
ቀማት ፡ ይነሣሉና ፡ በታላቅ ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ጸንቶ ፡ በመኖር ፡ አይደለም ፤ በእ
ውነትም ፡ አይደለም ። በማይገባ ፡ በሠሩት ፡
በሚያጠፋ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ከከበሩ ፡ የከበረ ፡
ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ያረክሳሉ ።
በዚያችም ፡ ትውልድ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ከእግ ፳፪ ፤
ዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡ ጽኑ ፡ መቅሠፍት ፡ ይደረ
ጋል ። ለቅጣትና ፡ ለሰይፍ ÷ ለመቀማትና ፡ ለመ
ማረክ ÷ ለጥፋትም ፡ ይሰጣቸዋል ፤ በእነርሱ ፡
ላይ ፡ ይቅርታና ፡ ቸርነት ፡ የሌላቸው ፡ የአሕ
ዛብ ፡ ወገኖች ፡ ያስነሣባቸዋል ።
ለማንም ፡ ፊት ፡ አያደሉም ። ከሰው ፡ ልጅ ፡ ፳፫ ፤
ሁሉ ፡ ይከፋ ፡ ዘንድ ÷ በእስራኤልም ፡ ክርክ
ርን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ በያዕቆብም ፡ በደልን ፡
ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ ብዙ ፡ ደምም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ያፈስሱ ፡ ዘንድ ÷ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ይከፋ ፡
ዘንድ ÷ ክፉዎች ፡ ኃይለኞች ፡ ናቸውና ፡ ለሽ
ማግሌም ፡ ቢሆን ፡ ለሕፃንም ፡ ቢሆን ፡ ለማ
ንም ፡ ለማን ፡ ፊት ፡ አያደሉም ። የሚሰበስብ ፡
የለም ፤ የሚቀብርም ፡ የለም ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ ጮኸው ፡ ይጣራሉ ፤ ከኃጢ ፳፬ ፤
አተኞች ፡ ከአሕዛብ ፡ እጅ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ ይጸ
ልያሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚያድን ፡ የለም ። የሕፃ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ናቱም ፡ ራስ ፡ በሽበት ፡ ይነጣል ። የሦስቱ ፡
ሱባኤ ፡ ዘመን ፡ ልጅ ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡
ሆነው ፡ ሽማግሌ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ቁመታቸ
ውም ፡ በመከራ ፡ በጭንቀት ፡ ይገጉብጣል ።
፳፭ በእነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ልጆች ፡ ሕጉን ፡ ይመረ
ምሩ ፡ ዘንድ ፡ ይጀምራሉ ። ሥርዓቱን ፡ ለመፈ
ለግ ÷ ወደ ፡ እውነት ፡ ሥራም ፡ ለመመለስ ፡
ይፈልጋሉ ። ዘመኖችም ፡ ፈጽመው ፡ ይበዙ ፡
ጀመር ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ ከልጅ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡
ይበዛ ፡ ጀመር ። ዘመናቸው ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡
ወደ ፡ መሆን ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ከቀንም ፡
ከቀን ፡ ይበዛ ፡ ጀመር ።
፳፮ ከብዙ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ዘመኖች ፡ ይደርሱ ፡
ዘንድ ፡ ሽማግሌ ፡ የለም ። ሁሉም ፡ የወር ÷
የሁለት ፡ ወር ÷ የዓመት ÷ የሁለት ፡ ዓመት ፡
ልጆች ፡ ይሆናሉና ፡ ዘመንን ፡ የሚጠግብ ፡ የለም ።
ሁሉም ፡ ዘመናቸውን ፡ በፍቅር ÷ በተድላና ፡
በደስታ ፡ ይፈጽማሉ ። በሕይወትም ፡ ይኖራሉ ።
፳፯ ባላጋራ ፡ የለም ፤ ዘመኖቻቸው ፡ ሁሉ ፡ የሕይ
ወትና ፡ የበረከት ፡ ዘመኖች ፡ ይሆናሉና ፡ የሚ
ያጠፉ ፡ ክፉ ፡ ጠላትም ፡ የለም ።
፳፰ ያንጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሪያዎቹን ፡ እስ
ራኤልን ፡ ያድናል ÷ በረድኤትም ፡ ይነሣሉ ÷
በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ብዙ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያያሉ ÷
ጠላቶቻቸውንም ፡ አስወጥተው ፡ ይሰዳሉ ።
ደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ ያመሰ
ግናሉ ። እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ። በጠላቶቻቸው ፡ የተደረገ ፡
መቻያን ፡ ሁሉ ፡ ስድባቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ያያሉ ።
ወገናቸው ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤
ልቡናቸው ፡ ደስታን ፡ ያበዛል ።
፳፱ ፍርድን ፡ የሚፈርድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለ ፡
ያውቃሉ ፡ ለሚወዱት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለጥ
ቂት ፡ ዘመን ÷ ለብዙም ፡ ዘመን ፡ ይቅርታን ፡
ያደርጋሉ ።
፴ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈ ፡ ነውና ፤ ሙሴ ! አን
ተም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ጻፍ ፤ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የዘላ
ለም ፡ ሥርዓት ፡ ሊሆን ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ይጽ
ፋሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩ አብርሃም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ እግ
ዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ይስሐቅን ፡ አከበረው ።
ከኬብሮንም ፡ ተነሥቶ ፡ ሄዶ ÷ በዚህ ፡ ኢዮቤ
ልዩ ፡ በሚቈጠር ፡ በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአ
ንድ ፡ ዓመት ፡ ራእይ ፡ በየበት ፡ ጕድጓድ ፡ አጠ
ገብ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።
፪ በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ ከተደረገው ፡ ከቀደመው ፡
ራብ ፡ ሌላ ፡ በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ራብ ፡ ሆነ ። ያዕ
ቆብ ፡ የምስር ፡ ንፍሮ ፡ ቀቀለ ፡ ዔሳውም ፡ ከም
ድረ ፡ በዳ ፡ ርበት ፡ መጣ ።
፫ ወንድሙ ፡ ያዕቆብን ፡— ከዚህ ፡ ከዳበው ፡ ሹሮና ፡
ከምስር ፡ ንፍሮው ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።
፬ ከመወለድ ፡ የሚቀድም ፡ ብኵርናህን ፡ መልስ
ልኝ ፤ እኔም ፡ ዳቦውን ፡ ከዚህም ፡ ንፍሮ ፡ እሰ
ጥሃለሁ ፡ አለው ።
፭ ዔሳውም ፡ በልቡ ፡— እኔ ፡ በራብ ፡ እሞታለሁ ፤
በመወለድ ፡ የቀደመ ፡ ይህ ፡ ብኵርና ፡ ምን ፡
ያደርግልኛል ? አለ ፤ ለያዕቆብ ፡— ብኵርና
ውን ፡ ሰጠሁህ ፡ አለው ።
፮ ያዕቆብም ፡— አሁን ፡ ማልልኝ ፡ አለው ። ማለ
ለት ። ያዕቆብም ፡ ለወንድሙ ፡ ለዔሳው ፡ ዳቦ
ውንና ፡ ንፍሮውን ፡ ሰጠው ፤ እስኪጠግብ ፡
ድረስ ፡ በላ ፤ ዔሳውም ፡ ቀድሞ ፡ መወለድን ፡
ናቀ ።
፯ ስለዚህም ፡ መጀመሪያ ፡ ለመወለዱ ፡ ያዕቆብ ፡
ዳቦውንና ፡ ንፍሮውን ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ የዔሳው ፡
ስሙ ፡ ኤዶም ፡ ተባለ ። ፈታዊ ፡ ማለት ፡ ነው ።
፰ ያዕቆብ ፡ ከበረ ፤ ዔሳው ፡ ግን ፡ ከጌትነቱ ፡ ተዋ
ረደ ።
፱ በሀገር ፡ ራብ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ይስሐቅ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይወ
ርድ ፡ ዘንድ ፡ መጣ ፤ ከፍልስጥኤሙ ፡ ንጉሥ ፡
ከአቤሜሌክ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጌራሮ ፡ ሄደ ።
፲ እግዚአብሔር ፡ ታየው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡—
ወደ ፡ ግብጽ ፡ አትውረድ ÷ እኔ ፡ በልሁህ ፡ አገር ፡
ኑር ፤ ወደዚያች ፡ አገር ፡ ሂድ ፤ እኔም ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ በረድኤት ፡ እኖራለሁ ፤ ለልጆችህና ፡ ለአ
ንተ ፡ ይህችን ፡ አገር ፡ እሰጥሃለሁና ፡ አከብርሃ
ለሁ ፤ ለአባትህ ፡ ለአብርሃም ፡ የማልሁለትን ፡
መሐላ ፡ አጸናለሁ ÷ ልጆችህንም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡
ኮከብ ፡ አበዛልሃለሁ ፤ ይህችን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡
ለልጆችህ ፡ እሰጣለሁ ።
፲፩ አባትህ ፡ የእኔን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሰማ ፡ ትእዛዜንና ፡
ቃሌን ፡ ሥርዓቴንና ፡ ሕጌን ፡ መሐላዬንም ፡
ጠበቀ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡
ይከብራሉ ።
፲፪ አሁንም ፡ ቃሌንና ፡ ትእዛዜን ፡ ስማ ፤ በዚህ
ችም ፡ አገር ፡ ኑር ፡ አለው ። ሦስት ፡ የሱባዔ ፡
ዘመን ፡ በጌራሮ ፡ ኖረ ። አቤሜሌክም ፡ ስለ ፡
እርሱና ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ አዘዘ ፡— እርሱን ፡
የነካ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቡንም ፡ የነካ ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡
ይሙት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።
፲፫ ይስሐቅ ፡ በፍልስጥኤም ፡ ከበረ ÷ ብዙ ፡ ገንዘ
ብም ፡ በዛለት ፤ በጎችና ፡ ላሞች ፡ አህዮችና ፡
ግመሎችም ፡ በዙለት ። ብዙ ፡ ገንዘብም ፡ በዛ
ለት ። በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ ዘር ፡ ዘራ ።
፲፬ መቶ ፡ ዳውላ ፡ እህልም ፡ አገባ ። ይስሐቅ ፡ ፈጽሞ ፡
ከበረ ፡ ገነነ ። የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ቀኑበት ።
አብርሃም ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ የአብርሃም ፡ አሽከ
ሮች ፡ የቈፈሩትን ፡ ጕድጓድ ÷ አብርሃም ፡ ከሞተ ፡
በኋላ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ሞል
ተው ፡ ደፍነውት ፡ ነበር ።
፲፭ አቤሜሌክም ፡ ይስሐቅን ፡— ከእኛ ፡ ፈጽመህ ፡
ከብረሃልና ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ሂድ ፡ አለው ።
፲፮ ይስሐቅም ፡ በሰባተኛው ፡ ሱባኤ ፡ በአንደኛው ፡
ዓመት ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጌራሮን ፡ ቈላ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሄደ ።
፲፯፤ የአባቱ ፡ የአብርሃም ፡ አሽከሮች ፡ የቈፈሩአቸ
ውን ÷ አባቱ ፡ አብርሃም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የፍ
ልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ደፍነዋቸው ፡ የነበሩትን ፡
የውኃ ፡ ምንጮች ፡ ተመልሰው ፡ ቈፈሩ ። ስማቸ
ውንም ፡ አባቱ ፡ አብርሃም ፡ በወጣላቸው ፡ ስም ፡
ጠራቸው ። የይስሐቅም ፡ አሽከሮች ፡ በፋጋ ፡
ጕድጓዳቸውን ፡ ቈፈሩ ÷ በዚያም ፡ የጠራ ፡
ውኃን ፡ አገኙ ።
፲፰፤ የጌራሮን ፡ ዘላኖች ፡ ከይስሐቅ ፡ ዘላኖች ፡ ጋር ፡—
ይህ ፡ ውኃ ፡ የእኛ ፡ ውኃ ፡ ነው ፡ እየተባባሉ ፡
ተጣሉ ። ይስሐቅም ፡— ከእኛ ፡ ጋር ፡ ተጣልተ
ዋልና ፡ ሲል ፡ የዚያን ፡ ጕድጓድ ፡ ስም ፡ ዕፀብ ፡
አለው ። ሌላም ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፈሩ ፡ በእርሱም ፡
ተጣሉ ፤ ስሙን ፡ ጠብ ፡ የተደረገበት ፡ አለው ።
፲፱፤ ከዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ሄደው ፡ ሌላ ፡ ጕድጓድ ፡
ቈፈሩ ÷ በእርሱ ፡ ግን ፡ አልተጣሉም ፤ ስሙን ፡
ሰፊ ፡ አለው ።
፳፤ ይስሐቅም ፡— ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ አገር ፡
አሰፋልኝ ፡ በምድርም ፡ከበርን ፡ አለ ። ከዚ
ያም ፡ ተነሥቶ ፡ በአርባ ፡ አራተኛው ፡ ኢዮቤ
ልዩ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡
ዓመት ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ወጣ ።
፳፩፤ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡
እግዚአብሔር ፡ ተነጋገረው ። የአባትህ ፡ የአብ
ርሃም ፡ ፈጣሪ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡
በረድኤት ፡ አለሁና ፡ አትፍራ ÷ አከብርሃለሁ ፤
ልጅህንም ፡ ስለ ፡ ወዳጄ ፡ ስለ ፡ አብርሃም ፡ እንደ ፡
ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ፈጽሜ ፡ አበዛዋለሁ ፡ አለው ።
፳፪፤ አባቱ ፡ አብርሃም ፡ ቀድሞ ፡ መሠዊያ ፡ በሠራ
በት ፡ በዚያ ፡ቦታ ፡ መሠዊያ ፡ ሠርቶ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ስም ፡ ጠራ ። ለአባቱ ፡ ለአብርሃም ፡
ፈጣሪ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ፡ ጕድጓድንም ፡ ቈፈረ ፡
ጥሩ ፡ ውኃንም ፡ አገኘ ።
፳፫፤ የይስሐቅም ፡ አሽከሮች ፡ ሌላ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፈሩ ፡
ውኃ ፡ ግን ፡ አላገኙም ። ሄደውም ፡ ውኃ ፡ እን
ዳላገኙ ፡ ለይስሐቅ ፡ ነገሩት ።
፳፬፤ ይስሐቅም ፡— በዚህች ፡ ቀን ፡ ለፍልስጥኤም ፡
ሰዎች ፡ ማልሁ ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ ለእኛ ፡ ሆነ ፡
አለ ። ለአቤሜሌክ ፡ ለጠባቂው ፡ ለፋኮልና ፡
ለሁለተኛው ፡ ለአኮዘት ፡ በዚያ ፡ ምሎአልና ፡
የዚያን ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ የመሐላ ፡ ጕድጓድ ፡ ብሎ ፡
ስሙን ፡ ጠራው ።
፳፭፤ ይስሐቅም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ፍቅርን ፡ ለማድ
ረግ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ በግፍ ፡ እንደ ፡ ማለላቸው ፡
አወቀ ፤ ይስሐቅም ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ የፍልስጥ
ኤምን ፡ ሰዎች ፡ ረገማቸው ። መቅሠፍትና ፡
ቍጣ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀንም ፡ የፍልስጥኤም ፡
ሰው ፡ ርጉም ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ከአሕዛብ ፡
ሁሉ ፡ መካከል ፡ ለይቶ ፡ ለመርገምና ፡ ለሽሙጥ ፡
ለቍጣና ፡ ለመቅሠፍት ፡ ይሰጣቸው ÷ ያጠፋ
ቸውም ፡ ዘንድ ፡ በኃጢአተኞች ፡ አሕዛብና ፡
በኪጢኤም ፡ እጅ ፡ ይጣላቸው ።
፳፮፤ ከጠላትና ፡ ከኪጢኤም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጡትን ፡
በዘመናቸው ፡ ለልጆቹ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የለት ፡
ጠላት ፡ የቆየ ፡ ጠላት ፡ ይሆንባቸዋልና ፡ ደጋግ ፡
የሆኑ ፡ ወገኖች ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከዚህ ፡
ዓለም ፡ በፍርድ ፡ ያጥፉአቸው ።
የፍልስጥኤም ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ከምድር ፡ ተነቃ ፳፯፤
ቅሎ ፡ ለመጥፋትና ፡ ለመራቅ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነውና ፡
የልጅ ፡ ልጅ ፡ አይቀርላቸውም ። የቍጣ ፡ ፍርድ ፡
በሚደረግበትም ፡ ቀን ፡ የሚድን ፡ የለም ።
ሳይገረዝ ፡ ለቀረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንግዲህ ፡ ፳፰፤
ምንም ፡ ስምና ፡ ልጅ ፡ የለውም ፡ በምድርም ፡
ዘር ፡ የለውም ፤ እስከ ፡ ሰማይም ፡ ቢወጣ ፡ ከዚያ ፡
ይወርዳልና ፤ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ቢጸና ፡ ከዚያ ፡
ይጠፋልና ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ቢሰወር ፡
ከዚያ ፡ ይጠፋልና ፤
ወደ ፡ ሲኦልም ፡ ቢወርድ ፡ ከዚያ ፡ ቅጣቱ ፡ ይበ ፳፱፤
ዛልና ፤ ከዚያ ፡ ምንም ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ የለው
ምና ።
ሰውነቱን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈልጉአት ፡ ሰዎች ፡ ፴፤
እጅ ፡ ተማርኮም ፡ ቢሄድ ፡ በጎዳና ፡ መካከል ፡
ይገድሉታልና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚቀርለት ፡
ስምና ፡ ልጅ ፡ የለም ። ወደ ፡ ዘላለም ፡ መርገም ፡
ይሄዳልና ።
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ፍርድ ፡ በሚደ ፴፩፤
ረግበት ፡ ቀን ፡ ለማድረግ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ በሰማይ ፡
ጽላት ፡ እንደዚህ ፡ ተጽፎአል ፡ ታውቆአል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ÷ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ ውስጥ ፡ ፩፤
በሚቈጠርበት ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ርብቃ ፡
ልጅዋ ፡ ያዕቆብን ፡ ጠርታ ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ ከከ
ነዓን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሁለት ፡ ሚስቶችን ፡
እንዳገባ ፡ እንደ ፡ ወንድምህ ፡ እንደ ፡ ዔሳው ፡
ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡ አታግባ ፡ ብላ ፡ ነገ
ረችው ። ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ዝሙት ፡ መዳራት ፡
ነውና ፡ በሚያስጸይፍ ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ሰው
ነቴን ፡ አሳዘናት ፤ ሥራቸው ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ በእ
ነርሱ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ እውነት ፡ የለም ።
ልጄ ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ እጅግ ፡ እወድሃለሁ ። ልቡና ፪፤
ዬም ፡ ይወድሃል ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡
የሚጠብቅህ ፡ ቸርነቴና ፡ ማኅፀኔ ፡ ሁልጊዜ ፡
ይመርቅሃል ።
አሁንም ÷ ልጄ ፡ ሆይ ÷ ቃሌን ፡ ስማ ÷ የእኔን ፡ ፫፤
የእናትህንም ፡ ፈቃድ ፡ አድርግ ። ከአባትህ ፡
ወገን ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡
አታግባ ። የምታገባትን ፡ ከአባቴ ፡ ወገን ፡ አግባ ፡
አለችው ። ልዑል ፡ አምላክም ፡ ያከብርሃል ፤ ልጆ
ችህም ፡ የእውነት ፡ ልጆች ፡ ይሆናሉ ፡ የልጅ ፡
ልጅህም ፡ የከበረ ፡ ይሆናል ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያዕቆብ ፡ ከእናቱ ፡ ከርብቃ ፡ ጋር ፡ ፬፤
ተነጋገረ ፡— እናቴ ÷ እነሆ ÷ እኔ ፡ የዘጠኝ ፡
ሱባዔ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፤ ምንምን ፡ ሴት ፡
አላውቅም ፡ የሴት ፡ እጅ ፡ ጨብጬ ፡ አላፈር
ሁም ። ከአባታችን ፡ ከአብርሃም ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡
አስባለሁና ፡ ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡

ሚስት ፡ አገባ ፡ ዘንድ ፡ አላስብም ። ከአባቴ ፡
ወገን ፡ ልጆች ፡ ከዘመዶቼም ፡ ሚስት ፡ አገባለ
ሁና ፡ ከከነዓን ፡ ወገን ፡ ልጆች ፡ ምንም ፡ ምን ፡
ሚስት ፡ እንዳላገባ ፡ አዘዘኝ ።
፭፤ ለወንድምሽ ፡ ለላባ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ተወለዱ
ለት ፡ ሰማሁ ። ከእነርሱም ፡ ሚስት ፡ አገባ ፡ ዘንድ ፡
ልቡናዬን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አሳረፍኩ ።
፮፤ እንዳልበድል ፡ በሥራዬም ፡ ሁሉ ፡ በሕይወት ፡
የምኖርበትን ፡ ዘመን ፡ እንዳላጠፋ ፡ ስለዚህ ፡
ነገር ፡ በሰውነቴ ፡ ተጠበቅሁ ፤ ስለ ፡ መዳራትና ፡
ስለ ፡ ዝሙት ፡ አባቴ ፡ አብርሃም ፡ አብዝቶ ፡ አዝ
ዞኛልና ፤ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ይህንን ፡ አዝ
ዞኛልና ፡ ተጠበቅሁ ። ወንድሜ ፡ የሁለቱን ፡
ሚስቶቹን ፡ እኅት ፡ አንዲቱን ፡ ሴት ፡ አግባ ፡
እያለ ፡ ሲከራከረኝና ፡ ሲናገረኝ ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡
ዓመቱ ፡ ነው ።
፯፤ እኔም ፡ ወንድሜ ፡ እንዳደረገው ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡
አልወድም ፤ ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ ከከነዓን ፡
ልጆች ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ሚስት ፡ እንዳላገባ ፡ ወን
ድሜ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ እኔም ፡ ክፉ ፡
ሥራ ፡ እንዳልሠራ ፡ በፊትሽ ፡ እምላለሁ ።
እናቴ ÷ አትፍሪ ፤ ፈቃድሽን ፡ እንዳደርግ ፡ በቀ
ናም ፡ ሥራ ፡ ጸንቼ ፡ እንድኖር ፡ ሥራዬንም ፡
ለዘላለም ፡ እንዳላጠፋ ፡ እመኚ ፡ አላት ።
፰፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንገትዋን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቀ
ናች ፡ እጆችዋንም ፡ ዘረጋች ፤ አፍዋን ፡ ከፍታ ፡
ምድርና ፡ ሰማይን ፡ የፈጠረ ፡ ልዑል ፡ አም
ላክን ፡ አመሰገነችው ፡ ፍጹም ፡ ምስጋናንም ፡
አቀረበችለት ።
፱፤ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ የሰ
ጠኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመ
ስገን ፡ ስሙም ፡ ለዘላለም ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።
የአንተ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚ
ኖር ፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡
ድረስ ፡ ልጁ ፡ ለአንተ ፡ የሚገዛ ፡ ይሁን ።
፲፤ አቤቱ ÷ ባርከው ። አመሰግንህም ፡ ዘንድ ፡ በአ
ንደበቴ ፡ የእውነት ፡ በረከትን ፡ አኑር ። መንፈስ ፡
ቅዱስን ፡ አሳድርብኝ ፡ አለች ።
፲፩፤ ያንጊዜም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወርዶ ፡ በአንደበ
ትዋ ፡ አናገራት ÷ ሁለቱን ፡ እጆችዋንም ፡ በያ
ዕቆብ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አኖረች ። የእውነት ፡ ጌታ ፡
ዓለማትን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ የተመሰገንህ ፡
ነህ ።
፲፪፤ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ለይቶ ፡ አንተን ፡ ይባርክ ።
ልጄ ፡ ሆይ ÷ እውነተኛውን ፡ ሥራ ፡ ይስጥህ ፤
ለልጅህም ፡ እውነት ፡ ነገርን ፡ ይግለጥለት ፤ በሕ
ይወት ፡ ሳለህ ፡ ልጆችህን ፡ ያብዛልህ ፡ በዓመቱ ፡
ወር ፡ ቍጥር ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ይሁኑ ። ልጆቻ
ቸውም ፡ ይብዙ ፡ ከሰማይም ፡ ከዋክብት ፡ ይልቅ ፡
ይብዙ ÷ ቍጥራቸውም ፡ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡
ይብዛ ። ለአብርሃም ፡ ይሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ከእር
ሱም ፡ በኋላ ፡ ባለ ፡ ዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቹ ፡
ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ያችን ፡
የተወደደች ፡ አገር ፡ ይስጣቸው ።

ለዘላለም ፡ እጅ ፡ አድርገው ፡ ይዘዋት ፡ ይኑሩ ። ፲፫፤
ልጄ ፡ ሆይ ÷ በሕይወት ፡ ሳለሁ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡
ተወልዶልህ ፡ ልይ ÷ ልጅህ ፡ ሁሉ ፡ የተባረከ ÷
የከበረ ፡ ልጅ ፡ ይሁን ፤ በሕይወትዋ ፡ ሳለች ፡
የእናትህን ፡ ልቡና ፡ እንዳሳረፍህ ፤ የእናትህ ፡
ማኅፀን ፡ እንዲህ ፡ ትመርቅህ ÷ ማኅፀኔ ፡ ጡቱ ፡
አንተን ፡ ይመርቁ ፤ አንደበቴና ፡ አፌም ፡ ፈጽ
መው ፡ አንተን ፡ ያመስግኑ ÷ ፈጽመህ ፡ ብዛ ÷
በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ምላ ።
ልጅህም ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ ስፋት ፡ በዓ
ለሙ ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ይሁን ፡ ልጅህንም ፡ ደስ ፡
ይበለው ።
ብዙ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ፲፬፤
ተድላ ፡ ደስታ ፡ ይደረግለት ። ስምህና ፡ ልጅህ ፡
እስከ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ÷
ልዑል ፡ አምላክም ፡ አምላካቸው ፡ ይሁን ÷
የእውነት ፡ አምላክም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ በረድ
ኤት ፡ ይኑር ። ማደሪያው ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡
በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በእነርሱ ፡ ይሠራ ። የሚመ
ርቅህ ፡ የተመረቀ ፡ ይሁን ፡ በሐሰት ፡ የምትረግ
ምህ ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ የተረገመች ፡ ትሁን ፡
አለች ።
የእናትህ ፡ ልቡና ፡ እንደሚወድህ ፤ ማኅፀንዋም ፡ ፲፭፤
በአንተ ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ እንዲመርቅህ ፡
የዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ አንተን ፡ ይውደድህ ፡
ብላ ፡ ሳመችው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከመመረቅ ፡
ዝም ፡ አለች ።
በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈጠርበት ፡ በሰባተኛው ፡ ፲፮፤
ዓመት ፡ ይስሐቅ ፡ ታላቁን ፡ ልጁን ፡ ዔሳውን ፡
ጠርቶ ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ አረጀሁ ፤ እነሆ ÷
ዓይኖቼም ፡ ለማየት ፡ ፈዝዘዋል ፡ የምሞትብ
ትን ፡ ቀን ፡ አላውቅም ።
አሁንም ፡ የምታድንበትን ፡ ጦርህን ፡ ጐራጕሬ ፲፯፤
ህን ፡ ቀስትህን ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውጣ ።
ልጄ ፡ ሆይ ÷ አደን ፡ አድነህ ፡ አምጣልኝ ÷ ሰው
ነቴ ፡ የምትወደው ፡ መብልን ፡ አዘጋጅተህ ፡
እበላ ፡ ዘንድ ፡ አምጣልኝ ፤ ሳልሞት ፡ ሰውነ
ቴም ፡ ትመርቅህ ፡ አለው ። ርብቃ ፡ ግን ፡ ይስ
ሐቅ ፡ ለዔሳው ፡ ሲነግረው ፡ ነገሩን ፡ ትሰማ ፡
ነበር ።
ዔሳው ፡ አጥምዶ ፡ ይዞ ፡ ለአባቱ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ፲፰፤
ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ገሥግሦ ፡ ሄደ ።
ርብቃ ፡ ልጅዋን ፡ ያዕቆብን ፡ ጠርታ ፡— አባትህ ፡ ፲፱፤
ይስሐቅ ፡— አደን ፡ አድነህ ፡ አምጥተህ ፡ የምበላ
ውን ፡ አዘጋጅልኝ ፡ በልቼ ፡ ሳልሞት ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ ልመርቅህ ፡ ብሎ ፡ ከወንድምህ ፡
ከዔሳው ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ ሰማሁት ።
አሁንም ÷ ልጄ ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ የማዝዝህን ፡ ነገር ፡ ፳፤
ስማ ፤ ወደ ፡ መንጋህ ፡ ሄደህ ፡ ያማሩ ፡ ሁለት
የፍየል ፡ ጠቦቶችን ፡ አምጣልኝ ፤ እንደሚወ
ደው ፡ አድርጌ ፡ ለአባትህ ፡ ምግብ ፡ ላድርጋቸው ፤
ሳይሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይመርቅህ ፡
ዘንድ ÷ ለአባትህም ፡ አቅርበህለት ፡ ይብላ ÷
የተመረቅህ ፡ ትሆናለህ ፡ አለችው ።

፳፩ ያዕቆብም ፡ እናቱ ፡ ርብቃን ፡— አባቴ ፡ ስለሚበ
ላው ፡ ደስ ፡ ስለሚያሰኘው ፡ ሁሉ ፡ አልሽል
ግም ። ነገር ፡ ግን ፡ እናቴ ፡ ቃሉን ፡ ልብ ፡ እንዳ
ያደርገው ፡ እፈራለሁ ። ይዳስሰኝም ፡ ዘንድ ፡
ይወድ ፡ ይሆናል ። እኔ ፡ ጠጕር ፡ እንደ ፡ ሌለኝ ፡
ወንድሚ ፡ ዔሳው ፡ ጠጓር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንቺ ፡
ታውቂያለሽ ÷ በፊቱ ፡ የምንቀውና ፡ ያላዘዘ
ኝን ፡ የምሠራ ፡ ይመስለዋል ÷ ይቆጣኛል ፤ ምር
ቃት ፡ ያይደለ ፡ እርግማን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አመጣ
ለሁ ፡ አላት ።
፳፪ እናቱ ፡ ርብቃም ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ ነገሬን ፡ ስማ ፡
እንጂ ፡ መርገምህ ፡ በእኔ ፡ ይሁን ፡ አለችው ÷
ያዕቆብም ፡ የእናቱን ፡ የርብቃን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡
ሄዶ ፡ ያማሩና ፡ የሰቡ ፡ ሁለት ፡ የፍየል ፡ ጠቦቶ
ችን ፡ አመጣ ÷ ወደ ፡ እናቱም ፡ አቀረባቸው ÷
እናቱም ፡ ይስሐቅ ፡ እንደሚወደው ፡ አድርጋ ፡
አዘጋጀቻቸው ።
፳፫ ርብቃም ፡ የሚወደድ ፡ ከእርስዋ ፡ ዘንድ ፡ በቤ
ትዋ ፡ ያለ ፡ የታላቁን ፡ ልጅዋን ፡ የዔሳውን ፡
ልብስ ፡ አምጥታ ፡ ለታናሹ ፡ ልጅዋ ፡ ለያዕቆብ ፡
አለበሰችው ÷ የፍየሉን ፡ ጠቦት ፡ ቁርበቶች
ንም ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ አኖረች ፡ በአንገቱና ፡ በሰ
ውነቱ ፡ ላይ ፡ አለበሰችው ። ያዘጋጀቻቸውን ፡
ዳቦውንና ፡ ንፍሮውን ፡ ለልጅዋ ፡ ለያዕቆብ ፡
ሰጠችው ።
፳፬ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይስሐቅ ፡ ገብቶ ፡—
እኔ ፡ ልጅህ ፡ እንዳልኸኝ ፡ አደረግሁልህ ፤ ተነ
ሥተህ ፡ ተቀመጥ ፤ አባቴ ፡ ሆይ ÷ ሰውነትህ ፡
ትመርቀኝ ፡ ዘንድ ፡ አጥምጄ ፡ ካመጣሁልህ ፡
ብላ ፡ አለው ።
፳፭ ይስሐቅም ፡ ልጁን ፡— ልጄ ÷ እንዲህ ፡ ፈጥነህ ፡
ያመጣህበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ?
አለው ። ያዕቆብም ፡— ፈጣሪህ ፡ በፊቴ ፡ ያስገ
ኘልኝን ፡ አመጣሁ ፡ አለው ።
፳፮ ይስሐቅም ፡— አንተ ፡ ልጄ ፡ ዔሳው ፡ እንደ ፡
ሆንህ ፡ እንዳይደለህም ፡ ቅረበኝ ፡ ልዳስህ ፡
አለው ።
፳፯ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይስሐቅ ፡ ቀረበ ÷
ዳሰሰውም ። ቃልህስ ፡ የያዕቆብን ፡ ቃል ፡ ይመ
ስላል ፡ እጆችህ ፡ ግን ፡ የዔሳውን ፡ እጆች ፡
ይመስላሉ ፡ አለ ።
፳፰ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡ ልቡናው ፡ ወደ ፡
ያዕቆብ ፡ የሚመለስበት ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ አላወ
ቀውም ።
፳፱ ይመርቀው ፡ ዘንድ ፡ እጆቹ ፡ እንደ ፡ ዔሳው ፡
እጆች ፡ ጠጕራም ፡ ናቸውና ፡ ይስሐቅም ፡ አላ
ወቀም ።
፴ አንተ ፡ ልጄ ፡ ዔሳው ፡ ነህን ? አለው ፤ አዎ ፡ እኔ ፡
ልጅህ ፡ ዔሳው ፡ ነኝ ፡ አለው ። ሰውነቴ ፡ ትመር
ቅህ ፡ ዘንድ ፡ ልጄ ፡ አድነህ ፡ ካመጣኸው ፡ አቅ
ርብልኝ ፡ ልብላ ፡ አለው ።
፴፩ መብልን ፡ አቀረበለት ፤ በላ ። ወይንንም ፡ አቀ
ረበለት ÷ ጠጣ ።
፴፪ አባቱ ፡ ይስሐቅም ፡— ልጄ ÷ ቀርበህ ፡ ሳመኝ ፡
አለው ።
ቀርቦ ፡ ሳመው ። ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የልብሱን ፡ ፴፫
መዓዛ ፡ አሸተተ ። መረቀውም ። እነሆ ÷ የልጄ ፡
የልብሱ ፡ መዓዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳከበረው ፡
እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መዓዛ ፡ ነው ። እግዚአብ
ሔር ፡ ይስጥህ ፡ ከሰማይ ፡ በወረደ ፡ ጠል ፡ ከም
ድር ፡ በወጣ ፡ መስኖ ፡ ያብዛህ ፡ ስንዴውን ፡
ዘይቱን ፡ ያብዛልህ ።
አሕዛብ ፡ ይገዙልህ ፤ ሕዝቡም ፡ ይስገዱልህ ፡ ፴፬
ለወንድምህ ፡ ጌታ ፡ ሁነው ፡ የእናትህም ፡ ልጆች ፡
ይስገዱልህ ። እግዚአብሔር ፡ እኔን ፡ ያከበረበ
ቸው ፡ አባቴ ፡ አብርሃምንም ፡ ያከበረባቸው ፡
በረከቶች ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ ይሁኑህ ፤ እስከ ፡
ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ለልጆችህም ፡ ይሁኑ ። የሚረ
ግምህ ፡ የተረገመ ፡ ነው ። የሚመርቅህም ፡
የተመረቀ ፡ ነው ፡ አለው ።
ይስሐቅ ፡ ልጁን ፡ ያዕቆብን ፡ መርቆት ፡ ከጨ ፴፭
ረሰ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ።
ከወጣም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ። ያዕቆብ ፡ ከአ ፴፮
ባቱ ፡ ከይስሐቅ ፡ ዘንድ ፡ መጥቶ ፡ ተሸሸገ ።
ወንድሙ ፡ ዔሳው ፡ ግን ፡ ከአደኑ ፡ ደረሰ ፤ እር
ሱም ፡ መብልን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለአባቱ ፡ አቀረበ ፤
አባቱንም ፡— አባቴ ፡ ሆይ ÷ ሰውነትህ ፡ ትመ
ርቀኝ ፡ ዘንድ ፡ አደን ፡ አድኜ ፡ ካመጣሁልህ ፡
ተነሥ ፡ ብላ ፡ አለው ።
አባቱ ፡ ይስሐቅም ፡— አንተ ፡ ማን ፡ ነህ ? ፴፯
አለው ። እኔ ፡ የበኵር ፡ ልጅህ ፡ ዔሳው ፡ ነኝ ፤
እንዳዘዝኸኝ ፡ አደረግሁ ፡ አለው ።
ይስሐቅም ፡ እጅግ ፡ ፈጽሞ ፡ ተደነቀ ፡— አደን ፡ ፴፰
አድኖ ፡ አምጥቶልኝ ፡ አንተ ፡ ሳትመጣ ፡ ከሁሉ ፡
በልቼ ፡ የመረቅሁት ፡ ይህ ፡ ማን ፡ ነው ? የተመረቀ ፡
ይሁን ፡ ዘሩም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ የተመ
ረቀ ፡ ይሁን ፡ አለው ።
ዔሳው ፡ የአባቱን ፡ የይስሐቅን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ፴፱
ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ። በታላቅ ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡
ምር ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፤ አባቱን ፡— አባቴ ፡ ሆይ ÷
እኔንም ፡ መርቀኝ ፡ አለው ።
ወንድምህ ፡ በተንኰል ፡ መጥቶ ፡ በረከትህን ፡ ፵
ወሰደብህ ፡ አለው ።
ያዕቆብ ፡ ተብሎ ፡ በተጠራበት ፡ ስሙ ፡ እንዳ ፵፩
ሰነካከለኝ ፡ ዛሬ ፡ አወቅሁ ። እነሆ ÷ ይህ ፡ ሁለ
ተኛው ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ ብኵርናዬን ፡ ወሰደ
ብኝ ፤ ዛሬም ፡ በረከቴን ፡ ወሰደብኝ ፡ አለ ፤ አባቴ ÷
ምርቃትን ፡ አላስቀረህልኝምን ? አለ ።
ይስሐቅም ፡ ዔሳውን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፵፪
ለት ፡— እነሆ ÷ ለአንተ ፡ ጌታ ፡ አድርጌ ፡ ሾም
ሁት ፡ ወንድሞቹንም ፡ ሁሉ ፡ ተገዥ ፡ ይሆኑት ፡
ዘንድ ፡ ሰጠሁት ። ወይኑንና ፡ ስንዴውን ፡ ዘይ
ቱን ፡ በማብዛት ፡ አከበርሁት ። ልጄ ፡ ሆይ ÷
ዛሬ ፡ ለአንተ ፡ ምን ፡ ላድርግልህ ? አለው ።
ዔሳውም ፡ አባቱ ፡ ይስሐቅን ፡— አባቴ ÷ የአ ፵፫
ንተ ፡ ምርቃት ፡ አንዲት ፡ ብቻ ፡ ናትን ? አባቴ ፡
ሆይ ÷ እኔንም ፡ መርቀኝ ፡ አለው ። ዔሳውም ፡
ቃሉን ፡ አሰምቶ ፡ አለቀሰ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፴፬ ይስሐቅም ፡ መለሰለት ፡— እነሆ ፥ ኑሮህ ፡ ከም
ድር ፡ በተገኘ ፡ መስኖ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ካለ ፡
ከሰማይ ፡ በወረደ ፡ ጠል ፡ ይሁን ፤ ገድለህ ፡ ሰል
በህ ፡ ኑር ፤ ለወንድምህ ፡ ተገዛ ።
፴፭ አልገዛም ፡ ብትል ፡ ለእርሱም ፡ መገዛትን ፡ ከሰ
ውነትህ ፡ ብታርቃት ፡ ያንጊዜ ፡ ለሞት ፡ የሚያ
በቃ ፡ በደልን ፡ ሁሉ ፡ ትበድላለህ ። ልጆች
ህም ፡ ሁሉ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከምድር ፡
ተነቃቅለው ፡ ይጠፋሉ ። ዔሳውም ፡ አባቱ ፡
ስለ ፡ መረቀው ፡ ምርቃት ፡ ያዕቆብን ፡ ይጣላው ፡
ነበር ።
፴፮ በልቡም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— አባቴ ፡ ሞቶ ፡ የሚ
ለቀስበት ፡ ቀን ፡ አሁን ፡ ይደርሳል ፤ ወንድሜን ፡
ያዕቆብን ፡ አሁን ፡ እገድለዋለሁ ፡ አለ ። የታ
ላቁን ፡ ልጅዋን ፡ የዔሳውን ፡ ነገር ፡ ለርብቃ ፡
በሕልም ፡ መልአክ ፡ ነገራት ።
፴፯ ርብቃም ፡ ልካ ፡ ታናሹን ፡ ልጅዋን ፡ ያዕቆብን ፡
ጠራችው ፤ እነሆ ፥ ወንድምህ ፡ ዔሳው ፡ ይገድ
ልህ ፡ ዘንድ ፡ ተቀይሞሃል ፡ አሁንም ፥ ልጄ ፡
ሆይ ፥ ቃሌን ፡ ስማ ፤ ተነሥተህ ፡ ከወንድሜ ፡
ከላባ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ካራን ፡ ሽሽ ፤ የወንድምህ ፡
ቍጣ ፡ እስኪበርድ ፡ ድረስ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ ። ከአንተ ፡ ቍጣውን ፡
ይተዋል ፤ ያደረግኸውንም ፡ ይረሳዋል ፤ እኔም ፡
ልኬ ፡ ከዚያ ፡ እቀበልሃለሁ ፡ አለችው ።
፴፰ ያዕቆብም ፡— አልፈራም ፤ ይገድለኝ ፡ ዘንድ ፡
ቢወድ ፡ እገድለዋለሁ ፡ አለ ።
፴፱ ሁለታችሁንም ፡ ሁሉ ፡ ልጆቼን ፡ በአንዲት ፡
ቀን ፡ አጥቼ ፡ የወላድ ፡ መካን ፡ እንዳልሆን ፡
ሂድ ፡ አለችው ።
፵ ያዕቆብም ፡ እናቱን ፡ ርብቃን ፡ እንዲህ ፡ አላት ፡—
አባቴ ፡ እንዳረጀ ፡ እነሆ ፡ አንቺ ፡ ታውቂያለሽ ፤
ዓይኖቹ ፡ ፈዝዘዋልና ፡ አያይም ።
፵፩ ትቼው ፡ ከእናንተ ፡ ተለይቼ ፡ ስለ ፡ ሄድሁ ፡
አባቴ ፡ ተቈጥቶ ፡ ይረግመኛል ፡ አልሄድም ፥
ቢያሰናብተኝ ፡ ግን ፡ ያንጊዜ ፡ እሄዳለሁ ፡ አላት ።
፵፪ ርብቃም ፡ ያዕቆብን ፡— እኔ ፡ ገብቼ ፡ እነግረዋ
ለሁ ፡ ያሰናብትሃል ፡ አለችው ።
፵፫ ርብቃም ፡ ወደ ፡ ይስሐቅ ፡ ገብታ ፡ ይስሐቅን ፡
እንዲህ ፡ አለችው ፡— ዔሳው ፡ ለእርሱ ፡ ሚስት ፡
አድርጎ ፡ ከገባቸው ፡ ከሁለቱ ፡ ከኬጢ ፡ ልጆች ፡
የተነሣ ፡ ኑሮዬን ፡ ጠላሁ ፡ እንደነዚህ ፡ ለእርሱ ፡
ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ያዕቆብ ፡ ሚስት ፡ ካገባ ፡ የከ
ነዓን ፡ ልጆች ፡ ክፉዎች ፡ ናቸውና ፡ እንደ ፡
ምን ፡ እኖራለሁ ?
፵፬ ይስሐቅም ፡ ልጁን ፡ ያዕቆብን ፡ ጠርቶ ፡ መረ
ቀው ፡ መከረውም ፡— ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
ሚስት ፡ አታግባ ፤ ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ መስጴጦ
ምያ ፡ ወደ ፡ እናትህ ፡ አባት ፡ ወደ ፡ ባቱኤል ፡
ቤት ፡ ሂድ ፡ አለው ።
፵፭ ከዚያ ፡ ከእናትህ ፡ ወንድም ፡ ከላባ ፡ ልጆች ፡
ሚስት ፡ አግባ ። ሰማይን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡
ያከብርህ ። ፈጽሞ ፡ ያብዛህ ። የአሕዛብ ፡ ጌታ ፡
ሁን ። የአባቴን ፡ የአብርሃምን ፡ በረከት ፡ ለአ
ንተ ፡ ይስጥህ ። ተሰደህ ፡ ትኖርበት ፡ የነበረች ፡
አገርን ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለአ
ብርሃም ፡ የሰጣትንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ትወርሳት ፡
ዘንድ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችህ ፡ ይስጣ
ቸው ። ልጄ ፡ ሆይ ፥ በፍቅር ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፥
ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ አሰናበተው ። ከያዕቆብ ፡ ፵፮
እናት ፡ ከርብቃ ፡ ወንድም ፡ ከሶርያው ፡ ሰው ፡
ከባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ከላባ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡
ሄደ ።
ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ለመሄድ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ፵፯
እንዲህ ፡ ሆነ ። ልጅዋ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ የርብቃ ፡
ልብዋ ፡ አዝኖ ፡ ታለቅስ ፡ ነበር ።
ይስሐቅም ፡ ርብቃን ፡— እኅቴ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ፵፰
ልጄ ፡ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ አታልቅሺ ። በደኅና ፡ ሄዶ ፡
በደኅና ፡ ይመለሳልና ፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ከክፉ ፡
ሁሉ ፡ ይጠብቀዋልና ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ በረድ
ኤት ፡ ይኖራልና ፤ ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ አይለ
የውምና ፤ ወደ ፡ እኛ ፡ በደኅና ፡ እስኪመለስ ፡
ድረስ ፡ በሄደበት ፡ ጐዳናው ፡ እንዲቀናለት ፡
አውቃለሁና ፡ እኅቴ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ እርሱ ፡ አት
ፍሪ ።
በደኅና ፡ መጥቶ ፡ እናየዋለን ። እኅቴ ፡ ሆይ ፥ ፵፱
ስለ ፡ እርሱ ፡ አትፍሪ ። እርሱ ፡ በሥራው ፡ የቀና ፡
ነውና ፤ ፍጹም ፡ ነውና ፤ የታመነ ፡ ሰው ፡ ነውና ፤
በመከራ ፡ አይወድቅምና ፡ አታልቅሺ ፡ አላት ።
ስለ ፡ ልጅዋ ፡ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ ይስሐቅ ፡ ርብቃን ፡
ያረጋጋት ፡ ነበር ። እርሱንም ፡ መረቀው ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

ያዕቆብ ፡ በአርባ ፡ አራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ፩
በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
ወደ ፡ ካራን ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ከቤርሳቤህ ፡ ወጣ ።
በተራራ ፡ ወዳለች ፡ ወደ ፡ ሎዛም ፡ ደረሰ ። ይህ
ችውም ፡ ቤቴል ፡ ናት ።
በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ፪
ወደሚያድርበት ፡ በታ ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ።
በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ከመንገዱ ፡ ወደ ፡ ጋራ ፡
አልፍ ፡ አለ ። ፀሐይ ፡ ገብቶአልና ፡ በዚያ ፡ ተኛ ።
ከዚያ ፡ በታ ፡ ድንጋዮች ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ አም
ጥቶ ፡ በዚያ ፡ እንጨት ፡ ሥር ፡ አኖረው ። እር
ሱም ፡ ብቻውን ፡ ይሄድ ፡ ነበር ።
በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ ሕልምን ፡ አየ ። ፫
እነሆ ፥ መሰላል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተተክላ ፡
ጫፍዋ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሶ ፥ እነሆ ፥ የእግ
ዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ሲወጡባት ፡ ሲወርዱ
ባት ፥ እነሆ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በውስጥዋ ፡
ተቀምጦ ፡ አየ ።
ከያዕቆብም ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ። የአባትህ ፡ የአብ ፬
ርሃም ፡ ፈጣሪ ፡ የይስሐቅም ፡ ፈጣሪ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
ይህችን ፡ አንተ ፡ የተኛህባትን ፡ ምድር ፡ ለአ
ንተ ፡ እሰጣታለሁ ፥ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለዘርህ ፡
እሰጣታለሁ ። ዘርህ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይሆ
ናል ። በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ በደቡብና ፡
በሰሜን ፡ ትበዛለህ ። የአሕዛብ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡

በአንተ ፡ ይባረኩሉ ፥ በዘርህም ፡ ይባረኩሉ ፡፡
፭ እነሆ ፥ እኔም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁ ፥ ሁል
ጊዜም ፡ እጠብቅሃለሁ ፡፡ ያልሁህን ፡ ሁሉ ፡ እስክ
ደርግልህ ፡ ድረስ ፡ በረድኤት ፡ አልለይህምና ፡
ከሄድህበት ፡ ወደዚች ፡ አገር ፡ በደኅና ፡ እመል
ስሃለሁ ፡ አለው ፡፡
፮ ይህን ፡ ሲነግረው ፡ ያዕቆብ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፡፡
ይህ ፡ ቦታ ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደ
ሪያ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አላወቅሁም ፡ ነበር ፡ አለ ፡፡
፯ ይህ ፡ ቦታ ፡ ግሩም ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ማደ
ሪያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ተርታ ፡ ቦታ ፡
አይደለም ፡ ብሎ ፡ ፈራ ፡፡ ይህችም ፡ የሰማይ ፡
ደጃፍ ፡ ናት ፡ አለ ፡፡
፰ ያዕቆብም ፡ ሲነጋ ፡ ገሥግሦ ፡ ሄዶ ፥ በራስጌው ፡
ትራስ ፡ አድርጎ ፡ ያኖረውን ፡ ድንጋይ ፡ አመጣ ፥
ለምልክትም ፡ አቆመው ፥ በራሱም ፡ ላይ ፡ ዘይ
ትን ፡ አፈሰሰበት ፡፡
፱ የዚያንም ፡ ቦታ ፡ ስሙን ፡ ቤቴል ፡ አለው ፡፡ የእ
ግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ቀድሞ ፡
ግን ፡ የአገሩ ፡ ስሙ ፡ ሎዛ ፡ ነበረ ፡፡
፲ ያዕቆብም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ ተሳለ ፤
እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡ ቢኖር ፥
እኔ ፡ በምሄድበትም ፡ በዚህች ፡ ጐዳና ፡ ቢጠብ
ቀኝ ፥ እበላ ፡ ዘንድ ፡ እንጀራን ፡ ቢሰጠኝ ፥ እለ
ብስም ፡ ዘንድ ፡ ልብስ ፡ ቢሰጠኝ ፡ ወደ ፡ አባቴም ፡
ቤት ፡ በደኅና ፡ ብመልስ ፥ እግዚአብሔር ፡ አም
ላኬ ፡ ይሆነኛል ፤ አምልከዋለሁ ፡፡
፲፩ ይህም ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ለምልክት ፡ ሐውልት ፡
አድርጌ ፡ ያቆምሁት ፡ ድንጋይ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ማደሪያ ፡ ይሆናል ፥ ከዚህም ፡ ከሰጠኸኝ ፡
ሁሉ ፡ እኔ ፡ ለአንተ ፡ ለአምላኬ ፡ አሥራት ፡ እሰ
ጣለሁ ፡ አለ ፡፡
፲፪ ከርብቃ ፡ ወንድም ፡ ከላባ ፡ ዘንድ ፡ በምሥራቅ ፡
በኩል ፡ ወዳለች ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ተንሥቶ ፡ ሄደ ፡፡
፲፫ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ኖረ ፤ ስለ ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ራሔል ፡
አንድ ፡ ሱባዔ ፡ ተገዛለት ፤ በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡
በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡— ለአ
ንተ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ የተገዛሁላትን ፡ ሚስቴን ፡
ስጠኝ ፡ አለው ፡፡
፲፬ ላባም ፡ ያዕቆብን ፡— እኔ ፡ ሚስትህን ፡ እሰጥሃ
ለሁ ፡ አለው ፡፡ ላባ ፡ ሠርግ ፡ አደረገ ፥ ታላቂቱን ፡
ልጁን ፡ ልያን ፡ ወስዶ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሚስት ፡ ልት
ሆነው ፡ ሰጠው ፥ የምታገለግል ፡ ባሪያ ፡ ዘለፋ
ንም ፡ ሰጣት ፡፡
፲፭ ራሔልን ፡ መስላዋለችና ፡ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ አላ
ወቀም ፡ ነበር ፡፡ ደረሰባት ፡ እርስዋስ ፡ እነሆ ፡
ልያ ፡ ናት ፡፡
፲፮ ያዕቆብም ፡ በላባ ፡ ተቈጣ ፡፡ የተገዛሁልህ ፡ ስለ ፡
ልያ ፡ ያይደለ ፤ ስለ ፡ ራሔል ፡ አይደለምን ?
ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረግኸኝ ? ለምን ፡ በደል
ኸኝ ? ልጅህን ፡ ውሰድ ፤ በእኔ ፡ ክፉ ፡ አድርገ
ሃልና ፡ እኔ ፡ እሄዳለሁ ፡ አለው ፡፡
፲፯ የልያ ፡ ዓይንዋ ፡ ልም ፡ ነበረና ፡ ያዕቆብ ፡ ከልያ ፡
ይልቅ ፡ ራሔልን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡
መልክዋ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበረ ፡፡ ራሔል ፡
ግን ፡ ዓይኗ ፡ መልካም ፡ ነበረች ፤ መልክዋም ፡
የማረ ፡ እጅግ ፡ ደመ ፡ ግቡ ፡ ነበረች ፡፡
፲፰ ላባም ፡ ያዕቆብን ፡— እንዲህ ፡ አይደለም ፤ በሀ
ገራችን ፡ ታላቂቱ ፡ ሳለች ፡ ታናሽቱን ፡ መስጠት ፡
የለም ፡፡ ይህንንም ፡ ማድረግ ፡ አገቡብ ፡ አይደ
ለም ፡፡ ታላቂቱ ፡ ሳለች ፡ ታናሽቱን ፡ ልጁን ፡
የሚሰጥ ፡ እንደሌለ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ እንዲህ ፡
ታውቆአል ፡ ተጽፎአልና ፡ ታላቂቱን ፡ ልጅ ፡
አስቀድሞ ፡ ይሰጣል ፡፡
፲፱ ከእርስዋም ፡ በኋላ ፡ ታናሽቱን ፡ ልጁን ፡ ይሰጣ
ልና ፡ እንዲህ ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡
በደልን ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ይጽፉበታል ፡፡
፳ ይህ ፡ ሥራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡
ነውና ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ የሚጸ
ድቅ ፡ አይደለም ፡፡
፳፩ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዝ ፡፡ እጅግ ፡
ክፉ ፡ ነውና ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ እንዳያደርጉ ፤ አስ
ቀድመው ፡ ታላቂቱን ፡ ሳይሰጡ ፡ ታናሽቱን ፡
አስቀድመው ፡ እንዳይሰጡ ፡ እዘዝ ፡፡
፳፪ ላባም ፡ ያዕቆብን ፡— የዚህች ፡ የሠርግዋ ፡ በዓል ፡
የሚደረግበት ፡ ሰባቱ ፡ ቀን ፡ ይለፍ ፡፡ ዳግመ
ኛም ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ትገዛልኝ ፡ ዘንድ ፥ በመ
ጀመሪያው ፡ ሱባዔ ፡ እንዳደረግህ ፡ በጎቼን ፡ ትጠ
ብቅልኝ ፡ ዘንድ ፡ ራሔልን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ፡፡
፳፫ የልያ ፡ ሠርግ ፡ በዓል ፡ የተደረገበት ፡ ሰባቱ ፡
ቀን ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡
ይገዛለት ፡ ዘንድ ፡ ላባ ፡ ለያዕቆብ ፡ ራሔልን ፡
ሰጠው ፡፡ ለራሔልም ፡ የዘለፋን ፡ እኅት ፡ ባላን ፡
አገልጋይ ፡ ልትሆናት ፡ ሰጣት ፡፡ ልያ ፡ በብላሽ ፡
ተሰጥታለችና ፡ ስለ ፡ ራሔል ፡ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡
ዓመት ፡ ተገዛ ፡፡
፳፬ እግዚአብሔር ፡ የልያን ፡ ማኅፀን ፡ ከፈተ ፤ ፀነ
ሰች ፥ ለያዕቆብ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፡ ስሙ
ንም ፡ ሮቤል ፡ አለው ፡፡
፳፭ በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
ዘጠኝኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ አራተኛው ፡
ቀን ፡ ስሙን ፡ ሮቤል ፡ አለው ፡፡ እግዚአብሔር ፡
ልያ ፡ እንድትጠላ ፡ አይቶአልና ፡ የራሔል ፡ ማኅ
ፀን ፡ ተዘጋ ፡፡ ራሔል ፡ ግን ፡ ትወድ ፡ ነበር ፡፡
፳፮ ያዕቆብ ፡ በልያ ፡ ዳግመኛ ፡ ደረሰባት ፤ ፀነሰች ፡
ሁለተኛ ፡ ልጅንም ፡ ወለደችለት ፤ ስሙንም ፡
አሥረኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በሀያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
ስምዖን ፡ አለው ፡፡
፳፯ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ያዕቆብ ፡
ዳግመኛ ፡ በልያ ፡ ደረሰባት ፤ ፀነሰች ፤ ሦስተኛ ፡
ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ በመጀመሪያው ፡
ወር ፡ መባቻ ፡ ስሙን ፡ ሌዊ ፡ አለው ፡፡
፳፰ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ ያዕ
ቆብ ፡ ዳግመኛ ፡ በልያ ፡ ደረሰባት ፤ ፀነሰች ፤ አራ
ተኛ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ በአራተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ ሦስተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአ
ሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ በመጀመሪያው ፡
ዓመት ፡ ስሙን ፡ ይሁዳ ፡ አለው ፡፡

፲፱፡ እርስዋ ፡ አትወልድም ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡
ራሔል ፡ በልያ ፡ ትቀና ፡ ነበር ። ያዕቆብን ፡—
ልጅ ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ።
፳፡ ያዕቆብም ፡ — የማኅፀንሽን ፡ ፍሬ ፡ የከለከል
ሁሽ ፡ እኔ ፡ ነኝን ? መውለድን ፡ እኔ ፡ አስተው
ሁሽን ? አላት ።
፳፩፡ ራሔልም ፡ ልያ ፡ ለያዕቆብ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡
ስምዖንና ፡ ሮቤልን ፡ ይሁዳንና ፡ ሌዊን ፡ እንደ ፡
ወለደች ፡ በየች ፡ ጊዜ ፡— በባሪያዬ ፡ በባላን ፡
ድረስበት ፤ ፀንሳ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ትወልድል
ኛለች ፡ አለችው ።
፳፪፡ ደረሰበት ፤ ፀንሳ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ።
በሦስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡
ስድስተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በዘጠኝኛው ፡ ቀን ፡
ስሙን ፡ ዳን ፡ አለው ።
፳፫፡ ያዕቆብ ፡ ዳግመኛ ፡ በባላን ፡ ደረሰበት ፤ ፀንሳ ፡
ዳግመኛ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች
ለት ። በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡
ዓመት ፡ ሰባተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአምስተ
ኛው ፡ ቀን ፡ ራሔል ፡ ስሙን ፡ ንፍታሌም ፡ አለ
ችው ።
፳፬፡ ልያም ፡ እንደ ፡ መከነች ÷ ልጅ ፡ እንዳልወለ
ደች ፡ በየች ፡ ጊዜ ፡ እርስዋም ፡ በራሔል ፡ ቀንታ ፡
አገልጋይዋ ፡ ዘለፋን ፡ ለያዕቆብ ፡ ሚስት ፡ ትሆ
ነው ፡ ዘንድ ፡ ሰጠችው ። እርስዋም ፡ ፀንሳ ፡
ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ። በሦስተኛው ፡
ዓመት ፡ ስምንተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡
ሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ስሙን ፡ ጋድ ፡ አለችው ።
፳፭፡ ዳግመኛም ፡ ደረሰበት ፤ ፀንሳ ፡ ሁለተኛ ፡ ወንድ ፡
ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአ
ምስተኛው ፡ ዓመት ፡ አሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡
በባተ ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ልያ ፡ ስሙን ፡ አሴር ፡
አለችው ።
፳፮፡ ያዕቆብም ፡ በልያ ፡ ደረሰበት ፤ ፀንሳ ፡ ለያዕቆብ ፡
ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ በአራተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ አምስተኛው ፡
ወር ፡ በባተ ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ ስሙን ፡ ይሳ
ኮር ፡ አለችው ÷ ለሞግዚትም ፡ ሰጠችው ።
፳፯፡ ያዕቆብ ፡ ዳግመኛ ፡ ደረሰበት ፤ ፀንሳ ፡ ሴትና ፡
ወንድ ፡ ሁለት ፡ ልጆችን ፡ ወለደችለት ። በአርባ ፡
አራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡
በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ የወ
ንዱን ፡ ስም ፡ ዛብሎን ፡ አለችው ፤ የሴቲቱን ፡
ስም ፡ ዲና ፡ አለቻት ።
፳፰፡ እግዚአብሔርም ፡ ራሔልን ፡ ይቅር ፡ አላት ÷
ማኅፀንዋም ፡ ተከፈተ ÷ ፀንሳ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡
ወለደች ፤ በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡
ዓመት ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ስሙን ፡
ዮሴፍ ፡ አለችው ።
፳፱፡ ዮሴፍም ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ያዕቆብ ፡ ላባን ፡—
ልጆቼንና ፡ ሚስቶቼን ፡ ስጠኝ ÷ ወደ ፡ አባቴ ፡
ወደ ፡ ይስሐቅ ፡ ልሂድ ÷ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ልጆ
ችህ ፡ ፋንታ ፡ ለአንተ ፡ የተገዛሁላቸውን ፡ ዘመ
ኖች ፡ ፈጽሜአለሁና ፡ ቤት ፡ እሠራለሁ ÷ ወደ ፡
አባቴም ፡ ቤት ፡ እሄዳለሁ ፡ አለው ።
ላባም ፡ ያዕቆብን ፡— በደመወዝ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ፴፡
ተቀመጥ ፤ ዳግመኛ ፡ መንጋዎቼን ፡ ጠብቅልኝ ፤
ደመወዝህን ፡ ውሰድ ፡ አለው ።
አመድማ ÷ ዝንጉርጉር ÷ ነጭ ፡ ሆኖ ፡ የተወለ ፴፩፡
ደው ፡ ደመወዝ ፡ ሊሆነው ፡ ከፍየሉ ፡ ጠቦትና ፡
ከበጉ ፡ ጠቦት ፡ በጉን ፡ ሁሉ ፡ ደመወዝ ፡ ይሰ
ጠው ፡ ዘንድ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተዋዋሉ ።
በጎቹም ፡ ሁሉ ፡ ምልክት ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ አመ ፴፪፡
ድማውን ፡ ዝንጉርጉሩን ፡ ይወልዱ ፡ ጀመር ።
ዳግመኛም ፡ በጎቹ ፡ በእነዚያ ፡ አምሳል ፡ ይወ
ልዱ ፡ ጀመር ። ምልክት ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ለያ
ዕቆብ ፤ ምልክት ፡ የሌለው ፡ ለላባ ፡ ሆነ ።
የያዕቆብ ፡ ገንዘቡ ፡ እጅግ ፡ በዛ ፤ ላሙንና ፡ ፴፫፡
በጉን ፡ አህያውንና ፡ ግመሉን ፡ ገዛ ። ወንድ ፡
ልጅንና ፡ ሴት ፡ ልጅን ፡ ወለደ ።
ላባ ፡ ልጆቹም ፡ በያዕቆብ ፡ ቀኑበት ። በጎቹንም ፡ ፴፬፡
ከእርሱ ፡ ሰበሰበ ÷ በክፉ ፡ አስተያየትም ፡ ይመ
ለከተው ፡ ጀመር ።
ራሔል ፡ ዮሴፍን ፡ ከወለደች ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ፴፭፡
ሆነ ፤ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጎዳና ፡ ያህል ፡ ከእርሱ ፡
ርቀው ፡ ነበሩና ፡ ላባ ፡ በጎቹን ፡ ይሸልት ፡ ዘንድ ፡
ሄደ ።
ያዕቆብም ፡ ላባ ፡ በጎቹን ፡ ይሸልት ፡ ዘንድ ፡ እን ፴፮፡
ዲሄድ ፡ አይቶ ፡ ራሔልንና ፡ ልያን ፡ ጠርቶ ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡
ከልባቸው ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ። በሕ
ልም ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፤ ወደ ፡ አባቱ ፡ ቤት ፡ ይመ
ለስ ፡ ዘንድ ፡ የነገረውንም ፡ ሁሉ ፡ ነግሮአቸዋ
ልና ።
ወደምትሄድበት ፡ በታ ፡ ሁሉ ፡ እኛም ፡ ከአንተ ፡ ፴፯፡
ጋር ፡ እንሄዳለን ፡ አሉት ።
ያዕቆብም ፡ የአባቱን ፡ የይስሐቅን ፡ አምላክ ፡ ፴፰፡
የአባቱን ፡ የአብርሃምን ፡ አምላክ ፡ አመሰገነው ።
ተነሥቶ ፡ ልጆቹንና ፡ ሚስቶቹን ፡ በበቅሎ ፡ ፴፱፡
አስቀመጠ ። ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ያዘ ። ወንዙን ፡
ተሻግሮ ፡ ገለዓድ ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ ደረሰ ።
ያዕቆብም ፡ ለላባ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ መሄዱን ፡ ሰወ ፵፡
ረው ÷ አልነገረውም ። በአራተኛው ፡ ሱባዔ ፡
በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡
በሀያ ፡ አንደኛው ፡ ቀን ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ገለ
ዓድ ፡ ተመለሰ ። ላባም ፡ በኋላው ፡ ተከተለው ።
በሦስተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ ሦስተ ፵፩፡
ኛው ፡ ቀን ፡ ያዕቆብን ፡ በገለዓድ ፡ ተራራ ፡ አገ
ኘው ። በሕልም ፡ ሌሊት ፡ ተናግሮታልና ፡ ላባ ፡
በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ አላሰናበተውም ።
ላባም ፡ ለያዕቆብ ፡ ነገረው ። በዚያም ፡ ወር ፡ ፵፪፡
በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ ያዕቆብ ፡ ለላባ ፡
ፍሪዳ ፡ አረደ ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ለመጡ ፡ ሰዎ
ችም ፡ ሁሉ ፡ አረደ ።
አንዱ ፡ አንዱን ፡ በተንኰል ፡ እንዳይፈልገው ፡ ፵፫፡
በዚያች ፡ ሌሊት ፡ በገለዓድ ፡ ተራራ ፡ ያዕቆብ ፡
ለላባ ፡ ማለለት ÷ ላባም ፡ ለያዕቆብ ፡ ማለለት ።

ምስክር ፡ ሊሆን ፡ በዚያ ፡ ክረብታን ፡ ሠራ ÷
ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የዚያ ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ምስክር ፡
የተደረገበት ፡ ክረብታ ፡ ተባለ ፤
፲፬ ቀድሞ ፡ ግን ፡ ገለዓድ ፡ የኃይለኞች ፡ አገር ፡
ይሉአት ፡ ነበር ፤ ገለዓድን ፡ የኃይለኞች ፡ አገር ፡
ነበረችና ። ቁመታቸው ፡ አሥር ፡ ክንድ ፡ ዘጠኝ ፡
ክንድ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ የሚሆኑ ፡ አርበኞች ፡
ልጆች ፡ ተወለዱ ። መኖሪያቸውም ፡ ከአሞን ፡
ልጆች ፡ አገር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኤርሞን ፡ ተራራ ፡
ድረስ ፡ ነው ።
፲፭ የመንግሥታቸውም ፡ ከተማ ፡ አስጣሮስና ፡ ቆራ
ናኤም ÷ ሚሱርና ፡ አድራኦ ÷ ቢዮር ፡ ናቸው ።
እነርሱ ፡ እጅግ ፡ ክፉዎች ፡ ናቸውና ፡ ከክፉ ፡
ሥራቸው ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ አጠፋ
ቸው ።
፲፮ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ፋንታ ፡ ክፉ ፡ ኃጢአተኛ ፡ የሚሆን ፡
አሞሬዎን ፡ በሀገራቸው ፡ ኖረ ። ዛሬ ፡ የእነር
ሱን ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡ የለም ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዘመን ፡ ብዛትም ፡ የላቸውም ።
፲፯ ያዕቆብም ፡ ላባን ፡ አሰናብቶ ፡ ሰደደው ፤ በም
ሥራቅ ፡ ወዳለች ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሄደ ። ያዕቆ
ብም ፡ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ተመለሰ ። በዘጠኝኛው ፡
ወር ÷ ከወሩም ፡ በአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ቀን ፡
ያቦክን ፡ ተሻገረ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ወንድሙ ፡
ዔሳው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ደረሰ ፡ ተወቃቀሱ ።
፲፰ ከእርሱ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ሰዒር ፡ ሄደ ። ያዕቆብ ፡
ግን ፡ በድንኳን ፡ አደረ ። በዚህ ፡ ኢዮቤልዩ ፡
በአምስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
ዮርዳኖስን ፡ ተሻግሮ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ አደረ ።
፲፱ በክረብታው ፡ አጠገብ ፡ ካለ ፡ ባሕር ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ዶታአምና ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ስን ፡ ድረስ ÷
እስከ ፡ አም ፡ አቅራቢትም ፡ ድረስ ፡ በጎቹን ፡
ይጠብቅ ፡ ነበር ። ለአባቱ ፡ ለይስሐቅም ፡ ከገን
ዘቡ ፡ ልብሱንም ፡ ምግቡንም ፡ ሥጋውንም ፡
መጠጡንም ፡ ወተቱንም ፡ ቅቤውንም ፡ ዳቦው
ንም ÷ በቈላም ፡ ካለው ፡ ከተምሩም ፡ ሁሉ ፡
ይሰድ ፡ ነበር ።
፳ ለእናቱ ፡ ለርብቃም ፡ በአሥራ ፡ ሁለቱም ፡ ወር ፡
ጊዜዎች ፡ መካከል ፡ በአዝመራና ፡ በዘር ፡ መካ
ከል ÷ በበልግና ፡ በመከር ÷ በበጋና ፡ በክረምት ፡
መካከል ፡ በዓመት ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አብር
ሃም ፡ ድንኳን ፡ ይሰድላት ፡ ነበር ።
፳፩ ይስሐቅ ፡ ከቤርሳቤህ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡
ወደ ፡ አብርሃም ፡ ድንኳን ፡ ወጥቶ ፡ ነበርና ፤
ከልጁ ፡ ከዔሳው ፡ ተለይቶ ፡ በዚያ ፡ ኖረ ።
፳፪ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ዔሳው ፡
ማእሊትን ፡ ሚስት ፡ አድርጎ ፡ አገባ ። ይህች
ውም ፡ የእስማኤል ፡ ልጅ ፡ ናት ። የአባቱን ፡
መንጋዎች ፡ ሁሉ ፡ ሚስቶቹንም ፡ ሰበሰበ ።
፳፫ ወጥቶም ፡ በሴይር ፡ ተራራ ፡ ኖረ ። አባቱን ፡
ይስሐቅንም ፡ በመሐላ ፡ ጕድጓድ ፡ ብቻውን ፡
ተወው ።
፳፬ ይስሐቅም ፡ ከመሐላ ፡ ጕድጓድ ፡ ወጥቶ ፡ በኬ
ብሮን ፡ ተራራ ፡ ባለ ፡ በአባቱ ፡ በአብርሃም ፡
ግምብ ፡ ኖረ ።
ከዚያም ፡ ያዕቆብ ፡ ለእናቱና ፡ ለአባቱ ፡ ሁሉን ፡ ፳፭
ይሰድ ፡ ነበር ። ከጊዜው ፡ በየጊዜው ፡ የፈለጉ
ትን ፡ ሁሉ ፡ ይልክ ፡ ነበር ።
ያዕቆብንም ፡ በፍጹም ፡ ሰውነታቸውና ፡ በፍ ፳፮
ጹም ፡ ልቡናቸው ፡ ይመርቁት ፡ ነበር ፤ በስድ
ስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡
የሰቂማ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ሳሌም ፡
በአራተኛው ፡ ወር ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ወጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

በዚያም ፡ የያዕቆብን ፡ ልጅ ፡ ዲናን ፡ ወደ ፡ ፩
አገሩ ፡ ገዥ ፡ ወደ ፡ ኤዋዊን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡
ኤሞር ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ቤት ፡ ነጥቀው ፡
ወሰዱአት ። ደረሰባት ፡ አጐሰቈላትም ። እር
ስዋም ፡ የአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡
ነበረች ። ሚስት ፡ ሆና ፡ ትሰጠው ፡ ዘንድ ፡
ከአባትዋ ፡ ለመነ ÷ ከወንድሞችዋም ፡ ለመነ ።
ያዕቆብም ፡ ተቈጣ ። እኅታቸውን ፡ ዲናን ፡ ፪
አጐስቍለዋታልና ፡ ልጆቹም ፡ በሰቂማ ፡
ሰዎች ፡ ተቈጡ ። ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ በተንኰል ፡
ተናገሩ ÷ አታለሉም ፡ በዘበዙአቸው ።
ሌዊና ፡ ስምዖን ፡ ድንገት ፡ ወደ ፡ ሰቂማ ፡ ገብ ፫
ተው ፡ በሰቂማ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መቻያን ፡ አደ
ረጉ ።
በውስጥዋም ፡ ያገኙትን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገደሉ ። ፬
አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳን ፡ በውስጥዋ ፡ አላስቀሩም ።
እኅታቸው ፡ ዲናን ፡ አጐስቍለዋልና ፡ ቈስለው ፡
ሳሉ ፡ ሁሉን ፡ ገደሉ ።
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ የእስራኤ ፭
ልን ፡ ልጅ ፡ ለማጐስቈል ፡ እንዲህ ፡ አታድርጉ ።
በእስራኤል ፡ ኃፍረትን ፡ ስላደረጉ ፡ የሰቂማን ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ያጠፉአቸው ፡ ዘንድ ፡
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ በእነርሱ ፡ ቅጣት ፡ ተጽፎአ
ልና ፡ እንዲህ ፡ አታድርጉ ።
በሰይፍ ፡ ያጠፉአቸው ፡ ዘንድ ÷ በእነርሱም ፮
ላይ ፡ ቅጣትን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ የእስራኤል ፡
ወገን ፡ የምትሆን ፡ ድንግልን ፡ ማጐስቈል ፡ በእ
ስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዲህ ፡
እንዳይደረግ ፡ እግዚአብሔር ፡ በያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
እጅ ፡ ጣላቸው ።
በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልጁንም ፡ ቢሆን ÷ እኅቱ ፯
ንም ፡ ቢሆን ፡ ከአሕዛብ ፡ ልጆች ፡ ለተወለደ ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡
ቢኖር ÷ ሞትን ፡ ይሙት ። ኃጢአትን ፡ ሠርቶ
አልና ÷ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ኃፍረትን ፡
አድርጎአልና ፡ በድንጋይ ፡ ወግረው ፡ ይግደ
ሉት ።
ሴቲቱንም ፡ የአባትዋን ፡ ወገን ፡ ስም ፡ አስነቅ ፰
ፋለችና ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉአት ፤ ከእስራኤል ፡
ተለይታ ፡ ትጥፋ ። እስራኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የተለየ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ባለ ፡
ትውልድ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡
ሴሰኛ ፡ ኃጢአተኛ ፡ አይገኝ ።

፱፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡
ይሙት ፡ በድንጋይም ፡ ይውገሩት ። ስለ ፡ እስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ እን
ዲህ ፡ ተሠርቶአል ፡ ተጽፎአልና ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጅ ፡ የሚያጐሰቍል ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡
ይሙት ፥ በድንጋይም ፡ ይውገሩት ።
፲፡ ለዚህም ፡ ሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ዘመን ፡ የለውም ፡
የሚተውበትም ፡ የለም ። ልጁን ፡ ለጣዖት ፡ ሰጥ
ቶአልና ፥ ራሱን ፡ ለማሳደፍ ፡ እግዚአብሔር
ንም ፡ በድሎአልና ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡
ልጁን ፡ ያጐሰቈለ ፡ ሰው ፡ ይጠፋል ፡ እንጂ ፡
ይቅር ፡ የሚባልበት ፡ የለም ።
፲፩፡ ሙሴ ፥ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘ
ዛቸው ። ከልጆቻቸው ፡ ለአሕዛብ ፡ እንዳያጋቡ ፡
ከአሕዛብም ፡ ልጆች ፡ እንዳያጋቡ ፡ በእነርሱ ፡
ላይ ፡ አዳኝባቸው ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
የተናቀ ፡ ነውና ፡ እዘዛቸው ።
፲፪፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሕጉን ፡ ነገር ፡ ጻፍሁልህ ።
በዲና ፡ ላይ ፡ ያደረጉትንም ፡ የሰቂማን ፡ ሰዎች ፡
ሥራ ፡ ሁሉም ፤ የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡— ለእኛ ፡
ስድብችን ፡ ነውና ፡ እኅታችንን ፡ ላልተገረዘ ፡
ሰው ፡ አንሰጥም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፤ ጻፍ
ሁልህ ።
፲፫፡ ልጃቸውን ፡ ለአሕዛብ ፡ ልጆች ፡ ለሚሰጡ ፥
ከአሕዛብም ፡ ልጆች ፡ ሚስትን ፡ ለሚያገቡ ፡
ለእስራኤል ፡ ስድብ ፡ ነውና ፥ ርኩስ ፡ ነውና ፥
ለእስራኤልም ፡ የተናቀ ፡ ነውና ።
፲፬፡ ከአሕዛብም ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡ ያለው ፥ ከልጆ
ቹም ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ለተወለደ ፡ ሰው ፡
የሰጠ ፡ እስራኤል ፡ ከዚህ ፡ ኃጢአት ፡ አይነ
ጻም ። በመቅሠፍት ፡ ላይ ፡ መቅሠፍት ፥ በመር
ገም ፡ ላይ ፡ መርገም ፥ ቅጣትም ፡ መቅሠፍትም ፡
መርገምም ፡ ሁሉ ፡ ይመጣበታልና ፡ አይነጻም ።
፲፭፡ ይህነንም ፡ ነገር ፡ ቢያደርግ ፡ ኃጢአት ፡ ከሚ
ሠሩ ፡ ከእነዚህ ፡ ወገኖች ፡ በዓይኖቹ ፡ አይቶ ፡
ቸል ፡ ቢል ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ማደሪያ ፡
ከሚያጐሰቍሉ ፥ የከበረ ፡ ስሙንም ፡ ከሚያሳ
ድፉ ፡ ወገን ፡ አይቶ ፡ ቸል ፡ ቢል ፥ ስለዚች ፡
ኃጢአትና ፡ ስለዚች ፡ ሁሉ ፡ በደል ፡ ሕዝቡ ፡
ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ይጠፋሉ ።
፲፮፡ ፊት ፡ መመለስ ፡ የለም ። ፊት ፡ አይቶ ፡ ማድ
ላት ፡ የለም ። በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድርጎ ፡ ይቀበለው ፡
ዘንድ ፡ መሥዋዕቱንና ፡ ቍርባኑን ፥ ስቡንና ፡
የሚሰጠውን ፡ ከእጁ ፡ መቀበል ፡ የለም ።
፲፯፡ ወንድም ፡ ቢሆን ፥ ሴትም ፡ ብትሆን ፥ በእስራ
ኤል ፡ ዘንድ ፡ ሰውነቱን ፡ በኃጢአት ፡ የሚያሳ
ድፍ ፡ አይሁን ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ይህችን ፡ ምስ
ክር ፡ በእስራኤል ፡ አሰማባቸው ፡ ብዬ ፡ አዘዝ
ሁህ ።
፲፰፡ በሰቂማና ፡ በልጆችዋ ፡ የተደረገውን ፡ እይ ።
በሁለቱ ፡ በያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ለጥፋት ፡
እንደ ፡ ተሰጠች ፥ ታመው ፡ ሳሉ ፡ እንዳጠፉአ
ቸው ፥ጽድቅ ፡ ሆና ፡ እንደ ፡ ተቈጠረችላቸው ፡
እይ ።

እነርሱም ፡ በእውነተኛነት ፡ እንደ ፡ ተቈጠሩ ፡ ፲፱፡
የሌዊም ፡ ልጅ ፡ ለክህነት ፡ እንደ ፡ ተመረጠ ፥
እኛ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ እንዳገለገልን ፥ ሌዋው
ያንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያገለግሉ ፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተመረጡ ፡ እይ ። እውነት ፡ ነገ
ርን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ፍርድንም ፡ ይፈርድ ፡
ዘንድ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በጠላትነት ፡ ከሚ
ነሡ ፡ ብድራትን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ቀንቶአ
ልና ፡ ሌዊ ፡ ይክበር ፡ ልጆቹም ፡ ለዘላለም ፡ ይክ
በሩ ።
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ ሁሉን ፡ ወደ ፡ ፳፡
ፈጠረ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽድቅና ፡ በረከ
ትን ፡ እንዲህ ፡ ያቀርቡለታል ። ሰው ፡ በሕይ
ወት ፡ ሳለ ፡ የሠራውን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ እናስባለን ።
በዓመት ፡ በዓመት ፡ በሚመላለሱ ፡ ጊዜዎች ፡
ሁሉ ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ያቀር
ባሉ ። በረከት ፡ ይመጣለታል ፥ ከእርሱም ፡
በኋላ ፡ ለልጆቹ ፡ ይመጣላቸዋል ።
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ደግ ፡ ፳፩፡
ሰውም ፡ ተብሎ ፡ ተጻፈ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡
ጻፍሁልህ ። ኃጢአት ፡ እንዳይሠሩ ፡ ከሥርዓ
ትም ፡ እንዳይተላለፉ ፡ ይሠሩአት ፡ ዘንድ ፡ ይጽ
ፉአትም ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጆችን ፡
ሁነው ፡ ይጻፉ ። የተሠራላቸውንም ፡ መሐላ ፡
እንዳያፈርሱ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ትነግር ፡
ዘንድ ፡ አዘዝሁህ ።
መሐላውን ፡ ቢያፈርሱ ፥ ከኃጢአት ፡ ሥራ ፡ ፳፪፡
ወገንም ፡ ሁሉ ፡ ቢሠሩ ፡ ግን ፡ ጠላቶች ፡ ሆነው ፡
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ይጻፋሉ ፤ ከሕያዋንም ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ይጠፋሉ ፥ የሚጠፉ ፡ ሰዎች ፡ በሚጻፉ
በትም ፡ መጽሐፍ ፡ ይጻፋሉ ። ከምድር ፡ ላይ ፡
ከሚጠፉ ፡ ሰዎችም ፡ ጋር ፡ ይቈጠራሉ ።
የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ ሰቂማን ፡ ባጠፉበት ፡ ቀን ፡ ፳፫፡
የቀና ፡ ነገርንና ፡ እውነት ፡ ሥራን ፡ እንደ ፡
ሠሩ ፥ በሰቂማ ፡ ሰዎችም ፡ ብድርን ፡ እንደ ፡
መለሱ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተጻፈላቸው ። በረ
ከትንም ፡ ለመቀበል ፡ ተጻፉ ።
እኅታቸውን ፡ ዲናንም ፡ ከሴኬም ፡ ቤት ፡ አወጡ ። ፳፬፡
በሰቂማ ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ በጎቻቸውንም ፡
ላሞቻቸውንም ፡ አህዮቻቸውንም ፡ ገንዘባቸው
ንም ፡ ሁሉ ፡ መንጋቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ማረኩ ።
ሁሉንም ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡
አመጡ ።
በዚያ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከፌሬሳውያንና ፡ ከከነናው ፳፭፡
ያን ፡ የተነሣ ፡ ፈርቶአልና ፡ አገሩን ፡ ስላጠፉ ፡
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ።
በሰቂማ ፡ ዙሪያ ፡ ባሉ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚ ፳፮፡
አብሔር ፡ መፈራት ፡ ተደረገ ። በእነርሱ ፡ ድን
ጋጤ ፡ መጥቶአልና ፡ የያዕቆብን ፡ ልጆች ፡ ለማ
ሳደድ ፡ አልተነሡም ።
በወሩም ፡ መባቻ ፡ ያዕቆብ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ፳፯፡
ሁሉ ፡— ከኃጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ሁኑ ፡ ልብሳችሁ
ንም ፡ ለውጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።
ከወንድሜ ፡ ከዔሳው ፡ ፊት ፡ በሸሸሁ ፡ ጊዜ ፡ ፳፰፡

ከእኔ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡ ላለ ፥ ወደዚህችም ፡
አገር ፡ በደኅና ፡ ለመለሰኝ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ወደ ፡ ጸለይሁበት ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ተነሥተን ፡
እንውጣ ።
፳፱፤ በመካከላችሁ ፡ ያሉትን ፡ እንግዶች ፡ አማልክ
ትን ፡ አርቁ ። ልዩ ፡ የሆኑ ፡ አማልክትንም ፡
አጥፉአቸው ፤ በጆሮአችሁ ፡ ያለውንም ፡ በአ
ንገታችሁ ፡ ያለውንም ፡ ጌጥ ፡ አጥፉ ፡ ብሎ ፡
ተናገረ ።
፴፤ ራሔል ፡ ከአባትዋ ፡ ከላባ ፡ የሠረቀችውን ፡
ጣዖት ፥ ገንዘብዋንም ፡ ሁሉ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሰጠች ።
አቃጠለው ፥ ሰበረው ፥ አጠፋው ፥ በሰቂሞን ፡
አገር ፡ ባለ ፡ በዮርዳኖስም ፡ በታች ፡ ቀበረው ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

፩፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡
ወጣ ። በዚያ ፡ በተኛበትም ፡ በታ ፡ መሠዊያ ፡
ሠራ ። በዚያም ፡ ሐውልት ፡ አቆመ ።
፪፤ መሥዋዕት ፡ ወደሚሠዋበት ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡
ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይስሐቅ ፡ ላከ ።
ወደ ፡ እናቱ ፡ ወደ ፡ ርብቃም ፡ ላከ ።
፫፤ ይስሐቅም ፡— ልጄ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይምጣ ፥
ሳልሞት ፡ ልየው ፡ አለ ።
፬፤ ያዕቆብም ፡ ከአባቱ ፡ ከይስሐቅና ፡ ከእናቱ ፡ ከር
ብቃ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አብርሃም ፡ ቤት ፡ ሄደ ።
፭፤ ከልጆቹም ፡ ሁለቱን ፡ ልጆች ፡ ይሁዳንና ፡ ሌዊን ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይስ
ሐቅና ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ወደ ፡ ርብቃ ፡ መጣ ።
፮፤ ርብቃም ፡— እነሆ ፥ ልጅሽ ፡ ያዕቆብ ፡ ደረሰ ፡
እንዳሉአት ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ልቡናዋን ፡ ደስ ፡
ብሎታልና ፡ ያዕቆብን ፡ አቅፋ ፡ ትስመው ፡ ዘንድ ፡
ከአንዱ ፡ ግምብ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ግምብ ፡ በር ፡
መጣች ።
፯፤ ሳመችው ፥ ሁለቱን ፡ ልጆቹንም ፡ በየች ፡ ጊዜ ፡
አወቀቻቸው ። ልጄ ፡ ሆይ ፥ እነዚህስ ፡ ልጆ
ችህ ፡ ናቸውን ? አለችው ፤ አቅፋ ፡ ሳመቻቸው ።
የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ በእናንተ ፡ ይከበር ፡ እናን
ተም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለበረከት ፡ ትሆናላችሁ ፡
ብላ ፡ መረቀቻቸው ።
፰፤ ያዕቆብም ፡ ከአባቱ ፡ ከይስሐቅ ፡ ዘንድ ፡ ወደ
ዚያ ፡ እተኛበት ፡ እልፍኝ ፡ ገባ ። ሁለቱም ፡
ልጆቹ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ገቡ ።
፱፤ የአባቱን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ዘንበል ፡ ብሎ ፡ ሳመው ።
ይስሐቅም ፡ በልጁ ፡ በያዕቆብ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡
ተጠምጥሞ ፡ አንገቱን ፡ እቅፍ ፡ አድርጎ ፡ አለ
ቀሰ ። የይስሐቅንም ፡ ዓይኖች ፡ ሸፍኑአቸው ፡
የነበረው ፡ ተገፈፈ ።
፲፤ የያዕቆብን ፡ ሁለቱን ፡ ልጆቹን ፡ ይሁዳንና ፡
ሌዊን ፡ አይቶ ፡— ልጄ ፡ ሆይ ፥ ይመስሉሃልና ፡
እነዚህ ፡ ልጆችህ ፡ ናቸውን ? አለው ። እርሱም ፡
በእውነት ፡ ልጆቼ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ነገረው ፤ በእ
ውነት ፡ ልጆቼ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በእውነት ፡ አየህ ፡
አለው ።
፲፩፤ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡ ፤ መለስ ፡ ብሎ ፡ ሁሉንም ፡
አንድነት ፡ አቅፎ ፡ ሳማቸው ፤ ትንቢት ፡ የሚያ
ናግር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአፉ ፡ አናገረው ።
ሌዊን ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ያዘው ፤ ይሁዳንም ፡ በግራ ፡
እጁ ፡ ያዘ ።
መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ሌዊ ፡ ተመልሶ ፡ ከይሁዳ ፡ ፲፪፤
አስቀድሞ ፡ ይመርቀው ፡ ጀመር ። እርሱ ፡
እግዚአብሔር ፡ ያክብርህ ፤ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡
የፈጠረ ፡ ፈጣሪ ፡ ልጆችህንና ፡ አንተን ፡ በዓ
ለሙ ፡ ሁሉ ፡ ያክብር ፤ ክብር ፡ ሊሆንህ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ለአንተ ፡ ገናንነትን ፡ ይስጥህ ፤ ለልጆ
ችህም ፡ ይስጣቸው ።
አንተን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ያቅርብህ ፤ በቤተ ፡ መቅ ፲፫፤
ደስ ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ለይቶ ፡
ልጆችህንም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ያቅርባቸው ፤ በለ
ምዋልነት ፡ እንዳላቸው ፡ እንደ ፡ ከበሩ ፡ እንደ ፡
ሊቃነ ፡ መላእክትም ፥ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ልጆች
ህም ፡ ለክብር ፡ ለጌትነት ፡ ለምስጋና ፡ ይሁኑ ፤
በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያድርጋቸው ፤ ለያ
ዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ መሳፍንትና ፡
መኳንንት ፡ አለቆችም ፡ ይሆናሉ ።
የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ይናገ ፲፬፤
ራሉ ፤ ፍርዱንም ፡ ሁሉ ፡ በእውነት ፡ ይፈር
ዳሉ ፤ ለያዕቆብ ፡ ዘጠኙን ፡ ሕግጋት ፡ ለእስራ
ኤልም ፡ አምልኮቱን ፡ ይናገራሉ ፤ የያዕቆብን ፡
ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ይመርቁ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ በረከት ፡ በአፋቸው ፡ ይነገራል ።
አንተንም ፡ እናትህ ፡ ስምህን ፡ ሌዊ ፡ ብላ ፡ ፲፭፤
ጠራች ። ስምህንም ፡ በእውነት ፡ ጠራች ፤ ከእ
ግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ትሆናለህ ፤ ከያዕቆብ ፡
ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ትሆናለህ ፤ ማዕዱ ፡
ለአንተ ፡ ትሁን ። መሥዋዕቱ ።
ልጆችህና ፡ አንተ ፡ ብሉአት ፤ ማዕድህም ፡ ፲፮፤
ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ የመላች ፡ ትሁን ፤ በዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ እህልህ ፡ አይጕደል ፥ አይታጣ ፤ የሚጠ
ሉህም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በፊትህ ፡ ይውደቁ ፥
ጠላቶችህም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ ይጥፉ ፤ ሁሉም ፡
የተረገሙ ፡ ይሁኑ ፡ አለው ።
ይሁዳንም ፡— የሚጠሉህን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ታጠ ፲፯፤
ፋቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልን ፡ ጽና
ትን ፡ ይስጥህ ፤ አንተ ፡ ገዥ ፡ ሁን ፤ ከልጆች
ህም ፡ አንዱ ፡ ለያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ገዥ ፡ ይሁን ፤
ስምህ ፡ ከልጆችህ ፡ ስም ፡ ጋር ፡ በከተማውና ፡
በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሲጠራ ፡ የሚኖር ፡ ይሁን ።
ያንጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ከፊትህ ፡ የተነሣ ፡ ይፈራሉ ፥ ፲፰፤
አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ይታወካሉ ፥ ሕዝቡም ፡
ሁሉ ፡ ይሸበራሉ ፤ የያዕቆብ ፡ ረድኤት ፡ በአንተ ፡
ይደር ፥ የእስራኤልም ፡ ድኅነት ፡ በአንተ ፡ ትገ
ኛለች ።
እውነተኛ ፡ ክብር ፡ ባለው ፡ ዙፋን ፡ በተቀመ ፲፱፤
ጥህ ፡ ጊዜ ፡ ገናና ፡ ትሆናለህ ፤ ለያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ትደረግላቸዋ
ለች ፤ የሚመርቅህ ፡ ሰው ፡ የተመረቀ ፡ ነው ፤
የሚጠሉህ ፡ መከራንም ፡ የሚያጸኑብህ ፡ የሚ
ረግሙህም ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈጽመው ፡

ይጥፉ ፡ የተረገመውም ፡ ይሁኑ ፡ አለው ።
፳፤ ተመልሰ ፡ ዳግመኛ ፡ እቅፍ ፡ አድርጎ ፡ሳመው ፤
በእውነት ፡ የወለዳቸውን ፡ የልጁ ፡ የያዕቆብን ፡
ልጆች ፡ አይቶአልና ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለው ።
፳፩፤ ከእግሮቹ ፡ መካከል ፡ ወጥቶ ፡ በግምባሩ ፡ ወድቆ ፡
ሰገደለት ÷ መረቃቸው ፡ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡
በአባቱ ፡ በይስሐቅ ፡ አጠገብ ፡ በዚያ ፡ ተኛ ።
ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ በሉ ፡ ጠጡ ።
፳፪፤ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ የያዕቆብን ፡ ልጆች ፡ አንዱን ፡
በቀኙ ፡ አንዱን ፡ በግራው ፡ አቆመ ፤ ይህም ፡
ጽድቅ ፡ ሆኖ ፡ ተቈጠረለት ።
፳፫፤ ያዕቆብም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእርሱ ፡ ብዙ ፡
ይቅርታ ፡ እንዳደረገ ፡ ነገረው ፤ ጐዳናውን ፡
ሁሉ ፡ እንዳቀናለት ፡ ከክፉም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ ጠበቀው ፡ ሌሊት ፡ ለአባቱ ፡ ሁሉን ፡
ነገረው ።
፳፬፤ ይስሐቅም ፡ ከባሪያው ፡ ከይስሐቅ ፡ ልጅ ፡ ቸር
ነቱንና ፡ ይቅርታውን ፡ ያላረቀ ፡ የአባቱን ፡ የአ
ብርሃምን ፡ ፈጣሪ ፡ አመሰገነው ።
፳፭፤ ያዕቆብም ፡ ለአባቱ ፡ ለይስሐቅ ÷ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የተሳለውን ፡ ስእለት ÷ ያየውንም ፡
ራእይ ÷ መሠዊያውንም ፡ እንደ ፡ ሠራ ÷ ሲነጋ ፡
ለአባቱ ፡ ለይስሐቅ ፡ ነገረው ፤ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ እንደ ፡ ለመነ ÷ ለማድረግ ፡ ለመሥዋዕት ፡
የሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ÷ በበቅሎ
ውም ፡ አስቀምጦ ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
መጣ ፡ ነገረው ።
፳፮፤ ይስሐቅም ፡ ልጁን ፡ ያዕቆብን ፡— አርጅቻለሁና ፡
ከአንተ ፡ ጋር ፡ መምጣት ፡ አልችልም ፡ ጐዳና
ውንም ፡ መታገሥ ፡ አልችልም ፤ ልጄ ፡ ሆይ ÷
በደኅና ፡ ሂድ ፤ እኔ ፡ አሁን ፡ የመቶ ፡ ስድሳ ፡
አምስት ፡ ዘመን ፡ ልጅ ፡ ነኝና ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
መሄድ ፡ አልችልም ።
፳፯፤ እናትህን ፡ በበቅሎ ፡ አስቀምጠህ ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ ይዘሃት ፡ ሂድ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡
እንደ ፡ መጣህ ፡ አውቃለሁ ፤ በሕይወት ፡ ሳለህ ፡
እኔን ፡ ያየህበት ፡ እኔም ፡ በሕይወት ፡ ሳለሁ ፡
አንተን ፡ ያየሁበት ፡ ይህች ፡ ቀን ፡ የተባረከች ፡
ትሁን ።
፳፰፤ ልጄ ፡ ሆይ ÷ ተዘጋጅተህ ፡ የተሳልኸውን ፡
ስእለትህን ፡ ስጥ ፤ ስእለት ፡ ቢያስቀሩት ፡ በፍዳ ፡
ይመረመራልና ፡ ስእለትህን ፡ አታቆይ ÷ አታ
ስቀር ።
፳፱፤ አሁንም ፡ ታደርጋት ፡ ዘንድ ፡ ቸኩል ፤ ሁሉን ፡
የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተሳልኸውን ፡ ስእ
ለት ፡ ወዶ ፡ ይቀበልህ ፡ አለው ።
፴፤ ርብቃንም ፡— ከልጅሽ ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋር ፡ ሂጂ ፡
አላት ። ርብቃም ፡ ከልጅዋ ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋር ፡
ሄደች ፤ ዲቦራም ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ሄደች ÷ ወደ ፡
ቤቴልም ፡ ደረሱ ።
፴፩፤ ያዕቆብም ፡ ስእለቱን ፡ አባቱ ፡ ይስሐቅም ፡ ከሁ
ለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ከይሁዳና ፡ ከሌዊ ፡ ጋር ፡ የመረ
ቀውን ፡ ምርቃት ፡ አስበ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ የአባ
ቶቹን ፡ የይስሐቅንና ፡ የአብርሃምን ፡ ፈጣሪ ፡
አመሰገነው ።
አሁንም ፡ ለዘላለም ፡ ተስፋ ፡ እንዳለኝ ÷ ሁሉን ፡ ፴፪፤
በፈጠረ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለልጆቼም ፡
ተስፋ ፡ እንዳላቸው ፡ አወቅሁ ፡ አለ ።
ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ሠርቶአል ። ፴፫፤
ይስሐቅ ፡ እንደ ፡ መረቃቸው ፡ ለዘላለም ፡ ምስ
ክር ፡ ሊሆን ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ይጽፉላቸዋል ፡
በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ በቤቴል ፡ አደረ ።
ሌዊም ፡ እንደ ፡ ሾሙት ÷ ለልዑል ፡ አምላክም ፡ ፴፬፤
እርሱን ፡ አገልጋይ ፡ እንዳደረጉት ÷ ልጆቹንም ፡
እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ አገልጋይ ፡ እንዳደረጉ
አቸው ፡ ሕልም ፡ አየ ።
ከእንቅልፉም ፡ ተነሥቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፴፭፤
አመሰገነ ። ይህ ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ አራት ፡
ቀን ፡ ያዕቆብ ፡ በጥዋት ፡ ገሠገሠ ።
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ከመጣው ፡ ሁሉ ÷ ከሰው ፡ ፴፮፤
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ከብት ፡ ድረስ ÷ ከወርቅም ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሌላው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡
ልብስም ፡ ድረስ ÷ ከሁሉ ፡ ከሁሉም ፡ አሥራት ፡
አወጣ ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ ራሔል ፡ ልጅዋን ፡ ብንያ ፴፯፤
ምን ፡ ፀነሰች ፤ ያዕቆብም ፡ ከሮቤል ፡ ጀምሮ ፡
ልጆቹን ፡ ቈጠረ ።
ዕጣ ፡ ጣለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዕጣ ፡ በሌዊ ፡ ወጣ ፤ ፴፰፤
አባቱም ፡ የክህነት ፡ ልብስን ፡ አለበሰው ÷ እጁ
ንም ፡ ቀባው ።

ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

ይህ ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ፩፤
ቀን ፡ ከላሞች ፡ ወገን ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ገች ÷
ሀያ ፡ ስምንት ፡ የበግ ፡ ሙክት ÷ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡
በግ ÷ ዘጠና ፡ ስድስት ፡ የበግ ፡ ጠቦት ÷ ሀያ ፡
ዘጠኝ ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ አቀረበ ። በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ አድርጎ ፡ ሊቀ
በለው ፡ የሚያሸቱትን ፡ የተወደደ ፡ ቍርባን
ንም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ አገባ ።
አሥራት ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ ከተሳለው ፡ ስእለት ፡ ፪፤
ከመሥዋዕታቸው ፡ ጋር ፡ ያቀረበው ፡ መባ ፡
ይህ ፡ ነው ። ፍልቅ ፡ አድርገው ፡ የሚያፈሱ
ትም ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ።
እሳት ፡ በበላው ፡ ጊዜ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ ፫፤
ዕጣንን ፡ ያጥን ፡ ነበር ። ደኅንነት ፡ ለሚደረግ
በት ፡ መሥዋዕትም ፡ አራት ፡ ገች ÷ አራት ፡
የበግ ፡ ሙክት ÷ አራት ፡ በግ ÷ አራት ፡ የፍየል ፡
ሙክት ÷ ዓመት ፡ የሆናቸውን ፡ ሁለት ፡ የበግ ፡
ጠቦቶች ÷ ሁለት ፡ የፍየል ፡ ጠቦቶችን ፡ ያቀ
ርብ ፡ ነበር ። በነጋ ፡ ቍጥር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እን
ዲህ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።
ከቤተ ፡ ሰቦቹና ፡ ከልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ፬፤
ብሎት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።
ከጽኑ ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ያዳነውን ÷ የለመነው
ንም ፡ የሰጠውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሞ ፡
ያመሰግነው ፡ ነበር ። ንጹሕ ፡ የሆነውን ፡ ከብት ፡
ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ያልሆነውንም ፡ አሥራት ፡ አወጣ ።

፭፤ ስቡንም ፡ አሽተተ ፡ መሥዋዕት ፡ የማይገባውን ፡
ከብት ፡ ለልጁ ፡ ለሌዊ ፡ ሰጠው ። የሰውንም ፡
ወገን ፡ ሁሉ ፡ ሰጠው ።
፮፤ ሌዊም ፡ ከአሥሩ ፡ ወንድሞቹ ፡ ተለይቶ ፡ በአ
ባቱ ፡ በያዕቆብ ፡ ፊት ፡ በቤቴል ፡ አገለገለ ።
፯፤ በዚያ ፡ አገልጋይ ፡ ሆኖ ፡ ኖረ ፤ ያዕቆብም ፡ ስእ
ለቱን ፡ ሰጠው ፤ ዳግመኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
እንደዚሁ ፡ አሥራትን ፡ ሰጠ ። ይህንንም ፡
ለየው ፤ የተለየ ፡ ሆነ ።
፰፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አሥራት ፡ ለማውጣት ፡ ከዓ
መት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ስሙ ፡ ይጠራበት ፡ ዘንድ ፡
በተመረጠ ፡ በከበረ ፡ ቦታ ፡ ዳግመኛ ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ ለመብላት ፡ ሥርዓት ፡ ሆኖ ፡
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተወስኖአል ።
፱፤ ለዚህም ፡ ሕግ ፡ ለዘላለሙ ፡ የተወሰነ ፡ ዘመን ፡
የለውም ፤ ይኸውም ፡ ሥርዓት ፡ ከዓመት ፡ እስከ ፡
ዓመት ፡ ሊያደርጉት ÷ ዳግመኛ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ በተመረጠ ፡ ቦታ ፡ ሊበሉት ፡ በሰ
ማይ ፡ ጽላት ፡ የተጻፈ ፡ ነው ።
፲፤ የዓመቱ ፡ አዝመራ ፡ እስከሚደርስበት ፡ ወራት ፡
ድረስ ፡ ዘሩ ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይበላልና ፡
ከዚህ ፡ ዓመት ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ከእርሱ ፡
ማትረፍ ፡ የለም ፤ ወይንም ፡ ወይን ፡ እስከሚደ
ርስበት ፡ ወራት ÷ ዘይትም ፡ ዘይት ፡ እስከሚደ
ርስበት ፡ ወራት ፡ ይበላልና ፡ ማትረፍ ፡ የለም ።
፲፩፤ ከእርሱም ፡ የሚተርፈው ፡ ሁሉ ፡ የደለበው ፡
የረከሰ ፡ ይሁን ፤ የረከሰ ፡ ሆኖአልና ፡ በእሳት ፡
ይቃጠል ። እንደዚሁ ፡ በከበረበት ፡ ሆነው ፡
አንድነት ፡ ይብሉት ፤ አያድልቡት ።
፲፪፤ የበጉና ፡ የላሙ ፡ አሥራት ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የተለየ ፡ ነው ። ስለ ፡ አሥራቱ ፡ የሚሆ
ነው ፡ እንደዚሁ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተወስኖአ
ልና ፡ ተጽፎአልምና ፡ ካህናቱ ፡ ከዓመት ፡ እስከ ፡
ዓመት ፡ በፊቱ ፡ የሚበሉት ፡ ይሁን ።
፲፫፤ በሁለተኛይቱ ፡ ሌሊት ፡ ይህ ፡ ወር ፡ በባተ ፡
በሀያ ፡ ሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ያዕቆብ ፡ ያንን ፡ ቦታ ፡
ይሥራ ፡ ዘንድ ÷ ቅጥሩንም ፡ ሠርቶ ፡ ይለየው ፡
ዘንድ ÷ ለእርሱ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ የከ
በረ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ÷ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ለል
ጆቹ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ የከበረ ፡ ያደር
ገው ፡ ዘንድ ፡ መከረ ።
፲፬፤ እግዚአብሔርም ፡ ሌሊት ፡ ተነጋገረው ፡ አከበ
ረው ፡— ስምህ ፡ እስራኤል ፡ ይባል ፡ እንጂ ፡
ያዕቆብ ፡ ብቻ ፡ አይባል ፡ አለው ።
፲፭፤ ዳግመኛም ፡ ምድርንና ፡ ሰማይን ፡ የፈጠርሁ ፡
አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ አከብር
ሃለሁ ፡ ፈጽሜ ፡ እጅግ ፡ አበዛሃለሁ ።
፲፮፤ ነገሥታቱ ፡ ከአንተ ፡ ይወለዳሉ ፤ አራቱንም ፡
ማዕዘን ፡ ይገዛሉ ፤ የአዳም ፡ ልጅ ፡ የረገጠውን ፡
ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ይገዛሉ ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያለ ፡
አገርን ፡ ሁሉ ፡ ለልጆችህ ፡ እሰጣለሁ ፤ እንደ ፡
ወደዱ ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ይገዛሉ ።
፲፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አገሪቱን ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ያደርጋሉ ÷
ለዘላለምም ፡ ይወርሱአታል ፡ አለው ። ከእርሱ ፡
ጋር ፡ ተነጋግሮ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡
ወጣ ። ወደ ፡ ሰማይ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ያዕቆ
ብም ፡ ያይ ፡ ነበር ።
ለሊት ፡ በራእይ ፡ በየ ፡ ጊዜ ÷ እነሆ ÷ መልአክ ፡ ፲፰፤
ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየ ፤ ሰባት ፡ ብራናዎች ፡
በእጁ ፡ አሉ ።
ለያዕቆብ ፡ ሰጠው ፤ ያዕቆብም ፡ አነበባቸው ፤ ፲፱፤
በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቹና ፡ ለእርሱ ፡ የሚሆን ፡
በውስጣቸው ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ አነበበ ።
በብራና ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ አሳየው ።
ይህን ፡ ቦታ ፡ አትሥራ ÷ የዘላለም ፡ መቅደስ ፳፤
ንም ፡ አታድርገው ፤ ይህ ፡ ቦታ ፡ ቤተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ የሚሠራበት ፡ አይደለምና ፡ በዚህ ፡
ቦታ ፡ አትደር ። ወደ ፡ አባትህ ፡ ወደ ፡ አብርሃም ፡
ቤት ፡ ሂድ ፤ አባትህ ፡ እስከሚሞትበት ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ በዚያ ፡ በአባትህ ፡ በይስሐቅ ፡ ቤት ፡
ኑር ፤ በግብጽ ፡ ሳለህ ፡ በደስታ ፡ ትሞታለህና ።
በዚህች ፡ አገር ፡ ከአባቶችህ ፡ ከአብርሃምና ፡ ፳፩፤
ከይስሐቅም ፡ ጋር ፡ በአባቶችህ ፡ መቃብር ፡ በክ
ብር ፡ ትቀበራለህና ፡ አይዞህ ÷ አትፍራ ፤ እንዳ
የኸው ፡ እንዳነበብኸው ፡ እንደዚሁ ፡ ይደረጋ
ልና ።
አንተም ፡ ያየኸውን ፡ ያነበብኸውን ፡ ሁሉ ፡ ፳፪፤
ጻፍ ፡ አለው ። ያዕቆብም ፡— አቤቱ ÷ ሁሉን ፡
እንዳነበብሁ ፡ እንዳየሁ ፡ እንዴት ፡ አስባለሁ ?
አለ ። ጌታም ፡— እኔ ፡ ሁሉን ፡ አሳስብሃለሁ ፡
አለው ።
ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፤ ያዕቆብም ፡ ከእንቅልፉ ፡ ፳፫፤
ተቀሰቀሰ ፤ ያነበበውንና ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡ አሰበ ።
ያየውንና ፡ ያነበበውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጻፈ ።
ዳግመኛ ፡ በዚያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረገ ፤ ፳፬፤
በቀደሙት ፡ ዕለታት ፡ እንደሚሠዋው ፡ ሁሉ ፡
አድርጎ ፡ ሠዋበት ። ያች ፡ ቀን ፡ ተጨምራለችና ፡
ስምዋን ፡ ተውሳክ ፡ አላት ።
የቀደሙትንም ፡ ቀኖች ፡ በዓል ፡ ከእነርሱ ፳፭፤
በዓል ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ እንዲህ ፡ ይታይ ፡
ነበር ፤ ይህም ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተጽፎአል ።
ስለዚህም ፡ ነገር ፡ በዓል ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ÷ ፳፮፤
በዓል ፡ በሚደረግባቸው ፡ በሰባቱ ፡ ቀኖች ፡ ላይ ፡
እርስዋን ፡ ይጨምር ፡ ዘንድ ÷ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተገ
ለጠለት ። በዓመት ፡ እንደሚመላለሱ ፡ ቀኖች ፡
ቍጥር ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ መሥዋዕት ፡ የሚ
ሠዋበት ÷ በዓል ፡ የሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ናትና ፡
ስምዋ ፡ ተውሳክ ፡ ተባለ ።
ይህ ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በሀያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ ፳፯፤
ሌሊት ፡ የርብቃም ፡ ሞግዚትዋ ፡ ዲቦራ ፡ ሞተች ።
ከመንደሩ ፡ በታች ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ባለ ፡ ግራር ፡
ሥር ፡ ቀበሩአት ።
የዚያንም ፡ ወንዝ ፡ ስም ፡ ዲቦራ ፡ የተቀበረች ፳፰፤
በት ፡ ወንዝ ፡ አለው ። ግራሩንም ፡ የዲቦራ ፡
ልቅሶ ፡ የተለቀሰበት ፡ ግራር ፡ አለው ።
ርብቃም ፡ ተመልሳ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይስ ፳፱፤
ሐቅ ፡ ቤት ፡ ሄደች ። ያዕቆብም ፡ አባቱ ፡ እንደ
ሚወደው ፡ አድርጋ ፡ ለአባቱ ፡ ምግብ ፡ ታዘ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ጋሯ ፡ ዘንድ ፡ የፍየሎችን ፡ ሙክዮችና ፡ የበጎ
ችንም ፡ ሙክዮች ፡ በጎችንም ፡ በእጅዋ ፡ ላከ ።
፴፡ ከብራታን ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ እስኪቀርብ ፡
ድረስ ፡ ከእናቱ ፡ በኋላ ፡ ሄደ ። በዚያም ፡ አደረ ።
፴፩፡ ራሔልም ፡ ሌሊት ፡ ወለደች ። በወለደችው ፡
ጊዜ ፡ ተጨንቃ ፡ ነበርና ፡ ስሙን ፡ መከራ ፡ የተ
ቀበልሁበት ፡ ልጅ ፡ አለችው ።
፴፪፡ አባቱ ፡ ግን ፡ ስሙን ፡ ብንያም ፡ አለው ። በዚህ ፡
ኢዮቤልዩ ፡ በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአንደ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ስምንተኛው ፡ ወር ፡ በበተ ፡
በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ ራሔል ፡ ሞተች ። ኤፍ
ራታ ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ተቀበረች ፡ ይህች
ውም ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ናት ።
፴፫፡ ያዕቆብም ፡ በጎዳና ፡ ዳር ፡ ባለ ፡ በራሔል ፡ መቃ
ብር ፡ ላይ ፡ ሐውልትን ፡ አቆመ ።
፴፬፡ ያዕቆብም ፡ ሄዶ ፡ በመግደላ ፡ ድራኤፍ ፡ ግራ ፡
ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይስሐቅ ፡ ሄደ ።
፴፭፡ በአሥረኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ሮቤል ፡ የአባቱ ፡
ዕቁባት ፡ የምትሆን ፡ የራሔልን ፡ አገልጋይ ፡
ባላንን ፡ ተሰውራ ፡ በውኃ ፡ ስትታጠብ ፡ አየ ፡
ወደዳትም ።
፴፮፡ በሌሊት ፡ ተሰውሮ ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ባላን ፡ ቤት ፡
ገባ ፤ በቤትዋ ፡ ብቻዋን ፤ በአልጋዋ ፡ ላይ ፡
ተኝታ ፡ አገኛት ። ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ተኛ ፤ በነቃ
ችም ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፥ ሮቤል ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡
በመኝታዋ ፡ ተኝቶ ፡ አየች ።
፴፯፡ እጅዋን ፡ ዘርግታ ፡ ያዘችው ፤ ጮኸች ፤ ሮቤል ፡
እንደ ፡ ሆነም ፡ አወቀች ። ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡
አፈረች ። እርሱም ፡ ሸሸ ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ፈጽማ ፡
ታዝን ፡ ነበር ፤ ለማንም ፡ ለማን ፡ ሰው ፡ አልተ
ናገረችም ።
፴፰፡ ያዕቆብም ፡ መጥቶ ፡ በፈለጋት ፡ ጊዜ ፡— ሮቤል ፡
ስላሳደፈኝ ፡ ሌሊትም ፡ ስለ ፡ ደረሰብኝ ፡ ከአ
ንተ ፡ ተለይቻለሁና ፡ ለአንተ ፡ የምገባ ፡ አይደ
ለሁም ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ተኝቼ ፡ ነበር ፤ እጇን ፡ እስከ
ዘረጋ ፡ ድረስ ፡ አላወቅሁትም ፡ እርሱ ፡ ደርሶብ
ኛል ፡ አለችው ።
፴፱፡ በባላን ፡ ደርሶአልና ፥ የአባቱንም ፡ ኃፍረት ፡
ገልጦአልና ፡ ያዕቆብ ፡ በሮቤል ፡ ፈጽሞ ፡ ተቆጣ ።
፵፡ ሮቤል ፡ አሳድፎአታልና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ያዕ
ቆብ ፡ አልደረሰባትም ። የአባቱን ፡ ኃፍረት ፡
የገለጠ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡
ነውና ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ የተናቀ ፡
ነውና ።
፵፩፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ከአባቱ ፡ ሚስት ፡ እንዳ
ይደርስ ፥ የአባቱንም ፡ ኃፍረት ፡ እንዳይገልጥ ፡
በሰማይ ፡ ጽላት ፡ ተጽፎአል ፤ የማይገባ ፡ ሥራ ፡
ሠርቶአልና ፡ ሞትን ፡ ይሙት ።
፵፪፡ ከአባቱ ፡ ሚስት ፡ የሚደርስ ፡ ሰው ፡ ጐስቋላ ፡
ነው ። ሴትም ፡ ብትሆን ፡ ጐስቋላ ፡ ናት ። በዚህ ፡
ዓለም ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተዋልና ፡ እርሱም ፡ እር
ስዋም ፡ ይሙቱ ። በአምላካችን ፡ ፊት ፡ ለአገ
ዛዝ ፡ በመረጠው ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ የተጠላ ፡
አይሁን ።
ከአባቱ ፡ ሚስት ፡ የሚደርስ ፡ ሰው ፡ የአባቱን ፡ ፵፫፡
ኃፍረት ፡ ገልጦአልና ፡ የተረገመ ፡ ይሆን ፡
ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ ተጽፎአል ።
የእግዚአብሔር ፡ ወዳጆች ፡ ሁሉ ፡— የተረገመ ፡ ፵፬፡
ይሁን ፡ የተረገመ ፡ ይሁን ፡ አሉ ።
ሙሴ ፥ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘ ፵፭፡
ዛቸው ፤ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ፍርድ ፡ ነውና ፥
የማይገባ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ይጠብቁ ።
ይህን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለሠራ ፡ ሰው ፡ ለኃጢአቱ ፡ ፵፮፡
ለዘላለም ፡ ስርየት ፡ የለውም ። በእስራኤል ፡
መካከል ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
የተናቀ ፡ የተጠላ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ስንኳ ፡ መዋል ፡ አይገባውምና ፡
በአምላካችን ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ በድንጋይ ፡
ተወግሮ ፡ ይሙት ፡ እንጂ ፡ ለኃጢአቱ ፡ ስርየት ፡
የለውም ።
በአባቱ ፡ ሚስት ፡ ደርሶአልና ፡ ለሮቤል ፡ ድኅ ፵፯፡
ነት ፡ ስርየት ፡ ይገባዋል ፡ አይበሉ ።
እርስዋም ፡ ባልዋ ፡ አባቱ ፡ ያዕቆብ ፡ በሕይወት ፡ ፵፰፡
ሳለ ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሥርዓቱ ፡ ቅጣቱ ፡
ሕጉ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ እንደሚደረገው ፡ ሕግ ፡
አልተፈጸመምና ፡ ስርየት ፡ ይገባታል ፡ አይ
በሉ ። በልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመንም ፡ ለዘላለም ፡
ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ለዚህም ፡ ሕግ ፡ የዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ። ፵፱፡
በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡
ይጠፉ ፡ ዘንድ ፥ ይህችን ፡ ኃጢአት ፡ በሠሩበት ፡
ቀን ፡ ይገድሉአቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ለኃጢአታቸው ፡ ምንም ፡ ስርየት ፡ የለውም ።
ሙሴ ፥ አንተም ፡ ለእስራኤል ፡ ጻፍላቸው ፥ ፶፡
ይጠብቁአትም ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራም ፡ አይ
ሥሩ ፤ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ በደልንም ፡ አይበ
ድሉ ። ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያዳላ ፥ መማለጃን ፡
የማይቀበል ፡ እርሱ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ነውና ።
ይሰሙ ፡ ዘንድ ፥ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ከእነርሱም ፡ ፶፩፡
ይለዩ ፡ ዘንድ ፥ የተጠላ ፥ የሚያስጸይፍ ፥ የተ
ናቀ ፥ የተነቀፈ ፡ ነውና ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈጽ
መው ፡ እንዳይጠፉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በፈጣሪያ
ችን ፡ ፊት ፡ ይህችን ፡ ኃጢአት ፡ ለሚሠሩአት ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ የሥርዓቱን ፡ ነገር ፡
ንገራቸው ።
እስራኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየ ፡ ወገን ፡ ፶፪፡
ነውና ፥ ለፈጣሪውም ፡ ማደሪያ ፡ ነውና ፥ ለክህ
ነት ፡ ለመንግሥት ፡ የሚገባ ፡ ወገን ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ከሚሠሩት ፡ ከገሙት ፡ የሚበልጥ ፡
ኃጢአት ፡ የለም ። በንጹሕ ፡ ወገን ፡ መካከል ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ሊሠራ ፡ አይገባም ።
በዚህ ፡ በስድስተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሰባተኛው ፡ ፶፫፡
ዓመት ፡ ያዕቆብ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። ልጆቹም ፡
ይሄዱ ፡ ነበር ። በአባቱ ፡ በይስሐቅና ፡ በእናቱ ፡
በርብቃ ፡ አቅራቢያ ፡ በአብርሃም ፡ ቤት ፡ አደሩ ።
የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ፶፬፡
መጀመሪያው ፡ ሮቤል ፡ ይባላል ፤ ሁለተኛው ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ስምዖን፡ ይባላል ፤ ሦስተኛው ፡ ሌዊ ፡ ይባላል ፤ አራተኛው ፡ ይሁዳ ፡ ይባላል ፤ አምስተኛው ፡ ይሳኮር ፡ ይባላል ፤ ስድስተኛው ፡ ዛብሎን ፡ ይባላል ፤ እነዚህ ፡ የልያ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።
፳፫፡ የራሔል ፡ ልጆች ፡ ብንያምና ፡ ዮሴፍ ፡ ናቸው ።
፳፬፡ የባላንም ፡ ልጆች ፡ ንፍታሌምና ፡ ዳን ፡ ናቸው ።
፳፭፡ የዘለፋም ፡ ልጆች ፡ አሴርና ፡ ጋድ ፡ ናቸው ።
፳፮፡ ልያ ፡ ለያዕቆብ ፡ የወለደቻት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ዲና ፡ ብቻ ፡ ናት ። ሄደውም ፡ ለያዕቆብና ፡ ለርብቃ ፡ ሰገዱ ።
፳፯፡ በዩአቸውም ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹን ፡ ሁሉና ፡ ያዕቆብን ፡ መረቁአቸው ። የትንሹ ፡ ልጁን ፡ የያዕቆብን ፡ ልጆች ፡ አይቶአልና ፡ ይስሐቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ መረቃቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

፩፡ ከዚህ ፡ ከአርባ ፡ አራተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ከዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ በጎችን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጆቹን ፡ ላካቸው ። በሪያዎቹንም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰቂሞን ፡ መስክ ፡ ላካቸው ።
፪፡ በእንጨት ፡ ሥር ፡ ተሰውረው ፡ ያጠፉአቸው ፡ ዘንድ ÷ ሚስቶቻቸውንና ፡ ከብቶቻቸውንም ፡ ይማርኩ ፡ ዘንድ ፡ ሰባቱ ፡ ሁሉ ፡ የአሞሬዎን ፡ ነገሥታት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ።
፫፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ይሁዳና ፡ ሌዊ ፡ ዮሴፍ ፡ ከአባታቸው ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋር ፡ በቤት ፡ ነበሩ ። ልቡናው ፡ ያዝንበት ፡ ነበርና ÷ እርሱንም ፡ መተው ፡ አልተቻላቸውምና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ታናሹ ፡ ልጁ ፡ ብንያም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ።
፬፡ የአሬሳና ፡ የታፉ ፡ ነገሥታት ÷ የሴሎን ፡ ነገሥታትና ፡ የሰራጋን ፡ ነገሥታት ÷ የቤቴሮን ፡ ንጉሥና ፡ የጋዒዝ ፡ ንጉሥ ÷ የማአኒሲኪሮስ ፡ ንጉሥ ፡ በተራራ ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ÷
፭፡ በከነዓን ፡ ባለ ፡ ዛፍ ፡ በር ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ መጡ ። ለያዕቆብም ፡— እነሆ ÷ የአሞሬዎን ፡ ነገሥታት ፡ ልጆችህን ፡ ከበቡአቸው ÷ መንጋቸውንም ፡ ተነጠቁ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።
፮፡ እርሱ ፡ ከቤቱ ፡ ተነሣ ÷ ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ የአባቱም ፡ ብላቴኖች ፡ ሁሉ ፡ የእርሱም ፡ ብላቴኖች ፡ ተነሡ ።
፯፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ ሄዶ ፡ በሰቂሞን ፡ መስክ ፡ ወጉአቸው ።
፰፡ የሸሹትንም ፡ ተከትለው ፡ በሰይፍ ፡ አጠፉአቸው ። ታፋና ፡ አሬሳን ፡ ሴሎንና ፡ ሰራጋን ፡ አማኒሲኪሮስን ፡ ጋጋአስንም ፡ አጠፋቸው ÷ መንጋውንም ፡ ሰበሰበ ።
፱፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ። እነዚህ ፡ አምስቱ ፡ የምድራቸውን ፡ ፍሬ ፡ ግብር ፡ ይሰጡት ፡ ዘንድ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ ሠራ ።
፲፡ ታምና ፡ ታሬስንና ፡ ሮቤልን ፡ ቀጸረ ፤ በደኅናም ፡ ተመለሰ ።
፲፩፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ፍቅርን ፡ አደረገ ። ልጆቹና ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ እስኪወርዱ ፡ ድረስ ፡ አገልጋይ ፡ ሆኑት ።
ይህ ፡ ሱባዔ ፡ በሚቈጠርበት ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የወንድሞቹን ፡ ደኅንነት ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዮሴፍን ፡ ከቤቱ ፡ ወደ ፡ ሰቂሞን ፡ ላከው ። ፲፪፡
በዶታኤም ፡ አውራጃ ፡ አገኛቸው ። በዘበዙት ÷ ይገድሉትም ፡ ዘንድ ፡— እንግደለው ፡ ብለው ፡ መከሩ ። ፲፫፡
ተመልሰው ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ነጋዶች ፡ ሸጡት ። እነርሱም ፡ ግብጽ ፡ አውርደው ፡ የኤሊው ፡ አገር ፡ ካህን ፡ ለሚሆን ፡ ለእንጀራ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ለፈርዖን ፡ ባለምዋል ፡ ለፋጢፋራን ፡ ሸጡት ። ፲፬፡
የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አርደው ፡ የዮሴፍን ፡ ልብስ ፡ በደሙ ፡ ነከሩ ። ፲፭፡
ሰባተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ላኩ ። በዚያች ፡ ቀን ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ አለቀሰ ። ፲፮፡
ልብሱንም ፡ አመጡለት ፤ በሞቱ ፡ ኀዘን ፡ ተንቀጠቀጠ ። ዮሴፍን ፡ ክፉ ፡ አውሬ ፡ እንደ ፡ በላው ፡ ነገሩት ፤ የቤቱም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ አለቀሱ ፤ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያዝኑ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ። ፲፯፡
ሴቲቱ ፡ ልጁና ፡ ወንዶቹ ፡ ልጆቹ ፡ ያረጋጉት ፡ ዘንድ ፡ ተነሡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ አልተረጋጋም ። ፲፰፡
በዚያም ፡ ቀን ፡ ባላን ፡ ዮሴፍ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ሰማች ። ለእርሱም ፡ ስታለቅስ ፡ ሞተች ። እርስዋም ፡ በቅፍራቲፉ ፡ ትኖር ፡ ነበር ። ፲፱፡
ልጁም ፡ ዲና ፡ ዮሴፍ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሞተች ። በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ይህ ፡ ሦስቱ ፡ ኀዘን ፡ ደረሰበት ። ባላንም ፡ በራሔል ፡ መቃብር ፡ አንጻር ፡ ቀበሩአት ፤ ልጁን ፡ ዲናንም ፡ በዚያ ፡ ቀበሩ ። ፳፡
ዮሴፍ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሲያለቅስ ፡ ኖረ ። ስለ ፡ ልጄ ፡ ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ እያለቀስሁ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እወርዳለሁ ፡ ብሎአልና ፡ ልቅሶውን ፡ አልተወም ። ፳፩፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሰባተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ ያዝኑ ፡ ዘንድ ÷ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ሥርዓት ፡ ተሠራ ። የዮሴፍን ፡ መርዶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ባደረሱበት ፡ ቀን ፡ በፍየል ፡ ጠቦት ፡ ለእርሱ ፡ ያስተሰርይለት ፡ ዘንድ ። ፳፪፡
ሰባተኛው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ ከዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ተሠራች ፤ ስለ ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ የአባታቸውን ፡ ልቡና ፡ አሳዝነዋልና ። ፳፫፡
ይህችም ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ስለ ፡ በደላቸው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ስሕተታቸው ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ራሳቸውን ፡ ሊያነጹ ፡ ያዝኑበት ፡ ዘንድ ፡ ተሠራች ። ፳፬፡
ዮሴፍ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ለራሳቸው ፡ ሚስት ፡ አገቡ ። የአንዱ ፡ የሮቤል ፳፭፡

ሚስት ፡ ስምዋ ፡ አዳ ፡ ይባላል ።
፴፪ የሁለተኛው ፡ የስምዖን ፡ ሚስት ፡ ስምዋ ፡ አን ዲባአ ፡ ትባላለች ፤ ይህችውም ፡ የከነዓን ፡ ሴት ፡ ናት ። የሦስተኛውም ፡ የሌዊ ፡ ሚስት ፡ ስምዋ ፡ ሚልካ ፡ ይባላል ፤ እርስዋም ፡ ከቃራ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ከሚሆን ፡ ከአራም ፡ ልጆች ፡ የተወለ ደች ፡ ናት ።
፴፫ የአራተኛው ፡ የይሁዳም ፡ ሚስት ፡ ስምዋ ፡ ቤተ ፡ ሱኤል ፡ ይባላል ፤ እርስዋም ፡ የከነዓን ፡ ሴት ፡ ናት ። የአምስተኛው ፡ የይሳኮር ፡ ሚስ ትም ፡ ስምዋ ፡ ሒዛቃ ፡ ይባላል ።
፴፮ የስድስተኛው ፡ የዛብሎን ፡ ምስትም ፡ ስምዋ ፡ አኤሚን ፡ ይባላል ። የሰባተኛው ፡ የዳን ፡ ሚስ ትም ፡ ስምዋ ፡ ኤግላ ፡ ይባላል ። የስምንተኛው ፡ የንፍታሌም ፡ ሚስት ፡ ስምዋ ፡ የመስጴጦምያ ፡ ሴት ፡ የምትሆን ፡ ራሱኡ ፡ ናት ።
፴፱ የዘጠኝኛው ፡ የጋድ ፡ ሚስትም ፡ ስምዋ ፡ ሚካ ፡ ይባላል ። የአሥረኛው ፡ የአሴር ፡ ሚስትም ፡ ስምዋ ፡ ኢዮና ፡ ይባላል ። የአሥራ ፡ አንደኛው ፡ የዮሴፍ ፡ ሚስትም ፡ ስምዋ ፡ አስኔት ፡ ይባላል ፤ ይህችውም ፡ የግብጽ ፡ ሴት ፡ ናት ።
፵ የአሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ የብንያምም ፡ ሚስት ፡ ስምዋ ፡ ኢዮሳክ ፡ ይባላል ። ስምዖንም ፡ ተመ ልሶ ፡ ከሶርያ ፡ እንደ ፡ ወንድሞቹ ፡ ሁለተኛ ፡ ሚስት ፡ አገባ ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፭ ።

፩ በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጀ መሪያው ፡ ሱባዔ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ርብቃ ፡ ልጅዋን ፡ ያዕቆብን ፡ ጠርታ ፡ በያዕቆብ ፡ ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ያከብራቸው ፡ ዘንድ ÷ ስለ ፡ ወንድሙና ፡ ስለ ፡ አባቱ ፡ አዘዘችው ።
፪ ያዕቆብም ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ክብር ፡ ጌት ነት ፡ ነውና ÷ አከብራቸውም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ፊት ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ እኔ ፡ ያዘ ዝሽኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ፡ አለ ።
፫ እናቴ ! ከአንቺም ፡ ከተወለድሁበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ ለሁሉ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ እንዳስብ ፡ ሥራዬን ፡ ሁሉ ÷ በልቤ ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ታውቂያለሽ ።
፬ ወንድሜንና ፡ አባቴን ፡ አከብር ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝ ሽኝን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ አላደርግም ? በእኔ ፡ ምን ፡ ጥመት ፡ አየሽብኝ ? እናቴ ÷ እስኪ ፡ ንገሪኝ ÷ እኔም ፡ ከእርሱ ፡ ፈጽሜ ፡ እርቃለሁ ፤ ይቅርታ ፡ ይደረግልኛል ፡ አላት ።
፭ ልጄ ! ባለ ፡ በዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ የቀና ፡ ሥራን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በአንተ ፡ ያየሁት ፡ ምንምን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ የለም ።
፮ ነገር ፡ ግን ፡ ልጄ ! እውነት ፡ ነገርን ፡ እነግርሃ ለሁ ። እኔ ፡ በዚህች ፡ ዓመት ፡ እሞታለሁ ። ከመቶ ፡ አምሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ እን ዳልኖር ፡ የምሞትባትን ፡ ቀን ፡ በሕልሜ ፡ አይ ቻለሁና ፡ ይህችን ፡ ዓመት ፡ በሕይወት ፡ አላል ፋትም ።
፯ እኖርበት ፡ ዘንድ ፡ ያለኝን ፡ ዘመኔን ፡ ሁሉ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ ፈጽሜአለሁ ፡ አለችው ። እናቱ ፦ እሞታለሁ ፡ ብላዋለችና ፡ ያዕቆብ ፡ ስለ ፡ እናቱ ፡ ነገር ፡ ሳቀ ።
፰ እርስዋ ፡ ግን ፡ በአንጻሩ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ፤ ኃይ ልም ፡ ነበራት ፡ እየወጣች ፡ እየገባች ፡ ታይ ፡ ነበ ርና ። ጕልበትዋም ፡ አልደከመም ፡ ነበር ÷ ጥር ስዋም ፡ ጽኑ ፡ ነበረ ፤ በሕይወት ፡ በኖረችበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ምንምን ፡ መከራ ፡ አላገኛትም ፡ ነበር ።
፱ ያዕቆብ ፦ ዘመኔ ፡ በሕይወት ፡ ወደ ፡ ኖርሽበት ፡ ዘመን ፡ ከቀረበ ፡ እናቴ ፡ እኔ ፡ ደግ ፡ ነኝ ፤ ኃይ ሌም ፡ እንደ ፡ አንቺ ፡ ኃይል ፡ እንዲህ ፡ በእኔ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤ ስለ ፡ ሞትሽ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ በዋዛ ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ትናገሪያለሽና ፡ አትሞ ቺም ፡ አላት ።
፲ ወደ ፡ ይስሐቅም ፡ ገብታ ፦ አንድ ፡ ልመናን ፡ እለምንሃለሁ ፤ የዔሳው ፡ ልቡ ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቃለህና ÷ በእ ርሱም ፡ ቸርነት ፡ የለምና ÷ ከሞትህ ፡ በኋላ ፡ እርሱ ፡ ይገድለው ፡ ዘንድ ፡ ይወዳልና ÷ በያዕ ቆብ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንዳያደርግ ÷ በጠብም ፡ አስወጥቶ ፡ እንዳይሰደው ፡ ዔሳውን ፡ አምለው ፡ አለችው ።
፲፩ ወንድሙ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ካራን ፡ ከሄደ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ያደረገውን ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፤ በፍጹም ፡ እንደ ፡ ተወን ፡ በእኛም ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንዳደ ረገ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፤ መንጋህን ፡ ሰበሰበ ÷ ገንዘብህንም ፡ ሁሉ ፡ ከፊትህ ፡ ቀምቶ ፡ ሄደ ።
፲፪ ገንዘባችንን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ስንለምነው ፡ እርሱ ፡ እንደሚመጸውተን ፡ ሰው ፡ ያደርገዋል ፤ ፍጹም ፡ ቅን ፡ የሚሆን ፡ ልጅህ ፡ ያዕቆብን ፡ ስለ ፡ መረቅኸው ፡ አንተን ፡ ይጠላሃል ።
፲፫ ከደግነት ፡ በቀር ፡ ክፋት ፡ የለውምና ፡ ከካራን ፡ ከመጣ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ምን ምን ፡ የጐደለብን ፡ የለም ፤ ሁሉን ፡ በየጊዜው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ያመጣልን ፡ ነበርና ÷ ያመጣል ንን ፡ ከእጁ ፡ በተቀበልን ፡ ጊዜ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ናው ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ነበር ÷ ያከብረንም ፡ ነበር ፤ ከካራንም ፡ ከመጣ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከእኛ ፡ አልተለየም ።
፲፬ እርሱም ፡ እየረዳን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ሁለጊዜ ፡ በቤት ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ አለችው ።
፲፭ ይስሐቅም ፦ እኔም ፡ አውቃለሁ ÷ እርሱ ፡ በፍ ጹም ፡ ልቡናው ፡ እንዲያከብረን ÷ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ያለ ፡ የያዕቆብን ፡ ሥራ ፡ አያለሁ ። ቀድሞ ፡ ከተ ወለደበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከያዕቆብ ፡ ይልቅ ፡ ዔሳውን ፡ እወደው ፡ ነበር ፤
፲፮ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከዔሳው ፡ ይልቅ ፡ ያዕቆብን ፡ እወዳ ለሁ ። ክፉ ፡ ሥራውን ፡ አብዝቶአልና ÷ ለእር ሱም ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የለውምና ÷ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ በደል ፡ ነውና ÷ በልቡናውም ፡ እው ነት ፡ ነገር ፡ የለውምና ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፲፯ አሁንም ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ልቡናዬ ፡
ያዝናል ። የአብርሃምን ፡ ፈጣሪ ፡ ትቶ ፡ ሚስቶ
ቹን ፡ ስለ ፡ ተከተለ ፡ ጣዖታቸውንም ፡ ስላመ
ለከ ፡ እርሱ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ስሕተታቸውን ፡
ስለ ፡ ተከተለ ፡ እነርሱ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከለ ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚጠፉ ፡ ናቸውና ፡ እርሱ ፡
ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ለመዳን ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ።
፲፰ አንቺ ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ ያዕቆብን ፡ እንዳይ
ገድል ፡ አምለው ፡ ዘንድ ፡ አምለው ፡ ትያለሽ ፤
ቢምልም ፡ በመሐላው ፡ ጸንቶ ፡ አይኖርም ፤
ከክፉ ፡ ነገር ፡ በቀር ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ አይሠራም ።
፲፱ ወንድሙን ፡ ያዕቆብንም ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡
ቢወድ ፡ በያዕቆብ ፡ እጅ ፡ ይወድቃል ። በእጁ ፡
ይወድቃልና ፡ በእጁ ፡ አያመልጥም ።
፳ ዔሳውን ፡ ከሚጠብቀው ፡ ጣዖት ፡ ያዕቆብን ፡
የሚጠብቀው ፡ እግዚአብሔር ፡ ገናና ፡ ኃይለኛ ፡
የከበረ ፡ የተመሰገነ ፡ ነውና ፡ አንቺም ፡ ስለ ፡
ያዕቆብ ፡ አትፍሪ ፡ አላት ።
፳፩ ርብቃም ፡ ልከ ፡ ዔሳውን ፡ ጠራችው ፡ ወደ ፡
እርስዋም ፡ መጣ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ÷ ከአንተ ፡ የም
ለምነው ፡ ልመና ፡ አለኝ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ÷ የምለ
ምንህን ፡ ታደርግልኝ ፡ ዘንድ ፡ እሺ ፡ በለኝ ፡
አለችው ።
፳፪ እርሱም ፡— ያልሽኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ÷
ልመናሽንም ፡ እንቢ ፡ አልልም ፡ አላት ። በሞ
ትሁ ፡ ጊዜ ፡ በአባትህ ፡ እናት ፡ በሣራ ፡ መቃ
ብር ፡ አቅራቢያ ፡ ትቀብረኝ ፡ ዘንድ ÷ ወንድ
ምህ ፡ ያዕቆብና ፡ አንተም ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡
ትፋቀሩ ፡ ዘንድ ÷
፳፫ ከፍቅር ፡ በቀር ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ በወንድሙ ፡
ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንዳያደርግ ÷ ልጆቼ ፡ በሥ
ራችሁ ፡ ትከናወኑ ፡ ዘንድ ÷ በዚህ ፡ ዓለምም ፡
ትከብሩ ፡ ዘንድ ÷ ጠላትም ፡ በእናንተ ፡ ደስ ፡
እንዳይለው ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ እለምናለሁ ፤
፳፬ በሚወዱአችሁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ለይቅር
ታና ፡ በረከት ፡ ትሆናላችሁ ፡ አለችው ።
፳፭ እኔም ፡ ያልሽኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ፡ በሞት
ሽም ፡ ጊዜ ፡ አጥንቶችሽ ፡ በአጥንቶችዋ ፡ አቅ
ራቢያ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አጥንቶችዋን ፡ እንደ ፡
ወደድሽ ፡ በአባቴ ፡ እናት ፡ በሣራ ፡ አቅራቢያ ፡
እቀብርሻለሁ ፤ ወንድሜ ፡ ያዕቆብንም ፡ ከሥ
ጋዊ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ እወደዋለሁ ።
፳፮ ከእርሱ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለእኔ ፡
ሌላ ፡ ወንድም ፡ የለኝም ፤ ወንድሜ ፡ ነውና ፡
በማኅፀንሽም ፡ መካከል ፡ አንድነት ፡ ተዘርተ
ናል ፤
፳፯ ከማኅፀንሽም ፡ አንድነት ፡ ወጥተናልና ፡ ብወ
ደው ፡ ይህ ፡ የሚደነቅልኝ ፡ አይደለም ፤ ወንድ
ሜን ፡ ያልወደድሁ ፡ ማን ፡ እወዳለሁ ?
፳፰ ስለ ፡ ልጆቼና ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ያዕቆብን ፡ ትመክ
ሪው ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ እለምንሻለሁ ፤
አባቴ ፡ ከመረቀው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እርሱን ፡
ገዥ ፡ እኔን ፡ ተገዥ ፡ አድርጎአልና ፡ በልጆቼ ፡
ላይና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንዲነግሥ ፡ አውቃለሁ ።

እኔ ፡ እንድወደው ፡ በሕይወት ፡ በኖርሁበት ፡ ፳፱
ዘመን ፡ ሁሉ ፡ መቼም ፡ መቼ ፡ ከበጎ ፡ ነገር ፡
በቀር ፡ በእርሱ ፡ ክፉ ፡ ነገርም ፡ እንዳልፈልግ ፡
እኔ ፡ እምልልሻለሁ ፡ አላት ።
ስለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ማለላት ፤ ያዕቆብንም ፡ ፴
በዔሳው ፡ ፊት ፡ ጠርታ ፡ ከዔሳው ፡ ጋር ፡ እንደ ፡
ተናገረችው ፡ ነገር ፡ አዘዘችው ።
እኔ ፡ ፈቃድሽን ፡ እፈጽማለሁ ፤ በወንድሜ ፡ ፴፩
በዔሳው ፡ ከእኔም ፡ ከልጆቼም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እን
ዳይወጣ ፡ መቼም ፡ መቼ ፡ ከፍቅር ፡ በቀር ፡ አስ
ቀድሜ ፡ እንዳልጣላ ፡ ተዋሽኝ ፡ አላት ። እርስ
ዋም ፡ ልጆችዋም ፡ በሉ ፡ ጠጡ ።
በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የሦስት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የአ ፴፪
ንድ ፡ ሱባዔ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ የምት
ሆን ፡ ርብቃ ፡ ሞተች ። በዚያችም ፡ ሌሊት ፡
ሁለቱ ፡ ልጆችዋ ፡ ሁሉ ፡ ያዕቆብና ፡ ዔሳው ፡
እጥፍነት ፡ በላት ፡ ዋሻ ፡ በአባታቸው ፡ እናት ፡
በሣራ ፡ መቃብር ፡ አጠገብ ፡ ቀበሩአት ።
በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ ይስ ፴፫
ሐቅ ፡ ሁለቱን ፡ ሁሉ ፡ ልጆቹን ፡ ያዕቆብና ፡ ዔሳ
ውን ፡ ጠራቸው ÷ ወደ ፡ እርሱም ፡ መጡ ።
ልጆቼ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ አባቶቼ ፡ በሄዱበት ፡ ጐዳና ፡ ፴፬
አባቶቼ ፡ በዚያ ፡ ለዘላለም ፡ ወደምኖርበት ፡
ወደ ፡ መቃብር ፡ እሄዳለሁ ፤ አብርሃም ፡ ለመቃ
ብር ፡ በገዛው ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ባስቆፈርሁት ፡
በኬጡ ፡ ሰው ፡ በኤፍሮን ፡ እርሻ ፡ ባለች ፡ እጥ
ፍነት ፡ በላት ፡ ዋሻ ፡ በአባቴ ፡ በአብርሃም ፡ አጠ
ገብ ፡ ቅበሩኝ ፡ አላቸው ።
ልጆቼ ፡ ሆይ ! እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ የነ ፴፭
ገረውን ÷ ለልጆቹም ፡ የነገራቸውን ፡ ሁሉ ፡
እግዚአብሔር ፡ ለእናንተ ፡ ሁሉን ፡ እንዲያደር
ግላችሁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የቀና ፡ ሥራና ፡ እው
ነት ፡ ሥራን ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ አዝዣች
ኋለሁ ።
ልጆቼ ፡ ሆይ ! ሰው ፡ ራሱን ፡ እንዲወድ ፡ እርስ ፡ ፴፮
በርሳችሁ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ እየወደዳችሁ ፡
ኑሩ ።
ሰው ፡ ለወንድሙ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ በሚያደርግ ፴፯
ለት ፡ ገንዘብ ፡ ሲፈልግ ÷ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በል
ቡናው ፡ አንድ ፡ ለመሆን ፡ ሲሻ ÷ እርስ ፡ በርሳ
ቸው ፡ እንደ ፡ ራሳቸው ፡ እንዲፋቀሩ ÷ እርስ ፡
በርሳችሁ ፡ የምትፋቀሩ ፡ ሁኑ ።
ስለ ፡ ጣዖቱም ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ አገዛችኋለሁ ፤ ለሚ ፴፰
ያመልኩአቸው ፡ በሚሰግዱላቸውም ፡ ሰዎች ፡
እነርሱ ፡ ስሕተትን ፡ የተመሉ ፡ ናቸውና ፡ ትን
ቁአቸው ፡ ዘንድ ፡ ትጠሉአቸውም ፡ ዘንድ ፡
እንዳትወዱአቸውም ፡ እኔ ፡ አገዛችኋለሁ ።
ልጆቼ ፡ ሆይ ! የአባታችሁን ፡ የአብርሃምን ፡ ፴፱
አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቡት ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ አመለክሁት ። በእውነት ፡ ፵
በእውቀት ፡ በሰፋ ፡ ልቡናም ፡ ተገዛሁለት ።
ያበዛችሁ ፡ ዘንድ ÷ ልጆቻችሁንም ፡ እንደ ፡
ሰማይ ፡ ከከብ ፡ ለማብዛት ፡ ያሳድግላችሁ ፡
ዘንድ ÷ ለዘላለም ፡ ለሚኖር ፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



የማይነቀል ፡ የእውነተኛ ፡ ተክል ፡ አድርጎ ፡
በምድር ፡ ይተክላችሁ ፡ ያጸናችሁ ፡ ዘንድ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ አስቡት ።
፴፩ አሁንም ፡ እኔ ፡ በጽኑ ፡ መሐላ ፡ አምላችኋለሁ ።
ከእርሱ ፡ የሚበልጥ ፡ በሌላ ÷ በተመሰገነ ÷ በክ
በረ ÷ ገናና ፡ በሆነ ÷ በተመሰገነ ፡ ድንቅ ፡ በሆነ ÷
ኃያል ፡ በሆነ ÷ ጽኑ ፡ በሆነ ÷ ምድርንና ፡ ሰማ
ይን ፡ በፈጠረ ÷ ሁሉን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ በያዘ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከመማል ፡ የሚበልጥ ፡
መሐላ ፡ የለምና ፡ የምትፈሩት ፡ የምታመል
ኩት ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አምላችኋለሁ ።
፴፪ አንዱም ፡ አንዱም ፡ በይቅርታና ፡ በቸርነት ፡
ወንድሙን ፡ እየወደደ ፡ የምትፈሩት ፡ የምታ
መልኩት ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አምላችኋለሁ ።
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ በሕይ
ወት ፡ በኖራችሁበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በሥራ
ችሁ ፡ ሁሉ ፡ ትከናወኑ ፡ ዘንድ ÷ እንዳትጠፉም ፡
ሰው ፡ በወንድሙ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ማድረግን ፡
አይውደድ ።
፴፫ ከእናንተ ፡ በወንድሙ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ያደርግ ፡
ዘንድ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በእጁ ፡ እንዲ
ወድቅ ÷ ከደጎነኞች ፡ ሰዎች ፡ አገርም ፡ ከዛሬ ፡
ጀምሮ ፡ እንዲጠፋ ፡ እወቁ ።
፴፬ ልጅም ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፤ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋል ፤
እግዚአብሔር ፡ በሚነድ ፡ በሚበላ ፡ እሳት ፡
ሰዶምን ፡ እንዳቃጠለ ፡ እንደዚሁ ፡ አገሩንና ፡
መንደሩን ፡ ያቃጥላል ። የእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ የሆ
ነውንም ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋል ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተግ
ሣጽ ፡ ከተጻፈበት ፡ መጽሐፍ ፡ ይጠፋል ።
፴፭ እርሱ ፡ የሚጠፋ ፡ ነውና ÷ ዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ ለሚ
ኖር ፡ ለእርግማንም ፡ የሚያልፍ ፡ ነውና ፡ በሕይ
ወት ፡ መጽሐፍም ፡ አይጻፍም ። በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡
ቍርጥ ፡ ፍርዳቸው ፡ በመርገምና ፡ በስድብ ፡
በቍጣና ፡ በቍጣ ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚ
ኖር ፡ ደዌና ፡ መቅሠፍት ፡ የታደሰ ፡ ይሆን ፡
ዘንድ ፡ እርሱ ፡ የሚጠፋ ፡ ነውና ፡ በሕይወት ፡
መጽሐፍ ፡ አይጻፍም ።
፴፮ ልጆቼ ፡ ሆይ ! በወንድሙ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ያደ
ርግ ፡ ዘንድ ፡ በሚወድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡
እንዲመጣ ÷ እንዲጠፋም ፡ እነግራችኋለሁ ፤
አዳኝባችኋለሁ ፡ አለ ።
፴፯ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ለሁ
ለቱ ፡ ሁሉ ፡ አደለ ፤ ጌትነትን ፡ አስቀድሞ ፡ ለተ
ወለደው ፡ ልጁ ፡ ሰጠ ። ግንቡንም ፡ በዙሪ
ያው ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ሰጠ ።
፴፰ አብርሃም ፡ በቤርሳቤህ ፡ ያጠራቀመውን ፡ ገን
ዘብ ፡ ሁሉ ፡ ሰጠው ። ይህንን ፡ ጌትነት ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ለተወለደው ፡ ልጅ ፡ ሰጠሁ ፡ አለ ።
፴፱ ዔሳውም ፡— ለያዕቆብ ፡ ብኵርናዬን ፡ ሸጥሁ
ለት ÷ ጌትነት ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ብኵርናዬን ፡
ለያዕቆብ ፡ ሰጠሁ ፤ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አለችና ፡
ስለ ፡ እርስዋ ፡ ምንምን ፡ የምናገረው ፡ ነገር ፡
የለኝም ፡ አለ ።
፵ ይስሐቅም ፡ አሳርፋችሁኛልና ÷ ስለ ፡ ማርጀ
ቴም ፡ ልቡናዬ ፡ አላዘነችምና ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡
በዚህች ፡ ቀን ፡ በልጆቻችሁና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡
በረከት ፡ ትደር ። ስለ ፡ እርስዋ ፡ ክፉ ፡ ሥራን ፡
እንዳትሠሩ ÷ በጎ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰውን ፡
ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያከብረው ፤ ልጁም ፡
እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፯ ።

፩ ይህን ፡ አገዘአቸውና ፡ መርቆአቸው ፡ ከጨ
ረሰ ፡ በኋላ ፡ በፊቱ ፡ አንድነት ፡ በሉ ፡ ጠጡ ።
፪ በመካከላቸው ፡ መተካከል ፡ ሆኖአልና ፡ ደስ ፡
አላቸው ። ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ÷ በዚያችም ፡
ቀን ፡ ዐርፈው ፡ ተኙ ።
፫ ይስሐቅም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ በአ
ልጋው ፡ ላይ ፡ ተኛ ፤ የዘላለም ፡ እንቅልፍንም ፡
አንቀላፋ ፤ ሞተ ።
፬ የመቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ሞተ ።
ሀያ ፡ አምስት ፡ ሱባዔና ፡ አምስት ፡ ዓመትን ፡
ጨረሰ ። ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ ልጆቹ ፡ ያዕቆብና ፡
ዔሳው ፡ ቀበሩት ።
፭ ዔሳውም ፡ በኤዶምያስ ፡ አውራጃ ፡ ወዳለች ፡
ወደ ፡ ሴይር ፡ ሄደ ÷ በዚያም ፡ ኖረ ።
፮ ያዕቆብም ፡ አባቱ ፡ አብርሃም ፡ ተሰዶ ፡ ይኖር
በት ፡ በነበረ ፡ በኬብሮን ፡ አውራጃ ፡ ባለ ፡
ግምብ ፡ ኖረ ።
፯ እንደ ፡ ተወለደበት ፡ ወራት ፡ እንደሚታየው ፡
ትእዛዝ ፡ አድርጎ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናው ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ አመሰገነው ።
፰ በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ሚስቱ ፡
ልያ ፡ ሞተች ። በአባቱ ፡ እናት ፡ በሣራ ፡ መቃ
ብር ፡ ግራ ፡ በእናቱ ፡ በርብቃ ፡ መቃብር ፡ አጠ
ገብ ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ በሆነች ፡ ዋሻ ፡ ቀበራት ።
፱ ልጆቹና ፡ ልጆችዋ ፡ ሁሉ ፡ ለሚስቱ ፡ ለልያ ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያለቀሱላት ፡ ዘንድ ፡ ያለቅስላት ፡
ነበርና ፡ ስለ ፡ እርስዋም ፡ ያረጋጉት ፡ ዘንድ ፡
መጡ ። በሥራዋ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽማ ፡ ቅን ፡ ስለ ፡
ሆነች ፡ እኅትዋ ፡ ራሔል ፡ ከሞተች ፡ ጀምሮ ፡
ፈጽሞ ፡ ይወዳት ፡ ነበርና ፡ ያረጋጉት ፡ ዘንድ ፡
መጡ ።
፲ ያዕቆብንም ፡ ታከብረው ፡ ነበርና ÷ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ በኖረችበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ከአፍዋ ፡ አልሰማምና ÷ የዋህ ፡ ነበረችና ÷
ፍቅር ፡ ያላት ፡ ቅንነት ፡ ያላት ፡ ክብር ፡ ያላት ፡
ነበረችና ።
፲፩ በሕይወት ፡ ሳለች ፡ የሠራችውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
ያስብ ፡ ነበር ። በፍጹም ፡ ሰውነቱና ፡ በፍጹም ፡
ልቡናው ፡ ፈጽሞ ፡ ይወዳት ፡ ነበርና ፡ ያለቅስ
ላት ፡ ነበር ።
፲፪ የዔሳውና ፡ የያዕቆብ ፡ አባት ፡ ይስሐቅ ፡ በሞተ
በት ፡ ቀን ፡ የዔሳው ፡ ልጆች ፡ ይስሐቅ ፡ ለታ
ናሹ ፡ ልጁ ፡ ለያዕቆብ ፡ አለቅነቱን ፡ እንደ ፡
ሰጠው ፡ ሰሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ፈጽመውም ፡ ተቈጡ ፤ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ሳለህ ፡
ያዕቆብ ፡ የአንተ ፡ ታናሽ ፡ ሲሆን ÷ አባትህ ፡
አንተን ፡ ትቶ ፡ ለያዕቆብ ፡ አለቅነትን ፡ ለምን ፡
ሰጠው ? ብለው ፡ ከአባታቸው ፡ ጋር ፡ ተከራ
ከሩ ።
፲፬፤ እኔ ፡ ብኵርናዬን ፡ በትንሽ ፡ ምስር ፡ ንፍሮ ፡ ሽጪ
ለሁና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ አላቸው ።
፲፭፤ በልቶ ፡ ሊመርቀኝ ፡ አድኜ ፡ አመጣለት ፡ ዘንድ ፡
አባቴ ፡ በላከኝ ፡ ቀን ፡ በተንኰል ፡ መጥቶ ፡ የሚ
በላውንና ፡ የሚጠጣውን ፡ ለአባቴ ፡ አቀረበ ።
አባቴም ፡ መረቀው ÷ እኔን ፡ ለእርሱ ፡ ተገዥ ፡
አደረገኝ ።
፲፮፤ አሁንም ፡ ወንድም ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ በክፉ ፡
ነገር እንዳንፈላለግ ÷ ወንድም ፡ ከወንድሙ ፡
ጋር ፡ በፍቅር ፡ ጸንተን ፡ እንድንኖር ÷ ሥራች
ንንም ፡ እንዳናጠፋ ÷ አባታችን ፡ እኔና ፡ እር
ሱን ፡ አማለን ፡ አላቸው ።
፲፯፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ፍቅርን ፡ ለማድረግ ፡ አንሰማህም ፤
ከእርሱ ፡ ኃይል ፡ የእኛ ፡ ኃይል ፡ ይጸናልና ÷
እኛም ፡ ከእርሱ ፡ እንበረታለንና ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
ሄደን ፡ እንገድለዋለን ÷ ልጆቹንም ፡ እንገድላ
ለን ፡ አሉት ። ከእኛ ፡ ጋር ፡ ካልሄድህ ፡ በአን
ተም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እናደርግብሃለን ።
፲፰፤ አሁንም ፡ ስማን ፤ ወደ ፡ ፍልስጥኤምና ፡ ወደ ፡
አራም ፡ ወደ ፡ አሞንና ፡ ወደ ፡ ሞዓብ ፡ ልከን ፡
በሰልፍ ፡ የሚመክቱ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎችን ፡
ለራሳችን ፡ እንምረጥ ፤
፲፱፤ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሄደን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንዋጋ ፤
ኃይል ፡ ሳያደርግ ፡ እናጥፋው ፡ አሉት ።
፳፤ አባታቸውም ፡— አትሂዱ ÷ በፊቱ ፡ እንዳት
ጠፉ ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ጠብን ፡ አታድርጉ ፡ አላ
ቸው ።
፳፩፤ ከልጅነትህ ፡ ጀምሮ ፡ ሥራህ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነውን ?
አንተ ፡ አንገትህን ፡ ወደ ፡ ቀንበሩ ፡ አገዛዙ ፡ ታገ
ባለህ ፤ እኛስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አንሰማም ፡ አሉት ።
፳፪፤ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወዳጅ ፡ ወደ ፡ አዱራምና ፡
ወደ ፡ አራም ፡ ልከው ፡ የተመረጡ ፡ አርበኞች
ንና ፡ ጠበኞች ፡ የሚሆኑ ፡ ሺህ ፡ ሰዎችን ፡ ከእ
ነርሱ ፡ ጋር ፡ ተወዳጁ ።
፳፫፤ ከተወዳጁአቸው ፡ ከአሞን ፡ ልጆችና ፡ ከሞዓብ ፡
ልጆች ፡ የተመረጡ ፡ ሺህ ፡ አርበኞች ፤
፳፬፤ ከፍልስጥኤም ፡ የተመረጡ ፡ ሺህ ፡ አርበኞች ፤
፳፭፤ ከኰራውስና ፡ ከኤዶምም ፡ የተመረጡ ፡ ሺህ ፡
አርበኞች ፤
፳፮፤ ከኬጤዎንም ፡ ጽኑዓን ፡ የሆኑ ፡ አርበኞች ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ መጡ ።
፳፯፤ አባታቸውንም ፡— መጥተህ ፡ ምራቸው ፤ ይህ ፡
ካልሆነ ፡ እንገድልሃለን ፡ አሉት ። ወደ ፡ ወን
ድሙ ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ሊመራቸው ፡ ይሄድ ፡
ዘንድ ፡ ልጆቹ ፡ እንደ ፡ ተበራቱበት ፡ ልጆቹን ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ቍጣን ፡ ተመላ ።
፳፰፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በልቡ ፡ የተሰወረ ፡ ክፋትን ፡ ሁሉ ፡
በወንድሙ ፡ በያዕቆብ ፡ አሰበ ። ነገር ፡ ግን ፡ ባለ ፡
ዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በወንድሙ ፡ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡
ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንዳይፈልግ ፡ ለእናቱና ፡ ለአ
ባቱ ፡ የማለውን ፡ መሐላ ፡ አላሰበም ።
ያዕቆብ ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ፳፱፤
እንዲመጡ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አላወቀም ። እርሱ ፡
ግን ፡ ለሚስቱ ፡ ለልያ ፡ ያዝን ፡ ነበር ፤ ከተመ
ረጡ ፡ ከአራት ፡ ሺህ ፡ አርበኞች ፡ ጠበኞች ፡
ጋር ፡ በግምቡ ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እስኪ
ቀርቡ ፡ ድረስ ፡ አላወቀም ።
የኬብሮን ፡ ሰዎች ፡— እነሆ ÷ ወንድምህ ፡ ይዋ ፴፤
ጋህ ፡ ዘንድ ፡ ሰይፍ ፡ ከታጠቁ ÷ ጋሻቸውንና ፡
ጦራቸውን ፡ ከያዙ ፡ ከአራት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡
ጋር ፡ መጣ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ላኩ ።
ከዔሳው ፡ ይልቅ ፡ ያዕቆብን ፡ ይወዱት ፡ ነበርና ÷ ፴፩፤
ያዕቆብ ፡ ለጋስ ፡ ነበረና ÷ ከዔሳው ፡ ይልቅ ፡ ቸር ፡
ነበረና ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ያዕቆብ ፡
ግን ፡ ወደ ፡ ግምቡ ፡ አጠገብ ፡ እስኪቀርቡ ፡
ድረስ ፡ የነገሩትን ፡ አላመነም ። የግምቡን ፡ በር ፡
ዘጋ ።
በግምቡም ፡ ላይ ፡ ቆመ ÷ ከወንድሙም ፡ ከዔ ፴፪፤
ሳው ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ፡— ሚስቴ ፡ ስለ ፡ ሞተች ፡
በበጎ ፡ ማረጋጋት ፡ ታረጋጋኝ ፡ ዘንድ ፡ መጣህን ?
እናትህና ፡ አባትህ ፡ ሳይሞቱ ፡ ዳግመኛ ፡ ፈጥ ፴፫፤
ነህ ፡ የማልኸው ፡ መሐላ ፡ ይህ ፡ ነውን ?
ከማልኸው ፡ መሐላ ፡ ወጥተህ ፡ በደልህ ÷ ለአባ ፴፬፤
ትህ ፡ በማልህበት ፡ ጊዜ ፡ ተፈረደብህ ፡ አለው ።
ዔሳውም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መለሰ ።
ለምድር ፡ አራዊትና ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ እንዳይ ፴፭፤
ጣሉ ፡ በእውነት ፡ የተማማሉት ፡ መሐላ ፡ እስከ ፡
ዘላለም ፡ ድረስ ፡ የላቸውም ።
እየነጋ ፡ ይህ ፡ ለዚህ ፡ ክፋት ፡ ይፈልጋል ። አን ፴፮፤
ዱም ፡ አንዱም ፡ የጊዜውን ፡ የዘገየውን ፡ ጠላ
ቱን ፡ ይፈልጋል ።
አንተም ፡ እኔን ፡ ከልጆቼ ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ፴፯፤
ድረስ ፡ ትጠላኛለህ ፤ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ወንድማ
ማችነት ፡ የለንም ። እኔ ፡ የምነግርህን ፡ ይህንን ፡
ነገሬን ፡ ስማ ። እሪያ ፡ ጠጕሩንና ፡ ቁርበቱን ፡
እንደ ፡ ብዝት ፡ ቢለውጥ ÷
እንደ ፡ በግና ፡ እንደ ፡ ዋልያም ፡ ቀንድ ፡ በራሱ ፡ ፴፰፤
ላይ ፡ ቀንድ ፡ ቢወጣ ÷ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡
ወንድማማች ፡ እንሆናለን ።
ጡቶች ፡ ከእናታቸው ፡ ቢለዩ ፡ ወንድም ፡ በሆ ፴፱፤
ንኸኝ ፡ ነበር ። ተኵላዎችም ፡ እንዳይበሉአቸው ፡
እንዳይነጣጠቁአቸውም ፡ ከበጎች ፡ ጋር ፡ ፍቅ
ርን ፡ ቢያደርጉ ፡ ልቡናቸውም ፡ ለእነርሱ ፡ በጎ ፡
ነገርን ፡ ለማድረግ ፡ ቢያስብ ÷
ያን ፡ ጊዜ ፡ በልቡናዬ ፡ ለአንተ ፡ ፍቅር ፡ ይደ ፵፤
ረጋል ። አንበሳ ፡ ለላም ፡ ወዳጁ ፡ ቢሆን ÷ ከእ
ርሱም ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ ቀንበር ፡ ቢጠመድ ፡ ከእ
ርሱም ፡ ጋር ፡ ቢያርስ ÷ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ፍቅ
ርን ፡ ቢያደርግ ÷ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ፍቅ
ርን ፡ አደርጋለሁ ።
ቍራዎችም ፡ እንደ ፡ ሳቢሳ ፡ ቢነጡ ÷ እንደ ፡ ፵፩፤
ወደድሁህ ÷ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ፍቅርን ፡ እን
ዳደረግሁ ÷ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ አንተ ፡

ትጠፋለህ ፥ ልጆችህም ፡ ይጠፋሉ ። ለአንተ ፡
ፍቅር ፡ አንድነት ፡ አይደረግልህም ።
፳፪፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ያዕቆብ ፡ በእርሱ ፡ ልቡናውን ፡ እን
ዳስጨከነ ፥ ይገድለውም ፡ ዘንድ ፡ በፍጹም ፡
ልቡናው ፡ እንዳሰበ ፡ አየ ።
፳፫፤ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ወደሚገድለው ፡ ሰው ፡ እሪያ ፡
ፈጥኖ ፡ እንዲወጣ ፥ ከእርሱም ፡ እንዳይሸሽ ፥
ዔሳው ፡ ፈጥኖ ፡ ወጣ ።
፳፬፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ባሪያዎቹንና ፡ ወገኖቹን ፡ ወዳጆ
ቹንም ፡ ሁሉ ፡ ይከቡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።
፳፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይሁዳ ፡ አባቱን ፡ ያዕቆብን ፡ ተና
ገረው ፡— አባቴ ፡ ሆይ ፥ ቀስትህን ፡ሳብ ፥ ፍላጻ
ህንም ፡ ወርውረህ ፡ ጠላትህን ፡ ውጋ ፤ ጠላት
ህን ፡ ግደል ።
፳፮፤ እኛ ፡ ወንድምህን ፡ እንገድልምና ፥ እርሱም ፡
በአንተ ፡ ዘንድ ፡ አለና ፡ ይመስልሃልና ፥ በእ
ኛም ፡ ዘንድ ፡ ለመከበር ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነውና ፡
ኃይል ፡ ለአንተ ፡ ይሁን ፡ አለው ።
፳፯፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያዕቆብ ፡ ቀስቱን ፡ ስቦ ፡ ፍላጻውን ፡
ወርውሮ ፡ ወንድሙን ፡ ዔሳውን ፡ ወግቶ ፡ ገደ
ለው ።
፳፰፤ ዳግመኛም ፡ ፍላጻውን ፡ ወርውሮ ፡ የአሕዛብ ፡
ወገን ፡ የሚሆን ፡ አዱራንን ፡ የግራ ፡ ጡት ፡
ሥሩን ፡ ወጋው ፤ አሳዶ ፡ ገደለው ።

ምዕራፍ ፡ ፴፰ ።

፩፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
ባሪያዎቻቸውም ፡ ተከፍለው ፡ በግምቡ ፡ ዙሪያ ፡
በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ወጡ ።
፪፤ ይሁዳ ፡ በፊት ፡ ወጣ ፡ ጋድና ፡ ንፍታሌምም ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወጡ ፤ አምሳ ፡ ብላቴኖችም ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ነበሩ ። በግምቡ ፡ ግራ ፡ አንጻር ፡
ወጥተው ፡ በፊታቸው ፡ ያገኙትን ፡ ሁሉ ፡ ገደሉ ።
ከእነርሱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ ያመለጠ ፡
የለም ።
፫፤ ዳንና ፡ ሌዊ ፡ አሴርም ፡ በግምቡ ፡ ምሥራቅ ፡
አንጻር ፡ ወጡ ፤ አምሳ ፡ ብላቴኖችም ፡ ከእነርሱ ፡
ጋር ፡ ነበሩ ፡ የአሞንና ፡ የሞዓብን ፡ አርበኞች ፡
ወጉ ።
፬፤ ይሳኮርና ፡ ሮቤል ፡ ዛብሎንም ፡ በግምቡ ፡ ቀኝ ፡
አንጻር ፡ ወጡ ፡ አምሳ ፡ ብላቴኖችም ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ ነበሩ ፤ የፍልስጥኤምን ፡ አርበኞች ፡ ወጉ ።
፭፡ ብንያምና ፡ ስምዖን ፡ የሮቤል ፡ ልጅ ፡ ሄናክ ፡
በግምቡ ፡ ምዕራብ ፡ አንጻር ፡ ወጡ ። አምሳ ፡
ብላቴኖችም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ። ከኮሬዎ
ንና ፡ ከኤዶም ፡ ጽኑዓን ፡ አርበኞች ፡ የሚሆኑ ፡
አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ። ስድስት ፡ መቶ ፡
ሰዎች ፡ ሸሹ ፤ አራቱ ፡ የዔሳው ፡ ልጆችም ፡ ከእ
ነርሱ ፡ ጋር ፡ ሸሹ ።
፮፤ አባታቸው ፡ በከረብታው ፡ ላይ ፡ ሞቶ ፡ እንደ ፡
ወደቀ ፡ ትተውት ፡ ሸሹ ። ይህችውም ፡ በአዱ
ራም ፡ ያለች ፡ ከረብታ ፡ ናት ፤ የያዕቆብም ፡
ልጆች ፡ በኋላቸው ፡ ተከትለው ፡ እስከ ፡ ሴይር ፡
ተራራ ፡ ድረስ ፡ አሳደዱአቸው ።
ያዕቆብ ፡ ግን ፡ በአዱራም ፡ ባለች ፡ ከረብታ ፡ ፯፤
ወንድሙን ፡ ቀብሮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።
የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ የዔሳውን ፡ ልጆች ፡ በሴይር ፡
ተራራ ፡ አስጨነቁአቸው ።
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ፍቅርን ፡ ያደርጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፰፤
ይወጉአቸውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡
ላኩ ።
ከእነርሱ ፡ ፍቅርን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ያዕቆብ ፡ ፱፤
ወደ ፡ ልጆቹ ፡ ላከ ፤ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ፍቅር ፡
አንድነትን ፡ አድረጉ ።
በለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቹና ፡ ለያዕቆብ ፡ ፲፤
ይገብሩ ፡ ዘንድ ፡ የመገዛት ፡ ቀንበርን ፡ በእነ
ርሱ ፡ ላይ ፡ አኖሩ ፤ አገዛዝ ፡ አጸኑባቸው ።
ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ እስከሚወርድበት ፡ ቀን ፡ ፲፩፤
ድረስ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሲገብሩ ፡ ኖሩ ፤ የኤዶም ፡
ልጆች ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ከሠሩት ፡ ከመገዛት ፡ ግብር ፡
እስከዚያች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አላጐደሉም ።
እስከዚያች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፲፪፤
ንጉሥ ፡ ሳይነግሥ ፡ በኤዶምያስ ፡ የነገሡ ፡ ነገ
ሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።
በኤዶምያስ ፡ የቢዖር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡ ነገሠ ፤ የአ ፲፫፤
ገሩም ፡ ስም ፡ ዲናባ ፡ ይባላል ፤ ባላቅም ፡ ሞተ ።
ስለ ፡ እርሱም ፡ ፋንታ ፡ ከባሶር ፡ ወገን ፡ የሚ ፲፬፤
ሆን ፡ የዛራ ፡ ልጅ ፡ ዮባብ ፡ ነገሠ ። የዛራ ፡ ልጅ ፡
ዮባብም ፡ ሞተ ። ስለ ፡ እርሱም ፡ ፋንታ ፡ ከቴ
ማን ፡ አገር ፡ የተወለደ ፡ አሳም ፡ ነገሠ ። አሳ
ምም ፡ ሞተ ።
ስለ ፡ እርሱም ፡ ፋንታ ፡ በሞዓብ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ፲፭፤
የምድያምን ፡ ሰዎች ፡ የወጋ ፡ የበረድ ፡ ልጅ ፡
አዶታ ፡ ነገሠ ፤ የአገሩ ፡ ስም ፡ አውአት ፡ ይበ
ላል ። አዶታም ፡ ሞተ ።
ስለ ፡ እርሱም ፡ ፋንታ ፡ ከአሚሴት ፡ የተወለደ ፡ ፲፮፤
ሰልማን ፡ ነገሠ ። ሰልማን ፡ ሞተ ። ስለ ፡ እር
ሱም ፡ ፋንታ ፡ ሮብአት ፡ ከሚባል ፡ ወንዝ ፡
የመጣ ፡ ሳኦል ፡ ነገሠ ፤ ሳኦል ፡ ሞተ ። ስለ ፡
እርሱም ፡ ፋንታ ፡ የአክቡር ፡ ልጅ ፡ ብዑሉናን ፡
ነገሠ ፤ የአክቡር ፡ ልጅ ፡ ብዑሉናን ፡ ሞተ ።
ስለ ፡ እርሱም ፡ ፋንታ ፡ አዶታ ፡ ነገሠ ፡ የሚስቱ ፡ ፲፯፤
ስም ፡ ማየ ፡ ጠቢት ፡ ይባላል ፤ ይህችውም ፡
የመጥሪት ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ ይኸውም ፡ የዘአብ ፡
ሰው ፡ የሚሆን ፡ የመትቤድ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በኤ
ዶምያስ ፡ አገር ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ።
ያዕቆብም ፡ አባቱ ፡ ተሰዶ ፡ በኖረበት ፡ በያዕ ፲፰፤
ቆብ ፡ ዘመዶች ፡ አገር ፡ በከነዓን ፡ ኖረ ።
ዮሴፍ ፡ ግን ፡ የአሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ፲፱፤
ነበረ ። ወንድሞቹ ፡ ከሸጡት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡
ግብጽ ፡ አወረዱት ። የፈርዖን ፡ ባለምዋል ፡ የአ
ዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ፋጢፋራን ፡ ገዛው ። ዮሴፍን ፡
በቤቱ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።
ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ ደግነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ ፳፤
በግብጽ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ አደረች ። እግዚአብሔ
ርም ፡ የሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ያቀናለት ፡ ነበር ።

፳፩፤ የግብጹም ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዮሴፍ ፡
ጋር ፡ በረድኤት ፡ እንዳለ ÷ የሠራውንም ፡ ሥራ ፡
ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያቀናለት ፡ አይቶ
አልና ፡ ሁሉን ፡ በፊቱ ፡ ተወ ።
፳፪፤ ዮሴፍ ፡ ግን ፡ መልኩ ፡ ያማረ ፡ እጅግ ፡ ደመ ፡
ግቡ ፡ ነበረ ።
፳፫፤ የጌታውም ፡ ሚስት ፡ ዓይኖችዋን ፡ አቅንታ ፡
ዮሴፍን ፡ አየችው ። ወደደችው ፤ ይደርስባ
ትም ፡ ዘንድ ፡ ለመነችው ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ ሰውነ
ቱን ፡ አልሰጣትም ።
፳፬፤ እግዚአብሔርንም ፡ አሰበው ፤ ባል ፡ ባላት ፡
ሴት ፡ ማንም ፡ ማን ፡ ሰው ፡ እንዳይሴስን ፡ ከአ
ብርሃም ፡ ቃል ፡ አግኝቶ ፡ አባቱ ፡ ያዕቆብ ፡ የተ
ናገራቸውን ፡ ነገሮች ፡ አሰበ ። በሰማይ ፡ ልዑል ፡
በሆነ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ የሞት ፡ ቅጣ
ትም ፡ እንዳለበት ፡ አሰበ ። ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡
የእርሱ ፡ ኃጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለዘ
ላለም ፡ በመጽሐፍ ፡ እንድ ፡ ትጻፍ ፡ የነገረውን ፡
አሰበ ።
፳፭፤ ዮሴፍም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ በእርስዋ ፡ ይደ
ርስ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፤ አንድ ፡ ዓመት ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ አባበለችው ፤ መስማትን ፡ እንቢ ፡
አላት ።
፳፮፤ እርስዋ ፡ ግን ፡ ይደርስባት ፡ ዘንድ ፡ ልትጣላው ፡
በቤት ፡ አስጨንቃ ፡ ያዘችው ፤ የቤትዋንም ፡
ደጃፍ ፡ ዘጋች ፤ በገሃድ ፡ ያዘችው ፤ እርሱ ፡ ግን ፡
ከእጅዋ ፡ አመለጠ ፤ ልብሱን ፡ በእጅዋ ፡ ተወ
ላት ÷ ሳንቃውንም ፡ ሰብሮ ፡ ከፊትዋ ፡ ወደ ፡
ውጭ ፡ ሸሸ ።
፳፯፤ ያቺም ፡ ሴት ፡ በእርስዋ ፡ እንዳይደርስባት ፡
ባየች ፡ ጊዜ ፡— የምትወደው ፡ ይህ ፡ ዕብራዊ ፡
ባሪያህ ፡ ይደርስብኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፡ ብላ ፡ በጌ
ታው ፡ ፊት ፡ አጣላችው ።
፳፰፤ ቃሌን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ በጮኽሁ ፡ ጊዜ ፡
ልብሱን ፡ በእጄ ፡ ትቶልኝ ፡ ሸሸ ፤ በያዝሁትም ፡
ጊዜ ፡ ሳንቃውን ፡ ሰብሮ ፡ ሄደ ፡ አለችው ።
፳፱፤ የግብጹም ፡ ሰው ፡ የዮሴፍን ፡ ልብስ ÷ የተሰበ
ረውንም ፡ መዝጊያ ፡ አየ ፤
፴፤ የሚስቱንም ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ዮሴፍን ፡ ንጉሥ ፡
ያሰራቸው ፡ እስረኞች ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ እስር ፡
ቤት ፡ አገባው ።
፴፩፤ በዚያም ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ኖረ ። እግዚአብሔ
ርም ፡ ለዮሴፍ ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ጠባቂዎች ፡ አለቃ ፡
ፊት ፡ መወደድንና ፡ ይቅርታን ፡ ሰጠው ። እግ
ዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንዳለ ÷
የሠራውንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲያቀናለት ፡ አይቶአልና ፡ በፊቱ ፡ ሁሉን ፡
ተወለት ።
፴፪፤ ዮሴፍ ፡ ሁሉን ፡ ያደርግ ፡ ነበርና ÷ እግዚአብሔ
ርም ፡ ይፈጽምለት ፡ ነበርና ፡ የእስር ፡ ቤት ፡ ጠባ
ቂዎች ፡ አለቃ ፡ ያለ ፡ እርሱ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚ
ያውቀው ፡ አልነበረም ። በዚያም ፡ ሦስት ፡
ዓመት ፡ ተቀመጠ ።
፴፫፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡
በሁለቱ ፡ ባለምዋሎቹ ፡ በእንጀራ ፡ አሳላፊዎች ፡
አለቃና ፡ በጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡
ተቈጣ ። ዮሴፍ ፡ ተይዞ ፡ በዚያ ፡ በታሰረበት ፡
በእንጀራ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ቤት ፡ በእስ
ራት ፡ አኖራቸው ።
በፊታቸው ፡ ይላላክቸው ፡ ዘንድ ÷ በፊቱም ፡ ፴፬፤
ይላላከው ፡ ዘንድ ፡ የእስረኞች ፡ አለቃ ፡ ዮሴ
ፍን ፡ ሾመው ።
ሁለቱም ፡ ሁሉ ፡ የእንጀራ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለ ፴፭፤
ቃና ፡ የጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ሕልም ፡
አዩ ። ለዮሴፍ ፡ ነገሩት ፤ እንደ ፡ ተረጐመላቸው ፡
እንደዚሁ ፡ ሆነላቸው ።
የጠጅ ፡ አሳላፊዎችን ፡ አለቃ ፡ ፈርዖን ፡ ወደ ፡ ፴፮፤
ሥራው ፡ መለሰው ፤ የእንጀራ ፡ አሳላፊዎችን ፡
አለቃ ፡ ግን ፡ ገደለው ፤ ዮሴፍ ፡ እንደ ፡ ተረጐ
መላቸው ።
የጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚሆነ ፴፯፤
ውን ፡ ነግሮታልና ፡ ዮሴፍን ፡ በእስራቱ ፡ ቤት ፡
ረሳው ። ዘንግቶአልና ፡ ዮሴፍ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡
ለፈርዖን ፡ ይነግረው ፡ ዘንድ ፡ አላሰበም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

በዚያም ፡ ወራት ፡ ፈርዖን ፡ በአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ፩፤
ስለሚደረገው ፡ ራብ ፡ ነገርና ፡ ስለ ፡ ጥጋብ ፡
ነገር ፡ በአንዲት ፡ ሌሊት ፡ ሁለት ፡ ሕልም ፡ አየ ።
ከእንቅልፉ ፡ ነቃ ፤ በግብጽ ፡ ያሉ ፡ ሕልም ፡ የሚ ፪፤
ተረጕሙትን ፡ ሁሉ ÷ ጠበል ፡ የሚረጩትንም ፡
ጠርቶ ፡ ሁለቱን ፡ ሁሉ ፡ ሕልሙን ፡ ነገራቸው ፤
ነገር ፡ ግን ፡ መተርጐም ፡ አልተቻላቸውም ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ዮሴ ፫፤
ፍን ፡ አሰበው ÷ የእርሱንም ፡ ነገር ፡ በንጉሥ ፡
ዘንድ ፡ ተናገረ ።
ከእስር ፡ ቤት ፡ አወጡት ። ሁለቱን ፡ ሁሉ ፡ ሕል ፬፤
ሙን ፡ በፊቱ ፡ ተናገረ ።
ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ ሕልሞቹ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ፭፤
በፈርዖን ፡ ፊት ፡ ተናገረ ።
በግብጽ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ጥጋብ ፡ የሚደረግበት ፡ ፮፤
ሰባት ፡ ዓመት ፡ ይመጣል ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በአ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ የሆነ ፡ የሌለ ፡ ሰባት ፡
ዓመት ፡ ራብ ፡ ይመጣል ፡ አለው ።
አሁንም ፡ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለፈርዖን ፡ ፯፤
ጎተራ ፡ ይሥሩ ፤ ጥጋብ ፡ በሆነበት ፡ ዘመን ፡
ወራት ፡ በአገር ፡ የተገኘውን ፡ እህል ፡ ለአገር ፡
ምግብ ፡ ሊሆን ፡ ያኑሩት ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ራብ ፡
ለሚሆንበት ፡ ዘመን ፡ ምግብ ፡ ይሆናል ፤ ራቡ ፡
እጅግ ፡ የጸና ፡ ይሆናልና ፡ ከራብ ፡ ጽናት ፡ የተ
ነሣ ፡ አገር ፡ አትጠፋም ፡ አለው ።
እግዚአብሔርም ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ ለዮሴፍ ፡ ፰፤
ባለምዋልነትንና ፡ ቸርነትን ፡ ሰጠው ።
ፈርዖንም ፡ ሹማምቶቹን ፡— መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፱፤
አድሮበታልና ፡ እንደዚህ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ብልህ ፡
አዋቂ ፡ ሰው ፡ አናገኝም ፡ አላቸው ።
ዳግመኛም ፡ በግዛቱ ፡ ላይ ፡ ሾመው ፡ የግብጽ ፲፤
ንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ አስገዛው ÷ ዳግመኛም ፡

በሰረገላው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ፤ የነጭ ፡
ሐር ፡ ቀሚስ ፡ አለበሰው ፡ በአንገቱም ፡ የወርቅ ፡
ዝርግፍ ፡ አሰረለት ።
፲፩፡ ኤል ፡ ኤል ፡ አብሬር ፡ ብሎ ፡ በፊቱ ፡ አዋጅ ፡ ነገ
ረለት ፤ ብሬያ ፡ ጌታ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በእ
ጁም ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቱን ፡ አደረገለት ፡ በቤቱ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ አሠለጠነው ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረ
ገው ። ከዙፋኔ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ከአንተ ፡ የምበ
ልጥህ ፡ የለም ፡ አለው ።
፲፪፡ ዮሴፍም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሠለጠነ ፤ የፈ
ርዖን ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ሹማምንቱም ÷ የንጉ
ሡን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ሁሉ ÷ በቅንነት ፡ ጸንቶ ፡
ይኖሩልና ÷ ትዕቢትም ፡ የለውምና ÷ ልቡን ፡
ማነሣት ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ መማለጃንም ፡ መቀ
በል ፡ የለውም ፡ ነበርና ፡ ወደዱት ። በግብጽ ፡
ላሉ ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ይፈርድላ
ቸው ፡ ነበርና ።
፲፫፡ የግብጽ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ ደግነት ፡ በፈርዖን ፡
ፊት ፡ ተስማምታ ፡ ኖረች ። እግዚአብሔር ፡ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡ አለና ፡ በፈርዖን ፡ ዘመ
ዶች ፡ ሁሉ ፡ በሚያውቁት ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡
ፊት ÷ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ በሚቈጣጠሩት ፡ ሰዎ
ችም ፡ ፊት ፡ በለምዋልነትንና ፡ ይቅርታን ፡
ሰጠው ። የፈርዖንም ፡ መንግሥት ፡ ቀናች ። በለ
ጋራ ፡ አልነበረም ፡ ክፉ ፡ ነገርም ፡ አልነበረም ።
፲፬፡ ንጉሥም ፡ የዮሴፍን ፡ ስም ፡ ሰፍንጢፉንስ ፡
አለው ። ለዮሴፍ ፡ ሚስት ፡ አጋባው ፡ ይህች
ውም ፡ የእንጀራ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ የሚ
ሆን ፡ የኤሌዮጲስ ፡ ካህን ፡ የፉጢፉራን ፡ ልጅ ፡
ናት ።
፲፭፡ ዮሴፍ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡
ዘመን ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።
፲፮፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ይስሐቅ ፡ ሞተ ። ስለ ፡ ሁለቱ ፡
ሕልሙ ፡ ዮሴፍ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ የነገረው ፡
ነገር ፡ ደረሰ ።
፲፯፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ጥጋብ ፡
ሆነ ፤ የግብጽ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ፍሬን ፡ አፈራች ፤
አንዲቱ ፡ መስፈሪያ ፡ ሺህ ፡ ከስምንት ፡ መስፈ
ሪያ ፡ ሆነች ።
፲፰፡ ዮሴፍም ፡ ስንዴው ፡ እስኪመላ ፡ ድረስ ÷ ከብዛ
ቱም ፡ የተነሣ ፡ መቍጠር ፡ መስፈር ፡ እስኪሳና
ቸው ፡ ድረስ ÷ ለአገር ፡ ምግብ ፡ የሚሆን ፡ እህ
ልን ፡ ከአገሩ ፡ ሰበሰበ ።
፲፱፡ በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ይሁዳ ፡
ለበኵር ፡ ልጁ ፡ ለኤር ፡ ከአራም ፡ ሶርያ ፡ ልጆች ፡
ወገን ፡ ሚስትን ፡ አጋባው ፤ ስምዋም ፡ ትእማር ፡
ይባላል ።
፳፡ እናቱ ፡ ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡
ከእናቱ ፡ ወገን ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡ ወዶአ
ልና ፡ ጠላት ፤ በእርስዋም ፡ አልደረሰባትም ፤
አባቱ ፡ ይሁዳ ፡ ግን ፡ አላሰናበተውም ።
፳፩፡ ያም ፡ የይሁዳ ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡ ኤር ፡ ክፉ ፡ ነበረ ፤
እግዚአብሔር ፡ ቀሠፈው ።
ይሁዳም ፡ ልጁን ፡ አውናን ፡— ከወንድምህ ፡ ፳፪፡
ሚስት ፡ ድረስባት ፤ ወርሰህ ፡ ለወንድምህ ፡ ልጅ ፡
ውለድ ፡ አለው ።
አውናንም ፡ የእርሱ ፡ ልጅ ፡ እንዳልሆነ ÷ የወን ፳፫፡
ድሙ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቆ ፡ በወንድሙ ፡
ሚስት ፡ ደረሰባት ። ዘሩን ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ያፈስ ፡ ነበር ። ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡
ሆነ ÷ ቀሠፈው ።
ይሁዳም ፡ ምራቱን ፡ ትእማርን ፡— ልጄ ፡ ሴሎም ፡ ፳፬፡
እስኪያድግ ፡ ድረስ ፡ መበለት ፡ ሆነሽ ፡ በአባትሽ ፡
ቤት ፡ ተቀመጭ ፤ ለእርሱ ፡ ሚስት ፡ ትሆኚው ፡
ዘንድ ፡ እሰጥሻለሁ ፡ አላት ።
አደገ ፤ የይሁዳ ፡ ሚስት ፡ ቤድሱኤል ፡ ግን ፡ ትእ ፳፭፡
ማርን ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡ ልጅዋን ፡ ሴሎምን ፡ አላ
ሰናበተችውም ፤ የይሁዳ ፡ ሚስት ፡ ቤድሱኤ
ልም ፡ በዚህ ፡ ሱባኤ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡
ሞተች ።
በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ ይሁዳ ፡ በጎቹን ፡ ይሸ ፳፮፡
ልት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቴምናታ ፡ ወጣ ፤ ለትእማር ፡—
እነሆ ÷ አማትሽ ፡ በጎቹን ፡ ይሸልት ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ቴምናታ ፡ ይወጣል ፡ ብለው ፡ ነገሩአት ።
የመበለትነትዋን ፡ ልብስ ፡ ትታ ፡ መጐናጸፊያ ፳፯፡
ዋን ፡ ለበሰች ። ተኳኳላ ፡ ተቀብታ ፡ በቴምናታ ፡
ጐዳና ፡ አንጻር ፡ ባለ ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጠች ።
ይሁዳም ፡ ሲሄድ ፡ አገኛት ፤ ጋለሞታ ፡ እንደ ፡ ፳፰፡
ሆነች ፡ ተጠራጠራት ፤ ልድረስብሽ ፡ አላት ፤
እሺ ፡ አለችው ፤ ደረሰባት ፤ የዝሙቴን ፡ ዋጋ ፡
ስጠኝ ፡ አለችው ። በጣቴ ፡ ካለ ፡ ከወርቅ ፡ ቀለ
በቴ ÷ ከኵፍየቴና ፡ በእጄ ፡ ካለ ፡ ከወርቅ ፡ ዘንጌ ፡
በቀር ፡ በእጄ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የለኝም ፡ አላት ።
የዝሙቴን ፡ ዋጋ ፡ እስክትሰድልኝ ፡ ድረስ ፡ እነ ፳፱፡
ርሱን ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ፤ አንድ ፡ የፍየል ፡
ጠቦት ፡ እልክልሻለሁ ፡ አላት ። ለእርስዋም ፡
እነርሱን ፡ ሰጣት ።
ፀነሰችለት ፤ ይሁዳም ፡ ወደ ፡ በጎቹ ፡ ሄደ ÷ እር ፴፡
ስዋም ፡ ወደ ፡ አባትዋ ፡ ቤት ፡ ሄደች ።
ይሁዳም ፡ በበግ ፡ ጠባቂው ፡ በአዶላማዊው ፡ ፴፩፡
ሰው ፡ እጅ ፡ የፍየሉን ፡ ጠቦት ፡ ሰደደላት ፤
አጣት ፡— በዚህ ፡ አገር ፡ ያለች ፡ ጋለሞታ ፡
ወዴት ፡ ናት ? ብሎ ፡ በአገር ፡ ያሉ ፡ ሰዎችን ፡
ጠየቃቸው ፤ በዚህ ፡ አገር ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ጋለ
ሞታ ፡ የለችም ፡ አሉት ።
ተመልሶም ፡— አጣኋት ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፤ በአ ፴፪፡
ገሩም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችን ፡ ጠየቅኋቸው ፡— በዚ
ህስ ፡ አገር ፡ ጋለሞታ ፡ የለችም ፡ አሉኝ ፡ አለው ።
መዘባበቻ ፡ እንዳንሆን ፡ ተነሥ ፡ እንሂድ ፡ አለው ። ፴፫፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በሆናት ፡ ጊዜ ፡ እር
ስዋ ፡ እንደ ፡ ፀነሰች ፡ታወቀች ፡ ለይሁዳም ፡—
እነሆ ÷ ምራትህ ፡ ትእማር ፡ በዝሙት ፡ ፀነሰች ፡
ብለው ፡ ነገሩት ።
ይሁዳም ፡ ወደ ፡ አባትዋ ፡ ቤት ፡ ሄደ ፤ እናትዋ ፴፬፡
ንና ፡ አባትዋን ፡ ወንድሞችዋንም ፡— በእስራ
ኤል ፡ ዘንድ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርታለችና ፡ በእሳት ፡
አቃጥለው ፡ ይገድሉአት ፡ ዘንድ ፡ አውጡአት ፡

አላቸው ።
፳፭፤ በእሳት ፡ አቃጥለው ፡ ይገድሉአት ፡ ዘንድ ፡ በወ
ጡአት ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ። ለእርሱ ፡ ፀንሻለ
ሁና ፡ ይህ ፡ የማንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እወቅ ፡
ብላ ፡ ኩፍየቱንና ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቱን ፡ የወርቅ ፡
ዘንጉን ፡ ለአማትዋ ፡ ላከች ።
፳፮፤ ይሁዳም ፡ የእርሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቀ ፡— ትእ
ማር ፡ ከእኔ ፡ ተሻለች ፥ እንግዲህ ፡ በእሳት ፡
አቃጥለው ፡ አይግደሉአት ፡ አለ ። ስለዚህ ፡
ነገር ፡ ለሴሎም ፡ አልተሰጠችም ፡ ከዚያም ፡
በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ አልደረሰባትም ።
፳፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፀንሳ ፡ በዚህ ፡ በሁለተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ሁለቱን ፡ ልጆች ፡
ዛራንና ፡ ፋሬስን ፡ ወለደች ።
፳፰፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮሴፍ ፡ ለፈርዖን ፡ የነገረው ፡
ሰባቱ ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፪ ።

፩፤ በምራቱ ፡ ደርሶአልና ፡ ይሁዳ ፡ የሠራው ፡
ሥራ ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቀ ። በፊቱ ፡
ክፉ ፡ ሥራን ፡ ሠራ ። የልጁን ፡ እፍረት ፡ ገልጠ
አልና ፡ እንደ ፡ በደለና ፡ እንደ ፡ ሳተ ፡ አወቀ ።
፪፤ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያዝን ፡
ይለምን ፡ ጀመር ።
፫፤ ፈጽሞ ፡ ለምኖአልና ፡ አዝኖአልምና ፡ ኀጢአቱ ፡
እንዲሰረይለት ፡ በሕልም ፡ ነገርነው ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ኀጢአት ፡ አልሠራም ። ከኀጢአቱና ፡ ከስ
ሕተቱ ፡ ተመልሶአልና ፡ ኀጢአቱ ፡ ተሰረየለት ።
፬፤ በአምላካችን ፡ ፊት ፡ ጽኑ ፡ በደል ፡ ነውና ፡ እን
ዲህ ፡ የሚያደርግን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በምራቱም ፡
የሚደርስን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ ይጠፉ ፡
ዘንድ ፡ በእሳት ፡ አቃጥለው ፡ ይግደሉት ። በእ
ነርሱ ፡ ኀጢአት ፡ በደል ፡ ሆኖአልና ፡ ስለዚህ ፡
ነገር ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉአቸው ።
፭፤ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ፤
በመካከላቸው ፡ ኀጢአት ፡ በደል ፡ አይሁን ፤
በምራቱና ፡ በአማቱ ፡ የሚደርስ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
በደልን ፡ አድርጎአልና ፡ በእርስዋ ፡ የደረሰውን ፡
ሰው ፡ በእሳት ፡ አቃጥለው ፡ ይግደሉት ፤ ሴቲ
ቱንም ፡ ይግደሉአት ።
፮፤ ቍጣውም ፡ መቅሠፍቱም ፡ ከእስራኤል ፡ ይር
ቃል ።
፯፤ ለይሁዳም ፡ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ ልጆቹ ፡ እንዳልደረ
ሱባት ፡ ነገርነው ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ልጁ ፡ ለሌላ ፡
ነገድ ፡ ሆነ ።
፰፤ በየዋህነት ፡ ሄዶአልና ፥ ፍርድንም ፡ መርምሮ
አልና ፡ ልጆቹ ፡ አልጠፉም ። አብርሃም ፡ ለል
ጆቹ ፡ ያዘዛቸውን ፡ ፍርድ ፡ ወዶአልና ፡ ይሁዳ ፡
በእሳት ፡ ያቃጥሉአት ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ።
፱፤ በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተ
ኛው ፡ ሱባኤ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በአ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ድርቅ ፡ ይመጣ ፡ ጀመር ።
፲፤ ዝናብም ፡ በምድር ፡ መዝነቡን ፡ ተወ ። ምን
ምን ፡ የሚዘንብ ፡ ዝናብ ፡ አልነበረምና ፡ በም
ድር ፡ ድርቅ ፡ ሆነ ። በግብጽ ፡ አገር ፡ ግን ፡ ምግ
ባቸውን ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ዮሴፍ ፡ የሰበሰ
በው ፡ እህል ፡ ነበረ ፤ አዝመራ ፡ በሆነበት ፡ በሰ
ባቱ ፡ ዓመት ፡ ዮሴፍ ፡ የግብጽን ፡ እህል ፡ ሰብ
ስቦ ፡ አኑሮ ፡ ነበርና ።
፲፩፤ ምግባቸውን ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ የግብጽ ፡
ሰዎች ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ መጡ ። የመጀመሪያው ፡
ዓመት ፡ ስንዴ ፡ ያለበትን ፡ ጎተራ ፡ ከፍቶ ፡ በግ
ብጽ ፡ ላሉ ፡ አሕዛብ ፡ በወርቅ ፡ ሸመተላቸው ።
፲፪፤ ያዕቆብም ፡ በግብጽ ፡ እህል ፡ እንዳለ ፡ ሰማ ።
ከግብጽ ፡ እህል ፡ ሸምተው ፡ ያመጡለት ፡ ዘንድ ፡
አሥሩን ፡ ልጆቹን ፡ ላከ ፤
፲፫፤ ብንያምን ፡ ግን ፡ አልሰደደውም ። ወደ ፡ ግብጽ ፡
ከሚሄድ ፡ ነጋዴ ፡ ጋር ፡ ደረሱ ። ዮሴፍ ፡ አወ
ቃቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አላወቁትም ፤ ከእነር
ሱም ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ። እናንተ ፡ ጉበኞች ፡ አይ
ደላችሁምን ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፤ የአገሩንም ፡
መግቢያ ፡ ትሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ መጣችሁ ፡ ብሎ ፡
አሰራቸው ።
፲፬፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፈታቸው ፥ ስምዖንን ፡ ብቻ ፡ አስ
ቀረ ። ዘጠኙን ፡ ወንድሞቹን ፡ በአቅማዳቸው ፡
ስንዴውን ፡ ሞልቶ ፡ ሰደዳቸው ። ወርቃቸው
ንም ፡ በአቅማዳቸው ፡ ጨመረላቸው ፤ እነርሱ ፡
ግን ፡ አላወቁም ።
፲፭፤ አባታቸው ፡ በሕይወት ፡ እንዳለ ፡ ታናሽ ፡ ወን
ድማቸውም ፡ እንዳለ ፡ ነግረውታልና ፡ ታናሽ ፡
ወንድማቸውን ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።
፲፮፤ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ አገር ፡
ደረሱ ፤ ያገኛቸውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፥ የአገሩ ፡ ገዥ ፡
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ጭንቅ ፡ ነገርን ፡ እንደ ፡ ተና
ገረ ፡ ለአባታቸው ፡ ነገሩት ። ብንያምን ፡ እስኪ
ያመጡ ፡ ድረስ ፡ ስምዖንንም ፡ መያዣ ፡ አድ
ርጎ ፡ እንዳስቀረው ፡ ለአባታቸው ፡ ነገሩት ።
፲፯፤ ያዕቆብም ፡— የወላድ ፡ መካን ፡ አደረጋችሁኝ ፥
ዮሴፍ ፡ የለ ፥ ስምዖን ፡ የለ ፥ ብንያምንም ፡ ትወ
ስዱብኝ ፡ ነውን ? ክፉታችሁ ፡ በእኔ ፡ ደረሰ ፤
ልጄ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ አይሄድም ፤
፲፰፤ በመንገድ ፡ ቢታመም ፡ ይሞትብኛል ፤ እናታ
ቸው ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ወልዳ ፡ ነበርና ፡ አንዱ ፡
ሞተ ፤ ይህንንም ፡ ትወስዱብኝ ፡ ነውን ? በመ
ንገድ ፡ ታሞ ፡ ቢሞት ፡ ያረጀ ፡ ሰውነቴን ፡ በኀ
ዘን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ታወርዳላችሁ ፡ አላቸው ።
ወርቃቸው ፡ ሁሉ ፡ ተቋጥሮ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡
አይቶአልና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እርሱን ፡ መስደድ ፡
ፈራ ።
፲፱፤ ራቡም ፡ በከነዓን ፡ ፈጽሞ ፡ ጸና ፤ ከግብጽ ፡
ሰዎች ፡ ዮሴፍ ፡ ብዙ ፡ እህልን ፡ እንዲሰበስብ ፡
ዮሴፍን ፡ ካዩት ፡ ጀምሮ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡
ሊሆን ፡ እህላቸውን ፡ ሰብስበዋልና ፡ ከግብጽ ፡
አገር ፡ በቀር ፡ በአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ራብ ፡ ጸና ።
፳፤ በጎተራ ፡ አኑሮ ፡ ራብ ፡ ለሚሆንበት ፡ ዓመት ፡
ይጠብቀው ፡ ነበር ፤ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ራብ ፡ በሆ
ነበት ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ተመገቡት ።
፳፩፤ ያዕቆብም ፡ በአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ራብ ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡

ጻና ፡ ከራብም ፡ መዳን ፡ እንደሌለ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡
ልጆቹን ፦ በራብ ፡ እንዳንሞት ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
ሄዳችሁ ፡ እህል ፡ ሸምታችሁ ፡ አምጡልን ፡ አላ
ቸው ። እነርሱም ፦ ታናሽ ፡ ወንድማችን ፡
ከእኛ ፡ ጋር ፡ ካልሄደ ፡ አንሄድም ፡ አሉት ።
፴፪፤ ያዕቆብም ፡ ብንያምን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ካልሰደ
ደው ፡ በራቡ ፡ የተነሣ ፡ ሁሉም ፡ እንዲሞቱ ፡
አሰበ ፤ ሮቤልም ፦ በእጄ ፡ ስጠኝ ፥ መልሼ ፡
ባላመጣልህ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ፋንታ ፡ ሁለቱን ፡
ልጆቼን ፡ ግደላቸው ፡ አለው ።
፴፫፤ ከአንተ ፡ ጋር ፡ አይሄድም ፡ አለው ። ይሁዳም ፡
ቀርበ ፦ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ስደደው ፤ መልሼ ፡ ባላ
መጣልህ ፡ በሕይወት ፡ በኖርሁበት ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ፡ በፊትህ ፡ በደለኛ ፡ ልሁን ፡ አለ ።
፴፬፤ በዚህ ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በአሥ
ረኛው ፡ ወር ፡ መበቻ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሰደደው ።
ወደ ፡ ግብጽ ፡ ከሚሄዱ ፡ ነጋዴዎች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
ሄደው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ደረሱ ። እጅ ፡ መንሻቸ
ውንም ፡ በእጃቸው ፡ ያዙ ፤ ይኸውም ፡ የያ
ዙት ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ልባንጃ ፡ የሚባል ፡ ሽቱ ፡
ለውዝ ፡ ገውዝ ፡ ጠርቤንቶስ ፡ የሚባል ፡ ሽቱ ፡
የማር ፡ ወለላ ፡ ነው ።
፴፭፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ደረሱ ፡ በዮሴፍም ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፥
ወንድሙን ፡ ብንያምንም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ አወ
ቀው ።
፴፮፤ ትንሽ ፡ ወንድማችሁ ፡ ይህ ፡ ነውን ? አላቸው ።
አዎን ፥ ይህ ፡ ነው ፡ አሉት ። ልጄ ፡ ሆይ ፥ እግ
ዚአብሔር ፡ ይጠብቅህ ፡ አለው ፤ ወደ ፡ ቤቱ ፡
ሰደዳቸው ፥ ስምዖንንም ፡ አወጣላቸው ።
፴፯፤ ግብር ፡ አገባላቸው ፤ በእጃቸው ፡ ያመጡት
ንም ፡ እጅ ፡ መንሻቸውን ፡ አቀረቡለት ።
በፊቱ ፡ በሉ ፤ ለሁሉም ፡ ፈንታ ፡ ፈንታቸውን ፡
ሰጣቸው ። ከሁሉም ፡ ፈንታ ፡ ይልቅ ፡ የብን
ያም ፡ ፈንታ ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ በለጠ ። በልተው ፡
ጠጥተው ፡ ሄደው ፡ አህዮቻቸው ፡ በሉበት ፡
አደሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፵ ።

፩፤ ዮሴፍም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የደግንነትና ፡
የፍቅር ፡ አሳብ ፡ እንዳላቸው ፥ የጠብም ፡ አሳብ ፡
እንዳላቸው ፥ አሳባቸውን ፡ በሚያውቅ ፡ ገን
ዘብ ፡ አሳብን ፡ አሰበ ።
፪፤ በቤቱ ፡ ላይ ፡ የተሾመውን ፡ ሹም ፦ በአቅማ
ዳቸው ፡ ሁሉ ፡ እህልን ፡ ምላላቸው ፤ ወርቃቸ
ውንም ፡ በዳውላው ፡ አድርግላቸው ፤ የምጠ
ጣበትንም ፡ የብሩን ፡ ጽዋ ፡ በታናሹ ፡ ልጅ ፡ አቅ
ማዳ ፡ አድርገህ ፡ ስደዳቸው ፡ አለው ።
፫፤ ሹሙም ፡ ዮሴፍ ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ። በአቅ
ማዳውም ፡ እህልን ፡ ሁሉ ፡ መላ ፥ ወርቃቸው
ንም ፡ በአቅማዳቸው ፡ ጨመረላቸው ። የብሩ
ንም ፡ ጽዋ ፡ በብንያም ፡ አቅማዳ ፡ ጨመረ ፤ በነ
ጋም ፡ ጊዜ ፡ ፈጥነው ፡ ሄዱ ።
፬፤ ከዚያም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ። ዮሴፍ ፡
በቤቱ ፡ የተሾመውን ፡ ሹም ፦ ፈጥነህ ፡ ተከተ
ላቸው ፦ በጎ ፡ ነገር ፡ ስላደረግሁላችሁ ፡ ፈንታ ፡
ክፉ ፡ ነገርን ፡ ከፈላችሁኝ ፤ ጌታዬ ፡ የሚጠጣበ
ትን ፡ የብር ፡ ጽዋ ፡ ሰረቃችሁኝ ፡ ብለህ ፡ ተከራክ
ረህ ፡ ታናሽ ፡ ወንድማቸውን ፡ መልስልኝ ፤ ወደ ፡
አደባባይ ፡ ሳልወጣ ፡ ፈጥነህ ፡ አምጣው ፡ አለው ።
ፈጥኖ ፡ ተከትሎ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናገራ ፭፤
ቸው ። ለእኛ ፡ ለባሪያዎችህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ነገር ፡ አገባብችን ፡ አይደለም ። ይህንንስ ፡ ሥራ ፡
አንሠራም ፤ ከጌታህ ፡ ቤት ፡ ምንም ፡ ምን ፡
ገንዘብ ፡ አንሰርቅም ።
እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ቀድሞ ፡ በአቅማዳችን ፡ ያገ ፮፤
ኘነውን ፡ ወርቃችንን ፡ ስንኳ ፡ ከከንዓን ፡ መል
ሰን ፡ አመጣን ፤ እንዴት ፡ ገንዘብ ፡ እንሰርቃ
ለን ? እነሆ ፥ እኛም ፡ አለን ፤ አቅማዳችንም ፡
አለ ፤ በርብረን ።
ከእኛ ፡ ጽዋውን ፡ ያገኘህበት ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ፯፤
ይሙት ፤ እኛም ፡ አህዮቻችንም ፡ ለጌታህ ፡
እንገዛ ፡ አሉት ።
ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ጽዋውን ፡ ያገኘሁ ፰፤
በትን ፡ ሰው ፡ እርሱን ፡ ብቻ ፡ ይገዞ ፡ ባሪያ ፡ አደ
ርገዋለሁ ፤
እናንተ ፡ ግን ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ ተመ ፱፤
ለሱ ፡ አላቸው ። ገንዘባቸውንም ፡ ሲበረብር ፡
ከታላቁ ፡ ጀምሮ ፡ በታናሹ ፡ ጨረሰ ፤ በታናሹ ፡
በብንያም ፡ አቅማዳ ፡ ተገኘ ።
ደንግጠው ፡ ልብሶቻቸውን ፡ ቀደዱ ። እህላቸ ፲፤
ውን ፡ በአህዮቻቸው ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡
ተመለሱ ። ወደ ፡ ዮሴፍም ፡ ቤት ፡ በደረሱ ፡
ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ እግር ፡ ከግምባር ፡ አድርገው ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ሰገዱለት ።
ዮሴፍም ፦ ክፉ ፡ ሥራን ፡ ሠራችሁ ፡ አላቸው ። ፲፩፤
ምን ፡ እንናገራለን ? አንተ ፡ ጌታችን ፡ የእኛን ፡
የባሪያዎችህን ፡ በደል ፡ አገኘህብን ፤ ምን ፡ እን
መልሳለን ?
እነሆ ፥ እኛ ፡ ለጌታችን ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፡ አህዮ ፲፪፤
ቻችንም ፡ የአንተ ፡ ገንዘቦች ፡ ናቸው ፡ አሉት ።
ዮሴፍም ፦ እኔስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እፈራ ፲፫፤
ለሁ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አገራችሁ ፡ ሂዱ ፤
ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርታችኋልና ፡ ወንድማችሁ ፡
ብቻ ፡ ተገዥ ፡ ይሁን ፤ ሰው ፡ ጽዋውን ፡ እንዲ
ወድ ፥ እኔስ ፡ በዚህ ፡ ጽዋ ፡ እንድጠጣ ፡ አታ
ውቁምን ? እርሱን ፡ ሰረቃችሁኝ ፡ አላቸው ።
ይሁዳም ፦ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፥ አንተ ፡ በጆሮህ ፡ ፲፬፤
ስትሰማ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፡ አለ ። የዚህ ፡
የባሪያህ ፡ እናት ፡ ለአባታችን ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡
ወለደች ፤ አንዱ ፡ ወጥቶ ፡ ጠፋ ፤ ያገኘው ፡
የለም ፤ ይህ ፡ ግን ፡ ለእናቱ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ቀር
ቶአል ።
ባሪያህ ፡ አባታችን ፡ ይወደዋል ። ልቡናውም ፡ ፲፭፤
ከዚህ ፡ ከልጁ ፡ ልቡና ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ናት ።
ወደ ፡ ባሪያህ ፡ ወደ ፡ አባታችን ፡ ብንሄድ ፡ ይህ ፡
ሕፃን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ካልሄደ ፡ ይሞታል ።
ለሞት ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ እስኪያ ፲፮፤
ዝን ፡ ድረስ ፡ አባታችንን ፡ በኀዘን ፡ እንገድላ

ለን ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ በሪያህ ፡ ስለዚህ ፡ ልጅ ፡
ፋንታ ፡ ለጌታዬ ፡ ተገዥ ፡ ሆኜ ፡ ልኑር ፤ ልጁ ፡
ከወንድሞቹ ፡ ጋር ፡ ይሂድ ። ከበሪያህ ፡ ከአባታ
ችን ፡ እጅ ፡ ዋስ ፡ ሆኜ ፡ አምጥቼዋለሁና ፡ እኔ ፡
በሪያህ ፡ መልሼ ፡ ባልወስደው ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡
አባታችንን ፡ እበድላለሁ ፡ አለው ።
፲፯፤ ዮሴፍም ፡ የሁሉም ፡ ልቡና ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡
ጋር ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፡ መታገሥ ፡ ተሳነው ።
፲፰፤ እርሱ ፡ ዮሴፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገራቸው ፤ በዕብ
ራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ።
አንገታቸውን ፡ እቅፍ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ አለቀሰ ።
እነርሱ ፡ ግን ፡ አላወቁትም ፡ እነርሱም ፡ ያለቅሱ ፡
ጀመር ።
፲፱፤ በእኔ ፡ አታልቅሱ ፡ አላቸው ፤ አባቴን ፡ ፈጥ
ናችሁ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አምጡት ፡ ሳልሞት ፡ አባ
ቴን ፡ ልየው ፤ የወንድሜ ፡ የብንያምን ፡ ዓይኖች ፡
ሲያዩ ፡ ልየው ። ይህ ፡ የራቡ ፡ ዘመን ፡ እነሆ ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነው ። ዳግመኛ ፡ አምስት ፡
ዓመት ፡ አለ ፤ አዝመራ ፡ የለም ፤ የእንጨት ፡
ፍሬ ፡ የለም ፤ እርሻም ፡ የለም ። እናንተ ፡ ከን
ዛችሁ ፡ ጋር ፡ ፈጥናችሁ ፡ ኑ ፡ በራብ ፡ አትሙቱ ።
፳፤ ብዙ ፡ ወገኖች ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
እኔን ፡ አስቀድሞ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ሰዶኛልና ፤
ስለ ፡ ጓዛችሁም ፡ አትዘኑ ፡ እኔ ፡ ገና ፡ በደኅንነት ፡
እንዳለሁ ፡ ለአባቴ ፡ ንገሩት ።
፳፩፤ ለፈርዖን ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፤ በቤቱ ፡
በግብጽ ፡ አገርም ፡ ሁሉ ፡ እሠለጥን ፡ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሾመኝ ፡ እነሆ ፡ እናንተ ፡
አያችሁ ።
፳፪፤ ለአባቴም ፡ ጌትነቴን ፡ ሁሉ ፤ እግዚአብሔር ፡
የሰጠኝን ፡ ብልጥግና ፡ ክብርም ፡ ሁሉ ፤ ንገሩት ።
በፈርዖንም ፡ ትእዛዝ ፡ ለጐዳና ፡ ስንቅና ፡ ሰረገ
ላዎችን ፡ ሰጣቸው ።
፳፫፤ ለሁሉም ፡ አራት ፡ ኅብር ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ ብር
ንም ፡ ሰጣቸው ። ለአባታቸውም ፡ ብርና ፡ ልብ
ስን ፡ ስንዴ ፤ የሚወስዱባቸው ፡ አሥር ፡ አህዮ
ችንም ፡ ሰደደ ።
፳፬፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶ ፡ አሰናበታቸው ። ወጥተ
ውም ፡ ለአባታቸው ፡ ዮሴፍ ፡ እንዳለ ፤ በግብጽ ፡
ላሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ስንዴን ፡ እንዲሰፍር ፤
በግብጽ ፡ አገር ፡ ሁሉም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሠለ
ጠነ ፡ ነገሩት ።
፳፭፤ ልቡናው ፡ ደንግጦአልና ፡ አባታቸው ፡ አላመ
ናቸውም ።
፳፮፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮሴፍ ፡ የላከለትን ፡ ሰረገላዎች ፡
አይቶ ፡ ልቡናው ፡ ደስ ፡ አላት ።
፳፯፤ ይህ ፡ ለእኔ ፡ ደግ ፡ ነው ። ዮሴፍ ፡ ደኅና ፡ ነውና ፡
ሳልሞት ፡ ወርጄ ፡ ልየው ፡ አለ ።
፳፰፤ ያዕቆብም ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ በከ
ራን ፡ ካለ ፡ ቤቱ ፡ ተነሥቶ ፡ በቤርሳቤህ ፡ ጐዳና ፡
ሄደ ። ይህ ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡
ለአባቱ ፡ ለይስሐቅ ፡ አምላክ ፡ መሥዋዕትን ፡
ሠዋ ።

ያዕቆብ ፡ በቤቴል ፡ ያየውን ፡ ሕልም ፡ አሰበ ፤ ፳፱፤
ወደ ፡ ግብጽ ፡ መውረድንም ፡ ፈራ ። ወደ ፡ እርሱ ፡
ሲመጣ ፡ ይልክ ፡ ዘንድ ፡ ሲያስብ ፤ እርሱ ፡ ገና ፡
ሳይወርድ ፡ ሲያስብ ፡ ሰነበተ ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፮ ።

ይቀርም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይወርድም ፡ እንደ ፡ ፩፤
ሆነ ፡ ራእይ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
ተቀመጠ ። ከከረመው ፡ ስንዴ ፡ የስንዴው ፡ አዝ
መራ ፡ መጀመሪያ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በዓል ፡ አደ
ረገ ።
በከብቶችና ፡ በአውሬዎች ፡ ሁሉ ፡ በሰዎችና ፡ ፪፤
በወፎችም ፡ ድርቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በከነዓን ፡ አገር ፡
ሁሉ ፡ በምድር ፡ የሚዘሩት ፡ ምንምን ፡ እፍኝ ፡
ሙሉ ፡ ዘር ፡ አልነበረምና ፡ በዓል ፡ አደረገ ።
በአሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ቀን ፡ እግዚአብ ፫፤
ሔር ፡ ተነጋገረው ፦ ያዕቆብ ፤ ያዕቆብ ፡ ብሎ ፡
ጠራው ። ያዕቆብም ፦ እነሆ ፤ አለሁ ፡ አለ ።
የአባቶችህ ፡ የአብርሃምና ፡ የይስሐቅ ፡ ፈጣሪ ፡
እኔ ፡ ነኝ ። በዚያ ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ አደርግሃለሁና ፡
ወደ ፡ ግብጽ ፡ መውረድን ፡ አትፍራ ። እኔ ፡ ከአ
ንተ ፡ ጋር ፡ በረድኤት ፡ እወርዳለሁ ። እኔ ፡ እወ
ስድሃለሁ ፡ በዚያችም ፡ አገር ፡ ትቀበራለህ ።
ዮሴፍም ፡ እጁን ፡ በዓይኖችህ ፡ ላይ ፡ ያኖራል ፤ ፬፤
አማውቶ ፡ ይቀብርሃል ፤ አትፍራ ፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡
ውረድ ፡ አለው ።
ያዕቆብም ፡ ተነሣ ፡ ልጆቹም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹም ፡ ፭፤
ተነሡ ፤ አባታቸውንም ፡ ገንዘባቸውንም ፡ በሰ
ረገላ ፡ ጫኑ ።
ይህ ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ፮፤
ቀን ፡ ያዕቆብ ፡ ከቤርሳቤህ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡
ግብጽ ፡ ሄደ ።
ያዕቆብም ፡ ከእርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ ፯፤
ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ ይሁዳን ፡ ላከ ። ለእርሱ ፡ አቅራ
ቢያ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፤ በዚያ ፡ ሊኖሩ ፡ ይመጡ ፡
ዘንድ ፡ ወንድሞቹን ፡ ጠርቶአቸዋልና ፡ የጌሴ
ምን ፡ አገር ፡ ይጐበኝ ፡ ዘንድ ፡ ላከው ።
በግብጽ ፡ አገር ፡ ያለች ፡ ያችውም ፡ ምድር ፡ ፰፤
መልካም ፡ አገር ፡ ነበረች ። ለእስራኤልም ፡ ሁሉ ፡
ቅርብ ፡ ነበረች ፤ ለከብትም ፡ የተመቸች ፡ ናት ።
ከአባታቸው ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ፱፤
የወረዱ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡
ነው ። የያዕቆብ ፡ የበኩር ፡ ልጁ ፡ ሮቤል ፡ ነው ፤
የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ስማቸው ፡ መጀመሪያው ፡
ሄኖክ ፤ ሁለተኛው ፡ ፋሉስ ፤ ሦስተኛው ፡ ኤስ
ሮም ፤ አራተኛው ፡ ከራሚ ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
እነዚህ ፡ አምስቱ ፡ ናቸው ።
ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ሁለተኛው ፡ ስምዖን ፡ ነው ። ፲፤
የስምዖንም ፡ ልጆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤
ኢያሚንና ፡ ኤሙኤል ፤ ኢያኪምና ፡ አአ
ዎት ፤ የሰፍንስዋት ፡ ልጅ ፡ ሳውልና ፡ ሳኦር ፤
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እነዚህ ፡ ሰባቱ ፡ ናቸው ።
ሦስተኛውም ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ሌዊ ፡ ነው ። ፲፩፤
ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ጌድሶር ፤ ቀዓት ፤

ሚራሪ ፡ እሊህ ፡ አራቱ ፡ ናቸው ።
አራተኛውም ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ይሁዳ ፡ ነው ።
ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ። ሴሎምና ፡ ፋሬስ ፡ ዛራ ፤
እሊህ ፡ አራቱ ፡ ናቸው ።
፲፪ ፡ አምስተኛውም ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ይሳኮር ፡ ነው ።
የልጆቹም ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ። ፋአና ፡
ፉላ ፡ ሳምሮምና ፡ ኢያስብ ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
እሊህ ፡ አምስቱ ፡ ናቸው ።
፲፫ ፡ ስድስተኛውም ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ዛብሎን ፡
ነው ። የልጆቹም ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ኤሎ
ንና ፡ ሳአር ፡ ኢያሌኤል ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እነ
ዚህ ፡ አራቱ ፡ ናቸው ።
፲፬ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ልጆቻቸውም ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ፤ በሶርያ ፡ ልያ ፡ ለያዕቆብ ፡ የወለደች
ለት ፡ ስድስት ፡ ናቸው ።
፲፭ ፡ አንዲቱ ፡ እኅታቸው ፡ ዲና ፡ ናት ። ከልያ ፡ የተ
ወለዱ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከአባታቸው ፡ ከያዕ
ቆብ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የወረዱ ፡ ልጆቻቸ
ውም ፡ ሀያ ፡ ዘጠኝ ፡ ናቸው ። አባታቸው ፡ ያዕ
ቆብም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተቈጥሮ ፡ ሠላሳ ፡ ሆኑ ።
፲፮ ፡ የያዕቆብ ፡ ሚስት ፡ የልያ ፡ አገልጋይ ፡ ዘለፋ ፡
ለያዕቆብ ፡ የወለደችለት ፡ ልጆች ፡ አሴርና ፡
ጋድ ፡ ናቸው ። ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
የወረዱ ፡ የልጆቻቸውም ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ።
፲፯ ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ አሐዲና ፡ ሰፍዮን ፡ ሱኒና ፡
ኢጋቲ ፡ አረሌና ፡ አሶን ፡ አረዲና ፡ ኤረሴ ፤ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ እነዚህ ፡ ዘጠኙ ፡ ናቸው ።
፲፰ ፡ የአሴርም ፡ ልጆች ፡ ይሱአ ፡ አያምና ፡ በርያ ፡
ናቸው ። እኅታቸው ፡ ሣራ ፡ ናት ፤ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ እነዚህ ፡ አምስቱ ፡ ናቸው ።
፲፱ ፡ የዘለፋ ፡ ልጆች ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ናቸው ።
ከልያ ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አርባ ፡ አራት ፡
ሆኑ ።
፳ ፡ የያዕቆብ ፡ ሚስት ፡ የራሔል ፡ ልጆች ፡ ብንያ
ምና ፡ ዮሴፍ ፡ ናቸው ። አባቱ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
ሳይወርድ ፡ ለዮሴፍ ፡ በግብጽ ፡ ልጆች ፡ ተወለ
ዱለት ። የኤሊዮጺስ ፡ ካህን ፡ የሚሆን ፡ የፋጢ
ፋራ ፡ ልጅ ፡ አሰኔት ፡ የወለደችለት ፡ ኤፍሬ
ምና ፡ ምናሴ ፡ ናቸው ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እነዚህ ፡
ሦስቱ ፡ ናቸው ።
፳፩ ፡ የብንያምም ፡ ልጆች ፤ አስቤልና ፡ ላውባኤል ፡
ንእማንና ፡ ጉአው ፡ ራኤፍስና ፡ አብሮድዮ ፡
አፌምና ፡ ያኒማ ፡ ጋዕሞና ፡ የአም ፤ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ እነዚህ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ናቸው ።
፳፪ ፡ ንፍታሌምንና ፡ ዳንን ፡ የወለደችለት ፡ የያዕቆብ ፡
የሚስቱ ፡ የራሔል ፡ አገልጋይ ፡ የባላ ፡ ልጆች ፡
እነዚህ ፡ ናቸው ። ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
የወረዱ ፡ የልጆቻቸውም ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ።
፳፫ ፡ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ሰሞንና ፡ ኩሲም ፡ ኢያሳ
ክና ፡ አሱድ ፡ ሰሎሞን ፡ ናቸው ፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
እሊህ ፡ ስድስቱ ፡ ናቸው ።
፳፬ ፡ የንፍታሌምም ፡ ልጆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።
ገሃንና ፡ ኢያስኢል ፡ ያኩምና ፡ አስዓር ፡ አው ፡
ናቸው ። ከራብ ፡ በኋላ ፡ የተወለደ ፡ አው ፡ በግ
ብጽ ፡ ሞተ ። ከራሔል ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ፡ ሀያ ፡ ሰባት ፡ ሆኑ ፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የወ
ረዱ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ሰባ ፡ ሰዎች ፡
ናቸው ።
እነዚህ ፡ ልጆቹና ፡ የልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉም ፡ ፳፭
ሰባ ፡ ናቸው ። ሚስት ፡ ሳያገቡ ፡ በግብጽ ፡ የሞ
ቱት ፡ አምስት ፡ ናቸው ፤ ልጅም ፡ አልነበራቸ
ውም ።
የይሁዳ ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ አውናንና ፡ ኤር ፡ በከ ፳፮
ነዓን ፡ አገር ፡ ሞቱበት ፤ ልጅ ፡ አልነበራቸውም ፤
የሞቱትንም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቀበሩአ
ቸው ። እነዚህም ፡ ወገኖች ፡ ከሰባው ፡ ሰዎች ፡
ጋር ፡ ተቆጠሩ ።
በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተ ፳፯
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በአራተ
ኛው ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ያዕቆብ ፡ በግብጽ ፡ ወዳ
ለች ፡ ጌሴም ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ ገባ ።
ዮሴፍ ፡ አባቱን ፡ ያዕቆብን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ፳፰
ወደ ፡ ጌሴም ፡ መጣ ። የአባቱን ፡ አንገት ፡ አቅፎ ፡
አለቀሰ ። ያዕቆብም ፡ ዮሴፍን ፡— አይቼሃለሁና ፡
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ልሙት ፡ አለው ።
አሁንም ፡ ከበረያው ፡ ከያዕቆብ ፡ ይቅርታውንና ፡ ፳፱
ቸርነቱን ፡ ያላራቀ ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ የይ
ስሐቅና ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፤ በቤ
ቴል ፡ ያየሁት ፡ ራእይ ፡ እውነተኛ ፡ ሕልም ፡
ነውና ፡ እኔ ፡ በሕይወት ፡ ፊትህን ፡ ማየቴ ፡ ለእኔ ፡
ድንቅ ፡ ነው ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘላ
ለሙ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፤ ስሙም ፡ የተመሰ
ገነ ፡ ነው ፡ አለ ።
ወንድሞቹና ፡ ዮሴፍም ፡ በአባታቸው ፡ ፊት ፡ ፴
እንጀራን ፡ በሉ ፡ ወይንንም ፡ ጠጡ ፤ ያዕቆብም ፡
ዮሴፍን ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋር ፡ በፊቱ ፡ ሲበላ ፡
ሲጠጣ ፡ አይቶታልና ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለው ።
እርሱን ፡ የጠበቀው ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ልጆ
ቹንም ፡ የጠበቀለት ፡ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ አመሰገነው ።
ዮሴፍም ፡ በራሚስቲኖን ፡ ጌሴም ፡ በምትባል ፡ ፴፩
አገር ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ እነርሱ ፡ በሚገዙት ፡
በአውራጃዋም ፡ ሁሉ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቱ ፡
ገንዘብ ፡ ሰጠው ፡ ለወንድሞቹም ፡ ሰጣቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፭ ።

ያዕቆብ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ በም ፩
ትበልጥ ፡ ጌሴም ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ኖረ ። ያዕ
ቆብ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ የመቶ ፡
ሠላሳ ፡ ጎሬት ፡ ፤ መን ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።
ዮሴፍም ፡ ወንድሞቹንና ፡ አባቱን ፡ ከንዛቸው ፡ ፪
ጋር ፡ ለሰባቱ ፡ ለራብ ፡ ዓመት ፡ የሚበቃ ፡ ምግ
ብን ፡ መገባቸው ። ከራቡ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ የግ
ብጽ ፡ አገርም ፡ ተጨነቀች ።
ዮሴፍም ፡ የግብጽ ፡ አገርን ፡ ሁሉ ፡ በእህል ፡ ምክ ፫
ንያት ፡ ለፈርዖን ፡ ርስት ፡ አደረጋት ። ፈርዖን ፡
ሰውንም ፡ ከብቱንም ፡ ሁሉንም ፡ ገንዘብ ፡ አደ
ረገ ። የራቡም ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፬፤ ዮሴፍም ፡ በስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ዘር ፡ ይዘሩ ፡
ዘንድ ፡ በግብጽ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ ዘርን ፡ እህልን ፡
ሰጠ ፡፡ ፈሳሹ ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ መልቶ
አልና ፤ በሰባቱ ፡ ራብ ፡ ዘመን ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡
ካሉ ፡ ከጥቂቶች ፡ አገሮች ፡ በቀር ፡ አያጠጣም ፡
ነበርና ፡፡

፭፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ መልቶአልና ፡ ሰጣቸው ፡፡ የግብጽ ፡
ሰዎችም ፡ በምድር ፡ ዘርን ፡ ዘሩ ፤ ምድርም ፡
በዚያ ፡ ዓመት ፡ ብዙ ፡ ስንዴን ፡ አፈራች ፡፡ ያም ፡
ዘመን ፡ በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡
የአራተኛው ፡ ሱባኤ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው ፡፡

፮፤ ዮሴፍም ፡ ከዘሩት ፡ እህል ፡ አምስተኛውን ፡
እጅ ፡ ወስዶ ፡ ለንጉሥ ፡ አገባ ፡፡ አራቱን ፡ እጅ ፡
ለዘርና ፡ ለምግብ ፡ ሊሆናቸው ፡ ተወላቸው ፡፡
ዮሴፍ ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለግብጽ ፡ አገር ፡
ሰዎች ፡ ሥርዓት ፡ አደረገላቸው ፡፡

፯፤ ያዕቆብም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡
ዓመት ፡ ኖረ ፡፡ የኖራቸውም ፡ ዘመኖች ፡ ሁሉ ፡
ሦስት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ሆኑ ፤ ሦስት ፡ ኢዮቤልዩስ ፡
መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ዘመን ፡ ነው ፡፡ በአርባ ፡
አምስተኛው ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በአምስተኛው ፡
ሱባዔ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ሞተ ፡፡

፰፤ ያዕቆብም ፡ ሳይሞት ፡ ልጆቹን ፡ መረቃቸው ፡፡
በግብጽ ፡ አገር ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ሁሉ ፤ በኋ
ለኛውም ፡ ዘመን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚመጣበ
ቸውንም ፡ ሁሉንም ፡ ነገራቸው ፤ መረቃቸ
ውም ፡፡

፱፤ ለዮሴፍም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዕጣ ፡ ሰጠው ፡፡
እንደ ፡ አባቶቹም ፡ ሞተ ፡፡ በከነዓን ፡ አገር ፡ እጥ
ፍኝት ፡ ባላት ፡ ዋሻ ፡ በአባቱ ፡ በአብርሃም ፡ አጠ
ገብ ፡ ተቀበረ ፡፡ ይኸውም ፡ በከነዓን ፡ አገር ፡
እጥፍኝት ፡ ባላት ፡ ዋሻ ፡ ለራሱ ፡ በቆፈራት ፡
መቃብር ፡ ነው ፡፡ የአባቶቹን ፡ መጽሐፎችና ፡
የእርሱን ፡ መጽሐፎች ፡ ሁሉ ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ዘንድ ፤ ለልጆቹም ፡ ያድ
ሳቸው ፡ ዘንድ ፤ ለልጁ ፡ ለሌዊ ፡ ሰጠው ፡፡

፲፤ ያዕቆብ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ በዙ ፤ ብዙ ፡
ወገንም ፡ ሆኑ ፡፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ ይወድ ፡
ዘንድ ፤ ባልንጀራም ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋር ፡
ይረዳዳ ፡ ዘንድ ፡ ሁሉም ፡ በልቡናቸው ፡ የተካ
ከሉ ፡ ሆኑ ፡፡

፲፩፤ ዮሴፍ ፡ በኖረበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በአሥሩ ፡
በዘመነ ፡ ሱባዔ ፡ ፈጽመው ፡ በዙ ፡፡ ዮሴፍ ፡ በኖ
ረበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የግ
ብጽ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ያከብሩአቸው ፡ ነበርና ፡
አባቱ ፡ ያዕቆብ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዮሴፍ ፡ በኖረ
በት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ባለጋራ ፡ አልነበረም ፤ ምን
ምን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ፡፡

፲፪፤ ዮሴፍም ፡ የመቶ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሲሆን ፡
ሞተ ፤ በከነዓን ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፤
አሥር ፡ ዓመት ፡ ሲያገለግል ፡ ኖረ ፤ ሦስት ፡
ዘመን ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ ኖረ ፤ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡
ከንጉሥ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ የግብጽን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡
ሲገዛ ፡ ኖረ ፡፡ እርሱ ፡ ሞተ ፤ ወንድሞቹም ፡ ሁሉ ፡
ሞቱ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የወረደች ፡ ያችም ፡ ትው
ልድ ፡ ሁሉ ፡ ሞተች ፡፡

ከግብጽ ፡ በሚወጡበት ፡ ወራት ፡ ዓፅሙን ፡ ፲፫፤
ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ ሳይሞት ፡ የእስራኤልን ፡
ልጆች ፡ አዘዛቸው ፡፡ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ዕለቱን ፡
አውጥተው ፡ ዳግመኛ ፡ በከነዓን ፡ አገር ፡ እንዳ
ይቀብሩት ፡ አውቆአልና ፡ ስለ ፡ ዓፅሙ ፡ አማ
ላቸው ፡፡ የከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ መምክሮን ፡ አሱር ፡
በሚባል ፡ አገር ፡ ሲኖር ፡ ከግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡
በቆላ ፡ ተዋግቶአልና ፤ በዚያም ፡ ገድሎታልና ፡፡

እስከ ፡ ኤርሞን ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ግብጻውያንን ፡ ፲፬፤
ተከተለ ፤ በግብጽ ፡ ሁለተኛ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ነግ
ሦአልና ፡ መግባት ፡ ተሳነው ፤ ወደ ፡ ከነዓ
ንም ፡ አገር ፡ ተመለሰ ፤ የግብጽ ፡ በርም ፡ ተዘጋ ፡
ወደ ፡ ግብጽም ፡ የሚወጣና ፡ የሚገባ ፡ አልነበ
ረም ፡፡

ዮሴፍ ፡ በአርባ ፡ ሰባት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሦስተ ፡ ፲፭፤
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ሞተ ፡፡
በግብጽ ፡ አገር ፡ ቀበሩት ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡
ወንድሞቹ ፡ ሁሉ ፡ ሞቱ ፡፡

የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ከከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ፲፮፤
ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡ በአርባ ፡ ሰባተኛው ፡
ኢዮቤልዩ ፡ በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛ ፡
ዓመቱ ፡፡

የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከዮሴፍ ፡ ዓፅም ፡ በቀር ፡ ፲፯፤
የያዕቆብን ፡ ልጆች ፡ ዓፅም ፡ ሁሉ ፡ አውጥተው ፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ባለች ፡ እጥፍ
ኝት ፡ ባላት ፡ ዋሻ ፡ ቀበሩ ፡፡

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ተመለሱ ፤ ከእነርሱ ፡ ፲፰፤
ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በኬብሮን ፡ ቀሩ ፤ አባትህ ፡ እብ
ራንም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ቀረ ፡፡

የከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ የግብጽን ፡ ንጉሥ ፡ ድል ፡ ፲፱፤
ነሣው ፡፡ የግብጽንም ፡ በር ፡ ዘጋ ፡፡ መከራ ፡ ያጸ
ናባቸው ፡ ዘንድ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡
ክፉ ፡ አሳብን ፡ አሰበ ፡፡

የግብጽንም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— የእ ፡ ፳፤
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከእኛ ፡ እነሆ ፡ ፈጽመው ፡
በዙ ፤ ሳይበዙ ፡ እንተንከልባቸው ፤ ሰልፍ ፡ ሳይ
መጣብን ፡ እነርሱም ፡ ሳይወጉን ፡ በአገዛዝ ፡
መከራ ፡ እናጽናባቸው ፤ ይህስ ፡ ካልሆነ ፡ እነ
ርሱ ፡ ከጠላቶቻችን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡
ይወጉናል ፤ ልቡናቸውም ፡ ፊታቸውም ፡ ወደ ፡
ከነዓን ፡ ነውና ፡፡

በሥራ ፡ መከራ ፡ ያጸኑባቸው ፡ ዘንድ ፤ ሥራ ፡ ፳፩፤
የሚያሠሩ ፡ አለቆችን ፡ ሾሙባቸው ፤ አዘዙአቸ
ውም ፡፡ ለፈርዖን ፡ ጲጦት ፡ ራሚስ ፡ የሚባሉ ፡
ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ አምባዎችን ፡ ሠሩ ፡፡ ቅጥሩን ፡ ሁሉ ፤
በግብጽ ፡ አገር ፡ የፈረሰውንም ፡ ግምብ ፡ ሁሉ ፡
ሠሩ ፡፡ በግፍ ፡ ይገዙአቸው ፡ ነበር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ የሚያደርጉባቸውን ፡ ያህል ፡ እን
ደዚሁ ፡ ፈጽመው ፡ ይበዙ ፡ ነበር ፡፡ የግብጽም ፡
ሰዎች ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ይጸየፉአቸው ፡
ነበር ፡፡

፳፪፡ በአርበ፡ሰባተኛው፡ኢዮቤልዩ፡በሰባተኛው፡ ሱባዔ፡በሰባተኛው፡ዓመት፡አባትህ፡ከከነዓን፡ መጣ ፥ በአርበ፡ስምንተኛው፡ኢዮቤልዩ፡በአ ራተኛው፡ሱባዔ፡በስድስተኛው፡ዓመት፡ተወ ለድህ ፡ ይኸውም፡በእስራኤል፡ልጆች፡ላይ፡ መከራ፡የጸናበት፡ወራት፡ነው ።
፳፫፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንም፡የተወለደውን፡ ወንድ ፡ ወንዱን ፡ ልጆቻቸውን፡ሁሉ፡ወደ፡ ባሕር ፡ ይጥሉ ፡ ዘንድ ፡ በእነርሱ፡ላይ፡ትእዛ ዝን፡አዘዘ ።
፳፬፡ አንተ፡እስክትወለድ፡ድረስ፡ሰባት፡ወር፡ልጆ ቻቸውን፡ሲጥሉ፡ኖሩ።እናትህም፡ሦስት፡ወር፡ ሸሸገችህ ፨ ለእርስዋም፡ነገሩአት ። ሣጥን፡አሠ ራችልህ ፤ አደሮ ፡ ማር ፡ የባሕር ፡ አረፋ ፡ ለበ ጠቻት ፤ በወንዙ ፡ ዳር ፡ በሣር ፡ ፊላ ፡ ቅጠል ፡ ውስጥ ፡ አኖረቻት ። በውስጥዋ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ አኖረችህ ፤ እናትህም ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ እየመ ጣች ፡ ታጠባህ ፡ ነበር ፥ እኅትህ ፡ ማርያምም ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ ከአሞራዎች ፡ ትጠብቅህ ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፫ ።

፩፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ የፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ተርሙት ፡ በፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ትታጠብ ፡ ዘንድ ፡ ወጣች ። ስታለቅስ፡ቃልህን፡ሰምታ፡ያመጡህ፡ዘንድ፡ ደንገጡሮችዋን፡አዘዘች ። ወደ፡እርስዋም፡ አመጡህ ፤ ከሣጥንም፡አወጣችህ ፤ ራራችልህ ፨
፪፡ እኅትህም ፡— ከዕብራውያን ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ ሕፃን ፡ አጥብታ ፡ የምታሳድገው ፡ ሞግዚት ፡ ሄጄ ፡ ልጥራልሽን ? አለቻት ። ሂጂ ፡ እናትህን ፡ ጠራቻት ፤ ደመወዝዋን ፡ ሰጠቻት ፥ አሳደገ ችህም ።
፫፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በደግህ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ቤት ፡ ወሰዱህ ። ልጅ ፡ ሆንኸው ። አባትህም ፡ ዕብራን ፡ መጽሐፍን ፡ አስተማረህ ።
፬፡ ሦስቱን ፡ ሱባዔ ፡ ከፈጸምህ፡በኋላ፡ወደ፡ቤተ፡ መንግሥት ፡ አገባህ ፤ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ እስ ከምትወጣበት፡ወራት፡ድረስ፡ሦስት፡የዘመን፡ ሱባዔ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ኖርህ ። ከእስራ ኤል ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ዕብራዊን ፡ ሲደበድበው ፡ ግብጻዊን ፡ አየኸው ፤ ገድለህ ፡ በአሸዋ ፡ መካከል ፡ ቀበርኸው ።
፭፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሲጣሉ ፡ አገ ኘህ ። በደለኛውን ፡ አይተህ ፡— ወንድምህን ፡ ለምን ፡ ትመታዋለህ ? አልኸው ። ፈጽሞ ፡ ተቆጣ ፡— በእኛ ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ የሾመህ ፡ ማን ፡ ነው ? ወይስ ፡ ትላንትና ፡ ግብጻ ዊን ፡ እንደ ፡ ገደልኸው ፡ ትገድለኝ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለህን ? አለህ ።
፮፡ ከዚህ፡ነገር፡መገለጥ፡የተነሣ፡ፈርተህ፡ሸሸህ ፨
፯፡ በአርበ፡ዘጠኝኛው፡ኢዮቤልዩ፡በሦስተኛው፡ ሱባዔ፡በስድስተኛው፡ዓመት፡ወደዚያ፡ሄደህ፡ ስድስት ፡ ሱባዔ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ተቀመጥህ ፨ በዳግመኛው ፡ ሱባዔ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ተመለስህ ፤ ይኸውም ፡ ሃምሳ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ነው ።
በደብረ ፡ ሲና ፡ የተናገረህን ፡ አንተ ፡ ታውቃ ፰፡
ለህ ። ለኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ የሚገዛ ፡ ዲያብሎስ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ያደ ርግ ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ? ወደ ፡ ግብጽ ፡ በተመለስህ ፡ ጊዜ ፡ በጐዳና ፡ በጥላ ፡ በሚያደርጉት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በፍጹም ፡ ኃይሉ ፡ ይገድልህ ፡ ዘንድ ፡ የወ ደደ ፡ አይደለምን ?
በግብጻውያን ፡ በቀልንና ፡ ፍርድን ፡ ታደርግ ፡ ፱፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተላክህ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ግብጻውያ ንን ፡ ከእጅህ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ የወደደ ፡ አይደለምን ? ከእጁ ፡ አዳንሁህ ፤ በግብጽ ፡ በፈ ርዖንና ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፥ በሕዝቡ ፡ ላይና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ላይ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ በተላክህ ፡ ገንዘብ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራትን ፡ አደ ረግህ ፨
እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ በእነርሱ ፡ ፲፡
ጽኑ ፡ በቀልን ፡ አደረገ ። በንኮንቸርና ፡ በደም ፥ በውሻ ፡ ዝንብና ፡ በትንኝ ፥ ክፉ ፡ ቍስል ፡ በሆነ ፡ በሚፈላ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ።
ከብቶቻቸውን ፡ በዕብነ ፡ በረድና ፡ በሞት ፡ ፲፩፡
አጠፋ ፥ አገመራቸውንም ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ። ከበረድ ፡ የቀረውን ፡ በሚበላ ፡ በአን በጣ ፥ በጨለማ ፥ በከብቱና ፡ በሰውም ፡ የበ ኵር ፡ ልጅ ፥ በጣዖቶቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ እግዚ አብሔር ፡ በቀልን ፡ አደረገ ። በእሳትም ፡ አቃ ጠላቸው ፤ ሳይደረግ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ፡ በአንተ ፡ ሥልጣን ፡ ተላከ ።
የግብጽንም ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊትና ፡ በአገ ፲፪፡
ልጋዮቹ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ስትናገረው ፡ ኖርህ ። ሁሉም ፡ በቃልህ ፡ ተደረገ ። ታላላቆችና ፡ ክፉ ዎች ፡ የሚሆኑ ፡ አሥሩ ፡ መቅሠፍቶች ፡ ለእስ ራኤል ፡ በቀልን ፡ ትመልስበት ፡ ዘንድ ፡ በግ ብጽ ፡ አገር ፡ መጡ ። እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እስ ራኤል ፡ ሁሉን ፡ አደረገ ፨ በግፍ ፡ እንደ ፡ ገዙአ ቸው ፡ በእነዚያ ፡ ላይ ፡ በቀልን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ከአብርሃም ፡ ጋር ፡ መሐላን ፡ እንደ ፡ ተማማለበት ፡ ፈቃዱ ፡ አደረገ ፨
ለኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ ሁሉን ፡ አስቶ ፡ የሚ ፲፫፡
ገዛ ፡ ሰይጣን ፡ በፊትህ ፡ ይከራከርህ ፡ ነበር ፥ በፈርዖንም ፡ እጅ ፡ ይጥልህ ፡ ዘንድ ፡ ይወድ ፡ ነበር ፥ የግብጽንም ፡ ሰዎች ፡ በምዋርታቸው ፡ ይረዳቸው ፡ ነበር ። እስራኤልን ፡ ግን ፡ ይጠላ ቸው ፡ ነበር ። በፊትህ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። በፊትህ ፡ ክፉ ፡ ሥራን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ተውናቸው ፥ ድኅነት ፡ ግን ፡ በእጃቸው ፡ ይደ ረግ ፡ ዘንድ ፡ አላሰናበትናቸውም ። እግዚአብ ሔር ፡ በክፉ ፡ ቍስል ፡ አጠፋቸው ፤ አንድ ፡ ተአምራትን ፡ስንኳ ፡ ከማድረግ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አሳጥተናቸዋልና ፡ መከልከል ፡ ተሳናቸው ።
ግብጻውያን ፡ በሠራዊቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ በፈረ ፲፬፡
ሶቻቸውና ፡ በሰረገላዎቻቸው ፡ በግብጽ ፡ ሠራ ዊት ፡ ሁሉ ፡ ብዛት ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ይከለክሉ

አቸው ፡ ዘንድ ፡ እስኪበረታ ÷ ለግብጻውያንም ፡
እስኪያስማቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ÷ በኃጢአት ፡
ምክንያት ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ ሰይጣን ፡ በተአም
ራቱ ፡ ሁሉ ፡ አልፈራም ።
፲፭ በግብጻውያንና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ በእስራኤ
ልም ፡ መካከል ፡ ቆምሁ ። እስራኤልን ፡ ከሠራ
ራዊቱና ፡ ከእነርሱ ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ።
፲፮ እግዚአብሔር ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ በደረቅ ፡
እንደ ፡ መሄድ ፡ አሻገራቸው ። እስራኤልን ፡
ይከተሉ ፡ ዘንድ ፡ ያወጣቸውን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡
የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በባ
ሕር ፡ እንደ ፡ ጣሉ ÷ አምላካችን ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡
በኋላ ፡ በወንዙ ፡ ጥልቅ ፡ ጣላቸው ። ብዙ ፡ በቀ
ልን ፡ ተበቀላቸው ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡
በፈሳሽ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ጣሉት ፡ ስለሚጠባ ፡
ስለ ፡ አንዱ ፡ ልጅ ፡ ፋንታ ፡ ሺህ ፡ የሚሆኑ ፡
አርበኞች ፡ በሦስት ፡ ወገንም ፡ የሚመከከቱ ፡
ሰዎች ፡ ጠፉ ።
፲፯ በአሥራ ፡ አራተኛውና ፡ በአሥራ ፡ አምስተ
ኛው ÷ በአሥራ ፡ስድስተኛውና ፡ በአሥራ ፡ ሰባ
ተኛው ÷ በአሥራ ፡ ስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ በኃ
ጢአት ፡ ምክንያት ፡ ሰውን ፡ አስቶ ፡ የሚገዛ ፡
ሰይጣን ፡ እንዳይጣላቸው ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡
በኋላ ፡ ታስሮ ፡ ተግዞ ፡ ነበር ።
፲፰ በአሥራ ፡ ዘጠኝኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ የግብጽን ፡
ሰዎች ፡ ይረዱአቸው ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልንም ፡
ልጆች ፡ ይከተሉ ፡ ዘንድ ፡ አሰናበታቸው ። ልቡ
ናቸውንም ፡ አጸና ፤ አበረታቸው ፤ ግብጻውያ
ንን ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ÷ በባሕርም ፡ መካከል ፡
ይጥላቸው ፡ ዘንድ ፡ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዘው ፡ ተበረታቱ ።
፲፱ ከግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ልብስንና ፡ ገንዘብን ÷ የወር
ቁን ፡ መሣሪያና ፡ የብሩን ፡ መሣሪያ ÷ የእነርሱ
ንም ፡ መሣሪያ ፡ በሚዋሱበት ፡ ቀን ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ እንዳይጣላቸው ÷ በግፍ ፡ ስለ ፡ ገዙ
አቸው ፡ ፋንታ ፡ ይማርኩአቸው ፡ ዘንድ ፡ በአ
ሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ አሰርነው ። የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ባዶአቸውን ፡ አላወጣ
ናቸውም ።
፳ መጀመሪያው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ አራተ
ኛው ፡ ቀን ፡ ገና ፡ ሳይመሽ ፡ ትሠዋው ፡ ዘንድ ÷
በአሥራ ፡ አምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ፀሐይ ፡
ከሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሌሊት ፡ ይበሉት ፡
ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ፋሲካው ፡ ያዘዘ
ህን ፡ ትእዛዝ ፡ አስብ ፤ ይህች ፡ ሌሊት ፡ የበዓል ፡
መጀመሪያ ፡ ናትና ÷ የመሥዋዕትዋም ፡ መጀ
መሪያ ፡ ናትና ፡ አስብ ።
፳፩ እናንተም ፡ በግብጽ ፡ የፋሲካ ፡ በዓል ፡ አድርጋ
ችሁ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ትቀመጣላችሁ ፤ የዲያ
ብሎስ ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ከፈ
ርዖን ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ ጀምሮ ፡ ተማርካ ፡ ሄዳ ፡
በወፍጮ ፡ ሥር ፡ ሆና ፡ እስከምታገለግል ፡ በሪያ ፡
ድረስ ፡ የበኵር ፡ ልጁን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ ከብ
ቱንም ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ተላከ ።
እግዚአብሔር ፡ የሰጣቸው ፡ ምልክት ፡ ይህች ፡ ፳፪
ናት ፤ በበሩ ፡ የደም ፡ ምልክት ፡ ባለና ፡ በቤት ፡
ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ ሠራዊቱ ፡
አልፈው ፡ ይሄዳሉ ፡ እንጂ ፡ ዓመት ፡ የሆነውን ፡
የበግ ፡ ደም ፡ በቤቱ ፡ በር ፡ ወዳዩበት ፡ ቤት ፡
ለመግደል ፡ እንዳይገቡ ፡ የሰጣቸው ፡ ምልክት ፡
ይህች ፡ ናት ።
የእግዚአብሔር ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብ ፳፫
ሔር ፡ እንዳዘዛቸው ፡ መጠን ፡ ሁሉን ፡ አደረጉ ።
ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አልፈው ፡ ሄዱ ።
ከከብት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሰው ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡
ውሻም ፡ ድረስ ፡ ከእነርሱ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ለማ
ጥፋት ፡ መቅሠፍት ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ አልገ
ባም ።
መቅሠፍቱ ፡ በግብጽ ፡ እጅግ ፡ ጽኑ ፡ ሆነ ፤ በግ ፳፬
ብጽ ፡ በውስጥዋ ፡ በድን ፡ የሌለበት ፡ ቤት ፡ አል
ነበረም ፤ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ለፋሲካው ፡
የታረደውን ፡ ሥጋ ፡ እየበላ ፡ ወይኑንም ፡ እየ
ጠጣ ፡ የአባቶቹን ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ፈጽሞ ፡ ያመሰግን ፡ ነበር ። ከጽኑ ፡ አገዛዝ ÷
ከፉ ፡ ከምትሆን ፡ ከግብጽም ፡ ለመውጣት ፡ የተ
ዘጋጀ ፡ ይሆን ፡ ነበር ።
አንተም ፡ ባለ ፡ በዘመንህ ፡ ሁሉ ፡ ይህችን ፡ ቀን ፡ ፳፭
አስብ ፤ ከአንዱ ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ አንዱ ፡ ዘመን ፡
በሕይወት ፡ በኖርህበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡
ሥርዓቱ ፡ ዓመት ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አድ
ርጋት ።
የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነውና ፡ ከቀን ፡ ቀን ፡ ከወር ፡ ፳፮
ወር ፡ አታስተላልፍ ። በየዓመቱ ፡ ሁሉ ፡ ከዓ
መት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በየትውልዳቸው ፡ ሁሉ ፡
ዕለቱን ፡ በዓል ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ላይ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰማይ ፡
ጽላት ፡ ታውቆአል ። የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነውና ፡
የተወሰነ ፡ ዘመን ፡ የለውም ።
ሰው ፡ ንጹሕ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ዕለ ፳፯
ቱን ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ በዓሉ ፡ በሚከበርበት ፡
ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዶ ፡ የሚቀበለውን ፡
ቍርባን ፡ ለማቅረብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ለመብላትና ፡ ለመጠጣት ፡ ባይመጣ ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ቍርባን ፡ በየጊዜው ፡ ጊዜ ፡ አላቀረ
በምና ፡ ንጹሕ ፡ የሆነው ÷ አገሩም ፡ ቅርብ ፡ የሆ
ነው ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ይጥፋ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መጥ
ተው ፡ በቀኑ ፡ ጊዜ ፡ በዓል ፡ የሚያደርጉ ፡ ይሆኑ ፡
ዘንድ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ የኃጢአቱን ፡ ፍዳ ፡
ይቀበላል ። ቀኑ ፡ ሁለቱ ፡ እጅ ፡ ለብርሃን ÷ ሦስ
ተኛው ፡ እጅ ፡ ለጨለማ ፡ ተሰጥቶአልና ፡ መጀ
መሪያው ፡ ወር ፡ በባተ ፡ በአሥራ ፡ አራተኛው ፡
ቀን ፡ በምሽቱ ፡ መካከል ፡ ከቀኑ ፡ መጨረሻ ፡
ከሦስተኛው ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሌሊቱ ፡
ሦስተኛ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ከቀኑ ፡ በሁለቱ ፡ እጅ ፡
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ በዓል ፡ ያድርጉ ።
በምሽቱ ፡ መካከል ፡ በዓል ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፳፰
እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ሥርዓት ፡ ይህ ፡ ነው ።

የሚሠዋበትም ፡ በምሽቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ጊዜ ፡
ይሁን ፡ እንጂ ፡ በብርሃኑ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አይሁን ።
እስከ ፡ ሌሊቱ ፡ ማግሥት ፡ ድረስ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡
ይብሉት ። ከሌሊቱ ፡ ማግሥት ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
የተረፈውን ፡ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉት ።
፳፱ ፡ በእሳት ፡ አብስለው ፡ ጠብሰው ፡ ይብሉት ፡
እንጂ ፡ ቅቅሉን ፡ ብርንዶውን ፡ አይብሉት ።
ከእግሩና ፡ ከሆድ ፡ ዕቃው ፡ ጋር ፡ ራሱን ፡ በማ
ስተንተን ፡ ይጥበሱት ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ምንምን ፡ የሚጠፋ ፡ ሰውነት ፡ የለምና ፡ ከእ
ርሱ ፡ ምንምን ፡ የሚሰበር ፡ አጥንት ፡ አይኑር ።
፴ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ፋሲካን ፡ ያደ
ርጉ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡
ልጆች ፡ አዘዛቸው ። ከእርሱም ፡ ምንምን ፡
አጥንትን ፡ መስበር ፡ አይኑር ። በዓል ፡ የሚያ
ደርግበት ፡ ቀን ፡ ናትና ፥ በዓል ፡ ሊያደርግበት ፡
የታዘዘችም ፡ ቀን ፡ ናትና ፥ በዓል ፡ የሚደረግ
በት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ከእርሱ ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡
ቀን ፡ ከወር ፡ ወደ ፡ ወር ፡ መተላለፍ ፡ የለምና ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

፩ ፡ አንተም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በዘመናቸ
ውና ፡ በየዓመቱም ፡ ሁሉ ፡ ከዓመት ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ በጊዜው ፡ ፋሲካን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡
እዘዛቸው ።
፪ ፡ የሚወደው ፡ መታሰቢያ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ይመጣል ። በሁሉ ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ በየ
ጊዜው ፡ በዓልን ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡
ዘመን ፡ ፈጽሞ ፡ ለመጥፋት ፡ መቅሠፍት ፡ አይ
መጣባቸውም ።
፫ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚመሰገንበት ፡ በደብተራ ፡
ኦሪት ፡ አደባባይ ፥ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ አንጻ
ርም ፡ ቢሆን ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሊበሉት ፡
አይገባም ። በእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ያድርጉት ። የመጣ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ በሚመሰገንበት ፡ በደብ
ተራ ፡ ኦሪት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዕለቱን ፡
ይብላው ፤ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በደብ
ተራ ፡ ኦሪት ፡ ይበሉት ፡ ዘንድ ፡ እንደዚህ ፡ ተጽ
ፎአል ፡ ተሠርቶአልና ፡ ከሀያ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡
ያለው ፥ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ አምላካችሁ ፡
እግዚአብሔር ፡ በሚመሰገንበት ፡ በደብተራ ፡
ኦሪት ፡ ዕለቱን ፡ ይብላው ።
፬ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይዘዋት ፡ ወደሚኖሩ ፡
ወደ ፡ ከነዓን ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡
የሚመሰገንበት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በኢየሩሳ
ሌም ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ፡ ሠራዊቶቻቸው ፡
ከያዙአቸው ፡ አገሮች ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ የሚመሰገንበትን ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትን ፡
ይተክላሉ ።
፭ ፡ መጥተው ፡ በዓመት ፡ በዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡
በሚመሰገንበት ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ መካከል ፡
የፋሲካን ፡ በዓል ፡ የሚያደርጉ ፡ ይሁኑ ።
፮ ፡ በወረሱአት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በተሠራበት ፡ ቀን ፡ ወደ
ዚያ ፡ ሄደው ፡ ፀሐይ ፡ ሲገባ ፡ ከቀኑ ፡ በሦስተ
ኛው ፡ ሰዓት ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡ በጐኑ ፡ የፋሲካውን ፡
በግ ፡ ይረዱ ፤ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡
ይርጩት ። ስቡንም ፡ በመሠዊያው ፡ በለ ፡ በእ
ሳቱ ፡ ላይ ፡ ያኑሩት ። ሥጋውንም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በሚመሰገንበት ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በእሳት ፡ ጠብሰው ፡ ይብ
ሉት ።
በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ፯ ፡
ነው ፡ እንጂ ፥ ያም ፡ ባይሆን ፡ ስሙ ፡ በሚጠራ
በት ፡ በሀገረ ፡ ምስክይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በአገራ
ቸው ፡ በየአገሩም ፡ ሁሉ ፡ በዓል ፡ ማድረግ ፡
አይችሉም ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ ወጥ
ተው ፡ አይሳቱ ።
ሙሴ ! አንተም ፡ ዓመቱን ፡ በዓመት ፡ ቀኑን ፡ ፰ ፡
በቀን ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ታዘዘልህ ፡
የፋሲካውን ፡ ሥርዓት ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ የእ
ስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ። በዓሉን ፡ ሊያ
ደርጉ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡
በቂጣ ፡ የሚከበረውንም ፡ እዘዛቸው ። ከግብጽ ፡
በወጣችሁ ፡ ጊዜ ፡ ኤርትራን ፡ ተሻግራችሁ ፡
ወደ ፡ ሱር ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እስክትደርሱ ፡ ድረስ ፡
ይህችን ፡ በዓል ፡ በመቸከል ፡ አድርጋችኋታ
ልና ፡ በባሕርም ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ ፈጽማችኋታ
ልና ፡ መሥዋዕት ፡ በሚሠዋባቸው ፡ በእነዚህ ፡
በሰባቱ ፡ ቀኖች ፡ በአምላካችሁ ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡
ዕለት ፡ ዕለት ፡ ቍርባኑን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ እዘዛቸው ።
ከዚህም ፡ ሥርዓት ፡ በኋላ ፡ በሱባዔ ፡ የሚቈጠ ፱ ፡
ረውን ፡ ቀን ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነገርሁህ ።
ይህችውም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በሲናና ፡ በኤሎም ፡
መካከል ፡ ያለች ፡ ናት ። የምድር ፡ ሰንበታትንም ፡
በደብረ ፡ ሲና ፡ ነገርሁህ ። በዓመቶች ፡ ሱባዔ ፡
ውስጥ ፡ በኢዮቤልዩ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ዓመቶች
ንም ፡ ነገርሁህ ። ዓመቱን ፡ ግን ፡ ይዛችሁት ፡
ወደምትኖሩበት ፡ አገር ፡ እስክትገቡ ፡ ድረስ ፡
አልነገርንህም ። በእርስዋ ፡ ላይ ፡ በመኖራቸው ፡
ምድር ፡ ዕረፍትን ፡ ታድርግ ። በኢዮቤልዩ ፡
የሚቈጠረውንም ፡ ዘመን ፡ ያውቃሉ ።
ስለዚህም ፡ ነገር ፡ በዓመቶች ፡ የሚቈጠረውን ፡ ፲ ፡
ሱባዔ ፡ ሠራሁልህ ። አዳም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡
እስከዚህች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡
ዘጠኝ ፡ ኢዮቤልዩታትና ፡ አንድ ፡ ሱባዔ ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነው ። በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ዮር
ዳኖስን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ማዶ ፡
እስኪገቡ ፡ ድረስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡
ለማወቅ ፡ ገና ፡ አርባ ፡ ዘመን ፡ ቀርቶአል ። እስ
ራኤል ፡ ከገዘሙት ፡ ሁሉ ፥ ከበደል ፥ ከጣዖት ፥
ከማይገባ ፡ ሥራ ፥ ከኃጢአት ፥ ከስሕተት ፡ እስ
ኪነጻ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ኢዮቤልዩታት ፡ ያልፋሉ ።
በዓለሙም ፡ ሁሉ ፡ ተዘልሎ ፡ ይኖራል ፡ ማንም ፡ ፲፩ ፡
ማን ፡ ባለ ፡ ጋራ ፡ የለም ። ምንም ፡ ምን ፡ ክፉ ፡
ነገር ፡ የለበትም ። ምድርም ፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡

ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ከኃጢ
አት ፡ ትነጻለች ። በሱባዔ ፡ የሰንበታትንም ፡
ሥርዓት ፡ እነሆ ÷ ጻፍሁልህ ። የሥርዓቱንም ፡
ፍርድ ፡ ጻፍሁልህ ። በስድስቱ ፡ ቀኖች ፡ ሥራ
ህን ፡ ሥራ ።
፲፱፡ ሰባተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ አምላካችሁ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ከመፍጠር ፡ ያረፈበት ፡ ቀን ፡ ናትና ፡
እናንተ ÷ ልጆቻችሁም ÷ ሴቶች ፡ ባሪያዎቻች
ሁና ፡ ወንዶች ፡ ባሪያዎቻችሁም ÷ ከብቶቻች
ሁም ፡ ሁሉ ÷ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ የሚኖር ፡ መጻ
ተኛም ፡ ቢሆን ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩ
ባት ። በዚያች ፡ ቀን ፡ ምንምን ፡ ሥራን ፡ የሚ
ሠራበት ፡ ሰው ፡ ይሙት ። ይህችን ፡ ቀን ፡ የሚ
ሽራት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ የሚገ
ናኝባትም ፡ ሰው ÷ ገሥግሦ ፡ ሄዶ ፡ ሥራን ፡
ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ነገርን ፡ የሚነጋገርባት ፡ ሰው ፡
ሞትን ፡ ይሙት ።
፳፡ የሚሸጥባት ፡ የሚለውጥባትም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ÷
ውኃንም ፡ የሚቀዳ ፡ ሰው ፡ በስድስተኛይቱ ፡
ቀን ፡ ያላዘጋጀ ፤ ከድንኳኑ ÷ ከቤቱም ፡ ያወጣ ፡
ዘንድ ፡ የሚሸከመውን ፡ ሸክም ፡ ሁሉ ፡ የሚያ
ነሣ ፡ ሰው ፡ ይሙት ።
፳፩፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ያዘጋጃችሁትን ፡ በልታ
ችሁ ፡ ጠጥታችሁ ፡ ለማክበር ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡
ከሥራው ፡ ሁሉ ፡ ዕረፉበት ፡ እንጂ ÷ በዓል ፡
የምታደርጉባትን ፡ ቀን ፡ የሰጣችሁ ፡ አምላካች
ሁን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመስግኑባት ፡ እንጂ ፡
በሰባተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሥራን ፡ አት
ሥሩ ። የከበረች ፡ ቀን ፡ ናት ÷ የመንግሥትም ፡
ቀን ፡ ናት ፤ በዘመናቸው ፡ በቀኑ ፡ ሁሉ ፡ ይህች ፡
ቀን ፡ ለእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ የተቀደሰች ፡ ቀን ፡
ናት ።
፳፪፡ በዚህች ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ በልተው ፡ ጠጥተው ፡
ሊጠግቡባት ÷ በየቀኑ ፡ በየሱባዔው ፡ ዕጣንን ፡
ከማጠን ÷ ቊርባንን ፡ ከማቅረብ ÷ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ መሥዋዕትን ፡ ከመሠዋት ፡ በቀር ፡
ሰው ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሊያርፉባት ፡
እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ የሰጠው ፡ ታላቅ ፡
ክብር ፡ ናትና ፡ አክብሩአት ።
አምላካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚመሰገንባት ፡ ፳፫፡
በደብተራ ፡ አሪት ፡ ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡
ብቻ ፡ ይሠራ ። የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኃጢአት ፡
ያስተሰርዩ ፡ ዘንድ ÷ እግዚአብሔር ፡ ወድዶ ፡
ሊቀበለው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ መታሰቢያ ፡ ሊሆን ፡
መባን ፡ ያቅርቡ ። እንደ ፡ ታዘዘው ፡ ለዘላለሙ ፡
ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይቀበላቸዋል ።
ሥራን ፡ የሚሠራባት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ÷ መንገድ ፳፬፡
ንም ፡ የሚሄድባት ፡ ሰው ÷ የሚያርስባት ፡ የሚ
ቆፍርባትም ፡ ሰው ÷ በቤቱም ፡ ቢሆን ፡ በቦታ
ውም ፡ ሁሉ ፡ ቢሆን ፡ መንጠር ፡ የሚያቃጥል
ባትም ፡ ሰው ÷ አህያና ፡ በቅሎ ፡ የሚጭንባት ፡
ሰው ÷ በፈረስና ፡ በበቆሎ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚሄ
ድም ፡ ሰው ÷ በመርከብም ፡ ተጭኖ ፡ ወደ ፡
ባሕር ፡ የሚሄድ ፡ ሰው ÷
ማናቸውንም ፡ መትቶ ፡ የሚገድል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ÷ ፳፭፡
ወፍንና ፡ እንስሳንም ፡ አድኖ ፡ የሚያርድባት ፡
ሰው ÷ አውሬም ፡ ቢሆን ፡ ወፍም ፡ ቢሆን ፡
ዓሣም ፡ ቢሆን ፡ አጥምዶ ፡ የያዘባት ፡ ሰው ÷
የሚጾምባትም ፡ ሰው ÷ ቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ጠብን ፡
የሚያነሣ ፡ ሰው ÷ ቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ሥር
ዓት ፡ ወጥቶ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡
ሰው ፡ ይሙት ።
የበዓሉን ፡ የቀኑን ፡ ሥርዓት ፡ በየዘመኑ ፡ አከፋ ፳፮፡
ፈል ፡ እጽፍልህ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጁ ፡
በሰጠኝ ፡ በሰማይ ፡ ጽላት ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ÷
ምድር ፡ ዕረፍት ፡ እንደምታደርግበት ፡ ሥር
ዓት ÷ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በዓልን ፡ የሚያደ
ርጉ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥራን ፡ የሚሠራበት ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይሙት ።
በኩፋሌ ፡ የተጻፈው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ተፈጸመ ።
ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ለዘላ
ለሙ ፡ አሜን ።